
ክብረ ክህነት



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት
ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

፳፻፫ ዓ.ም

ክብረ ክህነት

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፫ ዓ.ም.

© ማኅበረ ቅዱሳን
፳፻፫ ዓ.ም.

የመጀመሪያ ኅትም ፲፱፻፺፱ዓ.ም
ሁለተኛ ኅትም ፳፻፫ ዓ.ም.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው::
All rights reserved.

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
የኤዲቶርያል ቦርድ ታርሞና ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው::

አድራሻ:- በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ. 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ማታሰቢያነቷ

ስማዕትነትን በዘመናችን ላሳዩን በጅማና በኢሊባቡር አውራጃዎች
ለቀናችው ሃይማኖት ታምነው በቤተ መቅደሱ ደማቸው ፈስሶ ለካህን
የሚገባ ሞት ለሞቱት ቀሳውስትና ማተባችንን አንበጥስም ብለው
አንገታቸው ለተበጠሰ ምእመናን ትሁንልኝ!

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ
✆ 251 091 2 08 18 29
✉ 24467 / 1000 አዲስ አበባ
henok_tsehafi@yahoo.com

መቅድም

ጌታችን «ስለመ ዘክነዘሲየስ ትዕዛዘ ዘተክሉ ገቢረ ወሲምነተኒ / ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና» ዮሐ፲፭÷፭ በማለት እንደተናገረ ያለ ረድኤተ እግዚአብሔር ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ነገርን መሥራት አይቻልም። እኔም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ በእርሱ ፈቃድ ይህችን የመጀመሪያ መጽሐፌን «ክብረ ክህነት» በሚል ርዕስ ይገኬላችሁ ቀርቤአለሁ።

«ክህነት» ማለት ተክህነ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ቃል ሲሆን አገለገለ ተሾመ ዲቁና ቅስና ተቀበለ የሚል ትርጓሜ አለው። አንድም ክህነት ማለት አገልግሎት የሚል ትርጓሜም አለው። ክህነት ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ሲሆን ይህ ምሥጢር የተፈጸመላቸው ሁሉ ደግሞ «ካህናት» ተብለው ይጠራሉ። «ካህን» የሚለው መጠሪያ መደበኛው ለቁስ ቢሆንም ዐቢይ መዐርገ ክህነት ተብሎ በሚጠራው ከዲቁና እስከ ጵጵስና ባለው እርከን ውስጥ ያሉት ሁሉም «ካህናት» ተብለው ይጠራሉ።

«ክብረ ክህነት» የሚለው ቃል «የክህነት ክብር» የሚል ትርጓሜ አለው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ክህነት ክብር ይናገራል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በመልክም የሚያተዳድሩ ሽማግሌዎች ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል›› በማለት ስለ ክብረ ክህነት ተናግሮአል። /፩ጢሞ. ፭÷፲፯/ እንዲሁም የክህነት ክብር ከእግዚአብሔር ካልተሰጠ በቀር እንዲሁ ሊያገኙት የሚቻል አለመሆኑን ‹‹እንደ አሮን በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ለራሱ ክብርን የሚወስድ የለም።›› /ዕብ. ፭÷፬/ ባለንበት ዘመን ምክንያቱ ምንም ሆነ ምን የክህነት ክብር እጅግ እየተቃለለ የመጣበት ጊዜ ላይ ነን። ይህ ደግሞ በቤተ ክርስቲያኒቱ የመጪው ዘመን ህልውና ላይ ከፍተኛ አደጋ የሚሆን ነው። ስለዚህ ይህች ስለ ክህነት የምታወሳ መጽሐፍ በዚህ ጉዳይ ቢያንስ እንዲታሰብበት ለማድረግ ታገለግላለች።

ይህ መጽሐፍ ስለ ምሥጢረ ክህነት የተጻፈ አይደለም። ምሥጢረ ክህነት በውስጡ እጅግ ብዙ ነገሮችን የያዘ ሰፊ ርእስ ነው። በዚህ መጽሐፍ ላይ ስለ ክህነት ክብርና ከክህነት ጋር ተያያዥ ስለሆኑ ጉዳዮች ተጽፎአል። ምናልባት ከክብረ ክህነት ባሻገር ሌሎች ቁም ነገሮችን የሚያስጨብጡ ሐሳቦች በዚህ መጽሐፍ የተካተቱ ቢሆንም በሚጸናው መናገር የመጻሕፍት ልማድ ነውና «ክብረ ክህነት» የሚለው ቃል በርእስነት ተቀምጧል። ይህ መጽሐፍ ከአምስት ዓመታት በኋላ በድጋሚ የታተመ በመሆኑ በድጋሚ የሚገዛው ሰው ሊኖር ይችላል። ይሁንና ይህ ጎትም ከቀድሞው ጎትም በይዘትም ሆነ በገጽ ብዛት ሰፊ ልዩነት ያለው በመሆኑ እንደ ኪሳራ የሚቆጠር አይሆንም።

ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፉን ለሚያነቡ ሁሉ አስቀድመው ከግምት እንዲያስገቧቸው የምፈልጋቸው ቁም ነገሮች አሉ። በዚህ መጽሐፍ ላይ የተቀመጡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ከነትርጓሜአቸው የተቀመጡ ናቸው። ስለዚህም ጥቅሶቹን ሰፋ ባለ እይታ ለመረዳት መሞከር የአንባቢያን ፈንታ ነው። «ወኢነገድኅ እንበለ ትርጓሜ ለኵሉ ዘነበብነ / የተናገርነውን ሁሉ ያለ ትርጓሜ አንተወውም» የሚሉት አባቶቻችን ፊደል እንደሚገድል መንፈስ (ትርጓሜ) ግን ሕይወትን እንደሚሰጥ አስተምረውናልና መጽሐፍ ቅዱስን ከነትርጓሜው መመልከት የእኛ ፈንታ ነው።

ሌላው ነጥብ ደግሞ በዚህ መጽሐፍ ተአምራትና ገድላት በአስረጂነት መቀመጣቸው ነው። ገድላት ይልቁንም ተአምራት ከተለመደው የተፈጥሮ ሕግ ውጪና ከሰው ልጅ አቅም በላይ የሚፈጸሙ የእግዚአብሔር ከሃሊነት መገለጫዎች በመሆናቸው እንደ አስረጂነት ለመቅረብ የሚከብዱ መሆናቸውን ስቼው አይደለም። ይሁንና በእነዚህ መጻሕፍት ከተአምራትና ከመንክራት በተጨማሪ በማንኛውም ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ትርጉም ያላቸው ፣ በየጊዜው

ከማስተማሪያነት ከምጠቀምባቸው ምሳሌዎች የተሻሉ ምሳሌ የሚሆኑ ታሪኮችና ብዙ ቁም ነገሮች እንዳሉም በማሰብ ነው እንጂ። በአዋልድ መጻሕፍት ላይ የዘመቱ መናፍቃን በሚያሳድሩት ተጽእኖ ሆነ በሌላ ምክንያት አዋልድ ከመጥቀስ መቆጠብ እየተለመደ መጥቷል። ሀም በጽንሰ ሃሳብ የምንቃወመውን አካሄድ በተግባር እየተከተልነው ነው የሚሰብል ነው።

ከዚህ ባሻገር እንደ ተአምረ ማርያም ባሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የዘመቱ መናፍቃንና ተቆርቋሪ መሳይ ከሐድያን እንደ አሸን የፈሉበት ወቅት ላይ በመሆናችን «መች እንዳላችሁት ሆነና ገድላትና ተአምራት እኮ ለተዟችን ምርኩዝ የሚሆኑን፣ ሕይወታችንን መመልከቻ መጽሔታት (መስታወቶች) ናቸው» በማለት ለምእመናን ተስፋ ለመናፍቃን ዘለፋ እንዲሆን ነው።

ይህ መጽሐፍ በዋነኛነት ክህነትን አስመልክቶ የተጻፈ ቢሆንም ማንኛውንም በመንፈሳዊ አገልግሎት ያለ ሰው የሚመለከቱ ሐሳቦችም አሉትና ይህ እኔን ይመለከታል እያሉ ማንበብ የአገልጋዮች ፈንታ ነው። እንዲሁም የካህናትና የምእመናን ግንኙነት፣ ለካህናት የሚገባ አክብሮትና አገልግሎት፣ ካህናትን መገሠጽና መንቀፍ ከትምህርተ ሃይማኖት አንጻር የሚሉት ምዕራፎች በቀጥታ ምእመናንን የሚመለከቱ ናቸው። ስለዚህ መጽሐፉ ሁሉንም የሚመለከት መሆኑንም ለማስታወስ እወዳለሁ።

በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ካህናትን መንቀፍን አስመልክቶ ምናልባትም አወዛጋቢ ሊሆኑ የሚችሉ ሐሳቦች ተቀምጠዋል። ይሁንና በዚያው ምዕራፍ ላይ ለመግለጥ እንደሞከርሁት አንባብያን በመንፈሳዊ ዓይን፣ ከመንፈሳዊ ማዕዘን እንዲመለከቱልኝ አደራ እላለሁ። መንፈሳዊ ጽሑፍ ከግል አመለካከት፣ ከቅሬታ፣ ከወቅታዊ ሁኔታ ፣ ከአድርባይነት ከመሳሰሉት ስሜቶች በጸዳ ሕሊና መጻፍ እንዳለበትም እምነቴ ነው። የቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ ግሮች ሲፈቱ የምንጸጸትበትና ለማስተባበል የምንገደድበት አቋም በጽሑፎቻችን ላይ መንጸባረቅ እንደሌለበትና አስተምህሮአችንም ሁኔታዊ (conditional) መሆን እንደሌለበት ከግምት ውስጥ ሊገባ ይገባል።

«የዋህ ብእሲ ኩሉ ዘነገርዎ የአምን / የዋህ ሰው የነገሩትን ሁሉ ያምናል» እንዲሉ በርቱዕ አንደበት የተነገረውን ሁሉ የሚያምነው የዋህ ምእመን ካህናትን መንቀፍን እንደትሩፋትና ለቤተ ክርስቲያን እንደማሰብ መቁጠር እየጀመረ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ነገር ቢያሳስበኝ ይህችን መጽሐፍ ጽፌአለሁ።

የዚህ መጽሐፍ የሽፋን ሥዕል በማቴ ፲፮፥፲፰፡- «አንተ ዓለት ነህ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም» በማለት ጌታችን ካህኑ ለቅዱስ ጴጥሮስ የተናገረውን ቃል መሠረት ያደረገ ሲሆን መነሻ ሐሳቡ ከመጽሐፈ መነኮሳት የተገኘ ነው። የሥዕሉ ገጽታም ከፊት ለፊት የሚታየው ጌታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ የመንግሥተ ሰማያት መክፈቻ ቁልፍ የተሰኘውን የማሰርና የመፍታት የክህነት ሥልጣን ሲሰጠው ሲሆን፤ ቅዱስ ጴጥሮስ ልብሰ ተክህኖ መልበሱ እስከ ምጽአት ድረስ ለሚነሡት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣነ ክህነት መሰጠትዋን ለማመልከት ነው። በዙሪያው የዓለም ሥዕል መሳሉ ደግሞ «አናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» ብሎ የተናገረውን ለማመልከት ሲሆን፤ ከላይ በዓለት ላይ የተቀመጠችው ቤተ ክርስቲያን ደግሞ «አንተ ዓለት ነህ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ» የሚለውን ቃል ይወክላል።

ይህችን መጽሐፍ የምታነቡ ምእመናን ብትችሉ መጽሐፉን ባትችሉ መልእክቱን ለሌሎች የማበርከት ድርሻ አለባችሁ። ከፍ ሲልም ለመምህረ ንስሐም ማበርከት መልካም ነው። ይህ መጽሐፍ መምህራነ ንስሓ ካህናትን የሚመለከት እንደ መሆኑ ምእመናን ለነፍስ አባቶቻቸው በሥጦታ ቢያበረክቱት የተመረጠ ነው። ምንም የሚነቀፍ ባይሆንም

ለነፍስ አባት የሚሰጠው የሚጠመጠም ሻሽ ብቻ አይደለም መጻሕፍትም እንጂ።

ይህችን መጽሐፍ የምታነቡ አባቶቼ ካህናትና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሆይ! ይህችን ጽሑፍ በዓይነ መንፈስ እንደምትመለከቱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፤ «በሊቃውንት ፊት አትጥቀስ» የሚለውን የኢያሱ ሲራክን መጽሐፍ ቃልም አልዘነጋሁትም። ይሁንና ከአበው ምንጭ ቀድቼ እንጂ ከራሴ አንቅቼ የጻፍኩት የለምና የጎደለውን ሞልታችሁ የተጣመመውን አቃንታችሁ እንድታነቡልኝ በአክብሮት እማጸናለሁ! በዚህች ጽሑፍ በዓይናችሁ ፊት ምገስን አግኝቼም እንደሆነ ረድኤተ እግዚአብሔር እንዳይለየኝ በጽንዕት ጸሎታችሁ እንድታስቡኝ አለምናለሁ!!

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሉ

መግቢያ

ይህ «ክብረ ክህነት» የተሰኘ መጽሐፍ በሰባት ምዕራፎች የተከፈለ ነው። መጽሐፉ በዓቢይ ርእስነት ክብረ ክህነትን አስመልክቶ የተጻፈ ቢሆንም በውስጡ ግን «ሕይወተ ካህን» ፣ «ንስሓና ኑዛዜን» የሚመለከቱ ሰፊ ሐሳቦችን ይዟል። የመጽሐፉ ጠቅላላ ይዘት እንደሚከተለው ነው።

የመጀመሪያው ምዕራፍ «ሥልጣነ ክህነት በሐዲስ ኪዳን» የሚል ሲሆን የክህነትን አመሠራረትና መስፋፋት፤ የሐዲስ ኪዳን ክህነት አያስፈልግም ለማለት የሚቀርቡ ተቃውሞዎችና መልሶቻቸው ፣ ክህነት ለማን እንደሚሰጥና ለማን እንደማይሰጥ ከነምክንያቱ፤ እንዲሁም ክህነትን መቀበልን ለሚሹና ለተቀበሉትም ጠቅለል ያለ ትምህርት የቀረበበት ነው።

ሁለተኛው ምዕራፍ «የካህናት ሥልጣን» የሚል ሲሆን በአንብሮተ ዕድ የምትሰጠውን የክህነት ሥልጣን ታላቅ ሹመት ስለመሆንዋ፤ የካህናት ሥልጣን በምን በምን ላይ እንደሆነ ፤ የካህኑ ምግባር በሥልጣኑ ላይ ተጽዕኖ እንዳለውና እንደሌለው በአጠቃላይ ሥልጣንን አስመልክቶ ሰፋ ያለ መረጃ ተቀምጦበታል።

ምዕራፍ ሦስት ደግሞ «የካህናት ጸር» የሚል ነው። ካህናት ላይ የሚመጣ የዲያቢሎስ ፈተናን በሚመለከት በአራት ንዑሳን አርእስት የተከፈለ ምዕራፍ ነው። እንደ እግዚአብሔር ፍጥረት ብዙውን እንደ አንድ ቆጥረን እንጂ በካህናት የሚመጣ ፈተና አራት ብቻ ነው ለማለት አይደለም። እንዲሁም በተለይ በካህናት ላይ የሚጸናውን ብቻ ለማስቀመጥ ተሞክሯል። በዚህ ምዕራፍ የካህናትን ጸር አስመልክቶ እንደ ማስረጃ የተቀመጡት በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡ የተደመሙ አባቶች ናቸው። ገደብ አልፈን «ዛሬ እንዲህ እየተደረገ ነው...» እያልን የሐሜተኞች ጥቅስ መሆንን አንሻምና!

አራተኛው ምዕራፍ «ለካህን የሚገባ» የሚል ሲሆን ድክመትን አንሥቶ የመፍትሔ አቅጣጫን መጠቆም ይገባልና በክህነት ውስጥ ያለ ሰው ምን ማድረግ እንደሚገባው የሚጠቁም ነው።

አምስተኛው ምዕራፍ «የንስሐ አባትና የንስሐ ልጅ» የሚል ሲሆን ስለ ንስሓ አባትና ንስሓ ልጅ ሰፊ ማብራሪያ የተቀመጠበት ነው። ምዕራፉ በሁለት ንዑሳን አርዕስት የሚከፈል ሲሆን በመጀመሪያው ርእስ የመምህረ ንስሓን ሓላፊነት፣ በሁለተኛው ርእስ ደግሞ ከምእመናንን የሚጠበቀውን መንፈሳዊ ድርሻ ያትታል። በዚህ ምዕራፍ ንስሓንና ጉዛዜን በሚመለከት ብዙ ቁም ነገሮች ተካትተዋል።

የመጨረሻዎቹ ሁለት ምዕራፎች በአመዛኙ ምእመናንን የሚመለከቱ ሲሆኑ ምዕራፍ ስድስት «ለካህናት የሚገባ አክብሮትና አገልግሎት» በሚል ካህናትን ለምንና እንዴት ማገልገል እንደሚገባ፣ ምን ጥቅምም እንደሚያስገኝ ያስረዳል። ሰባተኛው ምዕራፍ ምእመናንም ሆኑ የቅርብ አገልጋዮች ካህናት ጸር ጸንቶባቸው በኃጢአት ሊወድቁ ምን ዓይነት አቋም መያዝ እንደሚኖርባቸው የሚዘረዝር ሲሆን ርእሱ «ካህናትን መገሠጽና መንቀፍ ከትምህርተ ሃይማኖት አንጻር» የሚል ነው።

መልካም ንባብ!

ጸሐፊው

ምዕራፍ አንድ

ሥልጣነ ክህነት በሐዲስ ኪዳን

- የክህነት አመሠራረት እና መስፋፋት
- ክህነተ በሁሰቱ ኪዳናት
- የሐዲስ ኪዳን ክህነት ተገቢነት
  - ካህን ጌታችን ብቻ ነውን?
  - ሁሉም ካህን ነውን?
  - ሴቶች ሰምን አይሹትም?
- ክህነት ከሐዋርያት በኋላ ስለመዘናቱ
- ክህነትን መቀበል ስሚሻ
- ምዕራፍ ሁለት

የካህናት ሥልጣን

- ስጅግ የከበረ ሥልጣን
- የካህናት ሥልጣን በምን ላይ?
  - በነፍስና በሥጋ ላይ
  - በቅዱሳን መላእክት ላይ
  - በሠይጣት ስጋንነት ላይ
- ሥልጣንና ምግባር

ምዕራፍ ሦስት

የካህናት ጸር /ፈተና/

፩ ፡ ፍቅረ ነዋይ

፪. ድፍረት

፫. ፍቅርን ማጣት

፬. ክብርንና ተርእዮን /መታየትን/ መሻት

ምዕራፍ አራት

ለካህን የሚገባ

፩. ዘወትር ስመጣር ዝግጁ መሆን

፪. ስርእያ መሆንና ስስማሰናከል

፫. ትዕግሥተኛ መሆን

ፀ. ትረፋትን መስማመጽ
፰. ክህነትን ስክብር መያዝ
ምዕራፍ አምስት
የንስሐ አባት እና የንስሐ ልጅ
(ንስሐና ሥርዓተ ኑዛዜ)
፩. በንስሐ ሒደት የካህኑ ድርሻ
ሀ. ወሲካም ስደኛ መሆን
- ምሕረት ወነፈሳዊን በማድረግ
- በርኅራኄ በመገሠጽ
- ስለ ንስሐ ልጆቹ በመጸለይ
ለ. ሳጼታቱ ማስተማር
ሐ. ያስማድሳት ሁሱን ማገልገል
- በጸታና በሰይጣ ስለመጠያየት
- በዘርና በቋንቋ ስለመጠያየት
- በምግባር ስለመጠያየት
- በምድራዊ ክብር ስለመጠያየት
መ. የንስሐ ልጆችን ሕጸጠት መከታተል
ሠ. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማስከበርና ሳጼፈረ መገሠጽ
፪. በንስሐ ሒደት የምእመናን ድርሻ
ሀ. ወምህረ ንስሐ መያዝ
ለ. ኃጢአትን ስካሀን ወናዘዝ
- የኑዛዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት
- ሰምን ለእግዚአብሔር ብቻ ስንናዘዝም?
- ኑዛዜን ስንደሚገባ በዝርዝር መፈጸም
- በኑዛዜ ወቅት ተስፋ ስለመቁረጥ ስለ ተሰቢትና መዘናጋት
- ኑዛዜና ንጽጽር
ሐ. ቀኖናና መነፈሳዊ ሥርዓቱ
መ. መምህረ ንስሐ ስለ ወምረጥና ስለ መሰወጥ

ምዕራፍ ስድስት
ስካሀናት የሚገባ ስክብርትና ስንሰገሱት
ምዕራፍ ሰባት
ካሀናትን መገሠጽና መንቀፍ ከትምህርተ ሃጼግናት ስንጻር

ምዕራፍ አንድ

ሥልጣነ ክህነት በሐዲስ ኪዳን

የክህነት አመሠራረት እና መስፋፋት

የሐዲስ ኪዳንን ክህነት የመሠረተው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይሁንና የሐዲስ ኪዳን ክህነት ለሌዋውያን ብቻ ይሰጥ እንደነበረው እንደ ብሉይ ኪዳኑ ክህነት ለአንድ ወገን (ነገድ) ብቻ የተሰጠ ሳይሆን ብቁ ሆኖ ለተገኘ ሁሉ የሚሰጥ ነው። ፲፪ቱ ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነት የተቀበሉት ጌታችን እፍ ብሎባቸው «መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል የያዛችሁባቸውም ተይዘባቸዋል» ባላቸው ጊዜ ነው። ዮሐ ፳፥፳፪

እንዲሁም በሌላ ስፍራ «ሰንበሙ ትነብሩ ዲበ ዐሠርቱ መክልዔቱ መናብርት ወትዴኝኑ ዐሠርተ መክልዔተ ሕዝበ እስራኤል ፣ እናንተ ደግሞ በ02ቱ የእስራኤል ነገድ ልትፈርዱ በ፲፪ቱ መንበር ትቀመጣላችሁ» በማለት (ማቴ.፲፱፥፳፰) ሐዋርያት በሥልጣነ ክህነታቸው ዛሬ በዚህ ምድር ላይ የፈረዱት ፍርድ (ማሠርና መፍታት) በዕለቱ ምጽአትም እንደሚጸናላቸው አስረድቷል። እንዲሁም በቅዱስ ጴጥሮስ በኩልና ለሁሉም በአንድነት «በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሆናል ፣ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» በማለት ሾሞአቸዋል። (ማቴ.፲፮፥፲፰-፲፱፣፲፰፥፲፰-፲፱) ማሰርና መፍታት የተባለውም ሌላ ሳይሆን ከኃጢአት ማሰሪያ (ማዕሰረ ኃጢአት) ነው። በምድር በኃጢአት ከክርስቲያኖች ማኅበር ከመለየት ፣ በሰማይ ከገነት መንግሥት ሰማያት ከመለየት ሌላ አስር የለም። ማሰርና መፍታት የሚለውን ከኃጢአት ማሰሪያ ማሰርና መፍታት

መሆኑን ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በማያዳግም ሁኔታ በጻፈው ቃል «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ይቀርላቸዋል ፣ ኃጢአታቸውን የያዛችሁባቸው ተይዘባቸዋል።» በማለት የማሰርና የመፍታትን ትርጉም በግልጥ አስቀምጧል። (ዮሐ.፳፥፳፫)

በሌላ በኩል አልዓዛርን ከሞተ ከአራት ቀናት በኋላ ከሞት ያስነሣበት ተአምርም እንዲሁ ሥልጣነ ክህነትን የሚያስረዳ ነው። ጌታችን አልዓዛርን ከሞት ካስነሣው በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ፍቱትና ይሒድ ተዉት ብሎ ነበር። (ዮሐ.፲፩፥፵፬) የአራት ቀን ሬሳን ከሞት ያስነሣ ጌታ መግነዙን መፍታት ተስኖት ሳይሆን በትሕትና ሰዎችን በአምላካዊ ሥራው የሚያሳትፍ ስለሆነ ነው። የሊፖው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ አውግስጢኖስ ደግሞ ይህንን ታሪክ ሲተረጉም «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አልዓዛርን ከሞት አስነሣው ፣ በዙሪያው ያሉት (ሐዋርያቱ) ደግሞ የተገነዘበትን ጨርቅ ፈቱለት ፣ ሕይወትን የሚሰጥ መግነዝን መፍታት አይችልምን? መግነዝን በመፍታ ሐዋርያቱ ኃጢአትን ይቅር እንዲሉና እንዲፈቱ ጌታ ለእነርሱና ለተተኪዎቻቸው የሰጠውን ሥልጣን አሳየ» ብሏል።[1] እንዲሁም ጌታችን ባረገበት ጊዜ እስከ ፓትርያርክነት ድረስ ያለውን መዐርግ ሰጥቶአቸዋል ። (ሉቃ ፳፬፥፶)

ጌታችን ለቅዱሳን ሐዋርያቱ እንዴት ሥልጣንን ሰጣቸው ለሚለው ከላይ ከተሰጠው ገለጻ ባሻገር አባቶቻችን «ዘወሀቦሙ ሥልጣነ ለአበዊነ ሐዋርያት በዘአእመረ መንፈስ ቅዱስ» እንደሚሉ ‹‹መንፈስ ቅዱስ ባወቀ ለአባቶቻችን ሐዋርያት ሥልጣንን ሰጣቸው›› ብንል ይበቃል። ምሥጢረ ክህነትን ምሥጢር ከሚያሰኙዋት ምክንያቶች አንዱ በማይታይ አምላካዊ ጥበብ የምትሰጥ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ

[1] St.Augstin of Hippo, Homilies On the Gospel of Jhon

በመሆንዋ ነው።

ክህነት በሁለቱ ኪዳናት

ለቅዱሳን ሐዋርያትና በሥፍራቸው ለሚተኩ ካህናት የተሰጠችው የሐዲስ ኪዳን ክህነት ከቀደመችው የብሉይ ኪዳን ክህነት እጅግ የከበረችና የምትበልጥ ናት። በሥልጣንም የሐዲስ ኪዳን ካህናት የሚበልጥ ሥልጣን አላቸው። መተርጉማን በጸሎተ ኪዳን ላይ «*ዘመሀበክነ ክመ ንፍታሕ ዘኢይትፈታሕ* / የማይፈታውን እንፈታ ዘንድ የሰጠኸን» የሚለውን ሲተረጉሙ «ምድራውያን ነገሥታት የማይፈቱትን እንፈታ ዘንድ ፤ ሌዋውያን ካህናት አያስተሰርዩት የነበረውን ውሳጣዊ ኃጢአት እናስተሰርይ ዘንድ የሰጠኸን» በማለት የሐዲስ ኪዳንን ክህነት ትልቅነት በመመስከር ነው።

ሥልጣነ ክህነት ጌታችንን በመስቀል ከተባበሩ ከሌዋውያን ካህናት ተነጥቆ ለሐዲስ ኪዳን ካህናት ስለመሰጠቱ ጌታችን በምሳሌ ተናግሮአል። ‹‹የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ሰው ነበረ ቅጥርም ቀጠረለት ... ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ። የሚያፈራበት ጊዜ ሲቀርብ ፍሬውን ሊቀበሉ ባሮችን ላከ ፤ አነርሱን ገደሉአቸው። በኋላ ግን ልጁንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከባቸው። ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ ፦ ወራሹ ይህ ነውና እንግደለውና ርስቱን እናግኝ ተባባሉ። ይዘውም ከወይኑ አትክልት አወጡና ገደሉት። እንግዲህ የወይኑ አትክልት ባለቤት በመጣ ጊዜ ምን ያደርግባቸዋል አነርሱም ፦ ክፉዎችን በክፉ ያጠፋቸዋል <u>የወይኑንም አትክልት ፍሬውን በየጊዜው ሰሚያስረክቡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል።</u> ›› (ማቴ. ፳፩፥፴፫-፵፩) በዚህ ምሳሌ ላይ በነፍስ ገዳይ ገበሬዎች የተመሰሉት ነቢያትንና ወልደ እግዚአብሔርን የገደሉ የአሪት ካህናት ናቸው። የወይኑ አትክልት

የተባሉት የእግዚአብሔር ሕዝብ ሲሆኑ በቀድሞዎቹ ገበሬዎች ተተክተው እንዲጠብቁ የተሾሙት ደግሞ የሐዲስ ኪዳን ካህናት ናቸው።

የሐዲስ ኪዳን ካህናት ከቀደሙት የብሉይ ኪዳን ካህናት ይልቅ የከበሩና ወደ እግዚአብሔር የቀረቡ ናቸው። አበው ይህን በምሳሌ ሲያስረዱ በሰማያውያን መላእክት በመመሰል ነው። በሰማያት ከመንበረ ጸባኦት የቀረቡ ኪሩቤልና ከመንበረ ጸባኦት ርቀው የሚቆሙ ሀያ አራቱ ካህናተ ሰማይ አሉ። ከመንበሩ የራቁት ሃያ አራቱ ሊቃናት የካህናተ ብሊት (የብሉይ ኪዳን ካህናት) ምሳሌ ሲሆኑ ለመንበሩ የቀረቡ ኪሩቤል ደግሞ የካህናተ ሐዳስ (የሐዲስ ኪዳን ካህናት) ምሳሌ ናቸው።

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ክህነቱ ሲለወጥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና›› እንዳለ የሐዲስ ኪዳን ክህነት ሕገ ኦሪት ከሕገ ወንጌል የምትበልጠውን ያህል የበለጠ ነው። (ዕብ. ፯፥፲፪) የሐዲስ ኪዳን ካህናት የቀደሙት ሌዋውያን ሲገቡበትና ሊያገለግሉበት በማይቻላቸው በቤተ መቅደስና በሐዲስ ኪዳን መሠዊያ /ታቦት/ የሚያገለግሉ በመሆናቸው በክብር ይበልጣሉ። ‹‹መሠዊያ አለን ከእርሱም ሊበሉ /ከሥጋ ወደሙ/ ድንኳኒቱን የሚያገለግሉ /ሌዋውያን ካህናት/ መብት የላቸውም›› ዕብ. ፲፫፥፲

የሀዲስ ኪዳን ክህነት የዘር ሐረግ ተቆጥሮ የሚሰጥ ሳይሆን የቋንቋን የባሕልና የዘርን ገደብነት ተሻግሮ የሚሰጥ ነው። ለሐዲስ ኪዳን ክህነት ብቁ ያልሆነ ቋንቋና ነገድም የለም። ራሱ እግዚአብሔር በትንቢት እንዳጸፈ ‹‹አሕዛብንና ልሳናትን ሁሉ የምሰበስብበት ጊዜ ይደርሳል ፤ እነርሱም ይመጣሉ ፤ ክብሬንም ያያሉ ... ካህናትና ሌዋውያን እንዲሆን ከእነርሱ እወስዳለሁ።›› ኢሳ. ፷፮፥፲፰-፳፩

የሐዲስ ኪዳን ክህነት ተገቢነት

መናፍቃን የሐዲስ ኪዳንን ክህነት አስመልክቶ ሁለት ፈጽሞ ሊስማሙ የማይችሉ (የሚቀዋወሙ) ሃሳቦችን ያራምዳሉ። አንደኛው ሃሳብ ‹‹ካህን ክርስቶስ ብቻ ነው›› የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ሁላችንም ካህናት ነን›› የሚል ነው። አሳስተዋሉት ካልሆነ በስተቀር እነዚህ ሁለት መቅድመ ሃሳቦች (ሓቁስቂሽስቋ) ሲገጣጠሙ የሚሰጡት ትርጓሜ ‹‹እኛ ክርስቶስ ነን›› የሚል ነው።

ካህን ጌታችን ብቻ ነውን?

ጌታችን እንደ መልከ ጼዴቅ በዘር ያላገኘው የማይለወጥ ዘለዓለማዊ ክህነት አለው። ይህ ማለት ግን በሐዲስ ኪዳን ካህናት የሉም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። ቅድስና ፣ አምላክነት ፣ አዳኝነት ፣ ምስጋና የመሳሰሉት ሁሉ የባሕርይ ገንዘቦቹ ናቸው። እርሱ በባሕርይው ቅዱስ ሲሆን ‹‹ቅዱሳን ሁኑ›› /፩ጴጥ.፩÷፲፮/ ፣ እርሱ በባሕርይው አምላክ ሲሆን ‹‹አማልክት ናችሁ›› /መዝ. ፹፪÷፮÷፬/፣ እርሱ አዳኝ ሲሆን ታድናላችሁ። /መዝ. ፴፫÷፯፣ መሳ. ፫÷፲፭/ ሲል ከመለኮታዊ ባሕርይው ተካፋዮች አንድንሆን ሰጥቶናል።

«ካህን እርሱ ብቻ ነው» የሚል የክርክር ሀሳብ ለሚያነሡ ሰዎችም ይህንን የቸርነቱን ሥራ እንነግራቸዋለን። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ›› ባለበት አንደበት ‹‹የዓለም ብርሃን ናችሁ›› ብሏል። እርሱ ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ›› እንደተባለ ‹‹በስመ ለምናምን የእግዚአብሔር ልጆች እንባል ዘንድ›› ሥልጣንን ሰጥቶናል። ‹‹መልካም እረኛ እኔ ነኝ›› ብሎ እንደተናገረ ‹‹ግልገሎቼን አሰማራ ፣

ጠቦቶቼን ጠብቅ ፣ በጎቼን አሰማራ›› ብሎ እረኝነትን ሰጥቶናል። «ብርሃን ሆኖ ብርሃን ፣ ልጅ ሆኖ ልጆች ፣ እረኛ ሆኖ እረኞች» እንዳሰኘ ን ካህን ሆኖም ክህነትን ለሰው ልጆች አልከለከለም። (አረጋዊ መንፈሳዊ)

ስንታመም የሚያክሙንን ሰዎች ‹ሐኪም› ብለን የምንጠራው የእግዚአብሔርን ፈዋሽነት ሳናውቅ ቀርተን አይደለም። በሥጋ የሚወልዱን ወላጆቻችንን ፣ አሳዳጊዎቻችንን ፣ የምናከብራቸውን ሰዎች ‹አባቴ› የምንለው የእግዚአብሔርን አባትነት ክደን አይደለም። ካህናትንም ‹ካህን› ብሎ መቀበል የጌታችንን ክህነት ማቃለል አይደለም።

በሐዲስ ኪዳን ከአምላካችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ሌላ ክህነት ያላቸው እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ›› ሲል ተናግሯል። (፩ጴጥ. ፭÷፬) የእረኞች አለቃ ያለው መድኃኔዓለም ክርስቶስን ሲሆን እረኞች የተባሉት የሐዲስ ኪዳን ካህናት ናቸው።

ሊቀ ካህናት የሚለው የጌታችን መጠሪያም እንዲሁ ‹‹ከጌታችን በቀር ካህን የለም›› የሚለውን ሃሳብ ውድቅ ያደርገዋል። በዘመነ አሪት በክህነት ለማገልገል የተመረጡት ሌዋውያን /ከዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች መካከል የሌዊ ልጆች/ ነበሩ። የአገልግሎት መዓርጋቸው ግን ሦስት ዓይነት ነበር። አንደኛው <u>ሊቀ ካህናት</u> የሚባለው ሲሆን አሮንና ከእርሱ የሚወለድ የበኩር ልጅ የሚሰጠው ሥልጣን ነበር። ይህ የሊቀ ካህናትነት ሥልጣን የበኩር ልጆችን እየተከተለ ሲወርድ ኖሯል። የሊቀ ካህናቱም ሥራ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ውስጠኛይቱ ድንኳን የመግባት ሥልጣን የተሰጠው ሲሆን ስለራሱ እና ስለ ሕዝቡ ስኅተት እጆቹን

ዘርግቶ ደምን ያቀርብ ነበር።

ከሊቀ ካህናቱ ቀጥሎ ያሉት ደግሞ ‹‹ካህናት›› የሚባሉ ሲሆን እስከ መጀመሪያው ድንኳን ድረስ ብቻ የመግባት ሥልጣን ያላቸው ናቸው። እነዚህ ካህናት የአሮን ልጆች ሆነው ነገር ግን የበኩር ልጆች ያልሆኑ ናቸው። አብዛኛውን የቤተ መቅደስ ሥራ የሚፈጽሙና በሊቀ ካህናቱ የበላይነት የሚመሩ ናቸው። ሦስተኛዎቹ ደግሞ ከነገደ ሌዊ ሆነው የአሮን ልጆች ያልሆኑት ሲሆኑ ‹‹ሌዋውያን›› የሚባሉት ናቸው። እነዚህ ደግሞ እንደ ከሊቀ ካህናቱና ከካህናቱ በሥልጣን ዝቅ ያሉ ሲሆኑ በቤተ መቅደሱ አገልግሎት የሚራዱ ናቸው።

በሐዲስ ኪዳን ሊቀ ካህናት አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹የሃይማኖታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት›› ‹‹እንደ መልክ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ተጠራ›› (ዕብ.፫÷፩) ሲል የጌታችን ሊቀ ካህናትነት ያስረዳል። መድኃኒዓለም ክርስቶስ ‹‹ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም›› /ዕብ. ፱÷፳፭/ ሊቀ ካህናቱ እጁን ዘርግቶ በቤተ መቅደስ ደምን ሲያቀርብ እንደሚገባ እጁቹን በመስቀል ላይ ዘርግቶ ገዛ ደሙን ለዓለም ኃጢአት አንድ ጊዜ አቅርቦአል።

‹‹ካህናት›› የተባሉት ደግሞ በሐዲስ ኪዳን የሊቀ ካህናቱ የመድኃኔዓለም ክርስቶስ ረዳቶች የሆኑት የሐዲስ ኪዳን ቀሳውስት ናቸው። ሌዋውያን የተባሉትን የሚወክሉት ደግሞ ለካህናቱ ረዳቶች የሆኑት ዲያቆናት ናቸው። የቀደመው ሊቀ ካህናት ካህናቱንና ሌዋውያኑን እንደሚያዝዝና እንደሚያስተዳድር በሐዲስ ኪዳንም

መሥዋዕቱም ፣ መሥዋዕት አቅራቢውም ፣ መሥዋዕት አቅራቢ ሊቀ ካህናቱም አምላካችን ሲሆን በሐዲስ ኪዳን ክህነት የሚሾሙት ሁሉ የእርሱ ረዳቶች ናቸው። ሊቀ ካህናት ማለት ‹የካህናት አለቃ› ማለት ነው ፣ ካህናት በሌሉበት ደግሞ የካህናት አለቃ የሚለው አጠራር ሊሠራ አይችልም።

በክህነት ሥራቸው ጸንተው ከተገኙም በሰማያት ይሸው ሊቀ ካህናት ክርስቶስ የሰማዩን ሥርዓት ያስተምራቸዋል። ቅዱስ አትናቴዎስ እንዳለ :- ‹‹የካህናት አስቻ ሊየሱስ ክርስቶስም ከዚያ ወዳዚህ ምሥጢር ይገባል ፣ ስንዝር ሥርዓት ቀሳውስትን ዘቀኙ ዲያቆናትንም በገፌው ያቅማቸዋል ፣ የምሥጢርንም ሥርዓት ያሳያቸው ዘንድ ፤ ምን ደዘወሰላቤ ስሙስ ምንድር ነው የዚያን ጊዜውስ ምሥጢር ምን ይሳላሌ ዛፌ ሊናገሪት ልይቻልም በስው ሰውናም የሰም ፤ የተሾማችሁ ካህናት ሆይ ከሰማይና ከምድር ጌታ ጋፌ ካገለገላችሁ በእናንተ ክብር ይገኝችኋል ፣ የንጹሕ ወርቅ ሻሻቴ የምትመስሉ የተመረጣችሁ ዲያቆናት ሆይ በእናንተ ደስታ ይገባል ፣ ድንቅ ምሥጢርን ባያችሁ ጊዜ።›› /ቅዳሴ አትናቴዎስ/

«አበ ነፍስ /የነፍስ አባት/ የሚለው ስም ለክርስቶስ ብቻ የሚሰጥ ናቸው! ፣ አባት ተብሎ መጠራት የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው።» የሚሉ አሉ። ይህንን በተመለከተ በመልክዓ ኢየሱስ ‹‹ሰላም ለመላትሒከ እለ ይፈርያ አፈዋተ ከመ ርኄ አፈው ዘይዜኑ ርኑቀ ፍኖተ ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እስመ አበ ነፍስየ አንተ ፣ በሎመ· ለመላእክት ተፈሥሑ ሊተ ረከብኩዎ ለወልድየ በከንቱ ዘሞተ ›› በማለት ‹‹ኢየሱስ ክርስቶስ የነፍሴ አባት ነህና›› ይላል።

ይህ ማለት ግን ካህናት የነፍስ አባት መባል አይችሉም ማለት አይደለም። የሥጋ አባቶቻችን በሥጋችን የምንበሳውን የምንጠጣውን ፣

የምንለብሰውን አሟልተው ያላድጉናል ፣ በሥጋ ስታመም ያስታምሙናል። ካህናት ደግሞ ለነፍሳችን የመመገቢውን የእግዚአብሔር ቃል ምግብ ይመግቡናል ፣ በኃጢአት ስንራቆትና ስንታመም ይንከባከቡናል። በዚህ የተነሣ ‹የነፍስ አባት› መባላቸው ድንቅ አይደለም። የለም ነፍስን የፈጠረ እግዚአብሔር ነውና ከእርሱ በቀር ‹የነፍስ አባት› መባል የሚገባው የለም ቢባል ደግሞ ሥጋንም የፈጠረ እርሱ ነውና የሥጋ አባታችንንም አባት ማለት ላንችል ነው። እንዲሁም ከብሉ እስከ ሐዲስ ከአብርሃም እስከ ጳውሎስ አባት ተብለው የተጠሩ ልጅ ብለው የጠሩ እጅግ ብዙዎች እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። እርሱ ካህን አበ ነፍስ ነውና «ለምን ለሰው ልጆች ይህ ክብር ተሰጠ?» ለሚሉ «በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት የለኝምን?» የሚለው የጌታችን ቃል የሚመለከታቸው ይመስላሉ።

መናፍቃን ‹ካህን› መባል ተገቢ አይደለም ቢሉም ራሳቸው ግን ‹ፓስተር› ፣ /ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ/ ኤጲስቆጶስ ፣ መጋቢ መዘተርፈ በሚሉ መጠሪያዎች ሲጠሩ ግን እናያለን። ለካህናት የተሰጠውን የመባረክ ሥልጣን ቢነቅፉም እንዲሁ እርስ በእርሳቸው ‹ጌታ ይባርክህ› ከመባባል አላረፉም። ለእነርሱ ብቻ የሚፈቀድ ለሌላ የሚከለከል ነገር ስለሌለ ወይ የክህነትን አስፈላጊነት መቀበል ወይም የጠራ ማብራሪያ ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል።

ሁሉም ካህን ነውን?

መናፍቃን የሐዲስ ኪዳንን ክህነት የሚቃወሙበት ሁለተኛው ሃሳብ ደግሞ «ሁላችንም ካህናት ነን» የሚል ነው። ለዚህ የሚጠቅሱት ቅዱስ ጴጥሮስ «የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ ፣ የንጉሥ ካህናት ፣ ቅዱስ ሕዝብ ለርስቱ የተለዩ ወገን

ናችሁ» በማለት የተናገረውን ነው። (፩ኛ ጴጥ ፪÷፱)

በቅዱስ ጴጥሮስ መልእክት የተነገረው ቃል አስቀድሞ በአሪትም የተነገረ ነበር። «ርስት ትሆኑልኛላችሁ ፣ እናንተም <u>የካህናት መንግሥት</u> የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ።» ተብሎ ነበር። (ዘሌ. ፲፱÷፮) «የንጉሥ ካህናት» ወይም «የካህናት መንግሥት» የሚሉት ቃላት ‹ሁላችሁም ካህናት ናችሁ› የሚል ትርጉም የለውም። እንደዚህ የሚል ትርጉም ቢኖረው ኖሮ በአሪት በተመሳሳይ ተነግሮ ስለነበር በዘመነ አሪት የነበሩ ሰዎች ሁሉ ካህናት ነበሩ ማለት ነው። ሁሉም ካህናት ቢሆኑ ኖሮ እነ ቆሬ ዳታንና አቤሮን ክህነትን በመፈለጋቸው ለመቅሠፍት ባልተዳረጉ ነበር። (ዘኁ. ፲፮)

ሌላው ጥቅስ ደግሞ «ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን ለአምላኩና ለአባቱም ለእግዚአብሔር [2]<u>ንጉሥታትና ካህናት እንድንሆን</u> ላደረገን ለእርሱ ክብርና ኃይል ይሁን!» የሚል ነው። (ራእ. ፩÷፮) የሚለው ነው። ካህናት እንድንሆን አደረገን ማለት በምድር ላይ ሁላችንም ካህናት ነን ማለት ነው ተብሎ ከተተረጎመ ነገሥታት ነን የሚለውስ ትርጉመ ምን ሊሆን ነው ሁላችን በዙፋን ልንቀመጥ ፣ ዘውድ ልንደፋ ፣ ‹ማርማዊነትም› ልንባል እንችላለን?

ታዲያ ካህናት አደረገን ማለት ምን ማለት ነው? ሲባል የክህነትን መንፈሳዊ ትርጉም ማብራራት ያስፈልገናል። ካህን በእግዚአብሔር ፊት ዕጣን እያጠነ ፣ መሥዋዕት እያቀረበ እንደሚያገለግን ለምእመናን ሁሉ የተሰጠ ይህንን የሚመስል የክህነት ሥራ አለ። ስለዚህ ማዕጠንት ቅዱስ ዳዊት ‹ጸሎቴን በፊትህ እንደ

[2] ‹‹...made us kings and priests››

ዕጣን ተቀበልልኝ እጅ መንሣቴም እንደ ሠርክ መሥዋዕት ትሁን ፣ ‹‹ለአንተ የምስጋና መሥዋዕት አሠዋለሁ›› ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ‹‹እንግዲህ ወንድሞቼ ሆይ ስውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ አርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።›› ‹‹የምስጋናን መሥዋዕት ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት ፤ ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና ›› በማለት ለሁላችን ስለተሰጠው መንፈሳዊ ክህነት አስረድቶናል። (መዝ. ፻፵፥፪ ፤ መዝ. ፶፩፥፳ ፤ ሮሜ. ፲፪፥፩ ፤ ዕብ. ፲፫፥፲፮)

በሌላ በኩል ካህን ማለት ተክህነ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን አገልጋይ የሚል ትርጉምም አለው። ስለዚህ «ካህናት ናችሁ» ሲል የነገሥታት ንጉሥ የእግዚአብሔርን ክብር እንድትነግሩ የተመረጣችሁ «አገልጋዮች ናችሁ» የሚል ትርጉምም አለው። *«ያመነ ሁሉ ካህን ነው»* የሚለው አባባል *ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን አያስፈልግም ፤ ምሥጢራትም በየሜዳው መፈጸም አለባቸው ወዘተ* የሚሉ የኑፋቄ ሃሳቦችን ያዘለ ነው። ደግሞስ ሁሉ እረኛ ከሆነ መንጋው ማነው?

ቅዱስ ጳውሎስ «እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን ሁለተኛም ነቢያትን ሦስተኛም አስተማሪዎችን ቀጥሎም ተአምራት ማድረግን ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ እርዳታንም አገዛዝንም የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል። ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን? ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን? ሁሉስ ተአምራትን ይሠራሉን? ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን? ነገር ግን

የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ በብርቱ ፈልጉ» (፩ኛ ቆሮ ፲፪፥፳፰-፴፩) በማለት የተናገረው ቃል ክህነትም የሁሉም ላለመሆኑ ማስረጃ ነው። ደግሞስ ይኸው ሐዋርያ ለጢሞቴዎስና ለቲቶ ስለ ካህናት (ስለ ዲያቆናት ፣ ስለ ቀሳውስትና ስለ ኤጲስ ቆጶሳት) አመራረጥ የጻፈላቸው ሁሉም ካህን ቢሆን ነውን? አይደለም። ክህነት ምሥጢር የምትሰኘው አንድም ለተለዩ ሰዎች የምትሰጥ ስለሆነች ነው። ምሥጢር ለቀረቡና ለወዳጆች እንደሚነገር ክህነትም እግዚአብሔር ለመረጣቸው የሚሰጣት ጸጋ ናትና ምሥጢር ትባላለች።

ሴቶች ስለምን ስጸካኑም?

ክህነት በጸታ ረገድ ለወንዶች ብቻ ይሰጣል። እግዚአብሔር ለወንዶች ብቻ የሰጠው ለሴቶች ያልተሰጠ ፣ ለሴቶች ብቻ የሰጠው ለወንዶች ግን ያልተሰጠ ብዙ ነገር አለ። ክህነት ለሴቶች የማይሰጥ መሆኑን በመጻሕፍት ከቀደመው ዘመን ጀምሮ የሴት ካህን አለመኖሩንና በሐዲስ ኪዳንም ከተመረጡት ሐዋርያት መካከል ሴቶች አለመኖራቸውን በማስረጃነት ማቅረብ ይቻላል። በትርጓሜ ወንጌል በተመዘገበው ምሥጢርም ጌታችን ከሙታን በተነሣ ጊዜ ቀድማ ትገሣኤውን ያየችው ማርያም መግደላዊት ልትነካው ስትል «አትንኪኝ» ማለቱ ሴቶች ሥጋ ወደሙ ለመፈተት የሚያበቃው መዓርገ ክህነት እንደማይሰጣቸው ያስረዳል። (ዮሐ ፳፥፲፯) በዘመነ ሐዋርያትም ስለ ሴት ካህን የተጻፈ ነገር አይገኝም።

ከዚህም ባሻገር ግን እግዚአብሔር ሙሴን ለመንግሥት አሮንን ለክህነት ለምን እንደመረጠ እንደማይታወቅ ሁሉ ወንዶችን ብቻ ለምን ለክህነት እንደመረጠ የሚያውቀው እርሱ ባለቤቱ ነው። ምናልባትም አሁን በድንግዝግዝ እንደምናይ ነንና ባለንበት በሥጋዊ አእምሮ የማንረዳው ኋላ በአጸደ ነፍስ ወይም ከዚህ በተለየ አቅዋም ሆነን ልንረዳው የምንችል ረቂቅ ፍርዱ ነው ብለን ልናልፈውም እንችላለን።

ቅዱስ ዑራኤል እንዳሰ፦ «የልዑል እግዚአብሔር ፍርዱ ባለመመርመር ተወስኗልና የእግዚአብሔር የፍርዱን ምሥጢር ማወቅ እንደምን ይቻልሃል? የምትፈርስ የምትበሰብስ አንተ የማይፈርስ የማይበሰብስ የእግዚአብሔር ፍርዱን ማወቅ አትችልም።» (፬ዝ ሱቱ ፪፥፲፩)

«ሴቶች ክህነት ለምን አይቀበሉም?» የሚለው ጥያቄ አንድም ከሃይማኖታዊነት ይልቅ ፖለቲካዊነቱ እና [3]ፍልስፍናዊነቱ ያመዝናል። *የሴት «ካህናት»* ያሉአቸው መናፍቃንም አሉ እነዚህ ክህነታቸውም ክህነት ፣ እምነታቸውም እምነት ባይሆን ነው። እንኳን ሴትን ክህነት መሾም የግብረ ሰዶም ጋብቻን ሳይቀር ፈቅደው የሚያስፈጽሙ ናቸውና ለምን ሴትን ይከናሱ ብለን ከእሾህ ወይን ከኩርንችትም በለስ ለቀማ አንነሣም። (ማቴ ፯፥፲፮) መብት ያስከበሩ መስሎአቸው ይህን የሚደግፉም እንደ እግዚአብሔር ፍትሕ የሚያውቅ እንደሌለ ሊረዱ ይገባል።

ይህን ሴቶች ክህነት ይቀበሉ የሚል አመለካከት በሃይማኖታዊ መነጽር ስናየው ይህ በእግዚአብሔር አሠራር ላይ የሚነሳ ጥያቄ ሌላ ትርጉም አለው። እንዲህ ያለው ጥያቄ በእግዚአብሔር ረቂቅ አሠራር ላይ የሚነሳ ነው። አንድም ሴቶች ለምን ክህነት አይቀበሉም? ማለት *ወንዶች ለምን አይወልዱም* እንደ ማለት ነው። ምን አገናኘው ቢሉ ካህናትስ ምእመናንን በጥምቀትና በትምህርት የሚወልዱ ናቸው። ሕገ ተፈጥሮ እንዳይፈርስ የሚታሰበውን ያህል ለሕግ መንፈሳዊ ማሰብ ከተቻለ ምን ያህል የተሳሳተ ጥያቄ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

እንዲያው እንደ መናፍቃኑና እንደ ፈላስፎቹ ሀሳብ ሴቶች ክህነት ይቀበሉ ቢባል ተከትሎ የሚመጣው እጅግ አስቸጋሪና የተወሳሰበ ነገር ነው። ምክንያቱም ሥርዓተ ቤተክርስቲያንም ካልተከለሰ ሊያሰኝም ይችላልና ነው። ደግሞም ይህ ጥያቄ ክህነት ይቀበሉ በሚል ብቻ

[3] **Feminist theory**

የሚያበቃም አይሆንም። ሌላ ዘመን የሚወልዳቸውን ብዙ ጥያቄዎችንም ያስከትላል።

ሴቶች ሥልጣነ ክህነት አይቀበሉም ማለት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ድርሻ የላቸውም ማለት አይደለም። ከጥንት ጀምሮ እስከ ቅድስና መዐርግ ደርሰው መልካሙን ገድል የተጋደሉ ብዙ ቅዱሳት አንስት ብዙ ናቸው። የመሲሁን ዜና ለሰማርያ ሰዎች እንደለበሰችው [4]ሣምራዊቷ ሴት ትንሣኤውን ለሐዋርያት አንዳደረሰች እንደ ማርያም ነገረ ሃይማኖትን የማድረስ ፣ ትውልድን የመቅረጽ ድርሻ ለሴቶች ተሰጥቷል። በቤተ ክርስቲያን ሀብተ ክህነት ከሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች በላይ ያለ ክህነት የሚፈጸሙ በርካታ አገልግሎቶች አሉ። መናፍቃን ጸታ ፣ ዕድሜ ሳይለዩ ሁሉን እያዘመቱ ባለበት ወቅት ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን በመሉ ዐቅም መጠቀም ስለሚያስፈልጋት የእኅቶችና የእናቶች ድርሻን ‹ሴቶች በስልጣታ..!› ከሚል ትእዛዝ ባለፈ ማመቻቸት ይገባል።

ክህነት ከሐዋርያት በኋላ ስለመጽናቱ

የክህነት ሥልጣንን ጌታ ለሐዋርያት ብቻ የሰጠ አይደለም። ይልቁንም እስከ ዳግም ምጽአት ድረስ ለሚነሡ ብቁ ሆነው ለሚገኙ ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ይህን ሥልጣን ሰጥቶአል። ጌታችን ሥልጣነ ክህነትን የሰጠው ለሐዋርያት ብቻ ከሆነና ይህ ሥልጣን የሚሠራው በእነርሱ ዘመን ብቻ ከሆነ ክርስትና ለአንድ ክፍለ ዘመን

[4] ይህችን ሴት ተአምረ ኢየሱስ ‹ብርስፈንያ› ብሎ የሚጠራት ሲሆን ከጥምቀቷ በኋላ የምትጠራበት ስም ‹Photini› የሚል ነው። ከዚያው እስከ ፮ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ የግሪክ ጽሑፎች ‹ሐዋርያዊት› ፣ ‹ወንጌላዊት› /Apostle/ 'Evangalist'/ ብለው የሚጠሯት ሲሆን በበዓለ ጰራቅሊጦስ ከአምስት አኅቶቿና ከሁለት ልጆቿ ጋር ከተጠመቀች በኋላ በኤሮን ዘመንም ከሀገር ወጥታ

ብቻ ተቋቁሞ የፈረሰ ሃይማኖት በሆነ ነበር።

ይሁንና ጌታችን «እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» በማለት በተናገረው ንግግር የክህነተ ሐዋርያት ዘላቂነት ታውቆአል (ማቴ ፳፰፥፳) ምክንያቱም ቅዱሳን ሐዋርያት ሁሉም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በሕይወተ ሥጋ አይኖሩምና። ይህ ቃል በእግረ ሐዋርያት ተተክተው የእነርሱን አሠረ ፍኖት ተከትለው ለሚተኩ ለክህናተ ቤተ ክርስቲያን የተነገረ ነው። ‹‹በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ›› የተባሉት ሐዋርያትም በነጻ ያገኙትን ክህነት በቅተው ለተገኙ ሁሉ አስተላልፈዋል። /ማቴ. ፲፥፰/ እንዲሁም በሕይወት ዘመናቸው ጳጳሳት አድርገው የሾሟቸውንም ይህንን ሥልጣነ ክህነትና የማስተማር አደራ ለሌሎች እንዲያስተላልፉ አሳስበው አልፈዋል። ‹‹ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።››(፪ጢሞ. ፪፥፪) እንዲል ሐዋርያ።

«ፍትሐት ዘወልድ» በተሰኘው ጸሎት ላይም «አንተ እግዚኦ ይእዜኒ ጸጎስ ክህነተ ለላዕካኒስ ንጹሐን እለ ይገብሩ ግብረ ክህነት ዙሉ ጊዜ በቤተ ክርስቲያኒስ ቅድስት ከመ ይጎድጉ ኃጢአተ በዲበ ምድር / አቡቱ ጌታ ሆይ አሁንም ሁልጊዜ የክህነትን ሥራ ለሚሠሩ ለንጹሐን አገልጋዮችህ ክህነትን ሰጠህ ፤ በምድር ላይ ያስሩ ዘንድ ይፈቱ ዘንድ የኃጢአትን ማሠሪያ ሁሉ ከእኛ ያርቁ ዘንድ» የሚለው ለዚህ ነው።

ቅዱሳን ሐዋርያት ጌታ የሰጣቸውን ሥልጣን ለተተኪ ሊቃውንት ማስተላለፋቸውን እንዲህ ሲል ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ ያስረዳል። «ከመለኮትህ ገናንነት ምሥጢር ለደቀ መዛሙርትህ

በአፍሪካ ቅርጣግ /Carthage/ ተሰድዳ አስተምራለች። ብዙ አስርና መክራን ተቀብላም በክብር

እንዳልሠወርህ እነርሱም ከአኛ የሠወሩት የለም ፤ ለቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ሊቀ ጳጳስ ፤ ኤጲስ ቆጶስ ፤ ቀሳውስት ፤ ዲያቆናት አድርገው ሾሙን እንጂ» (ቅዳሴ አትናቴዎስ ቁ ፩)

ክህነትን መቀበል ስሚሽ

ሥልጣነ ክህነት ለወንዶችም ቢሆን ለሁሉም የሚሰጥ አይደለም። ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ «ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካሙን ሥራ ይመኛል» (፩ኛ ጢሞ ፫፥፩) ብሎ እንደተናገረ ክህነትን መሻት በጎ ነው። ቢሆንም ማንም ስለተመኘ ብቻ የሚያገኘው አይደለም። ለዚህ በቅቶ ሲገኝ ነው እንጂ። ክህነት በፈቃደ እግዚአብሔር ብቻ የሚገኝ ነው። ሰው ክህነትን የቱንም ያህል ቢመኝ ያለ ፈቃደ አምላክ ሊያገኛት አይችልም።

በወንጌል «መኑ አምኔክሙ ቡኪዞ ዘይክል ወሰኮ በዲበ ቆመ አሐደ አመተ / ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?» ተብሎ የተጻፈው ለክህነትም ይተረጎማል። በቁመት ላይ አንድ ክንድ መጨመር በመሳርያ ክህነት ከፍ ማለትን የሚወክል ሲሆን ሰውም በመጨነቁና በመጠበቡ ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር ክህነትን ገንዘብ ማድረግ እንደማይቻለው ያስረዳል። (ማቴ ፮፥፳፯)

ሥርዓት አፍርሶ ሕገ እግዚአብሔር ጥሶ በድፍረት መቀበል የሚሻም አይጠቀምም። «አሌ ሶሙ ለእለ ይትዓደዉ ሕገ ክህነት እስመ በፈቃድየ ይሰየም ካህን / የክህነትን ሕግ ለሚደፋፈሩ ወዮላቸው ካህን በእኔ ፈቃድ ይሾማልና» በማለት ጌታችንም ተናግሮአል። (ተአምረ ኢየሱስ ፫፥፱)

ክህነት ራስን በመስጠት የሚኖሩለት መንፈሳዊ ሕይወት እንጂ

አርፋለች።

መተዳደሪያ ሙያ ወይም የኑሮ አማራጭ አይደለም። በእንዲህ ዓይነት ሃሳብ ክህነት ውስጥ የሚገባ ወይም የገባ ሰው ቤተ ክርስቲያንን እንደ መሥሪያ ቤት፤ መንፈሳዊውን አገልግሎት እንደ ሥጋዊ ሥራ ቆጥሮ ስለሚኖር ጣዕመ መንፈስ ቅዱስን ሊቀምስና በመንፈሳዊ ሕይወቱም ሊያድግ አይችልም። የአገልግሎት ጊዜውንም ከሌሎች ጋር በመናቆርና በሽኩቻ እያሳለፈ ከመንፈሳዊው በረከት ይለያል። ስለዚህ ሥልጣነ ክህነትን የሚቀበሉ ሁሉ ስለ ክህነት ምንነት አስቀድመው ሊረዱ ይገባል። የተቀበሉትም እግዚአብሔር በሥጋዬ ይቀሥፈኛል በነፍሴ ይፈርድብኛል ብለው በፍርሃት ሊያገለግሉ ይገባል።

ክህነትን መቀበል መሻት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተመሰገኑ በጎ ምኞቶች አንዱ ነው። ‹‹መልካም ምኞት›› ተብሎም ተጠርቷል። (፩ጢሞ. ፫÷፩) ምንም ቢሆን ክህነትን መመኘት ራሱ በጎ ነው። ነገር ግን የክህነትን ምንነትና ኃላፊነት ከመረዳት ጋር ፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከማገልገልና ነፍሳትን ለማዳን ከማሰብ ቢሆን የተሻለ ነው። ምንም እንኳን ክህነት ያለ እግዚአብሔር በእርሱ ላይመረጡ ሊገኝ የማይችል ቢሆንም ለመመረጥም ዝግጁ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል።

እዚህ ላይ *«ካህን በእግዚአብሔር ምርጫ ብቻ የሚሾም ከሆነ የሐዲስ ኪዳን ክህነት ብቁ ሰዎች ሁሉ የተሰጠ መሆኑ ምኑ ላይ ነው? ፣ ሰተመረጡት ብቻ የሚሰጥ ነው እንጂ»* የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድና ምርጫ ያለበት መሆኑ የሐዲስ ኪዳንን ክህነት ለሚበቁ ሁሉ የተሰጠ ከመሆን አይከለክለውም።

አንድ ሰው ለቤት መሥሪያ እንጨት ፈልጎ ከጫካ ቢወርድና ቤቱን ለመሥራት የሚሆኑ ጥሩ እንጨቶችን መርጦ ቢወስድ አጻላ ሊባል አይችልም። ምክንያቱም ይህ ሰው ለቤት መሥሪያ ይሁኑ ብሎ እንጨቶችን አልለየም ፣ ምቹ ሆነው ያገኛቸውን መረጠ እንጂ። እግዚአብሔርም ሊመርጥ አድልቶ አይደለም። ይህንን ፈሪሳውያን

እንኳን ያፈዙ መስሎአቸው ሳያውቁ «ለማንም አታዳላም የሰውን ፊትም አትመለከትምና» ብለው መስክረውለታል፡ (ማቴ ፳፪÷፲፮) ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲመርጥ ሆኖ መገኘትም ያስፈልጋል። «ይታዘዙ ዘንድ ለተመረጡት» በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ በመልዕክቱ የተናገረውን አበው በዚህ መልኩ ተርጉመውታል። (፩ኛ ጴጥ ፩÷፩ ትር.) ይህ ማለት ግን *ለክህነት ያልተመረጠ ሁሉ ጠማማ ነው ወይም ለክህነት የበቃ ሁሉ የተቃና ነው* ማለትም አይደለም። የእግዚአብሔር ምርጫ ሰተለያየ ጸጋ ነውና ለክህነት ያልበቃ ሰው እግዚአብሔር ይጠላዋል ማለትም አይደለም።

ክህነትን ለመቀበል የሚያበቃ ትምህርት ቢኖራቸውም ክህነት ሊሰጣቸው የማይገባና አመክሮ የሚያሻቸውም አሉ። ለምሳሌ ከመናፍቅነትና ከአረማዊነት የሚመለሱ ንዑሳ ክርስቲያንን ምንም ቶሎ ቢማሩ እንኳን ቶሎ ክህነት መስጠት አይገባም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለካህን አመራረጥ እንዲህ ሲል ተናግሮአል፡- «በትዕቢት ተነፍቶ በዲያቢሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።» በማለት። (፩ኛጢሞ.፫÷፮)

«በትዕቢት ተነፍቶ እንዳይወድቅ» የሚለው ቃል ከኑፋቄ የተመለሰውን ወዲያው ክህነት ቢሾሙት *«ሰው አጥተው ነበር?! ፣እንደመጣሁ ሾሙኝ! »* ብሎ ይታበይልና ነው። በአደባባይ የመናፍቃንን ሴራ ስላጋለጠ ፣ የነበረበትን ስለነቀፈ ብቻ ደርሶ መሾም አይገባም። የመናፍቅ መመለስ ትልቅ ጉዳይነቱ ሰተመለሰው ሰው ነው እንጂ ሰልዕልት ቤተክርስቲያን አይደለም። በመመለሱም እሱ ይጠቀም ይሆናል እንጂ ቤተ ክርስቲያን የምታገኘው አዲስ ነገር የለም ፤ በውቅያኖስ ላይ አንድ ማንኪያ ውሃ የመጨመር ያህል ነው እንጂ።

እንዲሁም ተመለስሁ ያለው መመለሱ የእውነትም ላይሆን ይችላል። ኑፋቄን ለመዝራት ፣ ነበርኩበት ሁሉን አይቼዋለሁና

ለማለትናሌሎችን ለማስካድ እንዲመቸውም ሊሆን ይችላል። ይህ ሁሉ በጊዜ ብዛት ሊታወቅ የሚችል ስለሆነ ክህነትን ሳይሰጡ መጠበቅ ለዚህ ይጠቅማል። እንዲህ ላለው ሰው ቸኩለው ክህነት ቢሰጡት ግን ቅድስቲቱን ክህነት ለማይገባው በመስጠታቸው እንድትረገጥ ያደርጋሉ ፤ ቤተ ክርስቲያንንም ያስነክሱአታል። «ብእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሱአችሁ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ ዕንቁዎቻችሁንም በእርያዎች ፊት አትጣሉ» እንዲል (ማቴ. ፯፥፮)

ክህነት ከላይ እንደተቀመጠው በፈቃደ እግዚአብሔር ብቻ የሚገኝ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር ሳይመርጣቸው ራሳቸውን ለክህነት መርጠውና ይገባናል ብለው የተነሱት ቆሬ ፤ ዳታንና አቤሮን ምድሪቱ አፍዋን ከፍታ ውጣቸዋለች፤ በሕይወታቸውም ሲያል ወርደዋል። (ዘኁ ፲፮፥፩-፴፯)

ንጉሥ ያዝያንም ሌላው ራሱን በድፍረት የካነ (ካህን ያደረገ) ነበረ ፤ ይህ ንጉሥ ሊቀ ካህናቱ በቀኙ ሲቀመጥ ይቃወም ነበር ፤ እነርሱም «ወካህን ይነብር በየማኑ/ ካህን በቀኙ ይቀመጣል» ይላል ይሉታል። ዳግመኛም ካህኑ ፍርዱን ሲገስበት (ሲለውጥበት) ይቆጣል ፤ ክህነት ከመንግሥትነት እንደያመትበልጥ ነግረው ይረቱታል። ካህኑ ከእርሱ ይልቅ ያማረ ልብስ ለብሶ ሲያይ ይቀናል ፤ «ካህናቲክ ይለብሱ ጽድቀ /ካህናትህ ጽድቅን ይለብሳሉ» ያለውን ለልብስ ተርጉመው ይረቱታል። በዚህን ጊዜ ንጉሡ ያዝያን ተቆጥቶ «እኔም እንጂ (እኔም እሰ) በአናቱ የአሮን ዘር ነኝ» ብሎ በድፍረት ሊያጥን ወደ ቤተ መቅደስ ገባ ፤ ካህናቱ ቢነግሩትም አልሰማም። በዚህን ጊዜ እግዚአብሔር በለምጽ ቀጣው። እስራኤል ለምጻምን እንኳን ከቤተ መቅደስ ከከተማም አያቆዩትምና አዋክበው አስወጡት እስኪሞት ድረስ በማጀት አሳለፈ። (፪ኛ ዜና ፳፮፥፲፮ ፡- ፳)

ከላይ የተመለከትናቸው ሁለት ታሪኮች ክህነትን ለማን አንሸ በማለት ፤ በትዕቢት ፤ ከክህነት ጋር ተያይዞ የሚመጣ ክብርን (አልባሳትን ፤ ተሰሚነትን ፤ ታይታን) በመፈለግ ፤ የእገሌ ልጅ ነኝ / የእገሌ ዘር ነኝ ወ.ዘ.ተ. በማለትና በመሳሰሉ ፍላጎቶች ክህነትን ለመቀበል መነሣት ከጥቅሙ ጉዳቱ የሚያመዝን መሆኑን ያስረዳሉ።

በየበዓላቱ «ልብሰ ተክህኖ አልብሰኝ» ባዮች ፤ «ከቤተ ልሔም ፈቀቅ በሉ!» ሲባሉ አሻፈረኝ የሚሉ ፤ ድርገት ሲወርድ ገለል የማይሉና መርዘው የሚመለከቱ ሁሉ ከያዝያን ታሪክ ብዙ ሊማሩ ይችላሉ። ምንም ዘመኑ ሐዲስ ኪዳን ቢሆን የመቅደሱ ክብር ግን የጨመረ እንጂ የቀነሰ አይደለም። ታቦተ ምሥዋዑም (የመሠዊያው ታቦትም) ከቀደመው ታቦት ይልቅ በሥጋ ወደሙ መሠዊያነቱ የከበረና ሥልጣን የሌላቸው ሊቀርቡት የማይገባ ክቡር መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል።

ክህነትን የሚቀበል ሰው ከሁሉም ይልቅ የክህነትን ሕይወት ለመኖርና ቤተ ክርስቲያንን ለመወከል ፤ ለሕዝብ አረኛ ለመሆን ዝግጁ መሆን አለበት። አስቀድሞም «ከመጠምጠም መማር ይቅደም!» እንዲሉ ትምህርተ ሃይማኖትንና ግብረ ክህነትን ሊማር ይገባዋል። በዚህ መጽሐፍ ሌላ ምዕራፍ ላይ በሰፊው እንደተቀመጠው ክህነትን ከተቀበለ በኋላ አንዴ ተሹሜአለሁ ሳይል እድሜውን ሙሉ ለመማር መዘጋጀት አለበት።

ሥልጣነ ክህነት በየትኛውም ዘመን በየትኛውም ቦታ ቢሰጥ የሚኖረው ደረጃና ክብር አይለያይም። ቀድመው ክህነት የተቀበሉ በኋላ የሚቀበሉትን ፤ በገዳማት የተቀበሉት በአድባራት የተቀበሉትን ፤ በገጠር የተቀበሉት በከተማ የተቀበሉትን ክህነት ፤ በምሥራቅ

የተቀበሉት የምዕራቡን ፣ በደቡብ የተቀበሉት የሰሜኑን እያበላለጡ ክህነትን ማቃለል የሰዎች ደካማ አስተሳሰብ እንጂ ምንም ዓይነት ትውፊታዊ መሠረት የለውም።

በዘመነ አሪት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር በሙሴ አማካይነት ይገናኝና ይነጋገር ነበር። ታዲያ በአንድ ወቅት ሙሴ ሰባ ሽማግሌዎችን ሰበሰበ የእግዚአብሔርንም ቃል ነገራቸው። እግዚአብሔርም በደመናው ወርዶ ተናገረው በሙሴም ላይ ከነበረው መንፈስ ወስዶ በሽማግሌዎቹ ላይ አደረገ። መንፈሱም በላያቸው ባደረ ጊዜ ትንቢትን አንድ ጊዜ ብቻ ተናገሩ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ከሕዝቡ መካከል በሰፈር የቀሩ ኤልዳድና ሞዳድ የሚባሉ ሰዎች ነበሩ። መንፈስ ወርዶባቸው በሠፈር ሳሉ ትንቢት ተናገሩ። አንድ ጎበዝ ሰው እየሮጠ መጥቶ ፦ ኤልዳድና ሞዳድ በሰፈር ትንቢት ይናገራሉ» ብሎ ለሙሴ ነገረው። ከልጅነቱ ጀምሮ የሙሴ አገልጋይ የነበረው የነዌ ልጅ ኢያሱ፦ «ጌታዬ ሙሴ ሆይ ከልክላቸው» አለው። ሙሴም፦ «የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ነቢያት ቢሆኑ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ መንፈሱን ቢያወርድ አንተ ስለእኔ ትቀናለህን?» አለው። (ዘኁ ፲፩÷፳፱ ፦ ፴)

ይህን ታሪክ ከክህነት ጋር በተያያዘ ብንመለከተው ብዙ ቁም ነገርን ልናነሣበት እንችላለን። እርሱ ክህነት ተቀብሎ ሌሎች ክህነት ሲቀበሉ ዓይኑ ደም የሚለብስ ፤ ክህነትን የሚቀበሉ በበዙ ቁጥር ፈቃደ እግዚአብሔርን ሳያስተውል ዘመኑ እንደተበላሸ አድርጎ የሚቆጥር ፤ እርሱ ክህነትን ከተቀበለ በኋላ የተቀበሉ ሁሉ ክህነታቸው ክህነት እንዳልሆነ አድርጎ የሚያስብ አንዳንድ ሰው ይኖራል። ይህ ዓይነቱ ሰው ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የነገ ህልውና የማያስብ ነው። የሚያስብ

ቢሆን ምእመናን ሁሉ ተምረው ካህናት ቢሆኑ እግዚአብሔር ካልከለከላቸው እርሱ ምን ችገረው? ደግሞስ የቱንስ ያህል «አይገባውም» የተባለ ሰው ቢቀበላት ቅድስቲቱ ክህነት ትረክሳለችን? አትረክስም።

በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የተቀመጠውን መሥፈርት እስካሟላ ድረስ ማንኛውንም ምእመን ከክህነት የሚያግደው ነገር የለም። አፍአዊ ገጽታ ፤ ባዕለጸግነት ፤ ከተሜነት ወ.ዘ.ተ. ብዙዎች እንደሚገምቱት ከክህነት አያግድም። ግልጽ ለማድረግ ያህል አንዳንድ ጊዜ ውጪአዊ ገጽታን ብቻ በመመልከት እና ሰውን በመልክዓ ነፍሱ (በነፍሱ መልክ) ባለማየት ለክህነት እንደማይሆን የሚያስቡ ይኖራሉ። አንዳንዶች ደግሞ ምድራዊ ባዕለጸግነት ያለው ወይም የባዕለጸጎች ልጅ ክህነት ቢቀበል ዝቅ እንደሚል የሚያስቡና «አንተማ ዮትልቅ ሰው ልጅ ነህ...ነ» ብለው የሚያከለክሉ የገንዘብ አምላኪዎች ፤ ልጃቸውን የሚከለክሉና በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንደ ክፉ ነገር «ቁስ ሆነህ ልትቀር!?» የሚሉ ይኖራሉ። ነገር ግን ያክህነትን ክብር አለማወቃቸው እንጂ ልጅን ለክህነት ማድረስ ራሱ መንፈሳዊ ዋጋ አለው። «ልጃቸውን አስተምረው ለክህነት የሚያበቁ ንጹሕ መሥዋዕትን እንዳቀረቡ ይቆጠርላቸዋል።» /ተአምረ ኢየሱስ/

በሌላ በኩል ደግሞ የከተማ ልጅ ፤ ጸዳ ያለ ልብስ የለበሰ ወጣት ለክህነት የሚሆን የማይመስላቸውም አሉ። እርግጥ ነው ይህ አስተሳሰብ ያለ ምንም ምክንያት የመጣ አይደለም። በከተማ ከሚታየው ሥርዓት የለሽ የወጣቶች ሕይወት በመነሣት «ተቀብሎ አክብሮ አይዘው ይሆን?» ከሚል ሥጋት የመነጨም ነው። ይሁንና የከተማ ልጅ የሆነ ሁሉ ክህነትን ጠብቆ አይይዝም ብሎ መደምደም አይቻልም። ገጠር ተወልዶና አድጎም መሬት የማይበቃውም አለ። ሰውን ከኃጢአት

የሚከለክለው የከተማ ወይም የገጠር ልጅ መሆኑ ሳይሆን እግዚአብሔርን መፍራቱ ነው።

ምዕራፍ ሁለት

የካህናት ሥልጣን

እጅግ የከበረ ሥልጣን

የሐዲስ ኪዳን ሥልጣነ ክህነት በሥጋና በነፍስ በሰማይና በምድር ፣ በሰውና በመላእክት ላይ ነውና እጅግ የከበረ ደገኛ ሥልጣን ነው። የክህነት ሥልጣን ከሥልጣናት ሁሉ ከፍ ያለች ናት። ሌላው ቀርቶ የክህነት ሥልጣን ንጉሥ ሥልጣን ይበልጣል። ምክንያቱም ነገሥታት ሥጋን ለመጠበቅና ለማስተዳደር የሚሾሙ ሲሆን ካህናት ግን በእግዚአብሔር የሚሾሙት ሥጋንና ነፍስን ከጥፋት ይጠብቁ ዘንድ ነው።

ነፍስ ከሥጋ የሚበልጠውን ያህል ክህነት ከመንግሥት ይበልጣል። ፍትሐ ነገሥት «በከመ ነፍስ ትከብር እምሥጋ ከማሁ ክህነትኒ ትትሌዓል በኵር እመንግሥት /ነፍስ ከሥጋ እንደምትበልጥ እንደዚሁ ክህነት በክብር ከመንግሥት ትበልጣለች።» (ፍት.ነገ.መን, ፱፥፪) ሥጋ በዚህች ምድር ፈርሳና በስብሳ የምትቀርና በሌላ አካል የምትተካ ስትሆን ነፍስ ግን ወዚህች ምድርም በወዲያኛውም ዓለም የምትኖር ሕያዊት ናት። የመንግሥትነት ሥልጣንም በዚህች ምድር ሽረት ባይገኝም እንኳን በጎልፈት /በሞት/ የሚገታ ነው። የክህነት ሥልጣን ግን በወዲያኛውም ዓለም የማያቋርጥ ነው።

ሥልጣነ ክህነት [5]የጸጋ አምላክነት ሲሆን ካህናትም የጸጋ

[5] አምላክ የሚለው ቃል ‹መለከ› ገዛ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ገዥ የሚል ትርጉም አለው። እግዚአብሔር በባሕርይው ፈጥሮ የሚገዛ ጌታ ሲሆን

አማልክት ናቸው። በመዝ ፹፪÷፮ ላይ «እግዚአብሔር በአማልክት መካከል ቆመ ... እስከመቼ ሐሰትን ትፈርዳላችሁ ... ለድሆችና ለምስኪኑ ጽድቅ አድርጉ ... እኔ ግን የልዑል ልጆች ናችሁ አልሁ» ተብሎ የተጻፈው በሥልጣን ካህናት ለተሾሙ ለካህናትና በምገበራቸው እግዚአብሔርን ሳገለግሉ ቅዱሳን ነው። በጸሎተ ኪዳን ላይ አባቶች « . . . *ክመ አምሰብኬ ይኩኑ ለማልክተ* / ከሰው ወገን አማልክት ይባሉ ዘንድ ላመኑብህ ለመምህራን ቅን ልቦናን የሰጠህ» የሚሉትም ለዚህ ነው። (ኪዳን ዘነግህ)

የክህነትን ሥልጣን ክሁሉ የከበረ የሚያደርገው አንድም መላእክት ሊኮቱት የማይቻላቸውን ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደውን የአምላክ ሥጋና ደም የመፈተት ሥልጣን የሚሰጥ መሆኑ ነው። ‹‹ዘኢተንበረ ለመላእክት ተገብረ ለካህናት›› /ለመላእክት ያልተደረገ ለካህናት ተደረገ/ እንዲል።

አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ እንደተናገሩ፦ «ይህን ኤሳት ያለ ንጠት ሳይፈራ የሚጫስ ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ ለመጻሰሱ አንክሮ ይገባል። በመሠዊያ ላይ ይህን ሕብስቱን የሚፈትተው ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ አንክሮ ይገባል! ብላቴናውን በአባቱ ፊት በእናቱ ራስ ላይ ፈአኑሮ የሚሠዋ ይመስላል ፤ የምሥጢሩን ወይን በጽዋው የሚያዘጋጀው ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ ለማዘጋጀቱ አንክሮ ይገባል! የልጁን ደም በአባቱ ፊት በእናቱ ላይ ሲንጸፈጸፍ የሚቀዳ ይመስላል ፤ ሙሽራውን ያለ ወቅለምት የሚሠዋ ፤ ሙሽራይቱን የሙሽራውን ሥጋ እንድትበላ የሚጠራት ፤ ልጆችዋንም በአባታቸው ሥጋ የሚያሳድጋቸው ይህ ካህን እንደምን ያለ ነው? ለዚህ አንክሮ

ለቅዱሳኑ ደግሞ አምላክ /ገዝ/ እንዲባሉ ሰጥታቸዋል። /ዘጸ. ፯÷፩፤ ፬፱መ-

ይገባል! የእግዚአብሔርን በግ ለመሠዋት ጣቶቹ ወቅለምት የሆኑለት ይህ ካህን እንደምን ያለ ነው?! ለዚህ አንክሮ ይገባል! አንደበቱም መናፍቃንን ከምእመናን ለመለየት ሰይፍ ሆነለት ፤ ምእመናንን ከአምላካቸው ደም አንድ የሚያደርጋቸው ይህ ካህን እንደምን ያለ ነው?! ለዚህ አንክሮ ይገባል!» አርጋኖን ዘሰኑይ

የካህናት ሥልጣን በምን ላይ?

በነፍስና በሥጋ ላይ

ካህናት በሥጋ በሚገጥሙ ችግሮች መፍትሔ የመስጠትና በነፍስም ሥርየትን የመስጠት ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል። እንኪን የሐዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ካህን እንኪን ሥርየተ ኃጢአትን የመስጠት ሥልጣን ነበረው። (ዘሌ ፭÷፮) ፤ ዘሌ ፬÷፭ ፡- ፳፮) ይሁንና የቀደሙት ካህናት የሚሰጡት ይቅርታ ፍጹም አልነበረም። ከሥጋ መቅሠፍት እንጂ ከዘላለም የነፍስ ቅጣት አያድኑም ነበር ፤ የሐዲስ ኪዳን ካህናት ግን በምድር (በሥጋ) በሰማይ (በነፍስ) የመፍረድ (የማሰርና የመፍታት) ሥልጣን ተሰጥቶቸዋል። «*ዘወሀበከነ . . . ስመ ንፍቃህ ዘኢይትፈታሕ / የማይፈታውን እንፈታ ዘንድ የሰጠኸኝ*» (ጸሎተ ኪዳን) እንዲል።

የካህናት በነፍስና በሥጋ ላይ የመፍረድ ሥልጣን በአጸደ ሥጋ ሳሉ ብቻ ሳይሆን ከሞቱ በኋላም የሚዘልቅ ነው። ይህም በቅዱስ ባስልዮስ ታውቋል። እንዲት ሴት ዘመኗን ሁሉ ኃጢአቷን እየጻፉች ትኖር ነበር። ቅዱስ ኤፍሬም ዘንድ ሄዳ ብታሳየው ብዙውን ኃጢአቷን ፍቆላት አንድ ብቻ ሲቀር «ይህ ለእኔ አይቻለኝም ፤ ለቅዱስ ባስልዮስ

ዘጸ/

ነው እንጂ» ብሎ ላካት። ከባስልዮስ ዘንድ ብትሄድም «ለእኔ አይቻለኝም ለቅዱስ ኤፍሬም ነው እንጂ» ብሎ መለሳት። ተመልሳ ስትመጣ ቅዱስ ኤፍሬም ተመልሳ ወደ ቅዱስ ባስልዮስ እንድትሄድ ያደርጋታል።

ስትሔድም ሞቶ እንደሚቆያትና ኃጢአቷ የተጻፈበትን ወረቀት በአስከሬኑ ላይ እንድትጥለው አዘዛት። ይህን ትእዛዝ ተቀብላ ስትሄድ ሞቶ አገኘችው። በቅዱስ ባስልዮስ አስከሬን ላይ ያልተፋቀ የበደሏን ጽሕፈት ብትጥለው ተፍቆላታል። ይህም የካህናትን መዓርግ ደግነት ያጠይቃል። በሕይወተ ሥጋም ሳሉ ከሞቱም በኋላ ኃጢአትን እንዲያስተርዩም (እንደሚያስተሰርዩም) ያስረዳል። (መቅድመ ውዳሴ ማርያም)

ካህናት ለሥጋዊ ነገር ጉልበትና አቅም ባይኖራቸውም ሥልጣናቸው ግን ከሁሉ በላይ ኃያል ያሰኛቸዋል ፤ ከምድር ኃያላን ከነገሥታት በላይ ፈራጆች ያደርጋቸዋል። ካህናት በገብረ ጉንዳን የሚመሰሉትም ለዚህ ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን ጻሪ ጋሪ ስለሆነችው ገብረ ጉንዳን የተናገረው ለካህናት ይተረጎማል። ‹‹ወደ ገብረ ጉንዳን ተመልከት መንገድዋን ተመልክተህ ጠቢብ ሁን ፤ አለቃና አዛዥ ሳይኖራት መብልዋን በበጋ ታሰናዳለች ፤ መኖዋን በመከር ትሰበስባለች›› የሚለው ሃሳብ በትርጓሜ «ወደ ቁስ ተመለሱ ጻሪ ጋሪ እንደሆኑ እወቁ በሥራቸው አንዲሠሩ ፤ ሰነፎችንና አላዋቂዎች ነገሥታት ሕይወት ሊሆኗቸው ሥርየታቸውን ይቀበላሉ። በሁለቱ ዘንድ የሚከበሩ የሚወደዱም ናቸው። በኃይላቸው (በሥጋዊ ኃይል) ድኩማን ናቸው። በአሞር ታጥቀው ጋሻ ነጥቀው ዘገር ነቅንቀው አይዋጉምና በሥራቸው ግን ጽኑዓን ናቸው። ከዚህ (ከምድር) የለዩት በወዲያኛው (በሰማይ) ይለያል። ከዚህ የፈቱት ከወዲያም ይፈታል።» ተብሎ

ተተርጉሞአል። (ምሳ ፮፥፮ ትር)

ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ «ከጢሱም አንበጣዎች ወደ ምድር ወጡ የምድርም ጊንጦች ሥልጣን እንዳላቸው ሥልጣን ተሰጣቸው።» (ራእ ፱፥፫) በማለት የተናገረውም በምሥጢር ሲፈታ በአፏም በጅራቷም በምትናደፍ በጊንጥ የተመሰሉት በምድር የፈረዱት በሰማይ የማይገሰሰባቸው ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው። አንድም በአባብና በጊንጥ በሚመሰሉ በአጋንንት ላይ ሥልጣን ያላቸው ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው። አንበጣዎች የተባሉ ደግሞ በአግረ ሐዋርያት የተተኩ ሥልጣናቸውን ገንዘብ ያደረጉ ካህናት ናቸው።

ካህናት በሥልጣናቸው የሚናገሩትን ቃለ ግዝት መጣስ ፣ ያወገዙትን ግብር ማድረግ ያዘዙትን አለማድረግ እግዚአብሔርን መናቅ ነው። ዳግማዊ አጼ ምኒልክ እንደተናገሩ፦ በ፲፰፻፹፪ ዓ.ም. በትግራይ ክፍለ ሀገር አዝላ በምትባል ሥፍራ ሠራዊታቸውን ይዘው በመጡ ጊዜ ቤተ ክርስቲያንን የዘረፈ ወታደር ሁሉ ንዋያተ ቅድሳትን እንዲመልስ አዋጅ አስነገሩ ፤ ካህናትም መልሱ ብለው አዘዙ የማይመልሰውን አወገዙ። ይሁንና ከንጉሡ ወታደሮች መካከል የነበረ አረማዊ ወታደር ከመቅደስ የዘረፈውን መስቀል ላለመመለስ ወደ ኮራብ ሸሸ። ይህም ነገር ከአጼ ምኒልክ ጆሮ ደረሰ። ንጉሡም ወደ አመቤታችን ቤተ ክርስቲያን በመሄድ «አመቤቴ ሆይ የዚህን የሰነፍ ጭፍራ ያደረገውን መገዳደርና በልጅሽ መስቀል ላይ የፈጸመውን ድፍረት እንዲሁም በሰማይና በምድር ያስሩና ይፈቱ ዘንድ ሥልጣን በሰጣቸው በካህናት ላይ ያደረገውን ተሳልቆና ዝብብት ተመልከች» በማለት አለፉ። ከዚህ በኋላ ይህ አረማዊ በደዌ ተያዘ በሕልምም ይጨነቅ ጀመር። በዚህን ጊዜ መስቀሉን መለሰ መስቀሉም አባ ኃይለ ሥላሴ በሚባሉ ተንቤን በሚገኙ መነኩሴ እጅ ወደ አብርሃ ወአጽብሐ ቤተ ክርስቲያን ተልኳል። (ተአ.ማር. ፫፻፵፰)

ይህ ታሪክ የካህን ግዝትን መናቅ ማቃለል በነፍስም በሥጋ የሚያስፈርድ ለመሆኑ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው።

አገልጋዮቹን መናቅ ደግሞ እግዚአብሔርን መናቅ ነው ፤ አገልጋዮቹንም መፍራት እግዚአብሔርን መፍራት ነው። በአንድ ወቅት ነቢዩ ሳሙኤል ላይ ሕዝቡ ዐምጸው ‹‹አንተ ሸምግለሃል በአንተ አንመራም ፤ ንጉሥ አንግሥልን!›› ብለውት ነበር። ነቢዩ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ‹‹በእነርሱ ላይ እንዳልነግሥ እኔን አንጂ አንተን አልናቁም›› ብሎት ነበር። (፩ሳሙ. ፰፥፬-፯) በአንጻሩ የእግዚአብሔር ቁጣ በወረደ ጊዜ ‹‹ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርንና ሳሙኤልን ፈሩአቸው።›› ይላል። ፩ሳሙ. ፲፪፥፲፰ ስለዚህ አገልጋዮቹን መፍራት እርሱን እንደ መፍራት ፤ አገልጋዮቹ ካህናትን መናቅም እርሱን እንደ መናቅ ነው። ከሳሙኤል ታሪክ ሳንወጣ ንጉሥ ሳኦል ሥልጣኑን የተቀማውም መሥዋዕት የማሳረግ ሥልጣን የነበረውን ሳሙኤልን ሳይጠብቅ እርሱ የሚቃጠል መሥዋዕትን በማሳረጉ ነበር። (፩ሳሙ.፲፫፥፰-፲፬) ነገሥታት ምንም ኃያላን ቢሆኑ ካህናትም ምንም ያህል የምግባር ጉድለት ቢታይባቸው የክህነት ሥልጣን እጅግ የከበረ መሆኑ መዘንጋት የለበትም። የካህናትን ሥልጣን ከነገሥታት ጋር የምናነጻጽረው ሰዎች ለንጉሦቻቸው ይገዛሉና ንጉሡ ለካህናት ይገዛል ማለት ደግሞ ካህናት የገሹ ገሹ መሆናቸውን ያስረዳል።

በቅዱሳን መላእክት ላይ

«ዘኢተገብረ ለመላእክት ተገብረ ለካህናት /ለመላእክት ያልተደረገ ለካህናት ተደረገ» እንዲል የካህናት ሥልጣን ከመላእክት ሥልጣን በላይ ነው። ካህናት መላእክት ሊቀርቡት የማይቻላቸውን

ግሩም አምላክ ሥጋውና ደሙን ይፈትታሉ። (ኢሳ ፮፥፮) ስለዚህ የካህናት ሥልጣን ከመላእክትም ሥልጣን በላይ ነው።

ካህናት መላእክትን የማውገዝ ሥልጣን አላቸው። ቅዱስ ጳውሎስ «ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን የሚሰብክላችሁ ቢሆን የተረገመ ይሁን» (ገላ ፩፥፰) ብሎ እንደተናገረ ካህናት በሥልጣናቸው ከመላእክት በላይ ናቸው። ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ ደግሞ ፮ኛ ቆሮ ፮፥፫- «በመላእክት ስንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን?» በማለት በትዳር ጉዳይ በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ፍርድን ለማግኘት ካህናትን ትተው ወደ ዓለማዊ ፍርድ ቤት የሚሄዱ ምእመናንን ገሥጾአል። በዚህ ቃሉም በመላእክት ላይ መፍረድ እንደሚችሉ ገልጾአል። የሐዲስ ኪዳኑ ካህን ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም ለእግዚአብሔር መልአክ ሊሰግድ ሲል መልአኩ ‹‹ዮሐንስን ከመላእክት የተካከለ የንጽሕና ሕይወት /ድንግልና ፤ አለመሞት../ እንዲሁም የዮሐንስን መዐርግ በማሰብ እንዳታስቀሥፈኝ የማለት ያህል ተደናግጦ ‹‹እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ከወንድሞችህም /ከሐዋርያትም/ የኢየሱስ ምስክርም ካላቸው ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ›› ብሎት ነበር። የመልአኩን ሃሳብ የተረዳው ዮሐንስ ግን በትሕትና መስገዱን በድጋሚ ፈጽሞታል። ይህ ታሪክ በኦርቶዶክሳዊ መነጽር ስናየው ከብረ ከህነት ከክብረ መላእክት እንደሚበልጥ ያስረዳል። /ራእ. ፲፱፥፲፣ኛ፱፥፱/

በቤተ ክርስቲያናችን መጻሐፍት የተመዘገበው የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ታሪክም ይህን እውነታ ያጎላል። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ንጉሥ አርቃድዮስና ንግሥት አውዶክያ የተባሉ ወዳጆች ነበሩት። ልጅ

እየወለዱ ይሞትባቸዋል። ምክንያቱን ቢጠይቁ «ደግ ሰው (ክርስትና) ባያነሣላችሁ ይሆናል» አሏቸው። ከዮሐንስ አፈወርቅ የበለጠ ደግሰው አለን? ብለው ሴት ልጅ ሲወልዱ *መጥተህ አንሣልን* ብለው ላኩበት።

ሲሔድ በመንገድ መልአኩን አገኘው። (የበቃ ክንጻሬ መላእክት /መላእክትን ከማየት መጓርግ/ የደረሰ ነውና) *«መዴት ትሔዳለህ?»* አለው። *«አሁን አንተ የምትሄደባትን ብሳቴና ነፍሷን ከሥጋዋ ሲይተህ አምጣ ብሎኝ አሄዳለሁ»* አለው። *«ዳግመኛ በጥምቀት እንድትወለድ ነና ናትና ቆየኝ ላጥምቃት»* ብሎት ሔደ። አጥምቋት በሌላ መንገድ ተመለሰ። የካህናት መዓርጋቸው ደግ እንደሆነ እንዲታወቅ ይህ መልአክ ወደ ላይም ወደ ታችም ሳይል ዐሥር ዓመት ከዚያው ሥፍራ ቆሞ ኖረ። በዐሥር ዓመቷ ታጨችና መጥተህ ባርካት ብለው ላኩበት። በዚያ መንገድ ሲሄድ መልአኩን ቆሞ አገኘው። «ምነው ከዚህ ቆመሃል?» አለው። «የካህናት መዓርጋቸው ደግ አይደለምን? ወዲያ ወዲህ ያሰኛ ልን? አንተ ቆይ ካልከኝ ወዲህ ወዲያ ብዬ አላውቅም» አለው። *«አጥፍቼአለሁ»* ብሎ *«ሂድ የታዘዝከውን አድርግ»* አለው።

ነፍሷን ከሥጋዋ ለይቶ ከሄደ በኋላ ቢደርስ ሞታ ሲላቀሱ አገኘ ። *«ተዉት ነገሩ ከወደ አግዚአብሔር የሆነ ነው»* ብሎ አጽናንቶአቸው ሄዷል። *«ወሐዋርያት መላእክተ በሰማይ ኮነኑ* /ሐዋርያት በመላእክት በሰማይ ፈረዱ» እንዲል የሐዋርያትን ሥልጣን የያዙ ካህናት በመላእክት ላይ የመፍረድ ሥልጣን አላቸው (ማኅሌተ ጽጌ)

[6] (በምሥጢራት አፈጻጸም ላይ የካህኑ ደግነትና ክፉነት ተጽዕኖ ያለው ሆኖ አይደለም። ይህ የሰምቼ የግል አስተያየት ነው ፤ ግምታቸው ልክ እንዳልሆነ ከታሪኩ መረዳት ይቻላል ፤ የተወለደችውን ልጅ ወዲያው እንዳትሞት ያደረጋት የመልአኩ በግዝት መታሠር እንጂ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ ክርስትና መነሣቷ አይደለም።)

አባ ሳሙኤል ዘደብረ ቁልሞንም ቀውስጦስ የተባለው መልአክ ትእዛዘ እግዚአብሔርን ባለመፈጸሙ ጸጋውን ቢያጣና ከምድር ቢቀር በምልጃቸው ክንፈ ጸጋውን አስመልሰውለታል። እነዚህ ታሪኮች የሚያስረዱት የካህናትን ሥልጣን ከመላእክት የከበረ እንደሆነ ነው።

በሠራዊተ አጋንንት ላይ

አባቶቻችን *«ዘወሀብከነ በመንፈስ ኀጢኦ ሰጸላዒ* / በመንፈስም ሠራዊተ አጋንንትን ድል እንነሣ ዘንድ የሰጠኸን» በማለት በኪዳን ጸሎት እንደሚያመሰግኑት ካህናተ ቤተ ክርስቲያን አጋንንትን የማውጣትም የማዘዝም ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል። ስርየተ ኃጢአትን የማወጅ የማሰር እና የመፍታት ፣ የመንግሥተ ሰማይን ቁልፍ የመያዝ ሥልጣን ለተሰጠው ካህን አንድን የወደቀ መልአክ ማሸነፍ እንደ ትልቅ ሥልጣን ሆኖ የሚነገርለት አይደለም። አጋንንትን መርታትም ካህናት ሊሠሩት የሚችሉት እጅግ ትንሹና ከዓትም በታች የሆነ ሥራ መሆኑን እናምናለን።

በክርስትና አጋንንትን ከማውጣት በላይ የሆኑ ጸጋዎች አሉ። የካህናት ሥልጣን መለኪያ አጋንንትን ማውጣትም አይደለም። አጋንንት እነርሱ ያልጮኹለት ካህን ካህን ያልሆነ ያህል በምእመናን ሕሊና እየሣሉ ቤተ ክርስቲያንንም ከማመን ይልቅ በማየት የሚመላለሱባት ስፍራ ሊያደርጓት ይጥራሉ። ጌታችን አጋንንትን አወጣን ብለው ደስ የተሰኙ ካህናትን (ቅዱሳን ሐዋርያትን) ‹አጋንንት ተገዙልን› ብለው በነገሩት ጊዜ «መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ ፤ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለተጻፈ ደስ ይበላችሁ» ብሎአቸዋል። (ሉቃ ፲÷፳) ካህንም አጋንንት ከማውጣት ይልቅ ብጹዓን

አግብርት /የተመለጎ ባሪያዎች/ ከተባሉት ከካህናትና ለመንግሥተ ሰማያት ከታጨት ከክርስቲያኖች ወገን መደመሩ የሚበልጥ ክብሩ ነው። «ወገቢረ ተአምራት ወመንክራት ኢይክል ያድነን አምሥቃየ ኵነኔ / ተአምራትንና ድንቅ ነገርን መሥራት በፍርድ ከሚመጣው ሥቃይ ያድን ዘንድ አይችልም» (ተግሣጽ ፸፬) ተብሎም ተጽፎአል።

አጋንንትን ማውጣት የቅድስናና የጽድቅ ማረጋገጫ አይደለም ፣ ጸጋ ነው እንጂ። ጸጋ ደግሞ እግዚአብሔር ለፈለገው ሰው የሚሰጠው ሥጦታ ነው። ይህ ማለት ግን ያ ሰው ቅዱስና የሚናገረው ሁሉ ትክክል ነው ማለት አይደለም። «ኢታስተማስሎሙኬ ለገባሪያነ መንክራት ወተአምራት ወኃይላት ውስተ ዓለም በእለ ያረምሙ በለአምሮ / ተአምራትን የሚያደርጉትን በፈሊጥ ተባሕትዎ በያዙ (በተጋድሎ ሰዎች) አትመስላቸው፤እንደዚያ ናቸው /የተጋድሎ ሰዎች ናቸው/ አትበል።» ተብሎአልና። /ማር ይስሐቅ/

ጌታውን አሳልፎ የሰጠ ይሁዳም አጋንንትን አውጥቶ ነበር። አጋንንትን ማውጣቱ ግን አልጠቀመውም። አጋንንትን የሚያወጣ ሰው ሁሉም መንፈሳዊ ዋጋ ያገኛል ማለት አይደለም። ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጠው አጋንንትን ማውጣት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ጸጋ እንጂ ትሩፋት ባለመሆኑ ነው። ምናልባትም አጋንንትን የሚያወጣው ሰው «ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላውቃችሁም ፤ እናንተ አመጸኞች ከእኔ ራቁ ፤ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ» ብሎ ጌታችን ከተናገረባቸው ጋር ሊደመርም ይችላል። (ማቴ ፯፥፳፪) በተአምር ማመንን የለመደ ሕዝብ እምነቱ ሊጸና አይችልም። ደግሞስ የተአምር አድናቂ የሆነ ሰው «እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን

ምልክቶች ያደርጋል» ተብሎ የተነገረለት ዲያቢሎስን ሲያይ ምን ሊል ይሆን? እኛ ግን በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስም። (ራእ.፲፫፥፲፫)

አንዳንድ የዲያቢሎስን ተንኮል ያልተረዱ ሰዎች ምእመናንን አቡሃ ለሐሰት (የሐሰት አባት) (ዮሐ ፰፥፵፬) የተባለ የዲያብሎስን ምስክርነት ከካህን ቃል ይልቅ ወደ ማመንና ወደ መቀበል እየመሩዋቸው ነው። ይህም አጋንንት በየጠበል ሥፍራው ሲጮኹ የለፈለፉትን እንደ ትምህርት በመቁጠርና የአጋንንት መጮህ ለክብርት ቤተ ክርስቲያን የሚያኮራ ትልቅ ድል የሆነ ይመስል ከትምህርተ ሃይማኖት እንደሚበልጥ እንደ ትልቅ ማስረጃ እንዲደመጥ በማድረግ ነው። በተጨማሪም የአጋንንትን ልፍለፋ በመቅረጸ ድምጽና በመቅረጸ ምስል ቀድቶ ለምዕመናን በማሰራጨት ፤ ከፍ ሲልም «ይህን ካሴት የገዛችሁ ለሌላ ሰው ብታውሱ ትቀሠፋላችሁ!» የሚል ገንዘብን ያማከለ የቅጂ መብትን ማስከበሪያ ግዝት ቢጤ ማከልም የዚህ ድርጊት አሳዛኝ ገጽታዎች ናቸው።

ቅዱስ ጳውሎስ «በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ» ያለው ፤ ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ «በመጨረሻው ዘመን እንደራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባኞች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ» በማለት የተናገሩአቸው ትንቢቶች በዚህ ዘመን እየተፈጸሙ አይደለምን? (፪ኛ ጢሞ ፬፥፩ ፤ ፪ኛ ጴጥ ፫፥፫)

በአጋንንት የተያዘውን ሰው ራሱ አጋንንት የሆነ ይመስል ያለ ልክ መደብደብና ማሰቃየት ፤ አጋንንት እንዳሻው እንዲሆን መብት መስጠት ፤ የመስቀል ኃይል የሚገለጠው በበትርነት ይመስል

በመምሯነት መጠቀም የመሳለሉትን ድርጊቶች የቤተ ክርስቲያናችንን አስተምህሮ የሚቃረኑና ቤተ ክርስቲያን መዘበቻ እንድትሆን የሚያደርጉ ግብሮች ናቸው። እርግጥ ነው የጠላት ምስክርነት የታመነ ነው። ቢሆንም ግን ጋኔንን ጆሮ ሰጥተው ካዳመጡት ክህደትንም ሊዘራ እንደሚችል ማሰብ ይገባል። ስለዚህ ካህናት አጋንንት ባገኙት አጋጣሚ ክህደትና ኑፋቄን የሚዘሩ መሆናቸውን አውቀው ሲናገሩ መገሠጽና ራሳቸውንም ከውዳሴ ከንቱ ማትረፍ ይገባቸዋል።

ካህናት አጋንንትን እስከ ማዘዝ ድረስ ሥልጣን ተሰጥቶአቸዋል። ሚልኪ ቁልዝማዊ የተባሉ ቅዱስ አባት ዲያቢሎስን በሥልጣኑ ገዝቶ ፣ ለገዳም የሚሆን ደንጊያ በራሱ ላይ ደፍቶ እሸክሞ «አቤቱ ጌታ ሆይ አባብንና ጊንጥን እንረግጥ ዘንድ ሥልጣን የሰጠኸን» እያለ እየነዳ ወሰዶታል። (ስንክ.መስከረም ፩) ይህ ቅዱስ ሚልኪ ቁልዝማዊና ሌላው አባት ሳዊሮስ ዘገብሎን ደብዳቤ በመጻፍ ብቻ አጋንንትን ያወጡ ነበር። የእነዚህ አባቶች ታሪክ የሚያስረዳው ካህናት በሠራዊተ አጋንንት ላይ ሥልጣን እንዳላቸው ነው። ይህ ማለት ግን «አጋንንትን የማያወጣ ካህን አይደለም ፣ ወይም የሚያወጣ ሁሉ ካህን ነው ማለት አይደለም ፣ ምንም ሥልጣን ቢኖር የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነውና። ፩ኛ ቆሮ ፲፪÷፲፪

አጋንንትን በሚያወጡም ጊዜ ካህናት ለዲያቢሎስ ጆሮአቸውን ከሰጡ ለብዙ ፈተና ይጋለጣሉ። አጋንንት ካህንን *«ለደሎትህ ተቃጠልኩ! አንተ ጻድቅ ነህ»* ወዘተ. . . እያሉ የትዕቢት እሾህ ሊተክሉበት ይሞክራሉ። የሠራውንም ያልሠራውንም ጽድቅ እየዘረዘሩ በም መናን ፊት በማወደስ እንዲታበይና የራሱን ገድል መስማት እንዲሰምድ ያደርጋሉ። ውዳሴን ከለመደ በኋላ ግን *«ያእኔን ማንነትና ክብሬን ግለጽ»* ብሎ አጋንንትን እስከማዘዝም ይደርሳል። ስለዚህ ካህን

የአጋንንትን ሴራ መረዳትና መጠንቀቅ አለበት።

ቅዱሳን ሐዋርያት ዲያብሎስ በስውርም በግልጥም በውዳሴ ከንቱ አሽክላ ሊያዛቸው ሲሞክር ገሥጸው ያዋርዱት ነበር። ለምሳሌ በአንዲት ሴት ያደረ አጋንንት «የመዳንን መንገድ የሚነግሩዋችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው!» እያለ ሲያወድሳቸው «ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝዘንሃል።» ብለው አስወጥተውታል። (ሐዋ ፲፮÷፲፰) ይህም ሊቀ ካህናት ክርስቶስ «የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ሆይ ልታጠፋን መጣህን?» እያሉ የጮኹትን አጋንንት ዝም እንዳሰኘ በግብር ሲመስሉት ነው። (ማቴ ፰÷፳፱)

ሥልጣንና ምግባር

ካህናት ምንም በክብር ከፍ ከፍ ቢሉም ሥጋን የለበሱ ሰዎች ናቸውና በሌላው ሰው የሚመጣ ሥጋዊ ድካም በእነርሱም ላይ ሊታይባቸው ይችላል። ይልቁንም በሰው ልጆች መንፈሳዊ ክብር የሚቀናው ዲያብሎስ እርሱ ከሰማዩ ቤተ መቅደስ አፍርሶ የተባረረ አገልጋይ ስለነበር በካህናት ክብር በመቅናት ከሌላ ሰው የበለጠ ካህናትን ሊፈትናቸው ይችላል።

የካህናት ምግባር ምእመናን ከካህናት በሚያገኙት አገልግሎት ላይ የሚያመጣው አሉታዊና [7]ምናልባትም አወንታዊ ተጽእኖ የለም። ካህን በምግባሩ ቢደክም ሊቋረጥ የሚችለው በካህኑና በእግዚአብሔር መሀል ያለው መስመር እንጂ በካህኑ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙት የምእመናን መስመር አይደለም። ለዚህ ምክንያቱ

[7] ካህኑ ጻድቅ የሆነ እንደሆነ በረከቱ ያድርብናል ከተባለ በሚል ነው።

በማንኛውም በካህን እጅ በሚፈጸም መንፈሳዊ ምሥጢር ወቅት በካህኑ ሆኖ የሚሠራው ሊቀ ካህናት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ምእመናንን ያሰናክላል ከሚለው ውጪ በኃጥእ ካህን እጅ መጠመቅ ፣ ቅብዓ ሜሮን መቀባት ፣ መናዘዝና መቁረብ ሌሎችንም ምሥጢራት መፈጸም የሚያመጣው አንዳችም ችግር የለም።

በፍትሐ ነገሥት ላይ «እስመ ካህን ሕጸጸ ምግባር ከመ ማኅቶት ዘሰምዕ ውእቱ/ ምግባር የጎደለው ካህን እንደ ሰም መብራት ነው» ይላል። የሚነደው እሳት በክህነቱ ይመሰላል ፤ እሳቱ ሰሙን ያቀልጠዋል። ለሕዝቡ ግን ያበራል ኩበርሃኑ የተነሣ ጨለማ አያገኛቸውም። (ፍትሐ ነገሥት መን ፱፥፩)« ኃጢአተኛ ካህንም በኃጢአቱ እርሱ ቢጎዳም ለምእመናን ግን እርሱ ያላገኘውን ጸጋና በረከት እንዲያገኙ የሚያደርግበት ሥልጣን አለው።

ነባቤ መለኮት ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ በድርሳኑ የሰጠው ምሳሌ ደግሞ የበለጠ ይህንን ሃሳብ ግልጥ ያደርግልናል።:- ክፉ ምግባርና በጎ ምግባር ያላቸውን ሁለት ካህናት በሁለት ማኅተም ይመስላቸዋል። ማኅተሞቹ አንዱ የወርቅ አንዱ የብረት ሲሆን ያወጡላቸው የአንድ ንጉሥ መልክ ተቀርጾባቸዋል። ምእመናኑን በሰምዕ ይመስላቸዋል። ሁለቱ ማኅጸሞች ላይ ያለው የንጉሡ መልክ በሰምዕ ላይ በታተመበት ጊዜ የንጉሣዊውን አርማ ቅርጽ ለማስገኘት (ለማተም) በወርቅ ማኅተም በታተመውና በብረት በታተመው መካከል ልዩነት የለም። እንደዚሁም ካህናት ቢበድሉም ባይበድሉም የሚሰጡት አገልግሎት ግን አንድ ነው። የሚጠየቁትም በኋላ ነው። በካህን ጥፋት እግዚአብሔር ሕዝቡን አይቀጣምና።

በሌላ በኩል አንድ ምእመን በክፉ ካህን ምክንያት የደግነቱን ዋጋ አያጣም። ይህንንም ፍትሐ ነገሥት በምሳሌ ያስቀምጠዋል :-

ከንጉሥ ዘንድ አንድ ዓይነት ፈቃድ /የመፍረድ ሥልጣን/ ያላቸው ሁለት ዳኞች ነበሩ። አንዱ ደግ አንዱ ክፉ ነው። ሌሎች ሁለት መኳንንት ደግሞ አሉ። እነርሱም አንዱ ደግ አንዱ ክፉ ናቸው። እሊህ መኳንንት በዳኞቹ አማካይነት ፈቃዳቸውን ሊፈጽሙ (ሊያስፈጽሙ) ወደዱ።

ደጉ መኮንን ወደ ክፉው ዳኛ ሂዶ ፈቃዱን ይፈጽምለት ዘንድ ማለደው ፤ ክፉው መኮንን ደግሞ ወደ ደጉ ዳኛ ሂዶ ፈቃዱን ይፈጽምለት ዘንድ ማለደው። ንጉሡ ግን ሁሉን አዋቂ ነው። የሁለቱንም (የደጉንም የክፉውንም) መኳንንት ሥራቸውን ያውቃል። ስለ ግዳጃቸው (ስለሚፈልጉት ነገር) በማለዱት ጊዜ የደጉን መኮንን ፈቃድ በክፉው ዳኛ እጅ ጨረሰ። የዳኛው ክፋት የደጉን መኮንን ፈቃድ አልከለከለበትም ፤ የክፉውን መኮንን ፍላጎት ግን አዋቂው ንጉሥ ለደጉ ዳኛ ብሎ አልፈጸመለትም። የዳኛው ደግነት ክፉውን መኮንን አልጠቀመውም ይላል።

ምእመናን የካህናትን ሥልጣንና የሚያስተምሩትን ትምህርት እንጂ ምግባር መመልከት የለባቸውም። እንኳ ስለ ሐዲስ ኪዳን ደገኞቹ ካህናት ይቅርና ስለ ፈሪሳውያን እንኳ *«ኵሉ ዘይቤሉክሙ ግበሩ ወዘሰምግባሮሙሰ ኢትግበሩ፤ እስመ ዘይሜህሩ ሰብእ እሙንቱ አይገብሩ* / ‹‹ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ» ሲል ጌታችን ተናግሮአል (ማቴ ፳፫፥፫) እርሱም ማንነታቸውአ እያወቀ ከአይሁድ መምህራን አግር ሥር ቁጭ ብሎ ተምሯል። ስለ ጸሐፍት ፈሪሳውያን እንኳ

ምንም ሥራቸው ባያምር የሚሉትን አድርጉ ከተባለ ለከበሩት ሰሑዲስ ኪዳን ካህናትማ ይልቅ መታዘዝና ምግባራቸውን አለመመልከት እንዴት ይገባ ይሆን?

ካህናት ኃጢአትን ቢሠሩም ሁሉም እንደ ሥራው ይቀበላልና እነርሱን ሰበብ አድርጎ ከመንፈሳዊ ሕይወትም ሆነ ከካህናት መሸሽ አይገባም። የራስን ኃጢአት ማሰብ እንጂ ፤ በገላ ፮፣፬ ላይ- «ሰው ሁሉ ለሌላው ያይደለ ለራሱ ክብር በሚሆነው ገንዘብ ሥራውን ይመርምር ፤ ሁሉም እንደ ሥራው ፍዳውን ይቀበላልና» ተብሎ ተጽፎአል። ከዚህ ቃል ትርጓሜ ጋር የሚከተለው ታሪክ ተጽፎአል፦

አንድ ባለጸጋ ምእመን ገበሬ ነበረው። ይህን ገበሬ «*ሂድና የንስሓ አባቴን ርስት እረስ ብሎ*» ይልከዋል። ይህም ገበሬ ከመምህሪ ንስሓው ርስት ሆኖ ሲያርስ ድስት ሙሉ ወርቅ ያገኝና ሄዶ ለባለጸጋው ይነግረዋል። እርሱም «*ለእኔ ለምን ነገርኸኝ እኛማ ርስቱን ማረሳችን ፍሬ አፍሰን ልንበላ ነው? ወርቅ ለባለ ርስት ነው፤ ለእርሱ ንገረው ነገር ግን ነገርሁት አትበል ይጣላሃል*» አለው። ሄዶ ነገረው ያም ቄስ «*የምናወጣበትን ሲታሰናዳ ቆየኝ*» ብሎ እርሱን ሰዶ ሰይፉን ሲስል አመሸ። ሔደው ቆፍረው ወርቁን ካወጡ በኋላ አንገቱን በሰይፍ ብሎ ገድሎታል። ወርቁም ደም ተፈንጥቆ ቢያርፍበት ብረት ሆኗል። ያ ሰውም (ባለጸጋው) ከአሁን አሁን ይመጣል እያለ ቢጠብቅ ቀረ። ምን ሆኖ ይሆን እያለ እየፈለገ ሲሄድ ዐሠረ ደም (የደም ምልክት) አገኘ። «*ይ ከፉ ተጣልቶታል ልጣላው?*» ብሎ አሰበ። መልሶ «ምን ዕዳዬ! አንተም አንድ ጊዜ ብጹዓን አግብርት (ካህናት) ከተባሉት ተቆጥረሃል። እኔም ከእንግዲህ በቄስ እጅ ሥጋ ወደሙን አልቀበልም ቤተ እግዚአብሔርም አልገባም» ብሎ ተከለከለ።

በኋላ መልአክ የምታየው ነገር አለና ወደ ቤተ እግዚአብሔር ውጣ አለው ፤ ወጣ። ሰይጣን በዚያ ቄስ እጅ ላይ ሆኖ በእሳት ልንም ለጉሞ በእሳት አለንጋ እየገረፈ ይዞት ሲመጣ አየ። ካህኑ ከቤተ እግዚአብሔር ሲገባ ሰይጣኑ ሲወርድለት ሥራውን ሠርቶ ሲወጣ እንደቀደመው በላይ ላይ ሆኖ በእሳት ልንም ለጉሞ በእሳት አለንጋ እየገረፈ ይዞት ሲሄድ አይቶ «ለካስ ቅዱስ ጳውሎስ ሁሉም የራሱን ሸክም ይሸከማል ያለው ለዚህ ነው።» ብሏል ፤ ዳግመኛም የወርቅ ገደል (ውኃው የሚያርፍበት ወርቅ ፤ ማንኪያው የወርቅ ሆኖ ፤ አንድ እጁ እግሩ የቆሰለ ድውይ በማንኪያው እየጨለፈ እንካ ጠጣ ሲለው ተጸይፎ አልጠጣም ሲል ፤ «*ምነዋ ላይ ታቹ የወርቅ ማንኪያው የወርቅ ጠጣ እንጂ*» ሲለው ተመልክቶአል። «የቄሱን አተመልከት ሥጋውን ደሙን ተቀበል ሲለኝ ነው» ብሎ ተጸጽቶ ሥጋውን ደሙን የሚቀበል ሆኗል። ይላል። ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው ካህናትን ሰበብ አድርጎ ከመንፈሳዊ ጸጋ መለየት አለማስተዋል ነው።

ይልቁን በካህናት ዘንድ የጎላ የምግባር ሕጸጽ (ጉድለት) ሲታይ ምእመናን ስለ ኃጢአታችን ነው ብለው ወደ እግዚአብሔር ሊጸልዩ ይገባል ፤ «*ወሊይጽኦሙ ሕዝበ ነኪራን እለ ውጹአን እምኔነ /የማያምኑ የእንግዳ ወገን (የመናፍቃን ፤ የአለማውያን) መዘባበቻ አታድርገን*» እያሉ ሊያለቅሱ ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን «በእንተ ቅዱሳት» በተሰኘው ጸሎት ላይ ሕዝበ ክርስቲያኑ በእግዚአብሔር ፊት በግንባሩ ተደፍቶ ለጻጻሳት ለቀሳውስትና ለዲያቆናት ዕድሜ እንዲሰጣቸው ፤ ፈሪሐ እግዚአብሔርን እንዲያሳድርባቸው እና ድካመ ነፍሳቸውን አቅልሎ በትድስና ይቀርቡ ዘንድ እንዲያተጋቸው እንዲሰምን የምታደርገው ለዚህ ነው።

ምዕራፍ ሦስት

የካህናት ጸር /ፈተና/

አባቶች ካህናት በሹቱ አእማደ ምሥጢር ካሙኑ ከሹቱ ጸታ ምእመናን (የምእመናን ወገን) ውስጥ የሚመደቡ እንደመሆናቸው በእነርሱም ላይ እንደማንኛውም አማኒ ጸር (ፈተና) አለባቸው። ማንኛውም ምእመን ተፈትኖ እንደሚወድቅ ሊወድቁ ፣ እንደማይወድቅ ላይወድቁ ይችላሉ። ምንም በክብር ከፍ ያሉ ቢሆኑም ለእነርሱ ተለይቶ የተሰጣቸው ጸር ማጥፊያ የለም ፣ እነርሱም ዲያብሎስን ድል ሊነሡ የሚችሉት እንደማንኛውም ምእመን በጥምቀት ባገኙት ኃይል ነው። ስለዚህ ካህን ቢወድቅ ያልተለመደ ክስተት አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች *«ካህናት ከቤተ መቅደስ ሳይለዩ በእግዚአብሔር ፊት እያገለገሉ እንዴት ሰይጣን ሊፈትናቸው ይችላል?»* ብለው ይጠይቃሉ። ይሁንና ይህ ሃሳብ ልክ አይደለም። ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን በገዳመ ቆሮንቶስ ከጸመ በኋላ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ ዲያብሎስ በምድረ በዳ ከፈተነው በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ የሄደለት «ካህናትን ድል በምነሳበት በቤተ መቅደስ ቢሆን መች ድል ይነሣኝ ነበር» የሚል ሃሳቡን ስለተረዳ ነው። (ማቴ ፬÷፭ ትር.) ስለዚህ ዲያብሎስ ካህናትን ድል ሊነሣ የሚችልበት ስፍራ ቤተ መቅደስም ጭምር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ካህናት የሚጸናባቸው ጸር (የሚፈተኑበት ፈተና) ትዕቢት እንደሆነ መጻሕፍት ያስረዳሉ። «ካህን እም ኢተምህረ እምኢመጽአ ትዕቢት» «ካህን ባልተማረ ናሮ ትዕቢት ባልመጣበት ነበር» እንዲል

(ስንክሳር) ዕውቀት ካህንን ወደ ትዕቢት ሊገፋፉ ይችላል። ይህም አእምሮአችን (አውቀታችን) ረቂቅ ፣ ማዕረጋችን ምጡቅ እያሉ ይታበያሉና ሊል ነው። እርግጥ ነው ካህናት የሚያውቁት መለኮታዊ ምሥጢር ረቂቅ ነው ፣ ማዕረጋቸው ከመዐርጋት የበለጠ ምጡቅ ነው። ነገር ግን ለትዕቢት አይደለም። በክብራቸው ቢታበዩም ከክብራቸው ይዋረዳሉ (ያዕ.፬÷፮) ካህናት በትዕቢት ጸር ይፈተናሉ ሲባል ሌላ ጸር አይመጣባቸውም ማለት አይደለም። ሰይጣን በአንዱ ጸር ድል ሲነሱት በሌላ ጸር መፈተኑን አይተውም ነገር ግን የሚጸናባቸውን ለመናገር ነው።

ከዚህ በመቀጠል የተዘረዘሩት የካህናት ጸር ተብለው የተቀመጡት ሀሳቦች ከትዕቢት የሚመጡ ናቸው። ትዕቢት የፈረሐ እግዚአብሔርን መጉደል ያመጣል። ፈረሐ እግዚአብሔር ሲጎድል ደግሞ ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት ያሉ ግብሮች ከመፈፀም ያደርሳል።

፩ ፍቅረ ነዋይ

ፍቅረ ነዋይ ከትዕቢት ጋር የሚተካከል ሌላ ጸር ነው። ካህናትን በትዕቢት የሚፈትን ዲያብሎስ በፍቅረ ነዋይም ይፈትናቸዋል። ፍቅረ ነዋይ ማለት በቁሙ ገንዘብን መውደድ የሚል ትርጓሜ ሲኖረው በመንፈሳዊ አተረጓጎም ግን ከገንዘብ ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም። ልብ የሚቆምለት የሚመኙት ነገርን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። *«ሊይምሰልስ ኦ ፍቁር ከመ ለጥርዮ ወርቅ ወብሩር ውእቱ ባሕቲቱ ፍቅረ ጥሪት አላ ዙሉ ዘይሰቀል ቦቱ ፍትወታቲክ / ወዳጄ ሆይ ወርቅና ብርን ማከማቸት ብቻ ገንዘብን መውደድ አይምሰልህ ምኞትህ የሚሰቀልለት ነገር ሁሉ ነው እንጂ»* እንዲል (ማር ይስሐቅ)

ምዕራፍ ሦስት

የካህናት ጸር /ፈተና/

አባቶች ካህናት በሹቱ አእማደ ምሥጢር ካሙኑ ከሹቱ ጸታ ምእመናን (የምእመናን ወገን) ውስጥ የሚመደቡ እንደመሆናቸው በእነርሱም ላይ እንደማንኛውም አማኒ ጸር (ፈተና) አለባቸው። ማንኛውም ምእመን ተፈትኖ እንደሚወድቅ ሊወድቁ ፣ እንደማይወድቅ ላይወድቁ ይችላሉ። ምንም በክብር ከፍ ያሉ ቢሆኑም ለእነርሱ ተለይቶ የተሰጣቸው ጸር ማጥፊያ የለም ፣ እነርሱም ዲያብሎስን ድል ሊነሡ የሚችሉት እንደማንኛውም ምእመን በጥምቀት ባገኙት ኃይል ነው። ስለዚህ ካህን ቢወድቅ ያልተለመደ ክስተት አይደለም።

አንዳንድ ሰዎች *«ካህናት ከቤተ መቅደስ ሳይለዩ በእግዚአብሔር ፊት እያገለገሉ እንዴት ሰይጣን ሊፈትናቸው ይችላል?»* ብለው ይጠይቃሉ። ይሁንና ይህ ሃሳብ ልክ አይደለም። ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን በገዳመ ቆሮንቶስ ከጸመ በኋላ በዲያብሎስ በተፈተነ ጊዜ ዲያብሎስ በምድረ በዳ ከፈተነው በኋላ ወደ ቤተ መቅደስ የሄደለት «ካህናትን ድል በምነሳበት በቤተ መቅደስ ቢሆን መች ድል ይነሣኝ ነበር» የሚል ሃሳቡን ስለተረዳ ነው። (ማቴ ፬÷፭ ትር.) ስለዚህ ዲያብሎስ ካህናትን ድል ሊነሣ የሚችልበት ስፍራ ቤተ መቅደስም ጭምር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።

ካህናት የሚጸናባቸው ጸር (የሚፈተኑበት ፈተና) ትዕቢት እንደሆነ መጻሕፍት ያስረዳሉ። «ካህን እም ኢተምህረ እምኢመጽአ ትዕቢት» «ካህን ባልተማረ ናሮ ትዕቢት ባልመጣበት ነበር» እንዲል

(ስንክሳር) ዕውቀት ካህንን ወደ ትዕቢት ሊገፋፉ ይችላል። ይህም አእምሮአችን (አውቀታችን) ረቂቅ ፣ ማዕረጋችን ምጡቅ እያሉ ይታበያሉና ሊል ነው። እርግጥ ነው ካህናት የሚያውቁት መለኮታዊ ምሥጢር ረቂቅ ነው ፣ ማዕረጋቸው ከመዐርጋት የበለጠ ምጡቅ ነው። ነገር ግን ለትዕቢት አይደለም። በክብራቸው ቢታበዩም ከክብራቸው ይዋረዳሉ (ያዕ.፬÷፮) ካህናት በትዕቢት ጸር ይፈተናሉ ሲባል ሌላ ጸር አይመጣባቸውም ማለት አይደለም። ሰይጣን በአንዱ ጸር ድል ሲነሱት በሌላ ጸር መፈተኑን አይተውም ነገር ግን የሚጸናባቸውን ለመናገር ነው።

ከዚህ በመቀጠል የተዘረዘሩት የካህናት ጸር ተብለው የተቀመጡት ሀሳቦች ከትዕቢት የሚመጡ ናቸው። ትዕቢት የፈረሐ እግዚአብሔርን መጉደል ያመጣል። ፈረሐ እግዚአብሔር ሲጎድል ደግሞ ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት ያሉ ግብሮች ከመፈፀም ያደርሳል።

፩ ፍቅረ ነዋይ

ፍቅረ ነዋይ ከትዕቢት ጋር የሚተካከል ሌላ ጸር ነው። ካህናትን በትዕቢት የሚፈትን ዲያብሎስ በፍቅረ ነዋይም ይፈትናቸዋል። ፍቅረ ነዋይ ማለት በቁሙ ገንዘብን መውደድ የሚል ትርጓሜ ሲኖረው በመንፈሳዊ አተረጓጎም ግን ከገንዘብ ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም። ልብ የሚቆምለት የሚመኙት ነገርን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። *«ሊይምሰልስ ኦ ፍቁር ከመ ለጥርዮ ወርቅ ወብሩር ውእቱ ባሕቲቱ ፍቅረ ጥሪት አላ ዙሉ ዘይሰቀል ቦቱ ፍትወታቲክ / ወዳጄ ሆይ ወርቅና ብርን ማከማቸት ብቻ ገንዘብን መውደድ አይምሰልህ ምኞትህ የሚሰቀልለት ነገር ሁሉ ነው እንጂ»* እንዲል (ማር ይስሐቅ)

ፍቅረ ነዋይ ሌላው ቀርቶ ዲያብሎስ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከፈተነበት ፈተናዎች አንዱ ነበር ፤ በጸሊአ ነዋይ /ገንዘብን በመጥላት/ ድል ነሣው እንጂ! በቀደመው ዘመን «የብሉይ ኪዳኑ ይሁዳ ተብሎ የሚጠራው ነቢዩ በለዓም መንፈሳዊ ሥልጣኑን ለግል ጥቅሙ ለማዋል ክፉ ምክርን በመምከሩ የፍቅረ ነዋይ አብነት ነበር። መምህሩ ኤልሳዕ ከለምጽ ካነጻው ከንዕማን አታልሎ ገንዘብ የተቀበለውና የተቀሠፈው ግያዝም እንዲሁ መፍቀሬ ነዋይ ነበር።

የሐዲስ ኪዳኑ በለዓም ይሁዳ ለፍቅረ ነዋይ የተሸነፈ ነበር። «እንጀራዬን የበላ» ተብሎ እንደተነገረለት የመዳፍ ምጽዋትን ቁልፍ የሚይዝ ነበር (መዝ ፵፩፥፱) ከሚገባውም ከዐሥር አንድ ይደርሰው ነበር ፤ ለዚህም ነው ማርያም እንተ አፍረት ዋጋው የከበረ የናርዶስ ሽቱን በጌታችን እግር ላይ ስታፈስስ፡- «ይህ ሽቱ በሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው?» ያለው። ይህን የተናገረ ቅዱስ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ እንደገለጠው «ሌባ ስለነበር ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለነበረ ነው» (ዮሐ ፲፪፥፫-፮)።

ይሁዳ ምንም ሥልጣነ ክህነት ቢኖረው ፍቅረ ነዋይን በጸሊአ ነዋይ ድል መንሣትን ግን ገንዘብ አላደረገም ነበር። ይልቁንም በአጭሩ ያልተቀጨው ገንዘብ ወዳድነቱ አምላኩን በሠላሳ ብር ለመሸጥ አበቃው። ይሁዳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከጌታ እግር ሥር ቁጭ ብሎ የተማረ ፤ በዋለበት የዋለ በአደረበትም ያደረ ነበር። ነገር ግን በመጨረሻ የተማረው ትምህርት ሳይጠቅመው አምላኩን ብል በሚበላው ዝገት በሚያበላሸው ገንዘብ ለውጦታል።

ካህን ልቦናው በፍቅረ ነዋይ ከታሰረ ፈሪሐ እግዚአብሔር ከእርሱ ይርቃል ፤ ምንም ብዙ መንፈሳዊ እውቀት ቢኖረው ፤ ብዙ ጸጋ ቢሰጠውም እንኳ ይስታል። ንዋያተ ቅዱሳትን አስከ መሸጥ ፤ መንፈሳዊ አገልግሎትን ለገንዘብ መሰብሰቢያነት ብቻ እስከማዋልም ይደርሳል።

የመጀመሪያዎቹ ካህናተ ሐዲስ ቅዱሳን ሐዋርያት የተሰጣቸውን ክብር ጠንቅቀው የሚያውቁ መንፈሳውያን ስለነበሩ እንኳ በፍቅረ ነዋይ ሊታለሉ በዚህ አቅጣጫ የሚመጣባቸውንም ይገሥጹ ነበር። በአንድ ወቅት በአንብሮተ ዕድ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ሐዋርያት ሲሰጡ ባየ ጊዜ ሲሞን የተባለው ሰው፡- «እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ሥልጣንን ስጡኝ» አለ። በዚህን ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ *«ወርቅከ ወብሩርከ ምስሌከ ለይኩን ለሕርትምና ይመስለከኑ ዘበወርቅ ትሳየጦ ለጸጋ እግዚአብሔር* / የእግዚአብሔርን ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አስበሃልና ብርህ ከአንተ ጋር ይጥፋ» በማለት ከሦስቱ አካል አንዱን ሥግው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስን በካ ብር እንደሸጠው እንደ ይሁዳ ከሦስቱ አካል አንዱን መንፈስ ቅዱስን በብር እንደማይሸጡ ከተግሣፅ ጋር ነገረው። (ሐዋ ፰፥፲፯) ይህ ተግሣፅ በእዚህ ዓይነቱ ግብር /Simonist movment/ ለሚሰለፉ ሁሉ የተላለፈ መልእክት ነው።

የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በገንዘብ ለመሸጥ መሞከርና ከታለመለት ግብ ውጪ ለግላዊ ጥቅም ብቻ ማዋል ከይሁዳ ግብር የተለየ አይደለም። ይሁዳ ከሸጠው ከወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ዕሩይ (አኩል) የሆነውን መንፈስ ቅዱስን መሸጥ ነውና።

እዚህ ላይ ልናነሣው የምንችለው ሌላው ነገር ደግሞ የሲሞን መሠርይ ጥያቄ «ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ስጡኝ» የሚል ብቻ አለመሆኑን ነው ፤ ይልቁንም በሌሎች ላይ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳድርበትን ሀብተ ክህነት ከፍ ሲልም የሐዋርያትን ሥልጣን ጵጵስናን ነበር የጠየቀው ስለዚህ ከቅዱስ ጴጥሮስ ንግግር እንደምንረዳው የትኛውንም የመዐርገ ክህነት ደረጃ በገንዘብ ፤ በመግለጫ ፤ በጉቦ ለማይገባው መስጠትም ሆነ ሳይገባው መቀበል ከትምህርተ ሃይማኖት አንጻር በይሁዳ ግብር መሰለፍ ነው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ፍቅረ ነዋይን አስመልክቶ ካህንን ሲገሥጽ የምንመለከተው በዘመነ ሐዋርያት ብቻ አይደለም። በርግም በመንበሩ የተቀመጠ ሊቀ ጳጳስ ቅብዓ ሜሮንን ሸጦ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ በማድረጉ ቅዱስ ጴጥሮስ ተገልጦ «አንተ አመጸኛ በደለኛ የሆንክ ያልታመንክ፤ ቅዱስ ሜሮንን የሸጥክ ወዮልህ አንተ ጎስቋላና ሽንጋይ ሆይ! ሃይማኖታቸው የቀና የክርስቲያኖች ምልክት የሆነውን ይህን ሜሮን ትሸጥ ዘንድ እንዴት ደፈርህ? ወዮልህ በዚህ ዓለም በሚመጣውም ዓለም)ጊዜ ዕፅፍ ድርብ ፍርድ ይጠብቅሃል» ብሎታል። (ተአ.ማር ፪፻፸፱)

እግሩን ያታሰረ ሰው እንደልቡ ለመሮጥ እንደሚቸገር በጥቅም የታሰረ ካህን አገልግሎቱን እንደ ልብ መፈጸም አይቻለውም። ምእመናንንም እኩል አድርጎ ሊያገለግልም አይችልም። ባለጸጋውንና ነዳዩን እኩል ሊያገለግል ስለማይችል በባለጸጋው ዘንድ ንቀትን ፤ በነዳዩ ዘንድ ደግሞ ጥላቻን ያተርፋል። ይልቁንም መፍቀሬ ነዳያን /ድሆችን የሚወድ/፣ በቃሉም ‹‹ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልኮኛል›› ብሎ

ያናገረ አምላክ ነዳያን የሆነ የክርስቶስ መልእክተኞችንም ያጠራጥራል። ነዳያንንም ከቀቢጸ ተስፋ (ተስፋ ከመቁረጥ) ያደርሳቸዋል። (ሉቃ.፬፥፲፰)

ከዚህ ባሻገር ምንም መብቱ ቢኖረውም መንፈሳዊ አገልግሎቱን ለሚጠፋ መብልና ገንዘብ ማስገኛ ብቻ መጠቀም የለበትም። በቀደመው ዘመን መምህሩ ኤልሳዕ ለተጸየፈው ገንዘብ ንጉሶ ከንዕማን ዘንድ በመሄድ ገንዘብን የተቀበለው ግያዝ በለምጽ እንደተመታ ቢሮ መንፈሳዊ ሥራቸው ሥጋዊ ትርፍን የሚሹ ሁሉ አይጠቀሙም። (፪ነገ.፭፥፳ - ፳፯)

እንዲህ ዓይነቱ ግብር በጸሐፍት ፈሪሳውያንና በካህናተ አይሁድ ላይ የታየ ነበር። አይሁድ ጸሎት አብዝተው ሲጸልዩ ያዩአቸው ባልቴቶች «የሞቱ ባሎቻችንን ነፍስ ያስምሩልናል ልጆቻችንን ያሳድጉልናል» እያሉ ምግብም ገንዘብም ይለጡአቸው ነበር። የባልቴቶቹ ሐሳብ ትክክለኛ ቢሆንም ካህናተ አይሁድ ግን ጸሎታቸውን ገንዘብ እንደማስገኛ ይጠቀሙበት ጀምረው ነበር።

ለዚህም ነው ጌታችን *«አለ ትበልዑ አብያተ መበለታት· በምክንያተ አንሶ ጸሎትክሙ* / በጸሎታችሁ ርዝመት እያመካኛችሁ የባልቴቶችን ቤት የምትበሉ» በማለት የተናገራቸው (ማቴ ፳፫፥፲፬) ቅዱስ ጴጥሮስም በመልዕክቱ የሐዲስ ኪዳን ካህናትን በዚህ ግብር እንዳይገኙ ሲያስጠነቅቅ *«ሐውጽም/ እንዘ ኢትትራብሕሙ አላ በምልዓ ልብክሙ በትፍስሕት* / በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጎብኙት።» በማለት ካህናት በምእመናን እንብላባቸው እንጠጣባቸው ሳይሉ ፤ ጥቅም ሳይሹ እንዲጎበኙአቸው አዝዘአል። (፩ኛ ጴጥ ፭፥፪)

የካህናተ አይሁድ ግብር ይህ ብቻ አልነበረም። *«ቤተየሰ ቤተ ጸሎት ይሰመይ ወአንትሙሰ ረሰይክምዎ ቤተ ፈያት መሰረቅት / ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል እናንተ ግን የሌባና የወንበዴ ዋሻ አደረጋችሁት»* እንዳለ በቤተ መቅደስም ለሥጋዊ ጥቅም ይሮጡ ነበር። (ማቴ ፳፩ ፥ ፲፫) ሰው ለእግዚአብሔር የሚያቀርበውን መሥዋዕትና መባዕ ሳይቀር በየምክንያቱ እያጣጣሉ እና የናቁትን ሕገ እግዚአብሔር ሰበብ እያደረጉ ሁለት የከሳ ጠቦት በአንድ የሰባ ጠቦት እየለወጡ ፣ ሁለት ቀይ ወርቅ በአንድ ነጭ ወርቅ እየለወጡ ፣ የሚያስወግሽ (የሚያስደነብር) ልብስ ለብሰው እየቆሙ ከብት ደንብሮ ወደ መቅደስ ሲገባ *«ከል የገባ አይነጣ ፣ መቅደስ የገባ አይወጣ»* እያሉ በየምክንያት ጥቅምን ያሳድዱ ነበር። ቤተ መቅደሱንም ከሮም መንግሥት ቀረጥ ማምለጫ ዋሻ አድርገውት ነበር። እንደ እነርሱ ርግብ ባይሸጡም የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ በገንዘብ ለመስጠት የሚሞክሩ ግን በግብር ይመስሏቸዋል።

ይህ እንግዲህ በአሪት ካህናት ላይ የታየ ችግር ነው። ስለዚህ *«ወኵሉ ዘተጽሕፈ ለተግሣጻ ዚአነ ተጽሕፈ / የተጻፈ ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአል»* እንዲል ከእንዱ መውደቅ አንዱ ይማራልና የሐዲስ ኪዳን ካህናትም ከቀደሙት ስኅተት ሊማሩ ይችላሉ። (ሮሜ.፲፭ ፥ ፬)

የፍቅረ ነዋይ ጸር በካህን ላይ ሲጸና በቀጥታ ሥልጣኑን ገንዘብ መቀበያ አስከማድረግም ሊያደርሰው ይችላል። በየመንገዱ ቆመው በመስቀላቸው ጠቅሰው እየተጣሩ *«ገንዘብ ስጡ»* የሚሉ ፣ በየዋሐን ምእመናን እምነት ላይ የገንዘብ ጥቅምን የሚያሰሉ ሁሉ ከዚህ የሚመደቡ ናቸው።

ፍቅረ ነዋይ በአበው መካከል ሊኖር የሚገባውን ፍቅረ ቢጽ (የባልንጀራ መዋደድ) ኖሮ ከሆነ ያጠፋዋል ፣ ከሌለ ደግሞ እንዳይኖር ያደርገዋል። መቀናናትንና አንዱ ለአንዱ ክፉ መመኘትንም ያመጣል። የሁለት አኃው (ወንድሞች) ታሪክ እንዴት ያሳዝናል እነዚህ አባቶች በበረሃ ተፋቅረው ተሳስበው ይኖሩ ነበር። አንዱ ወጥቶ እስከሚመለስ ድረስ *«ወንድሜ ወዴት ሄደ?»* እያለ ይጨነቃል። ያም እንደዚያው ነው። ከዕለታት በአንዳቸው ቀን ድስት ሙሉ ወርቅ ያገኛሉ። አንዱ ታመመና *«ወንድሜ መድኃኒት አጠጣኝ»* አለው። በሆዱ ግን *«ወንድሜ ሞቶልኝ፣ ኦሶዬን ጠጥቼ፣ ጠላቴን (በሽታዬን) አውጥቼ ፣ ይህን ወርቅ ይዤ ፣ ከተማ ገብቼ ከብሬበት ኖሬ . . . . .!»* እያለ ይመኝ ነበር። ያም እንዲሁ አስቦ መድኃኒቱን ደቁሶ መርዝ ጨምሮ በጠበጠው። በሽተኛውም በበኩሉ ሰይፍ ሊስል ዋለ። *«ደርሶልሃልና ና ጠጣ»* አለው። *«ከመራት ለኑርልኝ»* አለው። ጎንበስ ሲል አንገቱን በሰይፍ ቀላው። ያም መድኃኒቱን ጠጥቶ ለብቻው ወደቀ ወርቁ ከመጫከል ቀረ።

ከዚህ ታሪክ ለሚያልፍ ብዕለ ዓለም (የዚህ ዓለም ሀብት) የማያልፍ መንግሥተ ሰማያትን የምታሰጥ ፍቅርን መተው ምን ያህል እንደሚጎዳ መረዳት ይቻላል። በፍቅረ ነዋይ የተያዘ ሰው ፍቅረ ቢጽ (የባልንጀራ ፍቅር) የለውም። ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ *«ኢታፍቅርዎ ለዓለም ወኢዘሀሉ ውስተ ዓለም ወዘሰአፍቀሮ ለዓለም ኢሀሉ ፍቅረ እግዚአብሔር ላዕሌሁ / ዓለምን ወይም በዓለም ውስጥ ያሉትን አትውደዱ ፣ ማንም ዓለምን ቢወድ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም»* በማለት በፍቅረ ነዋይ የተያዘ ሰው እግዚአብሔር ያዘዛት የባልንጀራ ፍቅር በእርሱ ውስጥ እንደማትኖር ገልጦአል። (፩ዮሐ ፪ ፥ ፲፭ ትር.)

ካህናት የሐዋርያትን አሠረ ፍኖት ተከትለው ለአገልግሎታቸው ክብርና ትምክህታቸውን ላለማጣት ሲሉ ራሳቸውን በመቻል በሥጋዊ ኑሮና በተግባረ ዕድ ለምእመናን አርአያ ቢሆኑ የተመረጠ ነው። (ቆሮ ፱፥፲፫) መጽሐፍ ካህናትን ጣሪ ጋሪ በሆነችው በገብረ ገንዳን ይመስላቸዋልና። (ምሳ ፮፥፳ ትር)

የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት የዓመት ልብስ የዕለት ጉርስ የሌለው ሰው ገንዘብ ተቀብሎ ሊያስተምር እንደሚገባው፣ ይህ ያለው ግን ያለዋጋ ማስተማር እንደሚገባው ይናገራሉ። ይህም የሚገባቸው የድካም ዋጋ (ደመወዝ) ሳይጨምር ነው። የሚገባቸውን ደመወዝ እየተቀበሉ ፣ ሥርየትን ፣ጥምቀትን፣ ሥጋ ወደሙን ያለዋጋ አንስጥም ቢሉ እግዚአብሔር ይጠይቃቸዋል። እንዲህ ሲል፦ «ገንዘብን እንጀራ ላይደለ የድካማችሁንስ ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ?»

ከዚህ ኃይለ ቃል ቀደም ብሎም ለምእመናን «እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ! ገንዘብም የሌላችሁ ኑና ግዙ!» ይላል። (ኢሳ ፶፭፩-፫) ይህ ቃል ሲተረጎም ከልጅነት ፣ ከመዓርግ ፣ ከሥርየት የተጠሙትን ምእመናን ተቀብለው ያለ ዋጋ የሚሸኙ መምህራን «የድካምን ዋጋ ከንቱ ከሚያደርግና ከማያጠግብ» ገንዘብ ይልቅ ለነፍሳቸው ጥጋብ እንደሚሆናቸው ስለዚህም ቀላውስት ልጅነትን ጥምቀትንና ሥርየትን ፣ ጳጳሳት መዓረግን ገንዘብ ተቀብለው እንዳይሰጡ ያለ ዋጋ ቢሰጡ ደግሞ ለጽጋበ ነፍስ (ለነፍስ ጥጋብ) እንደሚሆናቸው ያስረዳል።

፪ ድፍረት

የክህነት አገልግሎት ወደ ቤተ መቅደስ የሚያቀርብ እንደመሆኑ ከባድ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው። ካህናት አዘውትረው ወደ ቤተ

መቅደስ በመግባታቸውም ሆነ መንፈሳዊ ሥርዓቶችን ዕለት ዕለት የሚፈጽሙ በመሆናቸው የመለማመድና የመለሳቸት የመደፋፈር ፈተና ሊከሰትባቸው ይችላል። በቤተ መቅደስ ሲያገለግል በማስተዋልና በተዘክሮ ያልሆነ ሰው ያለው ፈሪሐ እግዚአብሔር እየታወቀው ከላዩ ይጠፋል። ቤተ መቅደሱን እንደ ተራ ቤት ወደ መቁጠርም ሊያመራ ይችላል።

በጠፋው ልጅ ታሪክ ላይ ጠፍቶ የመጣው ልጅ ‹‹አባቴ ሆይ ልጅህ ልባል አይገባኝም›› እያለ ሲለምን ከአባቱ ቤት የኖረው ታላቁ ግን አባቱን ከፍ ዝቅ አድርጎ ተናገረ። /ሉቃ.፲፭፥፲፩-፳፱/ ይህም በውጪ ካሉት ይልቅ ወደ መቅደሱ የሚቀርቡት የፍቅሩን መጠን ባወቁ መጠን እየተዳፈሩ የማይሰመደውን አምላክ ሲለምዱና ሊዳፈሩ ሊገኙ እንደሚችሉ ያሳያል። በመቅደሱም ቤተኝነት እየተሰማቸው ብዙ የድፍረት ንግግሮችን ፣ ዋዛ ፈዛዛን የመሳሰሉ ነገሮችን ወደማዘውተር ያመራሉ።

በብሉይ ኪዳን ካህናት የነበሩት የሊቀ ካህናቱ የዔሊ ልጆች እግዚአብሔርን የማያውቁና በቤተ መቅደስ ዝሙትን እስከ መፈጸም ደርሰው «ምታኝ» ብላ ዱላ እንደምትሰጥ ደረቅ ሴት እግዚአብሔርን «ቅሠፈን ቅሠፈኝ» ብለው የተፈታተኑ ነበሩ። (፩ኛ ሳሙ ፪፥፳፪) ይህም ከራሳቸው አልፎ ለብዙኃን ሞት ምክንያት ነበረ።

አፍኒንና ፊንሐስ አገልግሎታቸው ያለ ፈሪሐ እግዚአብሔር ነበር። በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት በርቶ በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት የሚጠፋ ፋና ነበር። ይህ ሙሴና አሮን የሠሩት ሥርዓት ነው። (ዘጸ ፳፯፥፴፯) እነርሱ ግን በመሰልቸት «ከባዶ ደብተራ አሪት ውስጥ ሲበራ ቢያድር

ምን ይሆናል? (ይጠቅማል?)» ብለው (የማይታየውን አምላክ ረስተው) አስቀሩት። ይህ የመጀመሪያ በደላቸው ነው።

ሌላው መሥዋዕት ሲሠዋ ስቡ ከተቃጠለ በኋላ በጉጠት መጀመሪያ የወጣውን ለሊቀ ካህናቱና ለሌዋውያን ይሰጥ ነበር። አፍኒንና ፊንሐስ ግን ስቡ ሳይቃጠል *«የምንጠብሰው ጥሬ ሥጋ ስጡን»* እያሉ እንደ ሕጉ ፣ እንደ ወጉ ደሙ ሳይፈስስ ይወስዱ ነበር። (፩ሳሙ ፪፥፲፪)

ሦስተኛው ሥራቸው ደግሞ የእስራኤል ሴቶች *«ቤተ እግዚአብሔር እጅ ነስተን እንመጣለን»* ብለው ሲሄዱ ለዝሙት ያስቸግሩአቸው ነበር። አንድም መቃጠሪያ አደርገውት ነበር። በዚህን ጊዜ ሴቶቹም *«ይህንማ ከቤታችንስ መች አጣን?»* ብለው ቀርተዋል። ባሎቻቸውም *«ሚስቶቻችንን ልንድር ነውን?»* ብለው አስቀርተዋቸዋል። ይህ እንግዲህ በቀደመው ዘመን በካህናተ ብሊት (በብሉይ ኪዳን ካህናት) የተፈጸመ ድፍረት ነው።

ወደ ካህናተ ሐዲስ ስንመጣ ደግሞ ሊፈተኑባቸው የሚችሉባቸው የድፍረት ውጤቶች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹን ለአብነት እንመለከታለን። የሐዲስ ኪዳን ካህናት መሥዋዕተ ወንጌልን (ሥጋ መለኮትንና ደመ መለኮትን) የሚፈትቱ እንደመሆናቸው አገልግሎታቸው በቀጥታ ከአምላክ ጋር የሚያገናኛቸው ነው። ዕለት ዕለትም ወደ ቅዱስ ምሥጢር የሚቀርቡ እንደመሆናቸው ፈሪሐ እግዚአብሔር እንዳይጎድልባቸው ሊጠነቀቁ ፣ በአምነትም ሊጠነክሩ ይገባል።

በቤተ መቅደስ ውስጥ ዋዛ ፈዛዛን መናገር ፣ ሳቅና ስላቅን ማድረግ ፣ ያለ ፍርሃትና ቅድመ ጥንቃቄ ወደ ሥጋው ደሙ መቅረብን

የመሳሰሉ ድርጊቶች የድፍረት መገለጫዎች ናቸው። በዚህ ንዑስ ርዕስ ስለ ሥጋወ ደሙ ክብር ለማብራራትም ሆነ ሥርዓቱን ለመዘርዘር አልተነሣንም። የትኩረት አቅጣጫችን በሥጋ ወደሙ ፊት ስለሚገባ ጥንቃቄ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደተናገረ ካህን *«ቀለም እንዳይወድቀው ሥጋ ወደሙ እንዳይነጥበው ተጠንቅቆ ሊያገለግል ያስፈልጋል።»* (ተግሣጽ ፸፬)

የሥጋ ወደሙ ምሥጢር ሰማያዊ ነው። ካህን ከግብር ንብቶ ከአእምሮ ደርሶ ባይታየው እንጂ በሥርዓተ ቅዳሴ ዘወትር እጁ በደመ መለኮት የሚታጠብ ነው። ይህ በሁለት አበው ታውቋል። እሊህ አበው አንዱ የበቃ ሌላው ያልበቃ ነው። ያልበቃው *«ሕብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአክብሔር መሆን እንደምን ይቻላል?»* እያሰ እየተጠራጠረ ለመናገር ግን እየፈራ ይኖር ነበር። የበቃው ባልንጀራው ነገሩን አወቀበትና ሄዶ *«የሥጋ ወደሙ ነገር ረቀብኝ ይኖራል»* አለው ያልበቃውም መልሶ *«አንተን ፈርቼህ ነው እንጂ ይህስ እኔም ይልቅ ረቀብኝ ይኖራል»* አለው።

ከመቅደስ ገብተው ሲያስቀድሱ ቁሱ «ሀበነ ንኅበር» ሲል በአምሳለ በግዕ (በበግ አምሳል) ሲያርደው ፣ ሲያወራርደው ዐሥሩ ጣቶቹ ሁሉ በደም ተነክረው አይቶ ያልበቃው ደንግጦ ወድቋል። «ለሁሉ በሚቻል መታየቱ ነው እንጂ ዘወትር እንዲህ አሆናለሁ» ብሎ ጌታችን ድምጽ አሰምቶታል። በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ሲገልጥ ለበቁት የታየ ሆኖ ሳለ ላልበቁት እንዳልታየ ማለት ነው። ላልበቃን ስዎች ደሙን ደም ሆኖ ዓይተን ቢሆነው በታወክን ነበር።

በሥጋ ወደሙ ፊትና በመቀበል ጊዜ የሚደረግ ያልተገባ ነገር የድፍረት ዳርቻ ነው። ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ *«ኦ እግዚኦ ዘኢትደፈር*

ይሁዳ ደፈረክ / አቤቱ የማትደፈረውን አንተን ይሁዳ ደፈረህ» በማለት የተናገረበት ይሁዳ የጌታችንን ሥጋና ደም ተቀብሎ ፣ ምሥጢረ ቁርባንን ተመልክቶ ለክፉ ግብር በመነሣቱና ተረከዙን በጌታ ላይ በማንሣቱ ነበር። «የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» የሚለው ቃል ምንኛ ከባድ ነው።(ዕብ፲÷፳፱)

ሥጋ ወደሙን ሳይበቁ (ንስሓ ሳይገቡ ፣ የሚገባውን ሳይፈጽሙ) መቀበልም ድፍረት ነው። ውጤቱም ወደ ታላቅ ፈተናና ዘላለማዊ መከራ መግባት ነው። መጽሐፈ ቅዳሴ «ሊታብሉነ እግዚኦ ውስተ መንሹተ / አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን» በማለት «ነአኩቶ» ሲባል የሚመለሰውን ተሰጥኦ በተረጎመበት ሥፍራ እንዲህ ይላል፡- «መንሹትኬ ነሢአ ሥጋሁ በድፍረት ፣ ወተመጥዎተ ደሙ ዘእንበለ ኃፍረት ፣ እንዘ ዕዕሌሁ ነውረ ኃጢአት፤ ደይኖ ወመቅሠፍቶ በልዓ ሰርአሁ ፣ ለአመ ሊያአመረ ሥጋ እግዚእነ ወአኰነ ንጹሐ ነፍሱ /ፈተናስ ነውረ ኃጢአት እያለበት ሥጋውን በድፍረት መቀበል ደሙንም ያለማፈር (ያለ ፍርሃት) መቀበል ነው። ነፍሱን ንጹሕ ካላደረገ የጌታችን ሥጋ መሆኑን ካላወቀ መቅሠፍትንና ሲኦልን ለራሱ በላ» ይላል። ስለዚህም «ሥጋህን ደምህን ሳንበቃ በድፍረት ከመቀበል አድነን» እያሉ መጸለይ ይገባል። ስለዚህ ካህናት ወደዚህ ምሥጢር ሲቀርቡ በድፍረት እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋቸዋል።

ሥጋ ወደሙን ለመፈተት በመንበሩ ፊት ቆመው ከመንፈሳዊ ሥቃታቸው የተነሳ ተለውጠ የተመለከቱ ካህናት አሉ። እሊህ በትተው የተገኙ ናቸው። አረጋዊ መንፈሳዊ ለዚህ ምሳሌ ነው። ይህ አባት ግብሩ ትሕትና ነበር። አንብብ ሲሉት እኔ መጽሐፍ አይዛለሁ እናንተ አንብቡ

፣ ቀድስ ሲሉት እኔ ማይ ቀድቼ መስዋዕቱን አሥምሬ አስጣችኋለሁ እናንተ ቀድሱ ፣ ጻፍ ሲሉት እኔ ቀለም በጥበጬ ብርዕ ቀርጬ ብራና ደምጬ አሰጣችኋለሁ እናንተ ጻፉ ይላቸው ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን የግድ ቀድስ ብለው አገብረውት ሊቀድስ ገባ። ሊቀድስ በገባባት በዚያች ዕለት ከቅዳሴው መካከል በዝምታ ቆይቶ ነበር። በሚቀድስ ጊዜ የገጠመውን ይህ አባት በድርሳኑ አንድ የማይዋሽ ሰው ነገረኝ ብሎ ጽፏል። (ቅዱሳን እኔ የሚለውን አነጋገር አይወዱትምና ለልማዳቸው ራሳቸውን አርቀው ይናገራሉና እንደ ቅዱስ ጳውሎስ በሰላ አድርጎ የተናገረው ስለ ራሱ ነው።) እንደሚከተለውም አስቀምጦታል፡-

«ሥጋ ወደሙን አከብር ዘንድ ወደ መንበር በቀረብኩ ጊዜ ፣ ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ ባደረግሁ ጊዜ ፣ በማኅፈድ በሸፈንኳቸው ጊዜ ፣ አቀድስ ዘንድ በጀመርኩ ጊዜ ፣ ስለ ሁሉ ቤዛ ራሱን የሠዋ ጌታን በማይመረመር ብርሃን በግዕ ሕጻን መስሎ አየሁት። ደስ ብሎኝ ደነገጥሁ አደነቅሁ ልቦናዬም ተለወጠ ነፍሴም ሥጋዬም በደስታው በፍቅሩ እሳት ተቃጠለ። በጣዕሙ ክብር ካገኘኝ አንክሮ የተነሳ የምሠራውን አላወቅሁትም። ልቡናዬ በፍቅሩ ከመንደዱ የተነሣ መልኩ ያማረ የተወደደ ጌታን ልታቀፈው ወደድሁ። ያን ጊዜ ፈጥኖ ረዓድ ያዘኝ ፣ በጥልቅ ባሕር እንደሰጠመ ሰው አሰጠመኝ የምዋረድ /ለዚህ አልበቃም የምል/ ሆንኩ ጸሎተ ቅዳሴውንም ዘነጋሁት በፍቅሩ እየተቃጠልሁ በአንክሮ ሆኜ ሳልናገር ከራእዩ የተነሳ እያደነቅሁ ብዙ ጊዜ ዘገየሁ» ሲል ይገልጻል።

ቀጥሎም «ከፊቴ በተሰወረኝ በተለየኝ ጊዜ ወዳለ አውቀቴ /ወደ አለማወቄ/ ተመለስኩ። የአእምሮዬን ደካማነት አወቅሁ» በማለት የሥጋ ወደሙ ምሥጢር እናውቅ ዘንድ በደካማ እውቀታችን እንደማይቻለን ይገልጻል። ከዚያም በኋላ «መአምኑ ለሜሃ ለአመርኩ ከመ ምሥጢራት

እም ጊዜ ያንብርምሙ በዳብ ምሥዋዕ ይትቀደሱ በንዑዕ ከዚህ ወዲህ ጎብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርገው ከመንበር ባሞጵዋቸው ጊዜ ሰምሥጢር በርቀት እንዲከበሩ እንዲለወጡ አወቅሁ» ብሏል።

ከዚህ ጋር አያይዞም ምንም በቅተው ማየት ባይቻላቸው ጎብስቱንና ወይኑን በረቂቅ ምሥጢር የሚከብሩ ናቸውና ካህናት በአገልግሎታቸው በፍርሃት ሆነው እንዲቀርቡ እንደሚገባ «ወባሕቱ ይደልወነ ንዕቀብ መዐርገ ተልእኮ /እንዲህ ከሆነ መዐርገ ክህነትን መጠበቅ ማክበር ይገባናል» በማለት ያስረዳል። (አረ.መን ፴)

ሌሎችም ከካህናት ወገን በመንበር ፊት ሲቆሙ እንደ ደብረ ሲና በአምሳለ እሳት ፤ እንደ ደብረ ታቦር በአምሳለ ብርሃን ሕጻን በግዕ መስሎ የታያቸው ብዙዎች አሉ። ካህን ግን ለዚህ ክብር ባይደርስ ያለ ድፍረት በፍርሃትና በትሕትና ሆኖ ሊቀርብ ይገባዋል።

ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ በቅዳሴው ካህን በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም በትሕትና መሆን እንዳለበት አብነት ሲሆን እንዲህ ብሏል፦ «ወበእንተ ንብርክ አነ ትሑት ዘጸዋዕከኒ በጸጋ ዚአከ እንዘ ኢይደልወኒ / አዕበይከኒ ወአልዓልከኒ እንዘ ኢመጠንዎ / ወአቅረብከኒ ቅድሜከ በምሕረትከ ከመ እቀም ቅድመ ምሥዋዒከ እግዚኦ / ሳይገባኝ በቸርነትህ ስለሾምኸኝ ትሑት ስለምሆን ስለ ባሪያህ ሳይገባኝ ፈጽመህ ስላከበርከኝ በቤተመቅደስህ እቆም ዘንድ በቸርነት ወደፊትህ ስላቀረብኸኝ !» በማለት በትሕትና ለዛሬው ካህን አብነት ሆኖአል። (ቅዳሴ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ)

የፊሪሐ እግዚአብሔር መጥደል ከኃጢአት ሳይነጹ ሳይዘጋጁ በድፍረት ወደ ሥጋ ወደሙ እስከ መቅረብ ድረስ ያደርሳል። ከዚህ በኋላ ኃጢአትን በማስተው ፈንታ በኃጢአት ላይ ኃጢአት በመጨመር

ከማይወጡበት ዓዘቅት መግባትን ያስተላልፋል። በዚሁ በድፍረት ምክንያት ሳይነጹ ሥጋ ወደሙን ስለተቀበሉ የደከሙ ፤ የታመሙ ብዙዎች ናቸው አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። (፩ኛ ቆሮ ፲፩ ፥ ፴)

በመንፈሳዊ ምሥጢር የሚሳተፉ ሁሉ ራሳቸውን መርምረው ሲቀርቡ ሲገባ እንደ ሥጋዊ ማዕድ መገባበጥ ማድረግ «ሕይዘሰ ፤ የዛሬን ቅዳሴ ግባልኝ?» መባባል ፍጻሜ ማቆየት ነው። «መክፈልት ሲሹ መቅሠፍት» እንዲሉ በበረከት ፈንታ መርገምን ፤ በኃጢአት ሥርየት ፈንታም ገሃነመ እሳትን መቀበል ነው።

ዕለት ዕለት ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉ ካህናት ሳይጣን በድፍረት ኃጢአት እንዳይጥላቸውና ፈሪሐ እግዚአብሔርን እንዳያጎድልባቸው መጸለይና መጠንቀቅ አለባቸው። ከተጠመቀና ሥጋ ወደሙን ከተቀበለባት ዕለት ጀምሮ ስድሳ ዓመት ሙሉ ምራቁን እንዳልተፋው እንደ አባ መቃርዮስ ዘአስክንድርያ መሆን ባይቻል ፤ የጌታን ሥጋና ደም የተቀበለ ሰው ያስመለሰውን ደም የተቀላቀለበት ትፋት ሳይጸየፉ እንደተቀበሉት እንደ አባ ተክለ ሐዋርያት መሆን ባይቻል መለኮት የተዋሐደው መሆኑን አውቆ በፍርሃት መቀበልና ተቀብሎም መጠንቀቅ ይገባል።

«ሊታምስልም ለቁርባን ከመ ጎብስት ዕራቆ ፤ አስኑ ሥጋ መለኮት ዘይትሳጸቆ ፤ መቃርዮስ አብ ዕበየ ቁርባን ለአጠይቆ ፤ ደሀረ ተወክፈ በአሚን እንበለ ያብዕ ናፍቆ ፤ ስድሳ ዓመተ ኢተፍአ ምራቆ። /ጎብስት ብቻውን እንደሆነ ቁርባንን አታስመስሉት ፤ መለኮት የተዋሐደው ሥጋ አይደለምን? ፤ አባት መቃርዮስ የቁርባንን ታላትነት ለማስረዳት ፤ ጥርጣሬን ሳያስገባ በእምነት ከተቀበለ በኋላ ፤ ስድሳ ዓመት ምራቁን አልተፋም።» ተነግሮለታልና።

ድፍረት ሲጸና ሥጋ ወደሙን ከተራ ምግብ ለይቶ አለማየት ይመጣል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በቤታችሁ አትበሉምን›› ያሰኘው እንዲህ ዓይነቱ ድፍረት ነበር። (፩ቆሮ. ፲፩÷፳፪) እንደ አንድ ዲያቆን፡- በቅዳሴ ጊዜ ሥጋወ ደሙን ያለ ፍርሃትና ያለ ጥንቃቄ በቸልታ ሲቀበል እመቤታችን ተገልጻ «አንተ ደፋር ዲያቆን የልጄ ሥጋ እንጂ ነው ሥጋዊ ምግብ ታደርገዋለህን?» በማለት ገሥጻዋለች። (ሥር.ቅዱ.ትር) ነገር ግን ካባ ሳንቃውን ለብሶ ዘውዱን ደፍቶ መስቀሉን ይዞ ከፍ ካለ ቦታ ላይ ሆኖ *«አመዐ ዘዐ ነውረ ሕሊና ይትከላዕ ወኢይቅረብ* / የሃሳብ ነውር ያለበት ቢኖር አይቅረብ» እያለ በሕዝቡ ላይ የሚያጸኝ (የሚያስፈርድ) ዲያቆን ከሁሉ ይልቅ በፍርሃት ለቀርብ ይገባው ነበር።

ቅድመ እግዚአብሔር መቆሙን ያላስተዋለ ካህን በቤተ መቅደስ ከመንፈሳዊ ግብር የተለየ ነገርን ያደርጋል። ብሎም *«ወረሰይዎ ለቤተ ክርስቲያን ከመ ኢምንት* / ቤተ ክርስቲያንን እንደ ኢምንት (እንደ ምንም) አደረጉአት» እንዲል ቤተ ክርስቲያንን እንደ ገበያ እንደ በረት አድርጎ ዋዛ ፈዛዛን ሳቅ ስላቅን ያበዛል።

በቤተ መቅደስ መሳቅ ይልቁንም በቅዳሴ ጊዜ ከሆነ እጅግ ትልቅ ስኅተት ነው። በቅዳሴ ጊዜ መሳቅ ጌታ በመንበር ተቀምጦ ጸጋው እንደሚሰጥ ኅብስቱንና ወይኑን እንደሚለውጥ አለማወቅ ከሃሊነቱን መናቅ ነውና። ይህን የሚያደርጉ ሁሉ ይቀጣሉ። ምክንያቱም *«ወአንዘ አስተሐቀሩ ዕበየ ክሂሎቱ ለክርስቶስ* / የከሀሊነቱን መጠን አቃልለዋልና» እንዲል የክርስቶስን ሁሉን ቻይነት ስለናቁ ስላቃለሉ ነው። (ተግሣጽ ዘቅዱሐ.አፈ.) አንድም ሳቅ የጥርጥር ምልክት መሆኑ የልጂ የይስሐቅን መወለድ እግዚአብሔር ሲነግራት ተጠራጥራ

በሳቀችው በሣራ ታውቆአል። ስለዚህ በቅዳሴ ጊዜ መሳቅ የሚፈጸመውን ምስጢር ከመጠራጠር ሊቆጠር ይችላል።

በመሆኑም ካህናት ሥጋ ወደሙን በሚቀበሉበት ጊዜ በፍርሃት ሆነው ሊያገለግሉ ይገባል። በአንድ ወቅት አንድ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂ የተናገረው ንግግርም ይህን ያስረግጥልናል። ይህ ሰው ትዕቢተኛ የነበረና የኤጲስ ቆጶስን ትእዛዝ ሳይቀር የሚንቅና የሚያቃልል ነበር። በኋላ መላእክት በረቂቅ ሥልጣን አስረው አንጠልጥለው የሚቀጣው ሳይታይ ጽኑ ግርፋትን ገረፉት።

ከዚህ በኋላ በዙሪያው የተሰበሰቡ ካህናትን በትሕትና እና በተሰበረ ልቡና እንዲህ ሲል መልእክት ነገራቸው፡- *«ተወከቡ አኃውየ ወአበውየ ወኢትኩኑ ከማየ ዝኑራን ወዕቡያን ልብ ወኢትትለአኩ በድፍረት በሥርዓተ ምሥጢር ቅድሰት* /አባቶቼ ወንድሞቼ ተጠበቁ። እንደ እኔ ትዝጎርተኞች እና የልብ ትዕቢተኞች አትሁኑ የከበረ ሥጋ ወደሙን በምትቀበሉ ጊዜ በድፍረት አታገልግሉ» አላቸው /ተአ.ማር ፩፻፸፯/

እንኳን ሥጋ ወደሙ በሚፈተትበት በሥርዓተ ቅዳሴ በማንኛውም ሰዓት በቤተ መቅደስ መሳቅ መላለቅ አይገባም። *«አስመ ቤተ ክርስቲያን አኮ መካነ ነገር ይእቲ ዳዕሙ መካነ ጸሎት* /ቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ናት እንጂ የነገር (የዋዛ) ቤት አይደለችምና» (ሥ.ቅዳ ፭፥፬)

በቤተ መቅደስና በቅዳሴ ወቅት ሳቅ ስላቅ እንዲነግሥ የሚያደርግ ዲያብሎስ ነው። ካህናትና ምእመናንን ከብሏቸው ኃይለ ቃል እያቀበለ በመካከላቸው ሠልጥኖባቸው ከምከም ብለው እንዲስቁ እና ከጸጋ እግዚአብሔር እንዲርቁ የሚያደርግ እርሱ ነው። *«ወሰይጣን*

የዐውድ በማዕከሎሙ ተበዊሐ ላዕሌሆሙ /ሰይጣንም በመካከላቸው ይዞራል . . . » እንዲል ፤ ይህን ያስተዋለ ግን የሚያስቅ ነገር ሲገጥመው ራሱን በመግዛት ማላለፍን ገንዘብ ያደርጋል እንጂ ሰይጣን በቀደደው አይሄድም።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን የዋዛ ፈዛዛ ነገር ሊሞላባት አይገባም ስንል አንድም አከናውኖ በተናገረው የካህናት መዘበትንም ነው። ‹‹ዘነጠለው! ገለበጠው!›› እያሉ መሳለቅ አለና። ይህም አንዱ ካህን ሊጦን ፤ መስተበቁዕ በዜማ ቢናገር ፤ ቅኔ በምሥጢር ቢናገር ካህናት ይዘብቱበታልና በቀለም (በሚገደፍ ዜማና ንባብ) ምክንያት ዋዛ ፈዛዛ ሊሰለጥን ይችላል።

ሰያሚሆሙ ለካህናት (የካህናት ሿሚያቸው) ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሳቅን አሳስተማረም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ሲል ይጠይቃል፦ *«ንገረኒ እስኩ ምክንያተ ሰሐቀከ መአይቱ ሰማዕከ በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥቱ ስብሐት ከመ ሰሐቀ ዘእንበለ ጻዕሙ ዘገዘነ ወተከዘ* /አንተ የምትስቅ ሆይ የምትስቅበትን ምክንያት እስኪ ንገረኝ ማንን አብነት አድርገህ ትስቃለህ? ክብር ይግባውና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሳቀ የሚል ከየት ሰማህ? እንዳለቀሰ እንደተከዘ ነው እንጂ» በማለት ይገልጣል ፤ በእርግጥም ጌታችን ለአልዓዛር ፤ ለኢየሩሳሌም ማልቀሱ ተጸፈ እንጂ እንደ ሳቀ አልተጸፈም።

ይህ ሲባል ማልቀስና መሳቅ በሰው ተፈጥሮ ያለ ክስተት መሆኑን ዘንግተን ሰው ፈጽሞ ስሜት አልባ ድንጋይ መሆን ይገባዋል ማለታችን አይደለም። ለሳቅ ግን የእግዚአብሔር መቅደስ ቦታው አይደለም ፤ ጸሎተ ቅዳሴው ፣ማኅሌቱና ሰዓታቱም ጊዜው አይደለም። ‹ለመሳቅም ጊዜ አለው› እንዲል ሁኔታን መለየትና መመጠንም

ያስፈልጋል። «አኮ ሰሐቅ ዘይከውን ኃጢአተ አላ ሶበ ይከውን ዘእንበለ ጊዜ ወአብዝኖቱ ኃጢአት ውእቱ /ሳቅ ኃጢአት የሚሆን አይደለም ፤ ያለ ጊዜ ሲሆንና ሲበዛ ግን ኃጢአት ይሆናል» እንዳለ ቅዱስ ዮሐንስ ለዋዛ ፈዛዛ ገደብን ማበጀት ይገባል እንጂ በሆነ ባልሆነው አፍን በከጠላ እየሸፈኑ በመቅደስ መሳቅ መሳለቅ የተገባ አይደለም።

በቤተ መቅደስ ከመንፈሳዊ ግብር ውጪ ዋዛ ፈዛዛ ብቻ ሳይሆን ከሌላም ወሬ ቢሆን መሰብሰብ ያስፈልጋል። ለመንፈሳዊ ነገር እንኳን መነጋገር ቢያሻ በጥንቃቄ ነው። «በቅዳሴ ጊዜ የሚናገር አይኑር በፊውስ መንፈሳዊ መብራት ዕጣን አምጣ መጽሐፍ ያገ ለማለት ካልሆነ በቀር ቅዳሴ ከገቡ በኋላ ጎድሎ ቢገኝ አሽ ብሎ ጠቅሶ ማሳየት ነው እንጂ መናገር አይገባም።» (ሥር.ቅዳ ፩፥፵፭) ተብሎ ተጽፎአል። ይህ ትእዛዝ በቅዳሴ ሥርዓቱ ዙሪያ የተነገረ ቢሆንም ከቅዳሴም በኋላ ቤተ መቅደሱ የእግዚአብሔር ማደሪያ መሆኑን አይተውምና ለሁልጊዜ የሚሠራ ትእዛዝ ነው።

የሚጸናውንና የሚከፋውን አነሣን እንጂ የድፍረት መገለጫው ብዙ ነው። ክፋትን ፤ ቂምን ፤ በቀልን፣ ሐሜትንና መርገምን ከአንደበት ሳያርቁ ለጸሎት መነሣት በእግዚአብሔር ማላገጥ ነውና ድፍረት ነው። እመቤታችን ለአንድ ካህን እንዲህ ብላው ነበር፦ *«ምንተ ዘአብየከ ውስተ ምሥዋዕ ከመ ታስተራሕስ በአስትንፋስከ ርዙሰ ምሉዓ መርገመ ወጽልሖተ ወመኑ ዘለድፈረከ ይእዜኒ ከመ ትባእ ኀበ ምሥዋዕ ተንሥእ ፃእ ፍጡን* /ሽንገላና መርገምን በተሞላ ርዙስ አስትንፋስህ መሠዊያውን ታረክስ ዘንድ በመሠዊያው አጠገብ ምን ያስለቅስሃል? ወደ መሠዊያውስ ትገባ ዘንድ ማን አደፋፈረህ? ተነሥ

ፈጥነሀም ውጣ!» (ተሓ.ማር ፪፤፬፱) በአቁራሪተ መዓት በእመ አምላክ አንደበት እንዲህ መባል ወዮ እንደምን ይከብድ?!

ይህ ካህን ኃላ ምሕረትን አግኝቷል ፤ ነገር ግን ባይመለስና ባይጸጸት ኖሮ የሚጠብቀው ፍዳ ጽኑዕ ነበር። «የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉ እንጂ እግዚኦ እግዚኦ እያሉ የሚዘባበቱበት ሁሉ መንግሥቱን አይወርሱምና» (ማቴ.፯፥፳፩ ፤ ራእየ ማር.ያም)

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ሳያከብር ፤ እግዚአብሔር በሥጋዬ ይቀሥፈኛል በነፍሴ ይፈርድብኛል ሳይል በድፍረት የሚያገለግል ካህን ከእግዚአብሔር ጋር ጽኑ ጥልን ያደርጋል። መቅሠፍትንም በራሱ ያመጣል። ምናልባት ብዙ የድፍረትን ነገር እየፈጸመ ያልተቀሠፈ ይኖራል። ይህ የእግዚአብሔር ትዕግሥት መገለጫ እንጂ የኃጢአት ግብር በእርሱ ዘንድ የሚደገፍ ሆኖ አይደለም። ደግሞም «እግዚአብሔር ብዙ ዘመን ይታገሣልና ኃጢአት ሠርቼ ፍዳ አልተቀበልኩም አትበል» ተብሎ እንደ ተጻፈ (ሲራ. ፭፥፬) ለሚደፍሩት ሁሉ እንደየሥራቸው የሚሰጥበት ጊዜ አለው። «አመጸኛውም ወደ ፊት ያምጽ ፤ ርኩሰም ወደ ፊት ይርከስ ጻድቁም ወደ ፊት ጽድቅ ያድርግ ቅዱሱም ወደ ፊት ይቀደስ እነሆ እመጣለሁ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ» የሚል ቃሉ ለዚህ ምስክር ነው። (ራእ. ፳፪፥፲-፲፪) ስለዚህ አልተቀሠፍሁም ብሎ በኃጢአት መጽናትም ሆነ ፤ እነእገሌ እንዲህ እያደረጉ ምን ሆኑ?፣ በማለት ሌሎችን የድፍረት አብነት ማድረግ የሚገባ አይደለም።

ቀደም ሲል እንጠገለጥነው የድፍረት መገለጫ የሚሆኑ ብዙ ግብሮች አሉ ፤ ሁሉን በየወገኑ መዘርዘር «ይህም ለሰ ለካ !?» ማሰኘት ነውና እንደ ጸር አይታይ እንደሆነ ለጥቆማ ያህል ከቤተ ክርስቲያናችን

መጻሕፍት የተገኙትን ብቻ አንሥተናል። ስለዚህ የካህን ጸሎቱ «የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ» ማለትም ሊሆን እንደሚገባና ከዚህ ጸር መጠበቅ እንደሚያስፈልገው ከዚህ ንዑስ ርእስ መረዳት ይቻላል። (መዝ ፲፰፥፲፫)

፫ ፍቅርን ማጣት

ሰያሚሆሙ ለካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ለመጀመሪያዎቹ ካህናተ ሐዲስ መታወቂያ ይሁናችሁ ብሎ የሰጣቸው ፍቅርን ነበር። «እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ» በማለት እንደተናገረ (ዮሐ ፲፫፥፴፭)

ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ እንደገለጠው «ፍቅርን ማጣት» ምስጋናን እና አገልግሎት ፤ ጸሎትና ጾምን ከፍ ሲልም ሰማዕትነትን ሳይቀር ያለ ዋጋ ከንቱ አድርጎ የሚያስቀር ነው። (፩ኛቆሮ.፲፫፥፩-፴) ለዚህም ነው ካህናት በሥርዓተ ቅዳሴ በሚሰየሙበት ዕለት ሁሉ ለጸሎታቸው ውኩፍነት (ተቀባይነት ማግኘት) ሕዝቡንም ቀሳውስቱንም ዲያቆናቱንም «ይቅር በሉኝ፣ ማሩኝ» እንዲሉ ሥርዓት የሚያዝዘው (ሥር.ቅዳ ፪፥፯)

ፍቅርን የሚጠላ ዲያብሎስ በሰዎች ሁሉ ላይ እንደሚያደርገው በካህናትም መካከል ፍቅርን በማጥፋት ሊፈትናቸው ይችላል። እርግጥ ነው ከዲያብሎስ ብቻም ሳይሆን በካህናት ዘንድ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሲፋጠኑ ከመንፈሳዊ ቅንዓት የተነሳ አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። ይህ ለበጎ ነው።

ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስና በርናባስ አብረው ለስብከተ ወንጌል ሲፋጠኑ እገሌን ይዘን እንሂድ አንሂድ በሚል ተጣልተው ሁለቱም

አብረው መሄዳቸው ቀርቶ ወደ ተለያዩ ሀገራት ሄደው ነበር ፤ መጣላታቸው ግን «እከብር» ብለው አልነበረም ወንጌልን ለማዳረስ እንጂ ፤ አንድም መጣላታቸው ጥበበ እግዚአብሔር ነበረበት። ሁለቱ ወደ አንድ ሥፍራ ሄደው ቢያስተምሩ ሃይማኖት ይጸናል እንጂ አይሰፋም ነበር። ስለዚህ የሁለቱ በተለያየ አቅጣጫ መሄድ ሃይማኖት እንዲሰፋ አድርጎአል (ሐዋ ፲፭፥፴፮)

«ደቂቀ እምየ ተበሳሱ በእንቲያየ / የእናቴ ልጆች ስለ እኔ ተጣሉ» (መኃ ፩፥፮ ትር) እንዲል ካህናት ስለ ምእመናን ሕይወት ማማር ሲሮጡ በመካከላቸው አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። ሌላም ምሳሌ ብንጠቅስ ቅዱስ ጳውሎስ ወንድሞቹን ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዮሐንስን በጥፊ ተማትቶ ነበር። ይኸውም ሁለቱ ሐዋርያት በአንጾኪያ ሲያስተምሩ ሰዎች ደብድበው ጣሏቸው። ነገሩን የሰማው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹አሕዛብን እጠቅም ዘንድ እንደ አሕዛብ ሆንክ›› እንዳለ የሀገሪቱን ሰዎች ልብስ ለብሶ መጣ። ቅዱስ ጴጥሮስንም ባየው ጊዜ በጥፊ መታው። ቅዱስ ጴጥሮስ በነገሩ ግራ ተጋብቶ ቀድሞ አሳዳጅ የነበረውን ጳውሎስ *«ተመየጥክኑ ኀበ በዘቀዳሚ ግብርከ* / ወደ ቀደመ ግብርህ ተመለስክን?» ብሎ ጠየቀው። ከዚህ በኋላ ‹‹አምላክ አለን የሚትሉ ከሆነ እስቲ ሙት አስነሡና እንያችሁ›› ብሎ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ በቅርቡ ሞቶ ወደተቀበረ የንጉሥ ልጅ መቃብር ከሕዝቡ ጋር ወሰዳቸው። ሔደውም በመቃብሩ አንጻር ጸለዩ ፤ ሙቱም ተነሣ። ይሁንና በእግዚአብሔር ስም ከሞት ያስነሣው ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ እንደሆነ መሰከረ። ሐዋርያው በፈሊጥ ሕዝቡን አሳምኖ ወንድሞቹን ከሞት አዳነ። በዚህ ወቅት የመታቸው ምት፣ የተቆጣቸው መቆጣት ለአንጾኪያ ክርስቲያኖች ድኅነት ምክንያት እንደሆነ ሁሉ ካህናት

በአገልግሎት ነገር በሀሳብ ባይስማሙ ፍቅርን የማጣት ብቻ ሳይሆን ለመልካምም ሊሆን እንደሚችል ማሰብ ይገባል።

ካህናት በአገልግሎትና በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ቀለም ነጠበ ፤ ሕግ ተጣሰ ፤ ሥርዓት ፈረሰ ብለው የሚፈጥሩት አለመግባባት አንዳንድ ጊዜም ያላቸው ፍቅረ እግዚአብሔርና የደረሱበት ቅድስና መገለጫም ሊሆን ይችላል። ለዚህ አብነት የሚሆነን የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና የቅዱስ ኤጲፋንዮስ አለመግባባት ነው።

ንግሥት አውዶክስያ የምትባል ገፋዒተ ነዳይ መፍቀሪተ ነዋይ (ነዳያንን የምትበድል ገንዘብን የምትወድ) ንግሥት ነበረች። ይህች ሴት ከከተማ አቅራቢያ የምትሆን ቦታ የነበረቻትን ባልቴት ዐታዋን ቀማቻት። ይህች ባልቴት ወደ ኤጲስ ቆጶሱ ወደ ዮሐንስ አፈወርቅ ሄዳ ተማጸነች ፤ ጽርሐ ነዳያንን (የችግረኞችን ጩኸት) የሚሰማው ኤጲስ ቆጶስም ነገሩን ግራ ቀኝ ሰምቶ ንግሥቲቱን *«መልሺላት»* አላት ፤ ንግሥቲቱ አውዶክስያም *«መንግሥቱን የያዝን እኛ ነን እንጂ ዶርስዋ ናት?»* አለችውና እምቢ አለች ፤ ዮሐንስም «እንኪያስ ርስተ ምድር ነቅለሽ ርስተ ሰማይ ትወርሻለሽን? ከዐፀደ ቤተ ክርስቲያን አትድረሽ ከምእመናን አትገናኚ ሥጋወ ደሙን አትቀበይ ! » ብሎ አወገዛት ፤

ንግሥቲቱም ወደ ቆጵሮስ ሊቀ ጳጳስ ወደ ኤጲፋንዮስ ስሞታን ላከች። ስሞታዋም *«ያሃይማኖት ሕጸፅ ሳይገኝብኝ በምግባር አወገዘኝ ፤ አንድ ሥራን ሥራ! ፤ ባትሠራ ግን የቀደመ የአባቶቼን ዘመን አመጣለሁ! (በምእመናን ላይ መከራን አጸናለሁ)»* የሚል ዛቻ የተቀላቀለበት ነበር።

ቅዱስ ኤጲፋንዮስም «ምእመናን ከመከራ አረፉ ስንል በዚህ ምክንያት መከራ ቢመጣባቸው መልካም ነውን? ተው!» በማለት ቅዱስ

ዮሐንስን ተናገረው ፤ ዮሐንስም «ርስተ ምድር ነቅላ ርስተ ሰማይ ትወርሳለችን? የቀደመ አባቶቿን ዘመንስ ብታመጣ (በምእመናን ላይ መከራን ብታጸና) ለእርሷ ይብሳት እንጂ (የምትጎዳ የምትከነን እርሷ ናት እንጂ) እኔ ምን ቸገረኝ!» አለው። በኋላም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ፤ ኤጲፋንዮስ ሄድኩ ሲለው «ምነው በነገሬ ገባህብኝ?» አለው። ኤጲፋንዮስም «በነገርህስ አልገባሁም በነገርህ የገባውን መርምር» አለውና ሊሄድ ተነሣ። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ «መሄድንማ እንዳይሄዱ! (ምኑን ሄደክው ከመንገድ ትሞታለህ እንጂ)» አለው። ቅዱስ ኤጲፋንዮስም መልሶ «መቅረትንማ እንዳይቀሩ! (ለንተስ መች እዚሁ ትቀራለህ ታሰረህ ተግዘህ ትሞታለህ እንጂ)» አለው።

ይህ ሁሉ የሆነ በሁለቱ ቅዱሳን መጣላት መከራረፍ ኖሮባቸው አይደለም። የአንዱ ሞት ለአንዱ ተገልጦ መናገራቸው ክብራቸው ይታወቅ ዘንድ ነው። (የቅ. ዮሐንስና የቅ. ኤጲፋንዮስ ቅዳሴያት መቃድም) ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው እነዚህ ሁለት አበው ካህናት ሃሳባቸው ይለያይ እንጂ የሁለቱም ድርጊት ለመንጋው የሚራሩ ከመሆናቸው የመነጨ ነው። አንድም ሥጋ ለባሾች እንደመሆናቸው ሥጋ ለለበሰ ደካማ ሰው ሁሉን ቻይነት እንዳልተሰጠው ያሳያል። ስለዚህ ካህናት በአገልግሎት ወቅት ባይግባቡ ይህ የተለመደና ለመልካም ሊሆን የሚችል ነው። አንዳንዱም የካህናት አለመግባባት ከላይ እንዳየነው የደረሱበትንም ፍቅረ እግዚአብሔር ሊያስረዳ ይችላል።

ይህን ስንል ግን ለቤተ ክርስቲያን በመቆርቆር ሰበብ መቀራቆዝ ተገቢ እንዳልሆነም እያስታወስን ነው። ‹‹የአንድ ጎጃ የጣሪያ ክዳን የሚሠሩ ሰዎች ሣር አይሻሙም›› እንደሚባለው ብሂል ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ጥቅም የተለለፉ ሰዎች ልዩነቶቻቸውን እያስፉ ከመናቆር

በላይ የሚያስቀድሙት የክህነት አደራቸውንና ፍቅርን መሆን ይኖርበታል። ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከመቆርቆር ባሻገር ከግላዊ ጥቅም ፤ ከወገንተኛነት እና ከሥጋዊ አስተሳሰብ የሚመነጭ ፤ ከዲያብሎስ የሆነ አለመግባባትም በካህናት ዘንድ ሊከሰት ይችላል። ዓመፅ ማነሳሳትና ማሳደም ፤ አንዱ አንዱን ማቃለልና ማዋረድ ፤ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት መነሣት ፤ ነገር መሥራት ፤ ቀለም በገደፈው አንደቡቱ በተደናቀፈው ማፌዝ ፤ በሌላው መሾም መሸለም መከፋት የመሳሰሉት ሁሉ ፍቅርን የማጣት ውጤቶች ናቸው። ይህን ዓይነቶች ክፋ ግብሮች በቀደሙት ዘመናት የተከሰቱና በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገቡ ናቸው።

ለምሳሌ ካህናተ አይሁድ ከእነርሱ ይልቅ ተቀባይነትን ባገኙት በቅዱሳን ሐዋርያት ላይ ይቀኑ የነበረው ለሥርዓተ አሪት ከመቆርቆር ብቻ አልነበረም። የእነርሱን ቦታ የተቀሙ መሆናቸው ቆጭቶአቸው ነው እንጂ። ሌላው ቀርቶ በሐዋርያት የሚመራ ብዙ ጉባኤ ተዘርግቶ ሲያዩ እጅግ ይቀኑ ነበር (ሐዋ ፭፫÷፲፰) ከዚህም አልፈው ለአምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸመውን ጸም ቅዱስ ጳውሎስን ካልገደልን አንበላም ብለው ለክፋት ሊጠቀሙበት ሞክረው ነበር (ሐዋ ፳፫÷፲፪)

አንዱ በክብር ከፍ አለ ብሎ መቅናትም ሆነ በሌላው ላይ ተንኮል ለመፈጸም መንፈሳዊ ነገርን እንደማጥቂያ መሣሪያና መማማያ መጠቀም የሰቃልያን አይሁድ (ጌታን የሰቀሉ አይሁድ) ግብር ነው። አንዱ በሌላው መከበር ደስ መሰኘት አለበት እንጂ «ከኋላዬ መጥቶ . . . » ወዘተ በሚል ፈሊጥ በሌላው ላይ መመቅኘትና ነገር መሥራት አይገባም። ይህም ለሁሉ እንደ ቸርነቱ ጸጋን የሚያድል አምላክን ማስቆጣትና «ዓይንክ ሐማሚ / ዓይንህ ምቀኛ ሆነችን?» ማለኘት ነው።

ጥላቻ ከግል አለመግባባት አልፎ በመላእክተ ቤተ ክርስቲያን (በቤተ ክርስቲያን አለቆች) እና በአበምኔቶች ላይ እስከ ማመጽና እስከ ማሳደም ሊያደርስ ይችላል። ካህናት የሚመሯቸው አባቶች ባልሆነ መንገድ ሲመሯቸው መጠየቅና መብታቸውን ማስከበር ይገባቸዋል። ይሁንና ጠብና ግርግር ወዳድነት ሲለጥን ያለ ምክንያት ሁከት መፍጠር ብሎም ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ለማስጠበቅ የሚጥሩ አባቶች ላይም እስከ መነሳትና የአገልግሎት እንቅፋት እስከ መሆን ያደርሳል ያስቀሥፋልም። እንዲህ ያለ ግብር በመፈጸማቸውና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የሚያስከብር አበምኔት ላይ በማመጻቸው እንደ ዳታንና አቤሮን መሬት ተሰንጥቃ የዋጠቻቸውን መነኮሳት ታሪክ በዚህ ሥፍራ እንደ ምሳሌ ልንይዘው እንችላለን። (ተአ.ማር ፩፻፫፰)

በጎ የሠራን ፣ በጥሩ ጸጋ ያገለገለን ወንድም አለማመስገንና አለማበረታታትም ሆነ ሲመሰገን ደስ አለመሰኘት የፍቅር ማጣት ውጤት ነው ፤ አንጋፋ የሚባሉት ደራሲ ሐዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር በሚል ርዕስ በጻፉት ልቦለድ «ካህን በካህን አፍ ተመስግኖ አያውቅም» የሚል ትዝብት አዘል ሀሳብ አስቀምጠዋል። እርግጥ ይህ የደራሲው የግል አስተያየት ነው። ቢሆንም ግን ከእውነት የራቀ አይደለምና ካህናት በዚህ አይነቱ ግብር እንዳይነቀፉ ሊሆኑ ይገባል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አንዱ የአንዱን ክብር ከፍ ለማድረግ ሲሽቀዳደሙ የነበሩ ቀሳውስትን ባንዘነጋም ‹ፍቅር ትቀዘቅዛለች በተባለበት በዚህ ዘመን ፍቅርን ማጣት አሳሳቢው ችግር ነው። ‹‹ፍቅር ግን ከንቱ ነኝ›› የሚለው የሐዋርያው ቃል ምንኛ ከባድ ነው? ፍቅር በሌለበት ጸሎት አገልግሎት ሌላው ቀርቶ ሰማዕትነት ሳይቀር ዋጋ ቢስ ነው ብሏል። ፍቅር የለም ማለት አግዚአብሔር የለም ማለት ነው ፤ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።

ከዚህ ሌላ በካህናት ዘንድ ቀለም የሚገድፍ ፣ ዜማ የሚያበላሽ ፣ አውቀት የሚያንሰው ሲገኝ በየውሃት ከማቅናትና በፍቅር ከማረም ይልቅ በዚያ ሰው ማፌዝና ማዋረድ በካህናት ዘንድ ቀደም ባሉት ዘመናት የታየ ችግር ነበር።

እመቤታችን በርኅራኄዋ እንግዳ ድርሰትን እስከ መድረስ አበቃችው እንጂ የብህንሳው አባ ሕርያቆስንስ «ቀድሰህ ካላቆረብከኝ» ብለው ግድ ያሉት ካህናት ከሕዝብ ፊት ስቀው ሊያስቁበት አልነበር? ይሁንና በታላቁ የቅዳሴ ሥርዓት ሰማያዊ ምሥጢር እንደሚፈጸም ፣ ይህ ካህንም ስለ እነርሱም ኃጢአት ጭምር ይቅርታን ሲሰጠን ቅድመ እግዚአብሔር እንደሚቆም ሊያስቡና ተሳልቆን ሊተው በተገባቸው ነበር።

በተገሣጽ እንደተጻፈ «አነሆ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ካህን ቂሱ የሁሉን ጸሎት ያሳርግ ዘንድ ገብቶ ቆሟል። አንተ ግን ሳታቋርጥ ትስቃለህ» *«ወኢትፈርህ ምንተኒ ወውእቱሰ ናሁ ይጼሊ በእንቲኣከ ወአንተ ታስተሐቅሮ / ምንም አትፈራም እርሱስ እነሆ ስለ አንተ ይጸልይ ዘንድ ገባ አንተ ግን ትንቀዋለህ ታቃልለዋለህ!»* ተብሎአልና።

አባ ሕርያቆስ ግን ተንኰላቸውን የሚያውቅ ሆኖ ሳለ በትሕትና ፣ በተዋርዶ ፈቃዳቸውን ሲሞላ ለሥርዓተ ቅዳሴ ሲሰየም *እንደ ጠሉኝ ልጥላቸው ፣ እንደናቁኝ ልናቃቸው* ሳይል ፣ ልቦናውን ከቂም በቀል ንፁህ አድርጎ ነበረ *«ወእቀውም ቦም በትሕትና ወበፍቅር በዛቲ እለት ቅድመ ዝንቱ ምስጢር / በፍቅርና በትሕትና በዚህ ምሥጢር ፊት (በሥጋ ወደሙ ፊት) እቆማለሁ»* እንዳለ በቅዳሴው (ቅ.ማር ፩፥፮)

ጌታችን «በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናል ፤ ደግሞም እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ቢስማሙ በሰማያት ካለው አባቴ ዘንድ ይደረግላችኋል» (ማቴ ፲፰፥፲፱) እንዳለ ካህናት በአንድ ልቦና በፍቅር ሆነው ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡት ልመናና ማኅበራዊ ጸሎት ግዳጅ የሚፈፅም ፤ ለነፍስ የሚጠቅም ነው። ከሁሉም እበልጣለሁ በማለትም ሆነ በትዕቢት ከካህናት ማኅበራዊ ጸሎት «ሰዓታት ማኑሔት ቅዳሴ በእኛ ፈዘ ቀረ ወዘተ» በማለት የሚርቁ ሲጎድሉ እንጂ ሲጠቀሙ አልታየም ለዚህም የአንድ ሊቅ ታሪክ ምሳሌ ነው።

ይህ ሰው መንፈሳዊ ትምህርትን የዘለቀ ቢሆንም ግብረ ገብ የሌለው ሆዳምና ስካራም ነበረ ፤ ይሁንና ቤተ ክርስቲያን በገባ ጊዜ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ይገለፅለታል። «እውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል» የሚለው ቃል ለእንዲህ አይነቱ ሰው ሕይወት የተነገረ ይመስላል። (፩ቆሮ.፰፥፪) ይህ ሰው እመቤታችንን ከማክበሩ በቀር ትዕቢተኛ ስለነበረ ሌላው ቀርቶ ከካህናት ጋር አልቀላቀልም ብሎ ሰዓታትን ለብቻው ያደርስ ነበር። ይህ ሰው ከሞተ በኋላ በእመቤታችን ምልጃ ከሲኦል ወደ ገነት ተመልሷል። በአፀደ ነፍስ ሆኖ ለአንድ ዲያቆን በሕልም ተገልጦ ያለበትን ከነገረው በኋላ ለካህናት ሁሉ የሚሆን መልዕክትን ለዲያቆኑ ተናገር ብሎ ልኮታል እንዲህ ሲል፦

«ንግሮሙ ኦ ላዕከ ለካህናት አበዊከ ከመ ኢይኅድጉ ጸሎተ ማኅበሮሙ ቅድስት /አንተ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆይ አበው ካህናት የከበረች ማኅበራዊ ጸሎታቸውን እንዳይተዉ ንገራቸው!» (ተአ. ማር ፪፻፺) የካህናት የማኅበር ጸሎት እጅግ የከበረና እንኳን በአፀደ ሥጋ ያሉት በአፀደ ነፍስ ያሉትም ሳይቀር የሚሹት /የሚፈልጉት/ መሆኑ

በዚህ ታወቀ። ስለዚህ ካህናት አካላቸውም ፤ ልቦናቸውም በማኅበር ፤ በአንድነት ሆኖ ልመናን ሊያቀርቡ ይገባል።

በካህናት መካከል ሊኖር የሚገባው ፍቅር «ፍቅር ሥጋዊ» አይደለም ፤ ፍቅር መንፈሳዊ ነው እንጂ። በመብል መጠጥ ፤ በመገባበዝ ፤ በጥቅም መፋቀር ፍቅር ሥጋዊ ነው። ይህ ዓይነቱን ፍቅር ወንበዴዎችም ያደርጉታል። አነርሱ የሚፋቀሩት በመብል በመጠጥ በጥቅም ነውና። መንፈሳዊ ፍቅር ግን እንደዚህ አይደለም። *«ወባሕቱ ለነሰ ተዓርከትነ አኮ ከመዝ አላ ይእቲ ተዐርከትነ እሙነ እንዘ ናስተሓምም በበይናቲነ* /የእኛ (ፍቅር) ግን እንደ ሥጋዊ አይደለም። እርስ በእርሳችን እየተሳሰብን ፍቅራችን መንፈሳዊ ይሆን ዘንድ ነው እንጂ» ተብሎ እንደተነገረ። (ተግሣጽ ዘቅ.ዮሐ.አፈ)

በዚህ ንውስ ርዕስ መግቢያ ላይ እንደተገለጠው የካህናት መታወቂያቸው ፍቅር ነው ፤ መክባበራቸውና መተሳሰባቸው የካህናት ውበታቸው ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮቿ አንድ ልብ እንዲሆኑ በመሻት «ሁልጊዜ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለሚሰበሰቡ ሊቃውንት ፍቅርን ስጥ» በማለት ስለ አገልጋዮቿ ፍቅር ትሰምናለች።

ቅዱሳን ሐዋርያት በካህናት መካከል ሊኖር ስሚገባ ፍቅር በቃልም በግብርም ምሳሌዎች ነበሩ። ለምሳሌ ጌታችን በመቃብር ሦስት ቀንና ሌሊት ባደረ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቃብሩ ሄደው ነበር። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ዮሐንስ ሮጦ ከመቃብሩ ደጅ ሲደርስ ቆመና ቅዱስ ጴጥሮስን ጠበቀው ፤ ይህ ኤጲስ ቆጶስ ከቁስ ቀድሞ መቅደስ የመግባቱ ምሳሌ ሲሆን አንድም በካህናት መካከል መከባበርና መፋቀር እንደሚያስፈልግ ያስተምረናል። (ዮሐ ፳፥፩ ትር)

የቤተ ክርስቲያናችን ባሕል ፍቅርና ትሕትና ነው። አባቶቻችን ኪዳን ለማድረስ ፣ ለማሳረግ ወዘተ አንተ ቅደም አንተ ቅደም መባባላቸው ለይምሰል ሳይሆን ከሐዋርያት የተቀበሉት «ከእኔ ይልቅ ወንድሜ» የመባባል ባህል ነው። ቀሳውስት ኑዛዜን ሲሰጡ በማዕረግ የሚስተካሏቸውን «አባቶቼ» ፣ በመዓረግ የሚያንሱአቸውን «ወንድሞቼ» ብለው መጥራታቸው ትእምርተ ፍቅር ወትሕትና ነው። «ተዘከረኒ ኦ አቡየ ካህን በጸሎትከ ቅድስት!» እየተባባሉ በጸሎት መተሳሰባቸው የካህናት ፍቅር መገለጫ ነው።

ካህን ከካህን ጋር ሲጣላ ልጅ ወላጆቹ ሲጣሉ የሚሰማውን ያህል ምእመናንን ያሳቅቃል ፣ ፍቅርን ተቀባይነት አገኝ ብሎ ካህን ካህኑን ለምእመናን ቢያማና ቢተች ራሱን ያዋርዳል። የቀደሙት ቅዱሳን ካህናት ሌላውን ካህን እያቃለሉ በምእመናን ፊት የሚናገሩና ራሳቸውን ብቻ ጥሩ አድርገው የሚያሳዩ አልነበሩም ፣ እንዲያውም ከራሳቻው ክብር ይልቅ የሌላው ክብር በምዕመናን ፊት እንዲገለጥ የሚሹ ነበሩ።

ቀደም ሲል የሥልጣነ ክህነትን አስመልክቶ ያነሣነውን ታሪክ እዚህ ላይ ደግመን እናንሣ፡- ኃጢአቷን ጽፋ ያመጣችለትን ሌት የተጻፈውን ሁሉ ከእንዲት ኃጢአት በቀር እንደፋቀላት ስለ ቅዱስ ኤፍሬም አንብበን ነበር። ይህ አባት የቀረችውን አንዲት ኃጢአት ግን «ለእኔ አይቻለኝም ፣ ለቅዱስ ባስልዮስ ነው እንጂ» ብሏታል ፣ ቅዱስ ባስልዮስም እንዲሁ «ለእኔም አይሆንልኝም ፣ ለቅዱስ ኤፍሬም ነው እንጂ» ብሎ ነበር። ሁለቱም አባቶች ሥልጣን ሳይኖራቸውና መፋቅ ሳይችሉ ቀርተው አይደለም። የእኔ ክብር ከሚገለጥ የወንድሜ ክብር ይገለጥ ብለው ነው እንጂ።

ከካህን የሚጠበቅ ግን ጥል አይደለም «ወኩሉ ነፍስ ይትጋባእ ምስለ ዘከማሁ ወሰብእኒ ምስለ ዘይዛወን ይተሉ /ፍጥረት ሁሉ እንደ

እርሱ ካለ ፍጥረት ጋራ ወዳጅ ይሆናል። ሰውም የሚመስለውን ይከተላል» እንዲል (ሲራ ፲፫፡፲፯) ካህን በመዐርግ ከማይመስሉት ጋር ወዳጅነት መስርቶ ንቀትን ከሚያተርፍ ይልቅ ፣ ወታደር ከወታደር ፣ ሽማኔ ከሽማኔ ጋር አንድ እንዲሆን ካህን ከካህን ጋር በፍቅር ተወዳጅቶ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊደጋገፍ ይገባል።

ይልቁንም «ተአመኑ በበይናቲክሙ ኃጢአተክሙ /እርስ በእርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ» እንዲል ካህናት ለምእመናን ንስሓ ከመስጠት ባሻገር አንዱ ቁስ ለአንዱ ኃጢአቱን እየተናዘዘ እርስ በእርስ በመደጋገፍና በመገሣጸጽ የፍቅር አብነቶች መሆን ይጠበቅባቸዋል። (ያዕ ፭፡፲፮)፤ ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዳሴው «ኦ ካህናት አንትሙ ውእቱ አዕይንተ እግዚአብሔር ብሩሃት ተናጸሩ በበይናቲክሙ ፩ዱ ምስለ ካልዑ / ካህናት ሆይ የእግዚአብሔር ብሩሃን ዓይኖች እናንተ ናችሁ እርስ በእርሳችሁ አንዱ ከአንዱ ጋር ተያዩ» በማለት ካህን ከካህን ጋር በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊደጋገፍ እንደሚገባ ያስረዳል።

ዘወትር የሚሠዋውን ጎብስት በተራራና በኮረብታ፤ በበረሃና በቆላ
የተበተነ ሲሆን የሚሰበሰበውና አንድ የሚያደርገው አምላክ ከካህናት
ወገን አሳቡ የተለያየውን አንድ ያድርገው አሜን!
«ፍቅር ወሰንዕው የሃሉ ምስለ ካህናተ እግዚአብሔር» ፍቅርና
መስማማት ከእግዚአብሔር ካህናት ጋር ይሁን!
(ሃይ. አበ. ዘቁርሎስ ፸፭፡፸፩)

፬. ክብርን ተርእዮን /መታየትን/ መሻት

ሰው ክብር የሚገባው ለእግዚአብሔር መሆኑን እያወቀ ለራሱ መክበርን የሚሻ ከሆነ በትዕቢት ጸር ተሸንፎአል ማለት ነው። ካህናትም ከክብራቸው አንጻር ለዚህ ጸር ሊጋለጡ ይችላሉ። የቀደሙት የሐዲስ ኪዳን ካህናት የዚህ ዓይነቱን ጸር ድል ነስተውት ነበር። እግዚአብሔር

የቤተ ክርስቲያናችን ባሕል ፍቅርና ትሕትና ነው። አባቶቻችን ኪዳን ለማድረስ ፣ ለማሳረግ ወዘተ አንተ ቅደም አንተ ቅደም መባባላቸው ለይምሰል ሳይሆን ከሐዋርያት የተቀበሉት «ከእኔ ይልቅ ወንድሜ» የመባባል ባህል ነው። ቀላውስት ኑዛዜን ሲሰጡ በማዕረግ የሚስተካሏቸውን «አባቶቼ» ፣ በመዓረግ የሚያንሱአቸውን «ወንድሞቼ» ብለው መዋራታቸው ትእምርተ ፍቅር ወትሕትና ነው። «ተዘከረኒ አ አቡየ ካህን በጸሎትከ ቅድስት!» እየተባባሉ በጸሎት መተሳሰባቸው የካህናት ፍቅር መገለጫ ነው።

ካህን ከካህን ጋር ሲጣላ ልጅ ወላጆቹ ሲጣሉ የሚሰማውን ያህል ምእመናንን ያሳቅቃል ፣ ፍቅርን ተቀባይነት አገኝ ብሎ ካህን ካህንን ለምእመናን ቢያማና ቢተች ራሱን ያዋርዳል። የቀደሙት ቅዱሳን ካህናት ሌላውን ካህን እያቃለሉ በምእመናን ፊት የሚናገሩና ራሳቸውን ብቻ ጥሩ አድርገው የሚያሳዩ አልነበሩም ፣ እንዲያውም ክፉሳቸው ክብር ይልቅ የሌላው ክብር በምዕመናን ፊት እንዲገለጥ የሚሹ ነበሩ።

ቀደም ሲል የሥልጣነ ክህነትን አስመልክቶ ያነሣነውን ታሪክ እዚህ ላይ ደግመን እናንሣ፦ ኃጢአቷን ጽፋ ያመጣችለትን ሴት የተጻፈውን ሁሉ ከአንዲት ኃጢአት በቀር እንደፋቀላት ስለ ቅዱስ ኤፍሬም አንብበን ነበር። ይህ አባት የቀረችውን አንዲት ኃጢአት ግን «ለእኔ አይቻለኝም ፣ ለቅዱስ ባስልዮስ ነው እንጂ» ብሏታል ፣ ቅዱስ ባስልዮስም እንዲሁ «ለእኔም አይሆንልኝም ፣ ለቅዱስ ኤፍሬም ነው እንጂ» ብሎ ነበር። ሁለቱም አባቶች ሥልጣን ሳይኖራቸውና መፋቅ ሳይችሉ ቀርተው አይደለም። የእኔ ክብር ከሚገለጥ የወንድሜ ክብር ይገለጥ ብለው ነው እንጂ።

ከካህን የሚጠበቅ ግን ጥል አይደለም «ወኩሉ ነፍስ ይትጋባእ ምስለ ዘከማሁ ወለብእኒ ምስለ ዘይዛወን ይተሉ /ፍጥረት ሁሉ እንደ

እርሱ ካለ ፍጥረት ጋራ ወዳጅ ይሆናል። ሰውም የሚመስለውን ይከተላል» እንዲል (ሲራ ፲፫÷፲፭) ካህን በመዐርግ ከማይመስሉት ጋር ወዳጅነት መስርቶ ንቀትን ከሚያተርፍ ይልቅ ፣ ወታደር ከወታደር ፣ ሽማኔ ከሽማኔ ጋር አንድ እንዲሆን ካህን ከካህን ጋር በፍቅር ተወዳጅቶ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊደጋገፍ ይገባል።

ይልቁንም «ተሰመኑ በበይናቲክሙ ኃጢአተክሙ /እርስ በእርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ» እንዲል ካህናት ለምእመናን ንስሓ ከመስጠት ባሻገር አንዱ ቂስ ለአንዱ ኃጢአቱን እየተናዘዘ እርስ በእርስ በመደጋገፍና በመገሣጸጽ የፍቅር አብነቶች መሆን ይጠበቅባቸዋል። (ያዕ ፬÷፲፮)፤ ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዳሴው «ኦ ካህናት አንትሙ ውእቱ አዕይንተ እግዚአብሔር ብሩሃት ተናጸሩ በበይናቲክሙ ፩ዱ ምስለ ካልዑ / ካህናት ሆይ የእግዚአብሔር ብሩሃን ዓይኖች እናንተ ናችሁ እርስ በእርሳችሁ አንዱ ከአንዱ ጋር ተያዩ» በማለት ካህን ከካህን ጋር በመንፈሳዊ ሕይወቱ ሊደጋገፍ እንደሚገባ ያስረዳል።

ዘወትር የሚሠዋውን ኅብስት በተራራና በኮረብታ፤ በበረሃና በቆላ የተበተነ ሲሆን የሚሰበሰበውና አንድ የሚያደርገው አምላክ ከካህናት ወገን አሳቡ የተለያየውን አንድ ያድርገው አሜን!

«ፍቅር ወሰንዕው የሃሉ ምስለ ካህናተ እግዚአብሔር» ፍቅርና መስማማት ከእግዚአብሔር ካህናት ጋር ይሁን!

(ሃይ. አበ. ዘቁርሎስ ፷፭÷፷፰)

፬. ክብርን ተርእዮን /መታየትን/ መሻት

ሰው ክብር የሚገባው ለእግዚአብሔር መሆኑን እያወቀ ለራሱ መክበርን የሚሻ ከሆነ በትዕቢት ጸር ተሸንፎአል ማለት ነው። ካህናትም ከክብራቸው አንጻር ለዚህ ጸር ሊጋለጡ ይችላሉ። የቀደሙት የሐዲስ ኪዳን ካህናት የዚህ ዓይነቱን ጸር ድል ነስተውት ነበር። እግዚአብሔር

በሰጣቸው ሥልጣን አጋንንትን ሲያወጡ ፣ ድውያንን ሲፈውሱ ሰዎች አይተው ሲያደንቋቸው እንኳ «ከራሳችን አንቅተን እንደዳንን አድርጋችሁ ለምን ታደንቃላችሁ ለምንስ ታከብሩናላችሁ?» እያሉ በመገሠጽ የሰዎች ልቦና ወደ እግዚአብሔር ይመልሱ ነበር። ከመከበራቸው የተነሣ እንደ አምላክ መሥዋዕት ሊያቀርቡላቸው የተነሡም ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን ሐዋርያት ውዳሴ ከንቱ ሳያሸንፋቸው መክረው አስተምረው ወደ እግዚአብሔር ዘወር እንዲሉ ያደርጓቸው ነበር። (ሐዋ. ፲፬፥፲፫)

አሊህ ካህናተ ሐዲስ ውዳሴ ከንቱንና ክብርን የማይሹ ትሑታን በመሆናቸው እንኳን በማይገባቸው በሚገባቸውም ገንዘብ እንኳ ክብር ሲሰጣቸው አይሹትም ነበር። ለምሳሌ፡- ቅዱስ ጴጥሮስ ለክህነቱ የሚገባ የጸጋ ስግደትን ቆርኔሌዎስ ሊያቀርብለት የማትፈርስ የማትበሰብስ ሥልጣነ ክህነትን ይዞ ሳለ «እንደ አንተ ያለሁ ፈራሽ በስባሽ ነኝ» ብሎ በትሕትና ሲያስነሣው እንመለከታለን። ቅዱስ ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስን ካጠመቀ በኋላ እንኳ ስለ ቆርኔሌዎስ መጠመቅ በይሁዳ ላሉ ክርስቲያኖች ሲተርክ ቆርኔሌዎስ ያቀረበለትን ስግደትና የመለሰለትን ምላሽ አልነገራቸውም ነበር። (ሐዋ. ፲፩፥፩)

ከዚህም ሁለት ነገሮች ለመረዳት ይቻላል። አንደኛ የቆርኔሌዎስ ለቅዱስ ጴጥሮስ መስገድ ስኅተት እንደሌለው ነው። /ቢኖረው ጠቅሶ ባስተማረበት ነበርና / ፤ሁለተኛ ቅዱስ ጴጥሮስ ለክብሩ ቦታ የማይሰጥ መሆኑን ነው። / የሚሰጥ ቢሆን #የመቶ አለቃው ግና ሲያየኝ ሰገደልኝ!. . .» ብሎ በተናገረ ነበርና/

ካህናት በአገልግሎታቸው ረድኤተ እግዚአብሔር በዝቶላቸው ጸንተው ቢያገለግሉና መንጋውን መጠበቅ ቢችሉ፣ ትሩፋታቸውም ቢበዛ ክብርን ከፈጣሪ እንጂ ከሰው መሻት አይገባቸውም። እንዲያውም በሰው መመስገን ክብር ያይደለ ተዋርዶ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለ ሰው

ሰውን ቢያከብረውና ስሌላው ሥራውን ቢያወራለት አመሰጋኙም ፤ ተመስጋኙም ፤ የሚመሰገንለት ሰሚውም መዋቲ ፈራሽ በስባሽ ናቸውና ተዋርዶ ነው። (፩ቆሮ ፬፥፫ ትር)

ደግሞ ካህናት መንጋውን ቢጠብቁ ጌታ ለሐዋርያቱ እንደ ነገራቸው «የማንጠቅም ባሪያዎች ነን ልናደርግ የሚገባንን አድርገናል» ሊሉ ይገባቸዋል። (ሉቃ.፲፯፥፲) እንጂ መታበይ አይገባቸውም። ይኖው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተናገሩት ንግግርም ለዚህ ምስክር ነው። እኚህ ደኅኖ አባት የወር ደመወዛቸውን ለእንለምውታን ይሰጡ ነበር። ይሁንና ይህ መልካም ሥራቸው እንዲነገር አይፈልጉም ነበር። ለምን ተብለው ሲጠየቁም «እናት ለልጆችዋ የምትሰጠውን ሁሉ ሀገር ይወቅልኝ ትላለችን?» በማለት መልሰዋል። ስለዚህ ካህን በክህነቱ በጎ ቢሠራ እንኳ «ቀድሞስ መሸሚ ለምን ሆነና» ብሎ ራሱን ከትዕቢት ሊያርቅ ይገባዋል። ጸሎቱም «ኦ እግዚኦ ለለትት እምኔየ ሰይጣነ ትዕቢት / አቤቱ ሰይጣነ ትዕቢትን ከእኔ አርቅ!» የሚል ሊሆን ይገባል።

ጌታችን እንዳስተማረው የሚኖር ካህን ለውዳሴ ከንቱ እጁን አይሰጥም። ደግሞም አዐ አዐ የሚል ፤ የሚያወድስ ሁሉ ከልቡ ነው ማለትም አይቻልም። ክብርን ተውዳጅነትን ሽቶ የሚያወድስም አለ። ጌታችን ቸር ሆኖ ሳለ ቸር መባልን እንዲሁ አልተቀበለም። ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ከሚሉት ከድንግል ተወልዶ ሳለ የወለዱህ ማኅጸኖች ያጠቡህ ጡቶች የተመሰገኑ ናቸው3 መባልን እንዲሁ አልተቀበለም። የውስጥ የአፍአን መርምሮ የሚያውቅ እርሱ ከሚያወድሱት በስተጀርባ ያለውን የአወድሰኝ ላወድስህ ጨዋታ ያውቅ ነበርና ነው።

ጌታችን በተሰደደ «ስለምን ቸር ትለኛለህ?» የሚል ጥያቄው ውዳሴን ስለመመርመር ለካህን ትልቅ ትምህርት ይሰጣል። ካህንም «ኃይለ ሊቅ!» ፣ «የሰነ አገሌ ልጅ!» ፣ «ኃይለ ሙያ!» በሚሉት ሰዎች ከመደሰት ይልቅ በትሕትና ጥጥ ጆሮውን መድፈን ፣ ሽንገላንም ማሸነፍ ይበጀዋል። ከተቻለው እንደ አቡነ ጎርጎርዮስ ካልዕ «እንደ ሰይጣን በውዳሴ ከንቱ አትምጣብኝ!» ብሎ መገሠጽም ይችላል።

ከዚህም ባሻገር «አመስጋኝ አማሳኝ» (አመስጋኝ አጥፊ) እንዲሉ የሚያመሰግን ሰው መንፈሳዊ ዋጋን የሚያሳጣ ፣ የትዕቢት ምንጭ ፣ የትሕትና ጠር ሊሆንም ይችላል። ስለዚህ ተመሰገንኩ ብሎ ከመደሰት ይልቅ ኃጢአተኛነትን በማሰብ ራስን መኮርኮምና የዲያቢሎስ ፈተና እንደሆነ ማሰብ የተመረጠ ነው።

የራስን ክብር መሻት የማያመሰግንን ሰው እስከመጥላትና ማራቅ ፣ ከፍ ሲልም ለራስ ክብርና ስም ሲሉ መንጋውን እስከ መተውና ለተኩላ እስከ መስጠት ሊያደርስ ይችላል ፣ ነቢየ እግዚአብሔር ዮናስ «ከሕይወት ሞት ይሻለኛል!» እስከ ማለት ያደረሰው ለስሙ ለክብሩ ትልቅ ቦታ መስጠቱ ነበር። በወቅቱ እንደዚህ ነቢይ ሀሳብ «*እረኩ ሐሰተኛ ነቢይ ተብሎ ከሚጠራ ይልቅ የነነዌ ከተማ ሕዝብ ቢጠፋ ይሻል ነበር።*»

ካህናት ለክብራቸው ብቻ የሚጨነቁ ከሆኑ እንደዚህ ነቢይ መንጋውን ይዘነጋሉ። አልፎም በኃጢአት ስማቸው የጠፋና ሕዝብ የናቃቸውን ድውያን ነፍስ እንደ ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ቀርበው ለመፈወስ «የኃጢአተኞች ወዳጅ» መሰኘትንም ለመታገስ ይቸገራሉ።

ተርእዮን መሻት ማለት ደግሞ መታየትን መፈለግ ማለት ነው ፣ ይህም ክብርን ከመሻት ጋር የተያያዘ ሲሆን መደነቅን መሻት ነው።

ወንጌል ተርእዮን መሻትን «ለሰው እንዲታዩ ሥራቸውን ያደርጋሉ» በማለት ያስቀምጠዋል። (ማቴ.፳፫፥፭)

ካህናት በቤተ መቅደስ በእግዚአብሔር ፊት በዜማ የሚያመሰግኑና የሚጸልዩ ፣ እጅግ ብዙ ምእመናን የሚከታተሉትን እንደ ቅዳሴና ማኅሌት ያለ መንፈሳዊ ሥርዓትን የሚመሩ ናቸው። ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ሥርዓት ከምድር ቤተ መቅደሱን የሞሉ ምእመናንና ምእመናት ፣ ከሰማይ ደግሞ ቁጥራቸው የማይታወቅ የብዙ ብዙ የሆኑ መላእክትና ሰማያዊው ንጉሥ እግዚአብሔር የሚመለከቱት ሥርዓት ነው።

ከሰማይም ከምድርም ተመልካች ባለው በዚህ መንፈሳዊ ሥርዓት ላይ የሚያገለግሉ ካህናት በአገልግሎታቸው ወቅት በተዘክሮ (በማስተዋል) ሆነው የሰማዩን ተመልካች አስበው ማገልገል ይጠበቅባቸዋል። ብፁዕ አቡነ ሺኖዳ «ካህኑ የሚያዳምጡትን ሰዎች ሰማስደሰት በማሰብ የሚጸልይ ከሆነ ግን በታይታ ኃጢአት ይወድቃል፤ በዚህ ጊዜ ጸሎቱን የሚያደርሰው ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለሰዎችና ለራሱ ነው» በማለት ያስቀመጡት ሃሳብ የበለጠ ከላይ ያነሳነውን ቁም ነገር ያጠናክርልናል። (መንፈሳዊ ውጊያዎች ገጽ ፯፫)

ጥንቀታቸውና መጠበባቸው ለምድራዊው ተመልካች ብቻ ከሆነ ግን ከተዘከሮና ከተመሰጠ የሚገኘውን መንፈሳዊ ጣዕም አይቀምሱም ፣ እንደ ቀደሙት ቅዱሳን ካህናት በልባዊና በጣዕመ ዝማሬ መዐርግ ሆነው ማገልገላቸው ይቀርና ለክብረ ሥጋ ወደሙ ክብር የለበሱትን ልብሰ ተክህኖ እንደጌጥ ልብስ ፣ አበው በእንባ የደረሱትን ንባብና ዜማ እንደ ድምጽ ማሳመሪያ እንጉርጉሮ መመልከት ይጀምራሉ።

እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋ በትሕትና ይዘው ለእግዚአብሔር ክብር በማዋል ፈንታ ቅዳሴውንና ማኅሌቱን ወዳጅ አድናቂ የሚያበጅበት ፣ የሚሾሙ የሚሸለሙበት አድርጎ በማሰብ መጽሐፍ ያልሰራውን ንባብና ዜማ እስከ መጨመር ያደርሳቸዋል። የመጽሐፈ ቅዳሴ ትርጓሜ ይህን ድርጊት እንዲህ ሲል ይገልጠዋል፦ « (ካህኑ) ዛሬስ ጌታው እገሌ ወይዘሮ እገሊት መጥተዋል ድምጼን ይስሙልኝ ቃሌን ይዩልኝ ብሎ በማቀማጠል በማደላደል አይቀድስ» (ሥር.ቅዳ ፭፣፲፱)

የሥርዓተ ቅዳሴንም ሆነ የስብሐተ እግዚአብሔርን አፈጻጸም በአዘቦት ቀናትና በበዓላት ቀናት የተለያየ የሚያደርገውም ይህ ተርእዮን መሻት ነው ብሎ መገመትም ይችላል ፣ ፍትሐ ነገሥት ግን «*ወአለ ይዘምሩ በውስተ ምሥዋዕ ኢይዘምሩ በትፍግዕት አላ በልባዊ* /በቤተ መቅደስ ውስጥ የሚያመሰግኑት ለተርእዮ እያመሰግኑ ልብ በማድረግ ነው እንጂ» ይላል (ፍ.ነገ ፲፱)

ከዚህ ሌላ ተርእዮን ከመሻት ጋር አያይዘን የምናነሳው ነጥብ ጌጠኛ ልብስን መውደድና ማለዋወጥ ነው። ካህን ስለ ክብረ ሥጋ ወደሙ ፣ ስለ ክብረ ወንጌል ያማረ ልብስ ቢለብስ የሚነቀፍ አይደለም። መቆሸሸንና አልባሌ ልብስን መልበስን እንደ ቅድስና ምልክት ፣ ያማረ የነጻ ልብስ መልበስን ደግሞ የደካማነት ምልክት አድርጎ ማሰብም አይገባም።

ለምሳሌ ቅዱስ ኤፍሬም በሕልሙ በብርሃን ዓምድ ተመስሎ የተመለከተውን ቅዱስ ባስልዮስን ለማየት በሄደ ጊዜ ባማረ ልብስ ተሸልሞ አይቶት ነበር። ቅዱስ ኤፍሬም ይህን ሲያይ ይህን አባት ለይጣን ተርእዮን በመሻት ጸር የተተናኮለው መስሎት ጥበብን አላገኝበትም ብሎ አሰቦ ነበር። «*እስመ በውስተ ምይንት ነፍስ*

ኢተንድር ጥበብ፤ ወበውስተ ሥጋ ዘቅኑይ ለንጢለት ኢተሐድር መንፈስ /ዲያቢሎስ በተተናኰላት ሰውነት ጥበብ አታድርምና። ለንጢስት በተገዛ ሰውነትም አታድርምና።» ተብሎ ተጽፎአልና (ጥበ ፩፣፬)

ይሁንና ቅዱስ ባስልዮስ ይህን ያደረገው ስለ ክብረ ወንጌል ነው። በመንፈሳዊ ሕይወቱ ግን ቅዱስ ኤፍሬም እንደተመለከተው ከክዊነ እሳት መዐርግ የደረሰ፤ ተሐዋስያን በላዩ ሲያርፉ አርረው የሚወድቁለት ፤ በሚያስተምርበትም ወቅት ከአፉ የሚወጣው ቃል ከሰማዕያኑ ጋር በእሳት አምሳል የሚዋሐድለት ቅዱስ አባት ነበር። ይህ እንግዲህ ስለ ክብረ አምላክ የሚደረግ ያማረ ልብስ መልበስ እንዳለ የሚያስረዳ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሚያገኙትን ገንዘብ ሁሉ ለጌጠኛ ልብስ በማዋል ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠብቁ (የለባሹን ማንነትና ማዕረግ ከግምት ውስጥ ያላስገቡ) የቅንጦት ጌጠኛ አልባሳትን መለዋወጥ ፤ አልፎ ተርፎም የክህነትን የማዕረግ ልብስ አውልቆ ጥሎ ተርታ ልብስን መልበስ እና ክርስቲያናዊ ያልሆነ የአለባበስ ወረትን (ፋሽንን) መፍጠር ተርእዮን መሻት እንጂ ምንም ሊባል አይችልም።

ከሁሉ የሚከፋው ደግሞ ዓለምን እንደ መርገም ጨርቅ ጠልተው ፤ እንደ ሞተ ውሻ ተጠይፈው መንነው ቆብ የደፉ መነኮሳት ጌጠኛ ልብስ የሚሹ ሲሆን ነው። ክህነትን ከምንኩስና አስተባብሮ የያዘው ወንጌላዊ ዮሐንስ ግን ያስተማረን ይህን አይደለም፦

እርሱ የወዳደቁ ጨርቆችን አያይዞ ሰፍቶ ከመንገድ ይጥል ነበር። ኃላፊ አማዳሚ ያነሳው እንደሆን «ለካ ወንድሜ የሚለብሰውን እኔ ይገፍዋለሁ» በማለት ለትምክህት ፣ ለተዝህሮ ፣ ለተርእዮ የሚሆን

መልካም ልብስን ከመልበስ ይከለክል ነበር። ሰው ተጸይፎት ከተወው ግን «ዛቲ ይእቲ መልበስየ / ይህች ልብሴ ናት» ብሎ ይለብስ ነበርና።

መነኮሳትም ሆኑ ካህናት ጌጠኛ ልብስን ከወደዱ ቤተ መቅደስንና ቅጽረ ቤተ ክርስቲያንን «የአለባበስ ማሳያ ስፍራ» ያስመስሏታል። መምህራነ ቤተ ክርስቲያንና ካህናት ከሚገባው በላይ ለመልበስና ለማጌጥ ታጥቀው የቆሙ ከሆኑ እንደ መምህራቸው ክርስቶስ «ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታቱ ቤት አሉ።» ብሎ ምእመናንን መገሠጽስ እንዴት ይችላሉ? (ማቴ ፲፩÷፰)

ምዕራፍ አራት

ለካህን የሚገባ

፩ ዘወትር ስመማር ዝግጁ መሆን

ካህናት ቅሩባነ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ቅርቦች) እንደ መሆናቸው ከማንም በላይ ነገረ ሃይማኖትን ሊረዱና ሊመረምሩ ይገባቸዋል። ካህናት መንፈሳዊ ትምህርት መማር አለባቸው ስንል ለግብረ ክህነት ከሚያበቃው ትምህርት አንሥቶ እስከ መጻሕፍት ትርጓሜ ድረስ ነው።

ካህኑ የሚያገለግልበትን ቋንቋ ፣ የሚፈጽመውን ሥርዓት ፣ የሚያነብባቸውን የሥርዓት መፈጸሚያ መጻሕፍትና የሚፈጽማቸውን ምሥጢራት ምንነት ጠንቅቆ መረዳት ይኖርበታል። የጎሸም ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ማርቆስ «ግእዝ የማያውቅ ካህንና አብድ አንድ ናቸው ፣ ሁለቱም የሚናገሩትን አያውቁትም!» በማለት ይናገሩ ነበር። በአርግጥም ካህን የሚያነብበውን ወንጌል ፣ ተአምር ፣ ድርሳን የሚደግመውን ጸሎት ፣ የሚፈጽመውን ሥርዓት ምንነትና ትርጉም ማወቅ ይገባዋል። ይህ ከሆነ በአት ሳይዘጋ በረሃ ሳይሄድ በአገልግሎቱ ብቻ ከቅድስና ማዕረግ ይደርሳል።

ሃይማኖትን ያቀኑ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት «ወኅዲ ኩን በሊሐ ንባብ /ምሥጢሩን በማስተዋል የምታነብ ሁን» (ሃይ.አበ.ዘሰ ፭፪) በማለት እንደተናገሩ ካህን ያለ አእምሮ (ያለ እውቀት) አንባቢና ተናጋሪ ሳይሆን የሚለውን የሚያስተምረውን የሚያውቅ ሊሆን ይገባል። (፪ኛቆሮ ፲፩÷፲፮)

«አስመ ውእቱ ለእሙ ኮነ የአምር ዘይብሎ አሉኒ ይሰምዕዎ የአምሩ ዘይብሎሙ / እርሱ የሚያስተምረውን ካወቀ የሚሰሙትም የሚላቸውን ያውቃሉና» ተብሎ እንደተጻፈ (ፍ.ነገ ፩፤፲፪) የሚናገረውን የማያውቅ ካህን ግን ቅዱስ ጳውሎስ «ወእንዘ ይፈቅዱ መምህራን ይኩኑ ኢየአምሩ ዘለሊሆሙ ይነብቡ / መምህራን ሊሆኑ ሲወዱ የሚናገሩትን አያውቁትም» ካላቸው ጋር ይቆጠራል (፩ጢሞ ፩፥፯ ትር)

ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ በጻፉልን «ጎበረ ብዙኀ» በተሰኘ መጽሐፋቸው እንደገለጹት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህን ሆኖ ምንም አያውቅም ማለት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም እስከ ሥልጣነ ክህነት መዐርግ ለመድረስ ቢያንስ ውዳሴ ማርያምንና መልክአ መልኮችን ሳይደግም ቅዳሴን ሳያውቅ አይሆንም። እነዚህ የጸሎትና የሥርዓት መጻሕፍት ደግሞ በውስጣቸው ታላላቅ ሃይማኖታዊ ምሥጢራትን የያዙ ናቸው ለዚህም ነው እንደ ብፁዕነታቸው አገላለጽ፡- «ካህን ሆኖ አላውቅም አልተማርኩም የሚል ብዙ ገንዘብን ይዞ የሚችገርን ሰው ይመስላል።» ችግሩ ምንም አለማወቅ ሳይሆን የሚውቁትን አለማወቅ ነው ማለት ይቻላል።

ካህን ምእመናንም መናፍቃንም ለሚያነሡአቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የግድ ትምህርተ ሃይማኖትን ማወቅ ይገባዋል። ቅዱስ ጳውሎስ ለቲቶ ስለ ካህን ሲነግረው *«ዘምሁር ቃለ ሃይማኖት ዘይክል ገስጾ በትምህርት ሕይወት ወይዘልፎሙ ለእለ ይትዋሥኡ /*የሃይማኖትን ነገር የተማረ የሚከራከሩትንም የሚረታ ይሁን» ብሎአል። (ቲቶ ፩፥፱) ስለዚህ ካህናት ለሚጠይቋቸው ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጁ ሊሆን ይገባል። (፩ኛጴጥ፫፥፲፭) መናፍቅን መርታትም ሲባል እንደ ዲያቢሎስ በጽርፈት (በስድብ) ፤ የመናፍቃንን ንግግር በማጣመም ፤ የተራቀቀ

የሃይማኖት ትምህርት ያላት ቤተክርስቲያንን ምላሽ እንደሌላት በሚያስመስል ተራ መከራከሪያ ነጥብና አስረጂ (ሎጂክ) በመዝለፍ አይደለም።

በመጽሐፍ «ካህኑ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነውና ከከንፈሮቹ እውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል» (ሚል ፪፥፯) ተብሎ ተጽፎአል። ካህን ለሌላው የሚተርፍበት የትምህርተ ሃይማኖት ግንዛቤ ከሌለው ግን ምእመናን ለኑፋቄ ይዳርጋል። የዕውር መሪም ያሰኝዋል። በዚህም ምእመናን በሃይማኖታቸው ላይ ያላቸው እርግጠኝነት እየላላ ይመጣል። ደግሞስ ከምእመናን (ከበጎቹ) የተሻለ እውቀት ከሌለው ምኑን አረኛ ሆነው?

መንፈሳዊ እውቀትን ያልያዘ ካህን ውኃ የሌለውን ወንዝ ይመስላል። ቅዱስ ዳዊት *«ፈለገ እግዚአብሔር ምሉዕ ማያተ»* /የእግዚአብሔር ወንዞች ውኃን የተሞሉ ናቸው በማለት መምህራነ ቤተ ክርስቲያንን ምድርን (ምእመናን) ለፍሬ የሚያበቃ ውኃን (ቃለ እግዚአብሔርን) በያዙ ወንዞች ይመስላቸዋል። (መዝ. ፷፬፥፱) ታዲያ ቃሉን ያልተሞሉ ካህናት ውኃ የሌለባቸው ወንዞች የተሰኙት ለዚህ ነው በባሕረ ሀሳብ መቅድም መርሐ ዕውርን ጠቅሶ ይህን ሀሳብ የሚያጠናክር ምሳሌን እንደሚከተለው ያስቀምጦልናል።

*«ካህን ዘኢየአምር ሀሳበ ባሕር ይመስል ከመ ፈለግ ዘአልቦ ማይ ውስቴቱ /*ባሕረ ሀሳብን ያልተማረ (የማያውቅ) ካህን በደረቅ ወንዝ ይመስላል።» ነጋድያን ከሩቅ ሆነው ቅጠሉን ስምልሞ ሲያዩ *ጥሬ ቆርጥመን ጠል ነሰተን እንነሣ* ብለው ይሄዳሉ። ሲያጡበት ተሰቅቀው ይመለሳሉ ይላል።

ባሕረ ሀሳብን ያልተማረ ካህን የአጽዋማትና በዓላትን መውጪያ እና መግቢያ ብቻ የሚጠይቁትን እንዲህ ካሉቀቀ ፤ መሠረታዊ የትምህርተ ሃይማኖት ጥያቄን ለሚያነሱ ምእመናን ምላሽ መስጠት በማይቻለው ካህን እንደምን ምእመናን ይሳቀቁ ይሆን? ተሳቅቀው ብቻ ቢያበቁ መልካም ነበር። ከዚያም አልፈው ለሁሉ ምላሽ ያላትን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ወደ መናቅና ወደ መጠራጠር ሊያመሩ ይችላሉ እንጂ።

ካህን ይታዘቡኛል ብሎ የማያውቀውን እንደሚያውቅ አድርጎ ቢናገር ደግሞ የበለጠ ይከፋል። የማናውቀው ነገር መኖሩ ፍጡራን የመሆናችን ማስረጃ ነውና አላውቅም ማለትም አንድ በጎ ነገር ነው። ጊዜው ደርሶ አስጨንቆ የሚይዘው ሲገጥመው ደግሞ ለባሰ ጎስቋላት ይጋለጣልና የማያውቀውን አላውቅም ማለትንም ካህን ገንዘብ ሊያደርግ ይገባል። *«ሊትንብቦ ለመኑሂ በዘኢለበውከ ወኢያእመርከ ከመ ኢትኅፈር በርእስከ / የማታውቀውንና ያላስተዋልከውን ነገር በራስህ እንዳታፍር ለማንም አትናገረው»* (ተግሣጽ ዘቅ. ዮሐ. አፈ.)

አንድም መንፈሳዊ እውቀት የሌለው ካህን ነፋስ የሚበትነው ደመናን ይመስላል። በመጽሐፍ ቅዱስ መምህራን በደመና ተመስለው ይነገራሉ። ደመና አቅፎ የያዘውን ውኃ በምድር ላይ እንደሚያፈስ መምህራንም የያዙትን የቃለ እግዚአብሔር ውኃ በምድር ምእመናን ላይ ያፈስላሉ እና በደመና ይመሰላሉ። ለምሳሌ አንድ ኃይለ ቃል ብናነሣ በመጽሐፍ «ዝናብንም እንዳያዘንቡበት ደመናዎችን አዝዛለሁ» ብሎ እግዚአብሔር የተናገረው መምህራን እንዳያስተምሩ አዝዛለሁ ሲል ነው። (ኢሳ ፭፥፮) «ደመናት ዝናም በሞሉ ጊዜ በምድር ላይ ያፈስሱታል» እንደሚል ካህኑ በቃለ እግዚአብሔር ውኃ ሲሞላ ለሌላው ማፍሰስ አይችልም። /መክ. ፲፩፥፫/

ወደ ቀደመ ነገራችን ስንመለስ ደመና በዘረ ጊዜ ገበሬ እርሻውን በቅብቅብ ፤ ዘሩን በዕንቅብ አድርጎና ይዞ በተስፋ ይጠብቃል። ነፋስ መጥቶ በበተነው ጊዜ ግን ተስፋ ይቆርጣል። እንዲሁም ካህኑን ምዕመናን አምላክ ጠምጥሞ ፤ መነሳነሱን ይዞ፤ ልብሱን አንጽቶ ባዩት ጊዜ ያልተማሩት *እንማራለን፤* የተማሩት *ምሥጢር እንረዳለን* ብለው ወደ እርሱ ይሄዳሉ። ደርሰው ምሥጢር ትምህርት ሲያጡበት ግን ተስፋ ይቆርጣሉ።

ያልተማረ ካህን በደረቅ ጉድጓድ ይመሰላል። ደረቅ ጉድጓድ ቀርበው ሲያዩት ባዶ ሆኖ እንደሚያገኙት ትምህርተ ሃይማኖትንም የማያውቀው ካህን ተርታ ደቀ መዝሙር (ተራ ተማሪ) ጠይቆ ምላሽ የሚያሳጣው ነው። እንዲሁም በጥቂት ኃይለ ቃልና ጥቅስ መናፍቁም ፤ አላዋቂውም ፤ ምንም የማያውቀውም የሚረታው የሚያሳፍረው ነውና ነፋስ በሚበትነው ደመና ተመስሏል። (፪ኛ ጴጥ ፪፥፲፯)

አለማወቅ ኃጢአት አይደለም። ለማወቅ አለመጣር ግን የከፋ ስንተት ነው። «ተክብሮ ያደርጋል ደንቆሮ» እንዲሉ «ካህን ሆኜ ሳለ እንዴት እማራለሁን?» ብሎ ከትምህርት መራቅ የለበትም። *«ርእሳ ለክህደት ጸገበ ትምህርተ ውስቱ / የክህደት ራሷ ትምህርት መጥገብ* ነው (በቃኝ ማለት ነው)» እንዲሉ ካህን ከመማር ወደኋላ ባለ ቁጥር ከእምነትም የዘያኑ ያህል እየራቀ ይመጣል። ይልቅስ ቃለ እግዚአብሔርን እንደ ማንኛውም አማኒ መስማት ፤ በመዐርግና እውቀት ከሚያንሱትም ቢሆን በትሕትና መማርና መገሰጽ ለካህን ክብር እንጂ ተዋርዶ አይደለም።

ካህናት የማይገባ ተግሣጽ ከማይገባው ሰውም እንኳ ቢሰነዘርባቸው በትሕትና መቀበል እንጂ *«ተሰደብኩ ክብሬ ተነሳ»* ብለው

መመለስ አይገባቸውም። ይልቁንም ሳይንቁ ሳያቃልሉ «አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወለድህ ፤ አንተም እኛን ታስተምረናለህ?»/ «ከኩተት እስከ ሽበት የኖርንበትን ሕግ እንዴት አልጠበቃችሁም እንባላለን» እንዳሉ አይሁድ ፤ ለክብራቸው ሳይጨነቁ መስማት ይጠቅማቸዋል (ሐዋ ፯፥፶፫ / ዮሐ.፱፥፴፬)

ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት የሳኦል ቤተ ዘመድ የሆነ የጌራ ልጅ ሳሚ የርግማንና የስድብን ቃል ሲናገረው «እግዚአብሔር ዳዊትን ስደበው ብሎ አዝዞታልና ይርገመኝ» ብሎ በአኩቴት ስድብን ተቀብሎ ነበር (፪ኛ ሳሙ ፲፮፥፯-፲) ካህናት እንኳ የሚገባው ሰው ፤ በማይገባው ሰውና ባልተገባ ሁኔታ ወቀሳ ሲሰነዘርባቸው በትዕግስት ለገስጸ ርእስ (ራስን ለመገሠጽ) ሊጠቀሙበት ይገባል። የተናጋሪውን ማንነትም ሳያዩ እግዚአብሔር እንደተናገራቸው አድርገው መቀበል ይገባቸዋል።

በአንድ ወቅት በሥርዓተ ቅዳሴ ላይ የነበሩ አበው ካህናት ሥጋ ወደሙን ሲያቀብሉ አንድ ሕጻን ሮጦ ወደ እነርሱ ቀረበ። ካህኑም «ጸጋ እግዚአብሔር ጠርታዋለች» ብሎ ሥጋውን አቀበለው ፤ ደሙንም በጽዋው አጠጣው። ሕጻኑም *«አንሰ አፈርሀ ሠለስተ ግብራተ ወይእቲ ጸአተ ነፍስ አም ሥጋ ወተራክበ ምስለ እግዚአብሔር ወጸአተ ፍትሕ ላዕሌየ / ሦስት ነገሮችን አፈራለሁ፤ ይህም የነፍስ ከሥጋ ተለይቶ መውጣት ፤ ከእግዚአብሔርም ጋር መገናኘት፤ በላዬ ላይ የሚመጣውንም ፍርድ ነው»* በማለት አለቀሰ፤ ካህናቱ ግን ይህን በሰሙ ጊዜ «እግዚአብሔር እንጂ በዚህ ሕጻን አድሮ ዘለፈን!» ብለው አልቅሰዋል። ይህ ሕጻን ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ነበር። ካህን እንኳ ከመንፈሳዊ ትምህርት ገበታ ከሕጻንም፣ ከባልቴትም ፤ ከሚሳደቡ አሕዛብም ቢሆን በትሕትና እየተማረና ራሱን እየመረመረ ሕይወቱን የሚያስተካክል የተዘከሮ ሰው ሊሆን ይገባዋል።

፪ አርአያ መሆንና አስማስናከል

«አስመ በከመ ይከውን ካህን ከማሁ ካዕበ ሕዝበኒ / ካህኑ እንደሚሆነው ሕዝቡም እንዲሁ ይሆናልና» እንዲል ሆሴዕ ነቢይ መምህሩ ደግ የሆነ ከሆነ ሕዝቡም እንዲሁ ይሆናል። ካህናት በበጎ ምግባር ከጸኑ ለምእመናን አብነት ይሆናሉ። በተቃራኒው ደግሞ ካህኑ በምግባሩ ቢደክም ሕዝቡም እንዲሁ ይደክማል።

ጌታችን በቃሉ «ዓይንህ ታማሚ ብትሆን ሰውነትህ የጨለመ ይሆናል በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ?» ሲል ተናገረ (ማቴ ፮፥፳፫) የዓለም ብርሃናት የሆኑ ካህናት ሥራቸው ያልቀና ከሆነ የሥራ መክፍወኛ አነርሱ ናቸውና የምእመናኑም ሥራ ያልቀና ይሆናል። «በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ ጨለማው እንዴት ይበረታ?» ሲል ደግሞ «የተሸመ ካህን የቀና ካልሆነ እንደምን ፍዳ ይጸናብህ? እንደምን መክበሪያ መጽደቂያ ይሆንሃል?» ለማለት ነው። ስለዚህ ካህናት በፈሪሐ እግዚአብሔርና በመንፈሳዊ ትጋት ለምእመናን አብነት ሊሆኑ ይገባል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ *«አርአያ ኩኑ ለመርዔቱ ክመ አመ አስተርአየ እግዚኦ ናዖት ትንሥኡ አክሊለ ስብሐት ዘኢያጸመሂ / ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ . . . የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ»* (፩ኛ ጴጥ ፭፥፫) በማለት እንደተናገረ ካህናት ከእረኞች አለቃ ክክርስቶስ ዋጋን ይቀበሉ ዘንድ ለመንጋው ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው የጸመ ፤ የጸለየ ፤ የተጠመቀ ምን ይረባኝ ምን ይጠቅመኝ ብሎ ነው? አርአያ ለመሆን እንጂ። ካህንም ምናልባት የማይጠቅመውንም ቢሆን

መንፈሳዊ ነገር እስከ ሆነና አርአያ የሚሆንበት ነገር ካለ ሊፈጽመው ይገባል።

ሌላው ነጥብ ደግሞ ለሌሎች ማሰናከያን ላለመስጠት መጠንቀቅ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ «አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ አንዳች ማሰናከያን አንሰጥም» እንዳለ (፪ኛ ቆሮ ፮፥፫)

ካህን ሆኖ ምእመናንን ሰንጢአት የሚገፋፋ ምግባርን ማሳየት መንጋን ካለመጠበቅ አልፎ በጎችን እንደ መግደል የሚቆጠር ነው። ወደ መልካም መንገድ መምራት አለመቻል አንድ ጥፋት ሆኖ ሳለ ወደ ክፉ መንገድ መምራት የበለጠ ጥፋት ነው። ካህኑ አደራ የተሰጠው ልጆቹን እየመራ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገባ እንጂ ወደ ሲኦል እንዲነዳ አልተሾመም።

በታሪክ ከራሳቸው አልፈው ለብዙዎች ጥፋት ምክንያት የሆኑ ብሎም ለቤተ ክርስቲያን ጠላት ሆነው ጠላት ያፈሩ ካህናት ተከስተዋል።እነ አርዮስ ፣ ንስጥሮስ ፣ መቅዶንዮስን የመሳሰሉት አርእስተ መናፍቃን ቤተ ክርስቲያን በክብር ያስቀመጠቻቸው እስከ ጵጵስና መዓርግ ጭምር የደረሱ ካህናት ነበሩ። ይሁንና መንጋውን ካለመጠበቅም አልፈው ለብዙዎች ክህደትና በተኩላ እጅ መውደቅ ምክንያት ሆነዋል።

ዛሬም ድረስ የእነርሱ ክፉ እርሾ ለቤተ ክርስቲያን እሾህ ሆኖ ምእመናንን የሚያቆስል ብሎም ለክህደት የሚዳርግ ሆኖ ቀርቶአል። ቅዱስ ጳውሎስ «ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ፣ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንደሚነሱ እኔ አውቃለሁ» ያለው እንዲህ ስላሉት ነው። (ሐዋ ፳፥፳፱)

ከእነ አርዮስ በኋላም ቢሆን እስካለንበት ድረስ ከትፋቱ እስከ ባዕድ አምልኮ ድረስ ጠልቀው እየገቡ ይሁዳ ከአይሁድ ጋር እንደተስማማ ከጠንቋዮች ከሥር ማሾች ቅጠል በጣሾች ጋር እየተባበሩና እየተወዳጁ «ላዩ ሰንሰለት ውስጡ ዓውደ ነገሥት» እንደሚባለው ባሕታዊ ስመ አጋንንትን እየጠሩ ፣ መተት እየመተቱ ቤተ ክርስቲያንን አለስሚ ስም ፣ አለግብሯ ግብር ያሰጧትና ምእመናንን ለክህደትና ለባዕድ አምልኮ የዳረጉ ካህናት ተነሥተዋል።

እንዲህ ያሉት በክህነት ስም እየነገዱ ለሥጋዊ ብዕል (ሀብት) የሚሮጡ ካህናት ምእመናን ታቦትን ከጣያት ፣ ክርስቶስን ከቤልሆር ፣ ጸሎትን ከመተት ለመለየት እንዲቸገሩ ፣ ፍጽምት ቤተ ክርስቲያንን እንደ ርኩስ ነገር እንዲቆጥሩ ምክንያት ሆነዋቸዋል። በላይኛው ስፍራ የሚጠብቃቸው ፍዳ ጽኑዕ ነው። ሕዝብ ስቤ ፡ ገንዘብ ሰብስቤ ፣ ሰው አሳብሬ ጥንቆላ አስክብሬ ፣ የልቤን ሠርቼ ኋላ ንስሓ ገብቼ ድኜ እሞታለሁ የሚል ዕቅድ ያላቸውንም «ታሠግራ ነፍስ ሕዝብየ ወታሐይዋኑ ነፍስክን /የሕዝቤን ነፍስ አጥምዳችሁ ነፍሳችሁን ልታድኑ? አታድኑም» ይላቸዋል። (ሕዝ. ፲፫፥፲፰)

በታሪክ እንዲህ ያሉ በክህነታቸው ክፉ ግብርን የሚያስተምሩ ፣ በጠንቋዮች ደጅ የማይጠፉ ፣ ሲሞትም ጸሎተ ፍትሐት የሚያደርሱ ፣ «ጌታዬ ጌታዬ» አያሉ የሚያለቅሱ ለብዙኃን እንቅፋት የሆኑ ካህናት እንደተነሡ ሁሉ ፣ እንደ ቅዱስ ባስልዮስ ያሉ ጠንቋዮችንና መተተኞች አሳፍረው ቤተ ክርስቲያንን ያከሩ አበው ካህናት ተነሥተዋል። ለቤቱ የሚያውቅ አምላክ ይክበር ይመስገንና እየተነሡም ነው!! ይህ ካህን በደዌው ሳለ ጸልዮ የሦስት ቀናት ዕድሜ ተጨምሮለት ምክረ አጋንንትን አፍርሶ ጠንቋዩን አሳምኖ አጥምቋል። ቤተ ክርስቲያን የምትሻው እንዲህ ያለውን ካህን ነው።

ካህናት አምልኮተ እግዚአብሔርን ሲፈጽሙና አገልግሎታቸውን ሲያካሂዱ በፍርሃትና በጥንቃቄ መሆን እንዳለበት ቀደም ባሉት ንዑሳን አርእስት ተገልጧል። የካህናት ሁኔታ የምእመናንን እምነትና ፈሪሐ እግዚአብሔር ይወስነዋል። ካህኑ በድፍረት የሚያገለግል ሲሆን ምዕመናን «*አርሱ መምህር አረኛ ሆኖ እንዲህ ካደረገ . . .* » የሚል አሳስፈላጊ ንጽጽር ውስጥ ይገባሉ። «ብእናንተ ለበብ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ይሰደባል» (ሮሜ ፪፥፳፬) የተባለውም ምእመናን ካህናትን ወጥተው ሲያሙ ይፈጸማል። ትምህርተ ሃይማኖትን ሳያመረምሩ «*ካህን ይህን አደረገ*» ብለው ብቻ ወደ ክህደት የሚያመሩ አሉ። ይህ ሞኝነት ቢሆንም ካህናት ግን መሰናክልን ላለመስጠት መጠንቀቅ አለባቸው።

የካህን ፈሪሐ እግዚአብሔር መጥደል ምእመናንን ወደ ኦፋቄ ሊመራ እንደሚችል አንድ የመጽሐፍ ቃልን በማስረጃነት ልንጠቅስ እንችላለን። «*ወዘይስሕቅ በረዚ ቅዳሴ ለእመ ኮነ ካህን ኩነኔሁ ፭ ሱባኤ ወለእመሰኮነ ሕዝባዊ ይጸዕ በውእቱ ጊዜ ወኢይትመጠ እምቁርባን*/በቅዳሴ ጊዜ የሚስቅ ሕዝባዊ (ጨዋ) ከሆነ ሳይቀበል ይውጣ ካህን ከሆነ ግን አንድ ሱባኤ ይለይ» ይላል።» በዚህ ትእዛዝ ላይ ሕዝባዊውን ወዲያው ይውጣ ብሎ ካህኑን ያቆየበት ምክንያት አለ ፤ ካህን ከመቅደስ ከውስጥ ይቆማል። ከምእመናን ወገን ምን ድርጊት እንደፈጸመ የሚያየው የለም ወጥቶ ቢሄድ «አባ እገሌ ከመሥዋዕቱ ምን አይተውበታል?» ብለው መሥዋዕቱን ሳይቀር ይጠራጠሩታልና ነው። እዚህ ላይ የምንይዘው ቁም ነገር ካህን ፈሪሐ እግዚአብሔር ሲጎድለው ለሥጋን ወደ ክህደት ሊመራ እንደሚችል ነው።

የእግዚአብሔር መልእክተኞች በበጎ ነገርም ቢሆን ለሌሎች ምክንያት ላለመስጠት ይጠነቀቃሉ። ነቢየ እግዚአብሔር ሳሙኤል

ሳያልን ለንግሥና ከቀባው በኋላ ፲ጀቱን ነገደ ጋኤል ይዞ ወጥቶ ነበር። ከዚያም «በትራችሁን ስጡኝ ዕጣ ላውጣላችሁ» ብሎ ዕጣው ሲወጣ መጨረሻ ለሳያል ወጣለት። ይህ ነቢይ ለንግሥና ሳያልን ከቀባው በኋላ እንዲህ ማድረጉ አንደኛ *መቼም እግዚአብሔር የሰጠውን አይነሳውም* ብሎ ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ግን ማማለጃ በልቶ ቃል ለቃል ተጨዋውቶ ዝምድና ኖሮት አድልቶ ነው ብለው እንዳያሙት ነበር። (፩ኛ ሳሙ ፲፥፲፱)

የሐዲስ ኪዳን ካህናት ቅዱሳን ሐዋርያትም እንዲሁ ለምዕመናን መሰናክል እንዳይሆኑ የሚጠነቀቁና አብነት የሚሆኑ ነበሩ። ለምሳሌ በይሁዳ ፈንታ ሐዋርያ ለመተካት ምርጫ ባደረጉ ጊዜ ቅዱስ ማትያስ እና ቅዱስ ዮሴፍ ተመርጠው ነበር። ከሁለቱ የቱ ለሐዋርያነት እንደሚበቃ የሚያውቁበት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሐዋርያት ነበራቸው። ይሁንና ምርጫውን የፈጸሙት በዕጣ ነበር። ይህን ያደረጉት ምንም ቢበቁ በራሳቸው ቢመርጡ ናሮ ምዕመናን «ተዘምዶተ ሥጋ ኖሯቸው አድልተው ነው፤ ማማለጃ በልተው ነው» ባሏቸውና በሐሜት በተጎዱ ነበር። ስለዚህ ይህን በማሰብ በዕጣ አደረጉ። (ሐዋ. ፩፥፳፭ ትር) እናም ካህን በጎ ሥራንም ጭምር የምእመናንን ድካም ከግምት ውስጥ እያስገባ ሊሠራ ይገባዋል።

ሐዋርያት መሰናክል ላለመሆን ከመጠንቀቅ ባሻገር ለሌሎች አብነት የሚሆኑበትን ነገርም ይፈጽሙ ነበር። በሐዋ ፫፥፮ ቅዱስ ዮሐንስና ቅዱስ ጴጥሮስ በምኩራብ ለመጸለይ የሄዱት «*ጸሊ በንዑሪ / ስትጸልይ በስውር ይሁን*» የሚለውን የጌታ ቃል ዘንግተውት አልነበረም። ለሰው አብነት የማይሆኑበትን ተሰውሮ መሥራት ለሰው አብነት የሚሆኑበትን ግን ገልጦ መሥራት እንደሚገባ ያውቃሉና አብነት ለመሆን ነው። ለምሳሌ መጠጥ መጠጣት አብነት የሚሆኑበት

አይደለምና ካህን መጥኖ ሊጠጣ ይገባዋበሰው ፊት ሊጠጣ ባይታይ መልካም ነው። እንደ ጻድቁ ኖኅ ለስካር ቢደርስ ግን ክብሩን ያዋርዳል። የሚመለከቱትም እርሱን በማማት እንዲቀጡ ያደርጋቸዋል። (ዘፍ ፱÷፳) *«ክብሩ ለብእሲ ተክልዖ እምጽዕለት / የሰው መክበሩ ከስድብ መከልከል ነው»* እንዳለ (ምሳ ፳÷፫) ካህን ከክፉ ንግግርና ከክፉ ሥራ መለየቱ ክብሩን ከፍ ያደርገዋል።

ካህናት በጎ ነገርም ቢሆን ምእመናንን የሚያሰናክል ከሆነ ሊተውት ይገባል። *«የልቤን አግዚአብሔር ያውቃል»* እያሉ በአፍአዊ ግብር ለሌላው መሰናክል መሆን አይገባም። ደግሞም የአፍአው የውስጥ ድምር ውጤት ነው። የሦስት ባልንጀሮች ቀሳውስት ታሪክ ለዚህ ማስረጃ ነው። እነዚህ ቀሳውስት ሐመረ ንጽሕናቸው ያልተሰበረ ፣ በአጋንንት ድል ያልተነሱ ፣ በሥጋዊ ማዕበል ሞገድ ያልተናወጹ መነኰሳት ነበሩ። ነገር ግን ያዩአቸው በልብሳቸው ጌጥ ብቻ አየገመቷቸው የሥጋቸውን ንጽሕና ሳያውቁ ይዘብቱባቸው ነበር። ይሁንና እሊህ አበው ምንም ንጹሐን ቢሆኑ ማጌጣቸው ለሌላው ሕሊና እንቅፋት መሆኑን አውቀው እርግፍ አድርገው ተውት (ተአ.ማርያም ፩፻፱፮) ስለዚህ ለካህን የሚገባው «መጽሐፉ መች ከለከለ?» ብሎ መከራከር ብቻ ሳይሆን ለምዕመናኑ ሕሊና መጠንቀቅ ነው።

ማንኛውም ሕዝባዊ /ምእመን/ ለራሱ እንዳይወድቅ ሊጨነቅ ግድ አለበት። ካህን ግን ቢወድቅ ይዞአቸው ሊወድቅ የሚችል ብዙ ነፍሳት በዘባነ ሥልጣኑ (በሥልጣን ትከሻው) ላይ አሉና ጉዞው ሁሉ በጥንቃቄ ያለ ሐሜት ሊሆን ይገባል። *«ሀሉ አንተ ዘእንበለ ሐሜት ከመ ሊይትዐቀፍ በእንቲያከ ፅዱሂ / አንዱስ እንኳ በአንተ እንዳይሰናከል ያለ ሐሜት ኑር»* እንደተባለ (ፍ.ነገ ፳) የካህን መንፈሳዊ አቋም ምን ያህል

በምእመናን ሕይወትና አመለካከት ላይ አሉታዊና አወንታዊ ተጽዕኖ እንዳለው በብሉይ ኪዳን የነበረ አንድን ካህን በመጥቀስ እንመለከታለን።

አንትያኮስ የተባለ አረማዊ ንጉሥ በሀገረ እስራኤል ላይ ፎልፎስ የተባለ ገዢን ሾሞ ነበር። ይህ ፎልፎስም በወቅቱ ሊቀ ካህን የነበረውን አልዓዛርን አስጠርቶ *«ለስተዋይና ብልህ ስለሆንህና ቀድሞ ለአንተ ፍቅር ስላለኝ ራራልሃለሁና ልገድልህ አልሻም ስለዚህ የንጉሡን ትእዛዝ ተቀብለህ ለምስሉ ስገድና መባውንም ብላ ከሞትም ትድናለህ»* አለው። ካህኑ አልዓዛር እንዲህ ሲል መለሰለት፦

«እኔ አረጋዊ ነኝ የሕዝብም አለቃ ነኝ። በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ሕዝቤን አስት ዘንድ ጎሊናቸውንም አደክም ዘንድ አይገባኝም። መከራን ስለ እግዚአብሔር ትዕዛዝ ልታገስና በሃይማኖት ልጸና አብነትም ልሆናቸው ይገባል። ሃይማኖትን እንዲጠብቁለት የማዝዛቸው ሆኜ ሳለ መከራን ተሰቅቄ ሃይማኖቴን ብተው *«ይህ አረጋዊ አዋቂ ሆኖ ሳለ ስለዚህች ዓለም መውደድ ትእዛዘ እግዚአብሔርን ካፈረሰ እኛ ወጣቶችማ እንደምን ይገበን? ከእርሱ እንማር በእርሱም እንመራ»* ይላሉ ለስኅተታቸውና ከሃይማኖት ለመውጣታቸውም ምክንያት እሆናለሁ ስለዚህ መሞት ይሻለኛል።» በማለት መስክሮለል (መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን /ዜና አይሁድ/)

የካህን አርአያነቱ በመንፈሳዊ ሕይወት ብቻ ሳይሆን በሥጋዊና ማኅበራዊ ሕይወቱም መሆን አለበት። «የቤት ቀጋ የውጪ አልጋ» እንደሚሉት ሰው ቤተ ለሠቹን በሚገባ የማያስተዳድር ፣ ማኅበራዊ ኑሮው ከኅብረተሰቡ ጋር ተግባብቶ መኖር የማይችል ከሆነ እንኳን አርአያ ሊሆን ማስናከሉም የማይቀር ነው።

ሐዋርያውም *«ወዘሰ ኢይክል ሠሪዓ ቤቱ እፎኑ ያስተሐምም ቤተ አግዚአብሔር / የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ*

የእግዚአብሔርን ቤት እንዴት ይጠብቃታል?» (፩ኛ ጢሞ ፫፥፭) በማለት እንደተናገረ ቤተሰቡን ሠርቶ ቀጥቶ ማሳደር የማይቻለው ካህን በአራቱ ማዕዘን ያሉ ምእመናንን ሠርቶ ቀጥቶ ያሳድራል ተብሎ አይገመትም። የአንድ ካህን ቤተሰቦች ቢበዙ ሰባት ወይም ስምንት ናቸው። እነዚህን ጠብቆ ፈሪሃ እግዚአብሔርን አስተምሮ ፣ ስነ ምግባር ማስያዝ ካልቻለ ብዙኃን ምዕመናንንማ እንዴት ይችላል? «ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።» ተብሎም ተጽፎአል፡(፩ኛጢሞ. ፭፥፰)

፫ ትዕግሥተኛ መሆን

ትዕግሥት (ጽናት) ለክርስቲያናዊ ጉዞ መሠረታዊ ነገር ነው። ይልቁንም ካህን እጅግ ትዕግስተኛ መሆን ይገባዋል። ካህናት በልዕልት ሥልጣን ላይ ያሉ ብርሃናት ናቸውና ሊስወሩ አይቻላቸውም። ስለዚህ እንደማንኛውም ሰው ደርሰው የሚቆጡና ለጸብ የሚነሳሱ መሆን የለባቸውም። ካህን ማንም ክፉ ቢያደርግበት የተሰጠውን ክብርና ኃላፊነት በማሰብ ሊታገስ ይገባዋል ፣ ቂም እየተያያዘና እየተራገመ ፣ ነገር እየሠራ ቢያገለግል ግን መቅሠፍትን ያመጣል።

ለካህኑ ከሰው ተጣልቶ ፣ በነገር ረትቶ ከሚኖር ይልቅ ተሸንፎ ፈሪ አላዋቂ ተብሎ መቀመጥ መንፈሳዊ ዋጋን ያሰጠዋል። ይልቁን ከክብሩና ከተሸከመው ከባድ ኃላፊነት የተነሣ ትዕግስተኛነት ይበልጥ ይጠቅበታል። ቅዱስ ጳውሎስም ለቲቶ ስለ ካህን ሲጽፍለት «*ዘይነሐሲ* /ነገር አላፊ ልበ ሰፊ ይሁን» ብሎአል። (ቲቶ ፩፥፯) ለክብሩ ከመጨነቅና *ተንካሦ* ከማለት ይልቅ እንደ ክርስቶስ ለጠላቶቹ መልካም የሚያደርግ ሊሆን ይገባዋል።

በአንድ ወቅት ሙሴ ነቢይ እኅቱ ማርያምና አሮን «ከሚስቱ ጋር እያደረ መቅደስ ይገባል ፣ ከአሕዛብ ተጋብቷል» እያሉ አሙት። እግዚአብሔር ስለ መረጠው አገልጋዩ ስለሙሴ ቀንቶ ወንድሟን ያማችው ማርያምን በለምጽ አነደዳት። ሙሴ ግን «እንኳን እንዲህ የሆነች» ሳይል ሥርየትን ለምናላት ፈውስን አሰጥቷታል። (ዘኁ ፲፪፥፩-፲፫)

መጽሐፍ ቅዱስ የሙሴን ትዕግሥትና የዋህነት እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡- «በትሕትናውና በጸሎቱ ይህን ያህል ሕዝብ ሲጠብቅ ያልተበሳጨ አንድ ሰው ስንኳ *'ያላጠፋ የእግዚአብሔር ባርያ ሙሴን* አስበው *፣አንተን በድለዋልና ለቤቱ ወገኖችህን ይቅር በል ቸል አትበል፣* እያለ ላሙት ፣ እግዚአብሔርም ያጠፋቸው ዘንድ ለወደደ ለእኅቱና ለወንድሙ በየዋህነቱ ወደ እግዚአብሔር ለምኖ ኃጢአታቸውን አስተሰረየላቸው እንጂ ፣ ያልተበሳጨ የእግዚአብሔርን አገልጋይ ሙሴን አስበው» (፪ኛ መቃ ፲፭፥፩)

በቁሙ ሲተረጎምም «*ዘኢያፈጥን ዕዩሠ ለዘቢጥ /ፈጥኖ* የማይማታ» ተብሎአልና ካህን እጁን ፈጥኖ ለመምታት የማይሰድ ትዕግስተኛ መሆን ያስፈልገዋል። ሥጋን ከነፍስ ጋር አስታርቆ አስማምቶ ሥርየትን የሚሰጥ ገባሬ ሠላም ካህን እጁን ለፀብ ማንሳት የለበትም። ደመ መለኮትን በሚቀዳበት ክቡር እጁ የሩቅ ብእሲን ደም ሊያፈስስ እጁን ሊያነሳ አይገባውም። እንኳን የሰው የእንስሳስ ደም ማፍሰስ መች ለካህን ተፈቀደ? ደግሞም ካህን ለመንፈሳዊ ሥራ እንጂ እንዲህ ያለው ግብር ከእርሱ የሚጠበቅ አይደለም።

አምላክ ለካህን መንፈሳዊ ሥልጣንን እንጂ ሥጋዊ ጉልበትን አለመስጠቱ የካህን እጅ ለመማታት እንዳይውል ሲል ነው። በወንጌል ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ለመያዝ ጭፍሮች በመጡ ጊዜ

ሰይፍ መዝዞ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ ማልኮስን ጆሮ ሊቆርጥ ጌታችን የገሠጸው መሆኑ ተጽፎአል ፤ በትርጓሜው ላይ ደግሞ አንድ ቁም ነገር እናገኛለን። ቅዱስ ጴጥሮስ ሰይፉን የሰነዘረው የማልኮስን አንገት አንኝ ብሎ ነበር። ነገር ግን የካህን እጅ አያቀናምና ለአንገቱ የሰደደው ለጆሮው ሆነ ይላል። ከዚህ ማብራሪያ ካህን የጥል ሰው አለመሆኑን ለመረዳት እንችላለን።

ካህን ትዕግስትን ገንዘብ ማድረግ አለበት ሲባል ዱላ ከመማዘዝ ብቻ ሳይሆን ክፉ ንግግርን ከመመለስ ቂም ከመያዝም ጭምር ነው ፤ አርሱ የእግዚአብሔር እንደራሴ ነውና ከየትም አቅጣጫ የሚመጣን በደል በይቅር ባይነት እንደ አምላኩ ተሸክሞ ታግሶ መኖር ይጠበቅበታል። ካህን ቂም በቀል ቢይዝ ከሕዝባዊው ይልቅ ይጎዳልና በትዕግሥትና በአኰቴት ስድብና ጥቃትን እየተቀበለ በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም ያስፈልገዋል። ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ እንኳን ኃጹሐ ባሕርይ ሆኖ ሳለ ስለ ሕዝቡ መዳን ስድብን ታግሷል። የክርስቶስ መልእክተኛ የሆነው ካህንም *«ትዕይርቶሙ ለእለ ይትዔየሩክ ወድቀ ላዕሌየ / የሰደቡህ ስድብ በላዬ ወድቃብኛለች»* እያለ ስለተሰጠው ሥልጣን መነቀፍንና መከራን መታገስ አለበት።(መዝ.፷፰፥፱)

እዚህ ላይ ቅዱስ ሙሴ ጸሊምን እንደ አብነት መጥቀስ ይኖርብናል። በአንድ ወቅት አባ ሙሴን አበምኔቱ ቀድስ ብሎ ረድኡን ላከበት ፤ አባ ሙሴም እሺ ብሎ ሊቀድስ ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ መጽሐፉን ደግሞ ሲጨርስ *«ለምን ደረሰ?»* ብሎ አበምኔቱ ረድኡን ጠየቀው ፤ ረድኡም *«ይኽው ሊገባ ነው ደግሞ ጨርሷል»* አለ። አበምኔቱም ረድኡን ሂድና *«ለንተ ሻንቅላ ደግሞ ለንተን ማን ከሥጋ ወደሙ አቅርቦህ?! ብለህ በጥሬ መትተህ አስወጣው»* አለው። ረድኡም የተባለውን በአባ ሙሴ ላይ አደረገና ወደ አበምኔቱ ተመለሰ ፤ አበምኔቱም *«ምን አለ?»* ብሎ ቢጠይቀው *«ዝም አለ»* አለው። ይህን

ጊዜ *«ብል ግባና ቀድስ በለው»* ብሎ ላከው። ረድኡም ሂዶ *«ግባና ቀድስ ተብለሃል»* ሲለው «እሺ» ብሎ ገብቶ ቀድሷል (ፊል.ተሰ ፪፱)

ይህ አበምኔት ይህን መልእክት ለአባ ሙሴ መላኩ የእምነቱን ጽናትና ትዕግስቱን ለማየት ነው። ይሁንና ይህን ንግግር መነሻ በማድረግ በመጀመሪያ አንድ ነገር እናነሳለን። አባ ሙሴ እንደ ኢትዮጵያዊነቱ ጥቁር ነውና በመልኩ የሚተቹት ሰዎች ነበሩ። ጥቁረት እና ቅሳት ወይም አፍአዊ ተክለ ሰውነት ለመንፈሳዊ አገልግሎት መመዘኛ አይደለም። ለአገልግሎት የሚያከለክል የአካል መጉደልንም ጨምሮ ሌሎች አፍአዊ ምክንያቶች መልክአ ነፍስን (የነፍስ መልክን) ብቻ በሚመለከት አምላክ ፊት ከማገልገል አያግዱም። ፍትሐ ነገሥትም *«እስመ ነውረ ሥጋ ሊክን ነውረ ወባሕቱ ነውርሰ ነውረ ነፍስ ውእቱ / የአካል ጉድለት ነውር አይደለም ፤ ነውርስ የነፍስ ነውር (ኃጢአት) ነው»* ይላል። ስለዚህ እንዲህ ባሉ ምክንያቶች ትችት የሚያደርስበት ካህን ትዕግስተኛ መሆንን ከአባ ሙሴ ጸሊም ሊማር ይችላል።

ማንኛውንም አይነት ስድብንና ያልተገባ ነቀፋን መታገስ ለጊዜው እንደአሾህ ነው። ኋላ ግን እንደ እሾህ አክሊል ሆኖ ዋጋን የሚያሰጥ ነውና መታገስን አንተው።

ከዚህም በተጨማሪ አባ ሙሴ አንዱ «ቀድስ» አንዱ «አትቀድስም» እያሉ ሲያጉላሉትና ሲመቱት ለክብሩ ሳይሳሳ በተዋርዶ ሁለት ጊዜም እሺ ማለቱ ሌላ ቁም ነገርን ያስጨብጠናል። ይህም መንፈሳዊ አገልግሎት የራስን ክብር ጥለው ፤ ተለማምጠውም ፤ እየተሰደቡም ቢሆን ሊፈጽሙት የሚገባ እንደሆነ ነው። ስለዚህ ካህናት በአገልግሎታቸው የሚያስከፋና የሚያስቆጣ ነገር ፤ አለዚያም በሰዎች መጠላትና መነቀፍ ቢገጥማቸው በተቻላቸው አቅም ማሰናከያን

ላለመስጠት እየጣሩ በጎ ሊሠሩ ፣ የሚመጣባቸውን ክፉ ነገር በመቀበል ስለ ስሙ የተጠሉና የተናቁ ይሆኑ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ስለ ተቆጠሩ አምላክን እያመሰገኑ መኖር ይጠቅማቸዋል።(ሐዋ.5.«1)

፬ ትሩፋትን መለማመድ

ብዙ የተሰጠው ብዙ ይጠበቅበታልና ካህን በመንፈሳዊ ማዕረግ ከሁሉ ከፍ እንዳለ ያንኑ ያህል በመንፈሳዊ ትሩፋት በጾም በጸሎት በስግደት ፣ በምጽዋት በመንፈሳዊ ግብር ሁሉ የቀደመ መሆን ይጠበቅበታል። በሐዋ ፳፥፳፰ «ወይእዜኒ ዕቀቡ ርእሰክሙ ወኵሉ መራዕየ / ለመንጋውና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» በማለት ካህን ለራሱ ካልተጠነቀቀ ለመንጋው እንደማይተርፍ አስምሮበታል።

ቅዱስ ጳውሎስ በሌላም ስፍራ «ሰፋሰን እንደሚጎስም ፣ ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም ፣ ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልኩ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምኩ አስገዛዋለሁ።» (፩ኛ ቆሮ ፱፥፳፯-፳፯) በማለት ፣ ሌሎችን የሚያስተምር ካህን ራሱን ትሩፋትን ምግባርን ባያስተምር የተጣለ እንደሚሆን አስረድቷል ፣ ሐዋርያው እንዲህ ዓይነቱን ካህን «የሌላ መምህር ራስህን አታስተምርምን?» በማለት ይጠይቀዋል። (ሮሜ ፪፥፳፩)

ጌታችን በወንጌል «ምንኮ ይበቁዖ ለሰብእ ለእመ ኵሎ ዓለመ ረብሐ ወነፍሶ ኀጕለ / ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» ያለውን ቃል አንድም ለዚህ ልንጠቅሰው እንችላለን። ብዙ ምእመናንን ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ መልሶ ራሱን ግን የተወ ካህን ይጎዳልና (ማር ፰፥፴፮)

ለሌላው አያበራ እርሱ እንደሚከስል ፋና ፣ ሌላው ታጥቦ ሲጠራበት እርሱ አያደፈ እንደሚሄድ መታጠቢያ ገንዳ ፣ ሌላው ተደግፎት ሲቆም ራሱ ግን ለመቆም እንደማይችል መቋሚያ ፣ ብዙ ተዳዳዎችን ሲሰፋ የራሱን ቀዳዳ ለመስፋት እንደማይችል መርፌ ፣ ካህኑም ሌላውን እያለመለመ እርሱ የሚደርቅ ፣ ለራሱ የማያውቅ እንዳይሆን ምግባር ትሩፋትን መለማመድና መሥራት ይኖርበታል። ትሩፋትን መለማመድ ሲባልም ጾም ፣ ጸሎት ፣ ስጊድ ፣ ምጽዋት ፣ እንቅልፍን መቀነስ ፣ ምግብን መክፈል የመሳሰሉትን ነው።

ዕድሜውን ሙሉ በመንፈሳዊ ተጋድሎ እና በማስተማር ሲፋጠን የኖረው የኢትዮጵያ ብርሃን ደገኛው ካህን አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንኳን ለዘመናት ካስተማረ በኋላ የዓመታት ትጋቱን እንደ ኢምንት ቆጥሮ በአቱን አጽንቶ ለመጸለይ በወደደ ጊዜ፡-

«ወለእመ ጠፍአ ማኅቶት አልቦ ዘየሐቱ ሎቱ ዘእንበለ ዘይከድኖ ጽልመት ፣ ለዓቃቤ ሥራይኒ መኑ ይፈውሶ ለእመ ኢየእመረ ፈውሰ ለርእሱ ከማሁ ኵነት ነፍስየ በላዕሌየ /መብራት ቢጠፋ የሚያበራለት የለም ጨለማ ይወርሰዋል እንጂ ፣ ባለመድኃኒትንስ ማን ይፈውሰዋል? ራሱ የሚድንበትን ካላወቀ ፣ ነፍሴም በእኔ ላይ እንዲሁ ሆነች፣ ሌሎችን አጣፊዋኩ ለራሴ ግን አልጫ ሆንኩ። ሕመማንን ፈወስኩ ለራሴ ግን ድውይ ሆንኩ። ለዓለም አበራሁ ለራሴ ግን ጨለምኩ» ብሏል።

እርግጥ ነው ይህ ቃል ከዚህ ቅዱስ አባት መንፈሳዊ ሕይወት ጋር የሚሄድ አይደለም ፣ ለትሕትና የተነገረ ነው እንጂ። ነገር ግን አባታችን በዚህ ንግግሩ የሚያንኳኩው የሌሎችን ሕይወት መሆኑ ጥርጥር የለውም።

ካህን በቸልተኝነት እንደ ካህን ቀርቶ የምእመናንን ያህል እንኳን መትጋት አስከማይችል ድረስ የሚደክምበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል። ይህም ጸሎትን በመተው ፣ ያለ ልክ በመብላትና በመጠጣት ፣ በመተኛ ት ወዘተ ነው። ካህን እንዲህ ሲደክም በመዓርግ እና በእውቀት ከእርሱ የሚያንሱ ምእመናን ሳይቀር ይታዘቡታል ፣ ይንቁታልም።

ከምእመናንንም አልፎ አንዳንዱ ኢአማንያን አሕዛብ ሳይቀር «*አርሰም ቁስ አይደሉ አንዴ . . . ?*» አስኪሉት ድረስ ሊደክም ይችላል ፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ዮናስ ነቢይ እንኳ መንፈሳዊ ጥንካሬው በዛለበት ወቅት «ተንሥእ ወጸውአ ስመ አምላክከ / ተነሣና የአምላክህን ስም ጥራ!» ብለው የቀሰቀሱት አሕዛብ ነበሩ። ስለዚህ የእግዚአብሔር መልእክተኛ የተሰጠውን ክብር አስቦ ሌሎች ላይነግሩት ቀድሞ ራሱን ለትሩፋት ማነሣሣት አለበት።

ብዙኃንን የሚያስተምርና የሚያበረታ ካህን ተፈትኖ ሲወድቅና ሰዲያብሎስ እጁን ሲሰጥ እንደምን ይከብድ?! መጽሐፍም እንዲህ ሲል ይወቅሰዋል፦ «አነሆ አንተ ብዙዎችን ታስተምር ነበር ፣ የደከሙትንም እጆች ታበረታ ነበር ፣ ቃልህም የሚሰናከለውን ያስነሣ ነበር ፣አንተም የሚብረከረከውን ጒልበት ታጸና ነበር ።አሁን ግን በአንተ ላይ መጥቶአል ፣ አንተም ደከምህ ፣ ደርሶብሃል አንተም ተቸገርህ።» (ኢዮ. ፬፡፫፡ ፭)

በየትኛውም የመዓርገ ክህነት ደረጃ ያለ ካህን ከሥጋ ወደሙ መራቅ የለበትም። ጌታችን በቃሉ «*አስመ ዘአኀዘሌየሰ ሰልዐ ዘተክሉ ገቢረ ወኢምንተኒ /ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም*» (ዮሐ ፲፭፡፭) እንዳለ ያለ ሥጋ ወደሙ የሰይጣንን ፈተና መቋቋምም ሆነ መንፈሳዊ ሥራን መሥራት አይቻልም። በማይረባ ምክንያት ከሥጋ ወደሙ

መራቅ መንፈሳዊ ሥራን ስመሥራትና የአጋንንትን ፈተና ስመቋቋም የሚያስፈልገውን ኃይል ያሳጣል።

ትሩፋትን መለማመድ ሲባል በዕለት የሚመጣ ነገር ሳይሆን ቀስ በቀስ የሚፈጸም ነው። መንፈሳዊ ትምህርትን የሚማር ሰው በአንዴ ተነሥቶ እንደማይዘልቅ ፊደል አጥንቶ ፊደለ ሐዋርያ እንዲደርስ ካህንም ቀስ በቀስ ትሩፋትን መለማመድ ይጠበቅበታል። በቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተግሣጽ ላይ እንደተገለጸው በመጀመሪያ ጥሪት ቁሪት ማኖርን በመተው ዕደ ሥጋን ከመቀማት በማራቅ ቀጥሎም ምጽዋትን በማድረግ ከዚያም ዋዛ ፈዛዛን ፣ በሰው መዘበትን ፣ መደላደል መቀማጠልን ፣ ሰውን መንቀፍን ፣ መናቅንና ማዋረድን በመተው ትሩፋትን መጀመር ይቻላል።

ቀጥሎም እንቅልፍን መቀነስ ነው። «*ለ ካህን ለአመ ኅንከ ጥውየ አምን ሕማም ይኩን ንዋምከ ጎዳጠ በሰዓ ጊዜ / ካህን ሆይ ከሕማም ጤናማ ከሆንህ እንቅልፍህ ሁልጊዜ በጥቂቱ ይሁን*» ተብሎ ተጽፎአል። (ሃይ.አበ ዘሠ ፹፩፡፷፫) ስለዚህ ካህን በአብዝኖ ንዋም (እንቅልፍን በማብዛት) የማይሰጥም ዘወትር ለጸሎት ፈጥኖ የሚነሣ መሆን ያስፈልገዋል ፣ ስለ ጸሎትም ቢሆን ካህኑ ሳያቋርጥ መጸለይ እንኳ ባይቻለው በተወሰኑ ሰዓታት እንዲጸልይ ታዝዟል። (ፍ.ነገ ፭) ካህን የሚያስተምረውን ወንጌል ከማንም በላይ ራሱ ሊኖርበት ያስፈልጋል። አንዳንድ ጊዜ ወንጌል የማይመለከተው የሚመስለውና በየአጋጣሚው ለሚፈጠር ክስተት ቃለ እግዚአብሔር ሲጠቀስለት «*አርሱማ ወንጌል ነው!*» ብሎ ወንጌል ለሌላ ጉዳይ ወይም ለማስተማሪያ ብቻ እንደ ተጻፈ የሚያደርግ ካህንም ይከሰታል። ነገር ግን ካህናት ሳይጸፉ የሚነበቡ መጻሕፍት ሊሆኑና በወንጌል እየተመሩ በሕይወታቸው ሊያስተምሩ ይገባል።

፭ ክህነትን ስክብር መያዝ

ሥልጣነ ክህነት ቸሩ አምላክ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው ትልቅ ክብር ነው። የሰው ልጅ በመዋቲ ሥጋው ኢመዋቲ ሥልጣንን (በሚሞት ሥጋው የማይሞት ሥልጣንን) ገንዘብ ያደርግ ዘንድ፤ መንፈሳዊ ሀብታትን ይሰጥ ዘንድ ፣ መሾሙ የእግዚአብሔርን ቸርነት ያስረዳል። ካህናት እሳታውያን መላእክት ሊኹት የማይቻላቸውን ነደ እሳት ሥጋ ወደሙን የሚፈትቱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው። ስለዚህም ይህን ዐቢይ ሥልጣን የያዘ ካህን ክብሩንና ሥልጣኑን ማወቅና ስክብሮ መያዝ ይገባዋል።

ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔርን ጸጋ (ሥጦታ) አልጥልም» (ገላ ፪፥፳፩) እንዳለ ካህን ክህነትን የምታህል መንፈሳዊት ሀብት የትም መጣልና ማቃለል የለበትም። ንጉሥ ከሕዝቡ መካከል አክብሮ የሾመው ባለሥልጣን ቢከዳው እና የጠላትነትን ሥራ ቢሠራ እንደሚያዝንበት ፣ ካህኑም ከሕዝቡ ለይቶ ሳይመርጠው መርጦ ሥልጣነ ክህነትን የሰጠውን አምላክ ፣ ከመቅደሱ መግባትን፤ ምሥጢራትን ማየትን፤ በሕዝብ ላይ መክበርን ያደለውን ንጉሥ ቢተውና ከክህዲያን ፣ ከመናፍቃን ፣ ከዘማውያን ከጠንቋዮች ጋር በግብር ቢመሳሰልና ቢተባበር እግዚአብሔር ያዘንብታል ይቀጣውማል።

ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መወለድ ሊያበሥር ቅዱስ ገብርኤል ወደ ካህኑ ዘካርያስ በሄደ ጊዜ ዘካርያስን ጸጥ እንዲሆን ያደረገው ባለማመኑ ብቻ ነበር? አልነበረም። ቅሩበ እግዚአብሔር ካህን ፣ ምሁረ አሪት (ኦሪትን የተማረ) ሆኖ ሳለ ሲማር የኖረውን የእግዚአብሔርን ክህሊነት በመጠራጠሩ ነበር። (ሉቃ ፩፥፳) ይህ የሚያሳየው ካህን እንኳን ከክፉ ግብር ሊተባበር በእምነት ጉዳይ እንኳ ከሌሎች ይልቅ ብዙ የሚጠበቅበት መሆኑን ነው።

ካህን በብጽዓተ ክህነት ለቤተ ክርስቲያን የታጨ ሙሽራ ነው። አንድ ወጣት እጮኛ ይዞ እስከሚያገባት ድረስ ሊነካት እንደማይፈቀድለት ሥልጣነ ክህነት የተቀበለውም ዕለቱን ገብቶ የማይቀድሰውና ቤተ ክርስቲያን እስክትፈቅድለት የሚጠብቀው ለዚሁ ነው። እንዲሁም ካገባት በኋላ ባል ሚስቱን ትቶ ከሌላ ሴት ቢደርስ ቃል ኪዳኑን አፈረሰ ፣ በገሙት ረከሰ እንደሚባል ሁሉ ካህንም በብጽዓተ ክህነት ለቤተ ክርስቲያን የታጨ ሆኖ ሳለ ዓለማዊ ግብርን ቢሠራ ከከሃድያን ከስር ማሾች ከቅጠል በጣሾች ፣ ከጠንቋዮች ፣ ከኮከብ ቆጣሪዎች ጋር በግብር ቢተባበር እንደዘሞተ ይቆጠራል።

ዝሙት ሲባልም በቁሙ ልንተረጉመው እንችላለን። በተጨማሪ ግን ዝሙት የወንድና የሴት ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ያላዘዘውን መሥራትም ዝሙት ነው። (ሆሴ ፩፥፪ ትር)

የካህን በማይገባ ግብርም ሆነ በዝሙት መገኘት ሥልጣንን የሚያፈርስ ከመሆኑ ባሻገር «በኃጥኡ ጻፋ ጻድቁ ይደፋ!» እንዲሉ ለብዙኃች መጥፋት ምክንያትም ይሆናል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ከፍተኛ ውድመት ስላደረሱ ሁለት አረማውያን ከሚነገር ነገር ጋር ይህንን መመልከት እንችላለን ፦ ዮዲት ጉዲትና ግራኝ መሐመድ።

እነዚህ ሁለት አረማውያን በተነሱባቸው ዘመናት በቤተ ክርስቲያንና በምዕመናን ላይ ከባድ መከራን ያጸኑ ፣ አብያተ ክርስቲያናትና ንዋያተ ቅድሳትን ያጠፉ ናቸው። ስለ ሁለቱም አነግሥ በቃልም በብራና መጻሕፍትም የሚነገሩ ታሪኮች አሉ። የታሪኮቹን እውነታነት በማረጋገጥ የተጻፈ ነገር ባላገኝም ይህ ጽሑፍ የታሪክ ጽሑፍ ስላልሆነ ማንሣት ወደ ፈለግሁት ነጥብ እመጣለሁ። በሁለቱ

አረማውያን ቅድመ ታሪክ ላይ የሚነገሩት ነገሮች አንዳች ተመሳሳይ ነገር እንዳላቸው ማስተዋል ይቻላል።

ዮዲት ጉዲት ለዝሙት ይፈልጋት የነበረ «ዲያቆን» ለብሰ ተከሀኖ ጨርቅ ቆርጦ ሰለሰጣት በደረሰባት ቅጣት ቂም ይዛ እንደተበቀለች ፤ ግራኝ መሐመድ ደግሞ አባቱ የሚባለው ከመሰሊም ሴት ጋር በዝሙት አድሮ በቆብ ፈንታ የሴቲቱን ኩፍታ አሳስቶ በራሱ ላይ ደፍቶ ቤተ ክርስቲያን የገባ «ካህን» እንደሆነና መሐመድም የአባቱን አሟሟት ሰምቶ ቂም በመያዙ ይህን ጥፋት እንዳደረሰ ይነገራል። (የኢትዮጵያ ታሪክ ከዓፄ ልብነ ድንግል - ዓፄ ቴዎድሮስ ተ/ጻድቅ መኩሪያ ፤ ክርስትና በኢትዮጵያ ከፍል ሁለት እስከ ሰባት ዮሐ ገ/ማርያም)

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በጠቀስኳቸው መጻሕፍትም ቢሆን ስለዚህ ታሪክ በእርግጠኝነት የተጻፈ ነገር የለም። ይሁንና ይህ ድርጊት ሆኖም እንደሆነ ክብሩን የማይጠብቅ ካህን ምን ያህል የጥፋት ምክንያት እንደሚሆን ያስረዳል።

በሥልጣነ ክህነት መክሊት ማትረፍ የሚገባ ነው። ይህ ባይሆንና በመክሊት ማትረፍ ቢያቅት ግን መክሊትን አክብሮ ጠብቆ ማቆየት የተገባ ነው። አንድ መምህር በአንድ ወቅት የተናገሩትን እዚህ ላይ መጥቀስ ሳያስፈልግ አይቀርም። «ገብርኄር» እና «ገብር ኃላይ»ን (ማቴ.፳፭፥፲፱-፴) አስመልክቶ ሲያስተምሩ «አንድ መክሊቱን ቀብሮ የኖረው ሰው ዛሬ ቢኖር ጌታ ባመሰገነው ነበር። ምክንያቱም በዚህ ዘመን መክሊቱን ባያተርፍበት ቀብሮ እንኳ ማቆየት የቻለ ሰው አልተገኘ ምና» ብለው ነበር።

ካህን በተሰጠው መክሊት እንደ ክህነቱ የሚገባውን ያህል ተግቶ ምእመናንን ወደ መንግሥተ ሰማያት መርቶ ማስገባት ባይቻለው

በደንስ የተሰጠውን ሥልጣን አክብሮ ከኃጢአት ርቆ ንጽሕ ጠብቆ መኖር ይገባዋል። ስጦታን መናቅ ሰጪን መናቅ ነውና ለኃላፊው ምድራዊ ተድላና ደስታ የማታልፍ ክህነቱን የሚጥል ካህን እግዚአብሔርን ደስ አያሰኘውም። *«ወዘንቱ ካህን ኢያሠምሮ ለእግዚአብሔር በክህነቱ / ይህ ካህን እግዚአብሔርን ደስ አያሰኘውም»* እንዲል።

«ብርሌ ከነቃ አይሆንም እቃ!» እንዲሉ ሥልጣነ ክህነት ፈርሶ የሚታደስ አይደለም- ጥንቃቄ ያሻዋል። አስቀድሞ ክብሩን የጣለ ሰይጣን የካህንን ክብሩን ሰማስጣል የማይፈነቅለው ደንቢያ የለም። ከፍ ሲልም ሥልጣነ ክህነትን በቸልተኝነት እንዲያፈርሱና ካፈረሱ በኋላ ደፍረው ላገልግል እንዲሉ ሊያደርጋቸውም ይችላል። ስለዚህ በመዓርገ ክህነት ያሉ ሁሉ ራሳቸውን ለፈተና ከሚያጋልጥ ሁኔታ ማሸሽ አለባቸው። እዚህ ላይ በተለይ ዲያቆናትን ማንሣት ያስፈልጋል።

የዲቁና መዓርግ ከመዓርጋተ ክህነት የመጀመሪያውና ትንሹ ቢሆንም ከሁሉ ይልቅ ፈተና የሚበዛው በዚህ መዓርግ ባሉ ላይ ነው። ቀዳሜ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ለነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ (ቅድስት ሥላሴን ለመመልከት) የደረሰው እና በደንቢያ ተወግሮ ለጠላቶቹ ይቅርታን እየለመነ ለሰማዕትነት የበቃው በዲቁና መዓርግ ነው።

ቅዱስ እስጢፋኖስ በእርሱ ላይ ከነበረው የመንፈስ ቅዱስ ሀብትና መንፈሳዊ እውቀት የተነሳ አይሁድ ሊቋቋሙት አልቻሉም ነበር። *«ወበእኑ ተቃውሞቶ እስመ በጥበብ ወበመንፈስ ይትናገሮሙ / ሊቃወሙትም አልቻሉም ፤ በጥበብና በመንፈስ ይናገራቸው ነበርና»* እንደተባለ። (ሐዋ ፮፥፲) ይህ መንፈሳዊ ዲያቆን አእምሮ ጠቢዓይ ቀንቶለት ጥበብ መንፈሳዊ ተሰጥቶት አይሁድን በተከራከራቸው ጊዜ «ይህንንስ በአፍና በመጽሐፍ የሚችለው የለም» ብለው ነበር።

ቅዱስ እስጢፋኖስ ለዲያቆናት አርአያ ነው።ዲያቆናት ቡራኬ ሲሰጣቸው እንኳን «በረከተ እስጢፋኖስ ይኅድር በላዕሌክ / የእስጢፋኖስ በረከት በላይህ ይደር!» እየተባለ ነው።ቀሳውስት ስለዲያቆናት ሲጸልዩ ደግሞ «አብጽሖ ካዕበ ኀበ ዘየአቢ መዓርገ ሢመተ ክህነት አንቲአነ ወረሰዮ ምሉዓ ጸጋ ወጽድቅ ወሞገስ ከመ እስጢፋኖስ ዘርአየ ሀሱና ሥላሴ ዘበላዕሉ ፣ አንክረ ወተፋየጸ በርደተ መንፈስ ቅዱስ / ባሕርየ ሥላሴን እንዳየ እንደ እስጢፋኖስ ጸጋን ርዕይን ባለማጒደልንት የተሞላ አድርገው መንፈስ ቅዱስ ቢያድርበት እንዳደነቀ እንደ እስጢፋኖስ፤አካለ ሥላሴን እንዳየና እንዳደነቀ እንደ እስጢፋኖስ» እያሉ ነው።(ቅዳሴ ማርያም)

ቅዱስ አትናቴዎስም ቤተ ክርስቲያን ላይ ተረከዙን ያነሣው ርእሰ መናፍቃን አርዮስን በአደባባይ መልስ አሳጥቶ ዓምደ ቤተ ክርስቲያን የሆነው በዲቁና መዓርግ ነበር።-«ኦ ዲያቆናት ማኅቶተ ቤተ ክርስቲያን ወላእካኒሃ ምልኦ እም ውስቴታ ኢየሃሉ ተኩላ ምስለ በግዕ ፣ አንቁ ምስለ ርግብ ፣ክርዳድ ምስለ ሥርናይ / የቤተክርስቲያን መብራት ፣ አገልጋዮችዋም የምትሆኑ ዲያቆናት ሆይ ተኩላ ከበግ ጋራ ፣ ጭላት ከርግብ ጋራ ፣ ክርዳድ ከስንዴ ጋራ እንዳይኖር ከውስጥዋ ንቀሉ።።» በማለት ዲያቆናት ቤተ ክርስቲያንን ከመናፍቃን ለመጠበቅ እንዲነቁ አደራ ይላል። (ቅዳሴ አትናቴዎስ ቁ ፲፩)

እነዚህ ሁለት ቅዱሳን ለዲያቆናት አርአያ ናቸው። ቅዱስ እስጢፋኖስ ዲያቆን ማለት እጁን ለጥል ከመስብሰብ ይልቅ ስለ ሃይማኖቱ መከራን በአኩቴት እየተቀበለ እንደ ጌታችን ለሚጠሉት የሚጸልይ እንደሆነ ፣ ቅዱስ አትናቴዎስም ዲያቆን ማለት ትምህርተ ሃይማኖትን ተግቶ እየተማረና መጻሕፍትን እየመረመረ ቤተ ክርስቲያንንና ሃይማኖትን የሚያስከብር እንጂ ስለ ትምህርተ ሃይማኖት

ግድ የሌለውና በግብሩ ከዓለማውያን ጋር የሚተባበር እንዳልሆነ በተግባር አስረድተዋል።

ከዚህ ባሻገር ዲያቆናት የዝሙት ጸር በሚጸናበት በውርዙትና (በወጣትነት) ዕድሜ ላይ ያሉ ስለሆኑ በሕግ ተወስነው በጋብቻ እስካልኖሩ ድረስ እስከ ጊዜው እንደ መነኮሳት መሆናቸውን በማወቅ ራሳቸውን ከፈተና ማራቅና ማሸሽ አለባቸው። በጉያው እሳት ታቅፎ የማይቃጠል እንደ ሌለ በመረዳትም ወደ ኃጢአት ከሚመሩ ሁኔታዎች ከማንኛውም ክርስቲያናዊ ወጣት ይልቅ ዲያቆናት ሊሸሹ ይገባል። (ምሳ.፮÷፳፯)

በዲቁና ያሉ ወንድሞች በወጣትነት እድሜ እንደ መሆናቸው በዝሙት ይፈተናሉ በሚል በሰዎች ዘንድ ተአማኒነትን ሊያጡና ሊታሙ ይችላሉ። ይሁንና ማዕረጋቸውን ሳይዘነጉ ፣ ክብራቸውን ጠብቀው ለሕሊናቸውና ለፈጣሪያቸው ታምነው መኖር ይጠበቅባቸዋል። ክህነቱን ሳይጠብቅ በድፍረት የሚያገለግለውን ግን ሰዎች ባያሙትም ፣ እግዚአብሔር ባይገልጥበትም የማይሸሸው የሕሊና ዳኛ ይከተለዋል።

«በዲቁና ሥራ በመልኃም ያገለገሉ ለራሳቸው ትልቅ ማዐርግና በኢየሱስ ክርስቶስ ባለው እምነት ብዙ ድፍረት ያገኛሉ» እንዲል በዲቁና አገልግሎት መታመን እጅግ ታላቅ ዋጋ ያለው ነው። (፩ጢሞ÷፫፣)

ክህነታቸውን አክብረው የሚኖሩት ግን እግዚአብሔር ይጠብቃቸዋል። እንደ አንድ ዲያቆን፡- ይህ ዲያቆን የአንድ መኮንን ሚስት የሆነች ወዳጅ ነበረችው። ይህች ሴት ታማሚ ነበረች። ወደ ቤቷ እየሄደ ራእየ ዮሐንስን ይደግምላትና በጎ ትሆን ነበር። ወንድ ከሴት ከደረሰ መታማት ልማድ ነውና ሰዎች «አንተ በሌለህበት ፭ዘ ቤትህ

የሚገባ ሰው አለ» ብለው ለሴቲቱ ባል ነገሩት። ከዕለታት በአንድ ዕለት ቢገባ ዲያቆኑን ከፊቷ ቆሞ ሲደግምላት አገኘው። *«ለካ የነገሩኝ ሁሉ ሐሰት አይደለም»* ብሎ «ለቅናት የለውም ጽናት» እንዲሉ ከእነ መጽሐፉ አስጠቅልሎ ከባሕር አስጣለው። ወዲያው ብሩሕ ብእሲ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ተቀብሎ በደሴት አኖረው።

ሴቲቱ ደዌው ሲጸናባት አባ በአሚን የተባለ መነኩሴ «ከዚያ ዲያቆን በቀር የሚያድንልህ የለም» ብሎ ለመኮንኑ ነገረው። መኮንኑም *«ከባሕር አስጥዬው የለምን?»* አለ። አባ በአሚንም *«መስሎህ ነው እንጂ እንዲህ ካለ ቦታ ነው ያለው»* አለው። መኮንኑም ዲያቆኑን አስመጥቶት መጽሐፉን ቢደግምላት ድናለች። ይህ ዲያቆን ኋላ ላይ በሐገረ ሮሜ ለኤጲስ ቆጶስነት በቅቷል። ዲያቆን ክህነቱን ከጠበቀ እግዚአብሔርና ቅዱሳኑ እንዲህ ይጠብቁታል።(ስንክ.ታሕ.፱ ፤ ራእ.፩፥፫ ትር)

«ክህነትን መጠበቅ» በሚል ርዕስ ስለ ዲያቆናት አብልጠን መናገራችን «ቄስ ነበርኩ!» ከሚለው ይልቅ «ዲያቆን ነበርኩ!» የሚለው ይበዛልና ነው። ለመጠቅለል ያህል ዲያቆናት ወደ በለጠችው መዓርገ ቅስና ለመድረስ የሚተጉና የሚማሩ በዲቁናቸው ዘመን ቀሳውስትን በአባትነት የሚያከብሩና የሚታዘዙ ሲሆኑ ይገባል። ሐዋርያው በመልእክቱ *«ወከማሁኒ አንትሙ ወራዙት ተኰነኑ ለአለ ይልሕቁክሙ /* እንዲሁም ዝበዙች ሆይ ለሽማግሌዎች ተገዙ» በማለት ዲያቆናት ከእነርሱ በላይ ላሉ ለቀሳውስት እንዲገዙ አዝዟል። (፩ኛ ጴጥ ፭፥፭) «አህያ በወለደች ታርፋለች» እንዲሉ ዲያቆናት ለቀሳውስት ተግተው በመርዳት ቡራኬን የሚቀበሉ «ክህነትህን ይባርክልህ!» የሚሰኙ ሊሆኑ ያስፈልጋል።

የመማር ፈቃደኝነትና ፍቅረ ቤተ ክርስቲያን የሌለው ካልሆነ በቀር የዛሬ ዲያቆን የነገ ቄስ ለመሆን እንደሚሻና እንደሚሆን

ይጠበቃል። ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ በምሥጢር ተጽፎ እናገኘዋለን። በትንቢተ ዘካርያስ ፲፬፥፳ ላይ «በእግዚአብሔር ቤት ያሉ ምንቸቶች በመሠዊያው ፊት እንዳሉ ዳካዎች ይሆናሉ። . . . የሚሠዉትም ሰዎች ሁሉ ይመጣሉ።» ተብሎ ተጽፎአል። በዚህ ሥፍራ «በእግዚአብሔር ቤት ያሉ ምንቸቶች» የተባሉት ዲያቆናት ሲሆኑ «በመሠዊያው ፊት ያሉ ዳካዎች» ደግሞ በታቦተ ምሥዋዑ ፊት የሚቆሙ ቀሳውስት ናቸው። ዓረፍተ ነገሩም (የነገሩ ማረፊያም) ዲያቆናት እንደ ቀሳውስት ይሆናሉ ነው። «የሚሠዉት ሰዎች ይመጣሉ» ሲልም እግዚአብሔር የሚሻውን መሥዋዕት (የተሰበረ መንፈስን) በንስሐ በኑዛዜ ለማትረብ ምእመናን ወደ እነርሱ የሚመጡ መሆናቸውን ነው። ስለዚህ በዲቁና ሳሉ ለቀሳውስት ተግቶ ማገልገልና መታዘዝ ብድራትን ሰፍሮ ቆጥሮ በሚሰጥ አምላክ ፊት ብድርን ማቆየት ነው።

የካህን ኑሮ ጥንቃቄ የሚያሻው እንደመሆኑ አንድም በእንስራ ይመሰላል። እንስራ «ከእግዚአብሔር ብቻ የሚገኝ ውኃ ማምጫ ነው። እኽራ ዘወትር በመመላለስ ከዓለት ጋር ሊጋጭ ስለሚችል ተጠንቅቀው ካልጠበቁት መሰበር ከሌላው ሸክላ ሁሉ በእንስራ ላይ ይጸናበታል። ካህንም እንዲሁ ከጽኑዕ አለት ከእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ ነውና ካልተጠነቀቀ ከሰው ልጆች ሁሉ ይልቅ መቀጣትና መቀሰፍ በእርሱ ላይ ይጸናበታል ፤ ለሥጋዊ ምኞቱ ሲል አገልግሎቱን ለሥጋዊ ጌቶች ቢያደርግ ግን እንደ እንስራው ይሰበራል።» (ፍኖተ አእምሮ)

ካህን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲጥስ የሚያደርጉ አስገዳጅና አሳማኝ ምክንያቶች ቢገጥሙት እንኳ ለክህነት ኃላፊነቱ በማድላት ያከበረውን አምላክ ማክበር አለበት። ብዙ ሥጋዊ ፈተናዎችንና ምክንያቶችን ተቋቁመው ክህነታቸውን ጠብቀው ሥርዓቱን አውቀው የሚኖሩ ካህናት እግዚአብሔር በሰማይ ከሚሰጣቸው ክብር ባሻገር በምድርም ሞገስን ያድላቸዋል። እንደ አባ ብንያሚ፡-

በደቡብ ጎበፅ በሀገረ ቱና ይኖር የነበረው ይህ አባት ክህነቱን ጠብቆ ሥርዓቱን አውቆ የሚኖር ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ቤተ መቅደስ ከገባ በኋላ «*አባትህ ታሞ ለሞት ቀርቧል ፤ አርሱንም አምጠልኝ ብሏል*» ብለው መልእክተኞች ነገሩት ቀሲስ ብንያሚ ግን «የቁርባኑን ሥርዓት ሳልፈጽም ልብሰ ተክህኖውን አላወልቅም እግዚአብሔር ከፈቀደ ከመሞቱ በፊት ይቆየኛል ፤ ካልፈቀደ ግን እግዚአብሔር የወደደው ይሁን!» ብሎ ለእግዚአብሔር ሥርዓት መፈጸም አደላ። በዚህም የአባ ብንያሚ ክህነት የተባረከ በመሆኑ ልብሰ እጅግ መልካም መዓዛ ይሸት ነበር።

ለዚህም ነው እመቤታችን «*መዓዛ ጽጌያት ጥዕምት አምሳ ሄና ልብሰ ለአባ ብንያሚ* / ከአባ ብንያሚ የልብስ መዓዛ ይልቅ የሚበልጥ መዓዛ ያለሽ» ተብላ የምትመሰገነው (ማኅሌተ ጽጌ) በዚህ አባት ታሪክ ብዙ ሥጋዊ ፈተናዎችና አስገዳጅ ማኅበራዊ ችግሮችን ተቋቁሞ የክህነት ሥልጣን ማክበርን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማስከበርን መማር ይቻላል።

ስለዚህም ካህን ቃለ እግዚአብሔርን ከአንደበቱ የማይለይ የንስሓ መምህር ፤ሥልጣኑን የሚያከብር ፤ በአምላኩ ፊት በቅንነት የሚመላለስ ፤ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ የታመነ መሆን አለበት- እንደ ሌዊ። «በአውነት ሕግ በአፉ ውስጥ ነበረች ፤ በከንፈሩም ውስጥ በደል አልተገኘበትም። ከእኔም ጋር በሠላምና በቅንነት ሄደ። ብዙ ሰዎችንም ከኃጢአት መለሰ።» ብሎ አምላክ መስክሮለታልና። (ሚል ፪፥፮)

ምዕራፍ አምስት

የንስሐ አባትና የንስሐ ልጅ
(ንስሐ እና ሥርዓተ ኑዛዜ)

በንስሐ ሂደት የካህኑ ድርሻ

፩. መልካም እረኛ መሆን

❖ ምሕረት መንፈሳዊን በማድረግ!

«ምሕረት መንፈሳዊ» ማለት ክፉ ግብር በጎ ግብር መስሏቸው እየሠሩ ለሚኖሩት ለኃጥአን መራራት ማዘን ነው። (ማቴ ፱፥፮ ትር) በመጽሐፍ «እርስ በእርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ» (ያዕ ፭፥፲፮) ተብሎ የተነገረው ናዛዚው ካህን ከተነሳሒው ጋር በባሕርይ አንድ ስለሆኑ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል። ስለዚህ ካህን በባሕርይ የሚመስሉትን ምእመናንን በደል ሲሰማ በባሕርይው ከእነርሱ ጋር አንድ መሆኑ እንዲራራላቸው ችግራቸውንም እንዲረዳ ያደርገዋል።

ለዚህ ነው ለመናንያን መናኒ ካህን ፤ ለሰብአ ዓለም ደግሞ ሕጋዊ ካህን /ያገባ/ መምህረ ንስሓ እንዲሆናቸው የሚመከረው። ካህኑ እንደ ምእመናኑ በነገር ሁሉ የሚፈተን በመሆኑ ለምእመናን ድካም ሊራራ ይገባዋል። በመራራቱም ኃጢአታቸውን ለመናዘዝ እንዲበረታቱ

ምዕራፍ ስድስት

ለካህናት የሚገባ አክብሮትና አገልግሎት

ቅዱስ አትናቴዎስ *«ለ ካህናት ሰዩማን ክብር ለክሙ ሶበ ትትከሀሉ ምስለ እግዚአ ሰማያት ወምድር / የተሾማችሁ ካህናት ሆይ ከሰማይና ከምድር ጌታ ጋር ለማገልገል ትሳካላችሁና ክብር ይገባችኋል»* (ቅዳሴ አትናቴዎስ ቁ. ፲፭) በማለት እንደተናገረ እግዚአብሔር ለካህናት ትልቅ ክብርና ልዕልናን ሰጥቶአል። ከክብርት ሥልጣናቸው የተነሣ ደግሞ ካህናት ሊከበሩ ይገባቸዋል።

ካህናትን ማክበር ከሁሉ ይልቅ ለምእመናን የተገባ ነው አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው *«ለ አበዊነ ንዑራነ ዕድ ሰዩማን እለ መትልወ ሐዋርያት . . . / ከሐዋርያት ቀጥላችሁ መስላችሁ በእንበሮተ ዕድ የምትሾሙ አባቶቻችን እናከብራችኋለን እናገናችኋለን»* ብሎአልና (ቅዳሴ ማርያም ቁ ፲፫)

ፍትሐ ነገሥት ለካህናት የሚገባውን ክብር ጀኤል ለአሮንና ለሙሴ ይሰጡት የነበረውን ክብር እንደሆነ ያስረዳል። «ዲያቆኑ ዛሬ በአሮን ቦታ አለላችሁ ኤጲስ ቆጶሱም በሙሴ አምሳል» በማለት። (ፍት.ነገ.መን ፱፥፫፻፲፪) በተጨማሪም «አጋንንትን የሚያገለግሉ (ካህናተ ጣዖት) ከወገኖቻቸው (ከአምላኪያነ ጣዖት) የሚከብሩ ከሆነ ያለ ጣዖቱ ካህን ፈቃድ በቀር ምንም ሥራ የማይሠሩ ከሆነና የሚያዛቸውን ሁሉ የሚሠሩና የሚፈጽሙ ከሆነ ፤ የተረዳች ሃይማኖት ፤ የከበረች አለኝታ ፤ ያለ ፍርሃት ምስጋናን የተሞላች የዘላለም ዋጋን (መንግስቱን) ደጅ የምንጠና እኛ ክርስቲያኖችማ አስቀድመን አምላካችን እግዚአብሔርን ፤ ቀጥሎ ካህናቱን ማክበር እንዴት አይገባንም?» በማለት ይገልጻል።

(ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ፱፥፫፻፲፩)

ለካህናት ያለን ክብር ሌላው ቀርቶ እነርሱን ከምንጠራበት አጠራር ይጀምራል ፤ ካህናት «አባቶቻችን ፤ ጌቶቻችን፤ መምህሮቻችን» መሰኘት ይገባቸዋል። ይህም የለበጣ ሳይሆን ነገረ ሃይማኖትን ከመረዳት የሚመነጭ ጥሪ ነው። በሐዋ ፪፥፴፯ ጴጥሮስንና ሌሎችንም ሐዋርያት «ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?» ሲሏቸው ይላል ፤ ወንድሞች ሆይ ብለው መጥራታቸው ግብር ገብተው ከአእምሮ (ከማወቅ) ደርሰው ባይረዱት ነው እንጂ *«አበዊነ* (አባቶቻችን) ፤ *መምህራኒነ* (መምህሮቻችን) ፤ *አጋእዝቲነ* (ጌቶቻችን) *ሊቃውንቲነ* (ሊቃውንቶቻችን ፤ አለቆቻችን) » ሊሉአቸው በተገባ ነበር። (ሠ.ሐዲ.ዘሠሰስቱ) ስለዚህ ካህናትን አቃልሎ የሚጠራ ትምህርተ ሃይማኖት ያልተረዳ ነው ማለት ነው።

የካህናቱን ክብርና የታሰረውን የመፍታት ፤ የተዘጋውን የመክፈት ሥልጣን የተረዱ ግን «ጌቶቼ ሆይ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?» ይላሉ (ሐዋ ፲፮፥፴) የድኅነትን መንገድ እንዲመሩአቸውም ደጅ ይጸኑዋቸዋል። አንዳንዶች በማኅበራዊ ቅርበት (ዝምድና ፤ በጉርብትና) ከካህን ጋር በሚኖራቸው ትስስር ካህናትን አቃልለው ሲጠሩ ይታያል። ይሁንና ባልንጀራ ንጉሥ ሆኖ በተሾመ ጊዜ አፈር ስንፈጭ ውኃ ስንራጭ አድገናል ብሎ መናቅ እንደማይገባ ካህንንም ምን ቢቀርቡት አቃልለው ሊጠሩት ፤ ሊንቁት ግን አይገባም። *«ወለዘሂ ፍርሃተ ፍርሁ / መፈራት የሚገባውን ፍሩ»* እንዲል ሐዋርያው (ሮሜ ፲፫፥፯)

ሊቃውንትን *መምህራ* ፤ *አቡነ* ፤ *አለቃዬ* ብሎ መጥራት ጌታችን አስተምሮናል። ይህም ሊቀ መምህራን የሆነ እርሱ ኒቆዲሞስን «አንተ የእይሁድ መምህር . . . » ብሎ በመጥራቱ ነው። አንዳንዶች

«መምህር ተብላችሁ አትጠሩ» (ማቴ ፳፫፥፰) በማለት የተናገረውን ይዘው «መምህር» ብሎ መጥራትን ይቃወማሉ። ይሁንና ጌታችን በዚህ ቃል የተቃወመው «መምህር» ለመሰኘት የሚደረግን ሩጫና የትዕቢት ሀሳብ እንጂ አክብረው «መምህር» የሚሉትን አይደለም። ደግሞም «መምህር ተብላችሁ አትጠሩ» አለ እንጂ «መምህር ብላችሁ አትጥሩ» አላለም። ያን ማለቱ መምህር መሰኘትን አትሹት ሲል ነው።

ነገሩን በጥልቀት ካየነው በዚህ ስፍራ ጌታን ጨምሮ «አባት ብላችሁ አትጥሩ» ብሏል በዚህ መሠረት ከሔድን ደግሞ ወላጅ አባታችንንም አባቴ ማለት ልንከለከል ነው ማለት ነው። ይሁንና ይህ ቃል አባቴ የሚባሉ እንጂ ሌሎችን አባት ብለው ሲጠሩ ለማይገባቸው ሊቃነ ጳጳሳት ለሐዋርያቱ የተሰጠ ትእዛዝ ነው። «መምህር» ብሎ መጥራት ባይገባ ጌታ ኒቆዲሞስን «መምህር» ባላለው ነበር።

የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ቃል በተግባር እንዲያስተምር ተፈቅዶለታል። መምህር የሚለው መጠሪያ ደግሞ ትርጉሙ «የሚያስተምር ሰው» ማለት ነው። ከስሙ ደግሞ ተግባሩ ይከብዳል። በራሱ መምህር ፣ መካር የሆነ የሆነ አምላካችን ነው። ሰው ቢያስተምር «በከመ ይቤ» «ጌታችን እንዳለ» እያለ ነው ፣ እርሱ ግን ከራሱ ይናገራል። ኤሊሁ እንዳለው «እንደ እርሱስ ያለ አስተማሪ ማን ነው?» (ኢዮ. ፴፮፥፳፪) ይህ የራሱ የሆነው መምህርነት ለሰው ልጆችም እንደ ብዙ ሥጦታዎቹ ሁሉ ሰጥቶናል። «እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን አስቀድሞ ሐዋርያትን ሁለተኛም ነቢያትን ሦስተኛም አስተማሪዎችን ... አድርጓል።» ፩ቆሮ. ፲፪፥፳፰

ለካህናት [12]እጅ መንሳትና የጸጋ ፣ የአክብሮት ስግደትን ከጉልበታቸው ከአንገታቸው በአፍ ጢም ተደፍቶ መሳም ይገባቸዋል።

[12] እጅ መንሣት ማለት አለመጨበጥ የአክብሮት ሰላምታን በመግነስ ብቻ መስጠት ሲሆን በአፍጢም መደፋት ደግሞ ብአፍና በጢም መደፋትን ያመለክታል።

የካህናትን ጉልበትና ጫማ መሳም ፣ ለሚቀመጡበት ማንጠፍ ፣ የሾማቸውንና ሹመታቸውን ማክበር ነው። ለካህናት እጅ መንሳትን አክብሮ ተነሥቶ መቀበልን የማይሹ እነርሱ እንደ ቀላል በሚያዩት ነገር ከሰማያዊው ንጉሥ ጋር እየተጣሉና ከፍርድ እየገቡ መሆኑን ሊያውቁ ይገባል። እንኳን ለሕያዋን ካህናቱ ጌታ በአሀያ ላይ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ እንኳን ለአንተ ለተቀመጥክባም አህያ መሬት መርገጥ አይገባትም ሲሉ ልብሳቸውን አንጥፈውላታል።

የአስቆሮቱ ይሁዳ አያት ለዚያ ሁሉ ርግማን የገባው የእግዚአብሔርን ነቢይ አይቶ እጅ ላለመንሳት እንዳለየ በመሆኑ አልነበር? ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ምን ያህል ለሾማቸው ክብር እንደሚቀና እና ሲንቁበት እንደሚቆጣ ያሳያል።

እኛ ግን ቆርኔሌዎስ ለቅዱስ ጴጥሮስ (ሐዋ ፲፥፲፮) ቆስጠንጢኖስ ለሲሊቬት እንደሰገዱ ለአባቶቻችን በአክብሮት እንሰግዳለን። አበው ካህናት እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ በትሕትና እንደ አንተ ያለሁ ፈራሽ በስባሽ ነኝ አትስገድልኝ! ቢሉንና ቢያነሱንም እኛ ግን በመዋቲ ሥጋቸው የያዙትን ኢ መዋቲ ሥልጣንና ክብር በመዘከር (በማሰብ) እንሰግድላቸዋለን ፤ እናከብራቸውማለን።

ለካህናት ክብርን መስጠት የሁሉም ግዴታ ነው። ምናልባት እንደቆርኔሌዎስ በምድራዊ ክብር የከበረ ሰው ቢሆንም እንኳን ካህንን ማክበር ክርስቲያን እስከሆነ ድረስ የሁሉም ግዴታ ነው። በመንፈሳዊም ቢሆን ከክህነት ሌላ እንደ ምንኩስና ብሕትውና የመሳሰሉትን መንፈሳዊ መጠሪያዎች የያዘም ቢሆን ካህንን ማክበርና ምእመናንን ወደካህናት እንዲቀርቡ መምራት አለበት። አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ተደማጭነትን ያገኙ ሲመስላቸው ካህናትን የሚዘልፉና ምእመናንን ከካህናት የሚያሸሽ ፣ ተስፋ የሚያስቆርጥ «ገበሬ አስደንግጥ ስብከት» የሚሰብኩ

«ባሕታውያን» ሊኖሩ ይችላሉ። ብሕትውና እንዴት ነው? የሚለውን ጥያቄ እንተወውና የባሕታዊ ግብር ካህንን ማቃለል አለመሆኑ ግልጽ ነው። ታላቁ ባሕታዊ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ለሊቀ ካህናት ክርስቶስ «እሱ ሊልቅ እኔ ላንስ ይገባል» ብሎ ሥፍራውን በመልቀቅ ለባሕታውያን አብነት ሆኗል። ስለዚህ ባሕታውያን ምእመናንን ወደካህናት የመምራት ኃላፊነት አለባቸው።

የካህን ሥልጣን በሞት የማይገደብ በመሆኑ ለካህን የሚሰጠው አክብሮትም ከሞተ በኋላም ይቀጥላል። የካህኑን በድን ይፍቱኝ ብለን የምንሳለመው ፣ ከግንዘቱ እስከ መቅበርቱ (መቃብሩ) በክበረ ሃይማኖታዊ ሥርዓት የምንሰናበተውም ለዚህ ነው። «አኮኑ እንዘ ንፈንሦሙ በክብር ወናሜኒ ግንዘቶሙ በዐቢይ ጸሕቅ / በክብር የምንልካቸው ግንዘታቸውንም በታላቅ መጠበብ የምናሳምር አይደለምን?» እንዲል (ተግሣጽ) በብሩሕ ትንሣኤ እንደሚነሣ በማመን ካህኑን ነግተው ተግተው ይገንዙታል። መነኩሴ የሆነ እንደሆነ «በዓይንህ የማይገባ ነገር አላየህበትም!» ሲሉ እጁን በዓይኑ ጥለው ይገንዙታል። ቄስ የሆነ እንደሆነ «መስቀልን (መስቀሉን) ተቀብለሃል!» ሲሉ እጆቹን አመሳቅለው ይገንዙታል። ዲያቆን ከሆነ ደግሞ በተልእኮ ኑረሃል ሲሉ አስተላልፈው ይገንዙታል።

ከዚህ ባሻገር ወታደር ሲሞት ጋሻውን ጦሩን ይዘው እንደሚያለቅሱ፤ ካህን ሲሞትም ቅድመ እግዚአብሔር ሲያገለግልበት የኖረውን መቋሚያውን ጸናጽሉን ቋዱን ቀሽመሪውን ይዘው ጎዘንን ያደርጉለት ዘንድ ይገባል። (ኢሳ ፬፥፳፮ ትር)

ለካህናት ያለንን አክብሮት የምንገልጽበት ሌላው መንገድ ደግሞ ካህናትን ማገልገል ነው። ካህናት ከእግዚአብሔር የሚያስታርቁን ኃጢአታችንን የሚያራግፉልን ናቸውና። ልናገለግላቸው ይገባል።

«የሚያስታርቋችሁ ነቢያት እንደሆኑ ለምን አታስቡም ፣ የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደመሆናቸው ለምን አታገለግሏቸውም» ተብሏልና። (ቈላ.፩፡፳፫) ማገልገል ሲባል አቅም እንደ ፈቀደ የሚያስፈልጋቸውን ሥጋዊ ነገር ማሟላት ነው። ይህም እንደ እንግዳ ደራሽ ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ ደርሶ የመጣ ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ የነበረ ሥርዓት ነው። የብሉይ ኪዳን ካህናት (የሌዊ ወገን) ርስት ሰጀፀ ነገደ ጽኤል ሲከፋፈል ለእነርሱ አልተሰጣቸውም ነበር። «የጽኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዳላቸው ርስታቸው እርሱ ነው።» (ኢያ ፲፫፡፴፫) የዚህም ምክንያቱ ኑሮአቸው በመቅደስ መተዳደሪያቸውም ሕዝቡ የሚሰጠው ገንዘብ ስለነበረ ነው። ለአሪት ካህናት ይህ ከተደረገ ለደገኞቹ የወንጌል አገልጋዮችማ ምን ያህል ይገባቸዋል?

አቅሙ የፈቀደለት ሰው ካህናትን ከምግብና ልብስም ባሻገር መኖሪያም ሊሰጣቸው እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል ፣ ሚካ የተባለ የኤፍሬም ሀገር ሰው (ምንም የኋላ ታሪኩ ሌላ ቢሆን) አንድን ሌዋዊ ካህን «ከእኔ ዘንድ ተቀመጥ አባትና ካህንም ሁነኝ እኔም ልብሶችንና ምግብህን በየዓመቱም ፲ ብር እሰጥሃለሁ አለው» ይላል። ካህኑም መኖር ከጀመረ በኋላ ሚካ እንዲህ አለ። «ሌዋዊ ካህን ስለሆነልኝ እግዚአብሔር መልካም እንዲሠራልኝ አሁን አውቃለሁ» (መላ. ፲፯፥፲፫)

በሐዲስ ኪዳን የተሾሙት የመጀመሪያዎቹ ካህናት ቅዱሳን ሐዋርያትም ጌታችን ሲልካቸው የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብና ስንቅ ልብስ እንዳይዙ ነግሯቸዋል። ምክንያቱንም «ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና» በማለት አስረድቷል። (ማቴ.፲፥፲) ይህም ለመምህር *የዕለት ራት ፣ አንድ እንጀራ ጽዋ ውኃ ይገባዋልና የምታስተምሯቸው እዚያው ይመግቧችሁ* ሲል ነው። በሌላም ሥፍራ «የሰማይ አእዋፍ አይዘሩም

አያጭዱም» ሲል በምሳሌ የተናገረው ዘር መከር ሳይኖራቸው ከምእመናን ዘር መከር የሚመገቡ ካህናትን ነው። (ማቴ፮፥፳፭)

አንዳንድ ሰዎች ለካህናት የሚሰጥን አገልግሎት (መስተንግዶ) ከካህናት ከሚገኘው አገልግሎት እንደሚበልጥ እንደ ትልቅ ነገር አድርገው ሲናገሩና ሲነቅፉ ይታያል። ካህናትም ከሚያገለግሉት ሰዎች ወገንም አንዳንዶቹ የተንደዱ ይመስል ሲማረሩና ሲቆጩ ይስተዋላሉ። ይህ ዓይነቱ ድካምን ከንቱ የሚያደርግ ክፉ ዓመል በቆሮንቶስ ክርስቲያኖችም ላይ ታይቶ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ገሥጾአቸዋል፦

«ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማነው? ወይስ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማነው? ወይስ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማነው? ይህን በሰው ሥልጣን ብቻ እላለሁን? ሕግስ ደግሞ አይልምን? ፤ *የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር*፤ ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፎአልና (ዘዳ፳፭፥፬) እግዚአብሔርስ ስለ በሬዎች ይገደዋልን? ይህን የሚለው ፈጽሞ ስለ እኛ አይደለምን? የሚያርስ በተስፋ ሊያርስ ፤ የሚያበራይም እንዲካፈል በተስፋ ሊያበራይ ስለሚገባው በእውነት ስለ እኛ ተጽፎአል። እኛ መንፈሳዊን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተን የሥጋዊን ነገር ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን? *(መንፈሳዊውን ነገር እየሰጠናችሁ ለቁመተ ሥጋ ያህል ከእናንተ ሥጋዊውን ነገር ብንወስድ ፤ ተራራ የሚያህል /ልዕልተ ትምህርትን/ አስተምረናችሁ ድምብላል የምታህል ከእናንተ ብንወስድ)* ትልቅ ነገር ነውን?» በማለት ተናግሯል።

ለካህናት ለምን አገልግሎትና መስተንግዶ ይደረጋል? የሚሉ ሰዎች የካህናትን ድካም የማያውቁ ናቸው። የካህናት አገልግሎት ሌሊትና ቀን እንደ መሆኑ የሚሰጣቸው አገልግሎት የሚያንስባቸው

ነው። ይህን የማይዋጥላቸው ለአንድ ሰሁለት ለያልይ (ሌሊቶች) ማኅሌት / ሰዓታት አድረው ሊያዩና ሊረዱ ይችላሉ። በቅድስት እምነ ወለተ ጴጥሮስ ዘመን የተፈጸመውም ይኸው ነው።

ቅድስቲቱ ለካህናት ግብር ታገባ ነበር። በዚህ ጊዜ ልዩ ልዩ የመላላክና የወጥ ቤት ሥራ የምትሠራ አንዲት ሴት ከእርሷ ጋር ነበረች። ለካህናት ምግብ ማዘጋጀትን ይህች ሴት አትወድም ነበር። እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ይህችን ሴት በሌሊት ቤተ ክርስቲያን ወስዳ የካህናትን ድካማቸውን አሳየቻት። ይህችም ሴት የካህናትን ድካምና ትጋት በተመለከተች ጊዜ ስለ ሥራዋ ተጸጸትችና ካህናትን በደስታ ታገለግል ጀመር (ገድለ ወለተ ጴጥሮስ) ስለዚህ ከግብረ ሌሊት ሴት ተነስተው እንቅልፍን ያህል ሲሳይ ፤ *ብርድን ያህል ሰቃይ* ፤ እጥተውና ታግሰው የሚያገለግሉ ካህናት ታላቅ ክብርና አገልግሎት ይገባቸዋል።

አንዳንዶች እንኳ ሌላው መስተንግዶ ይቅርና ደመወዝም ጭምር ለካህናት አይገባም እስከ ማለት ይደርሳሉ። ከዚህም አልፈው ካህናትን *«የዲግሪ ደመወዝ እየበሉ . . .»* ወዘተ በማለት የሚነቅፉም አሉ። ይህ የነቀፋ ዓይነቱ ሀሳብ ከሁለት ነገር የሚመነጭ ነው። የመጀመሪያው ዘመናዊው ትምህርት ከመንፈሳዊው በላይ የተጋነነ አክብሮት መስጠት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የካህናትን ክብርና ጥቅም ካለመረዳት ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ካህናት የለ ምንም ዋጋ ያገለግሉ ማለት ወታደር በገንዘቡ ያገልግል እንደ ማለት ነው። በእርግጥም ካህናት ወታደሮች ናቸውና። አባ ሕጻነ ማርያም ጌታሁን የተባሉ አባት «ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ» በሚል መጽሐፋቸው «የነፍስ የሥጋ ጠላቶች ከሆኑት ከረቂቃን አጋንንትና ከነጻነት ገፋፊዎች ጋር ሌት ተቀን በጸሎት እየተዋጉ የሚጠብቁን መንፈሳውያን አርበኞት ቀሳውስት መሆናቸውን አንዘንጋ» በማለት ሲጥል እንጂ ሲወጋ በማይታየው «የአቡነ ዘበሰማያት ጦር» ከአጋንንት ጋር እየተዋጉ

የሚያስጥሉን የአምላክ ወታደሮች ካህናት መሆናቸውን ገልጠዋል።

ስለ ደመወዙም ቢሆን ደርሶ ሳይመጣ ሳይሆን ከመጻሕፍት የተገኘ ነው። ዘካርያስ ነቢይ እንኳን «*እመ አሥመርኩከሙ በቅድሜከሙ ድልው ሊተ ሠላሳ ብሩር/ ደስ ብሎኦችሁ እንደሆነ ዋጋዬን ስጡኝ አልሁ* እነርሱም ለዋጋዬ ሠላሳ ብር መዘኑ » በማለት ተናግሮ ነበር። (ዘካ.፲፩፥፲፪)

ፍትሐ ነገሥትን በጎላ በተረዳ ነገር ከላይ የጠቀስነውን ሃሳብ ያጠናክርልናል። «ልጄ ሆይ! የእግዚአብሔርን ቃል የነገረህንና ለሕይወት ምክንያት የሆነህን ካህን ከፊትህ ላብና ከእጅህ ድካም ባገኘኸው በኃይልህ ሁሉ እንደ እግዚአብሔር አክብረው (ርዳው) በማለት ካህንን በማገልገል ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት እንደሚቻል ከገለጸ በኋላ፡- «*ወእም ከመሰ እግዚአብሔር ናሁ ረሰየከ ድልወ ከመ ትንሣእ ለምኔሁ መብልዓ መንፈሳዌ ወሥጋዌ ወሕይወተ ዘለዓለም ወአንተኒ ይደልወከ ከመ ተህቦ ፈድፋደ መብልዓ ማሳኒ ወዘመናዌ* / እነሆ እግዚአብሔር ሥጋዊውንና መንፈሳዊውን ምግብ (ምግበ ሥጋን በጸሎቱ ፣ ምግበ መንፈስን በሥልጣኑ) የዘለዓለምንም ሕይወት ከእርሱ እንድትቀበል ዝግጁ ካደረገህ አንተም ፈጽሞ ጠፊውንና ዘመናዊውን ምግብ ትሰጠው ዘንድ ይገባሃል» በማለት ይደመድማል። (ፍት. ነገ. ሙኃ. ፱፥፫፻፲፱)

ካህናት ማስተናገድ ትልቅ ክብር ነው። ንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማያዊቷ የብርሃን ድንኳን በመዓድ አስቀምጦ ቀርበ የሚያገለግላቸውን ንዑዳን ክቡራን ማገልገልና ማስተናገድ መመረጥ ነው። (ቅዱስ አትናቴዎስ) ያከበራቸውን ሲያከብሩለት ደስ የሚለው እግዚአብሔር ለካህናት በማሰብ አገልግሎትና መስተንግዶን ለሚያደርግ ንዳውን ይሞላለታል። በአመቤታችን ተአምር ላይ የሚከተለው ታሪክ

ተጽፎአል።

ዘወትር ካህናት ቀድሰው ሲወጡ የሚያድሩበትን መክፈልት ወደ አመቤታችን ቤተ ክርስቲያን የሚያመጡ ባልና ሚስት ነበሩ። ባልየው ወርቅ ለማውጣት በመቆፈር ሥራ የሚተዳደር ነበር። ከአስታት በአንድ ቀን በሥራው ላይ ሳለ ዓለት ተንደበት አብረውት ከነበሩት ተለይቶ ጠፋ። ሰዎቹም ፈልገው ሲያጡት ለሚስቱ አለት ተንዶበት እንደሞተ ነገሩአት።

ሚስቱ በባልዋ ሞት ብታዝንም ለካህናት የምትወስደውን ምግብ አልተወችም። ወስዳም ታስቀምጥላቸው ነበር። ሆናም ካህናቱ ምግቡን አያገኙም ነበር። ሴቲቱም የተመገቡ ይመስላት ነበር። ካህናቱ ግን የዘወትሩ መክፈልት የቀረባቸው መስሎአቸው ነበር።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ቆፋሪዎች በአንድ ጉድጓድ አቅራቢያ ሲቆፍሩ ድምጽ ይሰማሉ። ደርሰው ሲመለከቱ ሞተ የተባለው የሴቲቱ ባል እንደዋሻ ባለ ጉድጓድ ውስጥ አገኙት። *እስከ ዛሬ ድረስ ምን እየበላህ በሕይወት ቆየህ* ሲሉት እመቤታችን ሚስቱ ለካህናት የምታመጣውን ምግብ ነሥታ ለእርሱ ትመግበው እንደነበር ነገራቸው። ይህ ሰው ለካህናት ማሰቡ የችግር ጊዜ ስንቅ እንዲሆነው እመቤታችን አስባለት ነበር። (ተአ.ማር ፪፻፸፮)

ሐውጸ ካህናት (ካህናትን መጎብኘት) ለንስሓና ለኃጢአት ሥርየት አጋዥ ነው። ይህች ሴት አጋንንት ሰልጥነውባት እየተሰቃየች ትኖር ነበር። የበቁ (ለቅድስና የደረሱ) ካህናት አይተዋት «የሰው ባሕርይ ጥንቱን ደካማ ነው። ደግሞ በዚሁ ላይ አጋንንት ሰልጥነውባት እንደምን ትሆናለች?» ብለው ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክቱ አጋንንቱ ተሰይተዋት ሲሄዱ አይታለች።

ከዚህ በኋላ እርሷም «ካህናት እዘኑልን ሳይሏቸው ቢያዝኑ (ጻልዩልን ሳይሏቸው ቢጸልዩ) እንዲህ የጠቀሙ እዘኑልን ብለዋቸው ቢያዝኑ እንደምን በጠቀሙ!» ብላ ካህናትን ስትረዳ የምትኖር ሆናለች። ስለዚህ ካህናትን በማገልገል የሚጸኑ ምእመናን የሚያገኙት መንፈሳዊ ዋጋ መኖሩ ግልጽ ነው። በወይን አትክልት የሚመሰሉ ምእመናን ባለቤት እግዚአብሔር ፍሬን ይቀበሉ ዘንድ የሚልካቸውን ባሮች አክብሮ መቀበልና የሚገባቸውን መስጠት እርሱን ማክበር ነው። ባሮቹን መናቅና ማቃለል ግን ባለቤቱን ማቃለል ነው። (ማቴ.፳፩÷፴፫)

ለካህናት የሚሰጥ አገልግሎት ሰው አቅሙ ካለው ሊያደርግ የሚገባው ነው እንጂ ግዴታ ወይም ከካህናት ለሚገኘው አገልግሎት የተተመነ ክፍያ አይደለም። ማንኛውም ምእመን ካህናትን የማስተናገድ እና የማገልገል አቅም ባይኖረውም በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የመኖር ፣ ንስሓ የመግባትና ሥጋው ደሙን የመቀበል ሙሉ መብት አለው። ንስሓ ላለመግባትና ሥጋ ወደሙ ላለመቀበል ይህን እንደ ሰበብ የሚያቀርቡም ልክ እንዳልሆኑም ሊገነዘቡ ይገባል። ከካህናቱም ወገን ምናልባት መንፈሳዊውን አገልግሎት ያለዚህ አልሰጥም ባይ ቢገጥም ጸጋ እግዚአብሔርን በገንዘብ የሚለውጥና በነጻ የሰጠኋችሁን በነጻ ስጡ የሚለውን የጌታ ቃል የዘነጋና የፍቅረ ነዋይ ጸር የጸናበት ነው። ይህ ገለጻ ግን ቤተ ክርስቲያን ለፍትሐት ፣ ለስም ጥሪ ፣ ለሰበካ ጉባኤ አባልነት ወዘተ. የምትጠይቀውን ተመጣጣኝ ያልሆነ አነስተኛ ክፍያ የሚጨምር አይደለም።

ምዕራፍ ሰባት

ካህናትን መገሠጽና መንቀፍ

ከትምህርተ ሃይማኖት አንጻር

በትምህርተ ሃይማኖት ማንንም የመንቀፍ ሥልጣን ለማንም አልተሰጠም በወንጌል «በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በወንድምህ ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ? በዓይንህ ያለውን ምሰሶ አተመለከትምን? ወይም ወንድምህን፦ ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ እነሆም በዓይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ» ተብሎ ተጽፎአል (ማቴ ፯÷፩) ይህም በክርስትና የሌላውን በደል ከመንቀስ የራስን ማንነት መመርመር የሚሻል እንደሆነ ያስረዳል።

የሌላውን በደል የሚቆጥር የራሱን በደል እግዚአብሔር ይቆጥርበታል። «በመስታወት የተሠራ ቤት ያለው ድንጋይ አይወራወርም» እንደሚባለው የራሱን ኃጢአት አስቦ የሌላውን በደል መንቀስ የማይተው ሰው እግዚአብሔር የሰወረለትን ኃጢአት እንዲገልጥበት እየታገለ ነው። አደረጉ ያለውን አድርጎ ፣ ወደቁ ባለበት ወድቆ ፣ የሰዎችን ድካም ተረድቶ ለሌላው መራራትንና ትሕትናን ገንዘብ እስኪያደርግ ድረስ እግዚአብሔር በሠራለው ቁና ይሰፍረዋል። ስለዚህ ሌሎች በኃጢአት ሲወድቁ የሚያይ ሁሉ በእነርሱ የመጣ ፈተና በእኔ ቢመጣ ፣ እነርሱ ባሉበት ቦታ (ማዕረግ) እኔ ብሆን ኖሮ ከእነርሱ

የባስኩኝ እሆን ነበር ብሎ ከመፍረድ ሊቆጠብ ይገባል። በሃይማኖት ሰዎችን በመንቀፍም ሆነ እግዚአብሔር ታግሶ የሸፈነላቸውን ነውር በመግለጥ የሚገኝ ዋጋ የለም። ይህ አንግዲህ ማንኛውም ክርስቲያን ማንንም መንቀፍ እንደማይገባው የሚያስረዳ ነው።።

ካህናተ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ባሉት ምዕራፎች እንደተገለጠው ሥጋ ለባሽ እደመሆናቸው ጸር ጸንቶባቸው ድክመት ሊታይባቸውና ኃጢአት ሊሠሩ ይችላሉ። ይህን ተከትሎ ታዲያ እንደየሁኔታው እርምጃ የመውሰድም ሆነ የመገሠጽ ሓላፊነት በመዐርግ ትይዩ የሆኑ የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው። (ፍት.ነገ ፱፥፫፻፴፱) ሊቃውንትም ቢሆኑ ተገቢውን ርምጃ መውሰድ እንጂ የነቀፋን ቃል መሰንዘር አልተፈቀደላቸውም።

ጌታችን በወንጌል «ዓይንህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ጣላት» ያለው አንድም «ካህንን (ኤጲስ ቆጶስን) የሚያስነቅፍ ነገር ብታገኝበት ሻረው የነቀፍኸውን ሹመህ ኖረህ ኖረህ ኋላ ገህነም እሳት ከምትገባ የነቀፍኸውን ኤጲስ ቆጶስ ሽረህ ኖረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃል» ነው። (ማቴ.፲፰፥፱ ትር) እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ ለክርስትና ልጁ ለቅዱስ ጢሞቴዎስ «ላዕለ ልሂቅ ኢትሰማዕ ውዴተ / ሽማግሌ ላይ ክስ አትቀበል» በማለት በቁሱ ላይ ነገር ሠሪን አንዳይሰማበት (እንዳይቀበል) ነግሮታል። ይህም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በስሞታና በክስ ብቻ ሳይመሩ ነገርን መርምረው እንጂ ደርሰው (ሳይመረምሩ) በካህን ላይ እንዳፈርዱ እንዳልተፈቀደላቸው ያስረዳል። (፩ኛ ጢሞ. ፭፥፲፱)

በመጀመሪያው ምእራፍ እንደተገለጠው ሥልጣነ ክህነት ከሥልጣነ መንግሥት ትበልጣለች። ንጉሥን የሚቃወም ሰው ምንም ልጁ ወዳጁ ቢሆን ቅጣት የሚገባው መሆኑ ግልጽ ነው። እንዲሁም

ካህናትን የሚቃወም ሰው ምን በጎ ምግባር ያለው ቢሆን ከመቀጣት አያመልጥም። ፍትሐ ነገሥት «ወበከመ ክህነት ትትሌዓል እመንግሥት ወከማሁኬ ለዘይትቃረና ለክህነት ይፈደፍድ እምኩነኔሁ ለዘተቃወሞ ለንጉሥ / ክህነት ከመንግሥት እንዲሁም ክህነትን የሚቃወም ሰው ቅጣት ንጉሥን ከሚቃወም ሰው ቅጣት ይበልጣል» ይላል። (ፍ.ነገ.ዜን. ፩፥፱፻፺)

በመዝ.፻፬፥፲፭ «ወኢኀደገ ይስሐጦሙ ሰብአ ወገሠጾ ነገሥተ በእንቲአሆሙ ፤ ወኢትግሥሡ መሲሐንየ ፤ ወኢታሕስሙ ዲበ ነቢያትየ / የቀባኋቸውን አትዳስሱ በነቢያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ ብሎ ሰው ማፍ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም። ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ» ተብሎ ተጽፎአል። እግዚአብሔር የሾምኳቸውን አትዳስሱ ሲል ኃጢአተኞቹንና ክፉ ግብር የሚሠሩትን ለይቶ አይደለም። «የቀባኋቸውን» አለ እንጂ እነ አባ እገሌን እንዲህ ያሉትን እያለ እየመረጠ አይደለም።

ካህናትንም በደል ቢሠሩ ከሾማቸው ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሊፈርድባቸውና ሊያቃልላቸው አይገባውም። ይህንን ማድረግም ለእግዚአብሔር ከራሱ በላይ «አውቅለሃለሁ» ባይነት ነው። ስለዚህ ምእመናን በካህናት ላይ ክፉ ግብርን ቢያዩ እንዲያቃልሏቸው አልተፈቀደላቸውም። ይልቁን እግዚአብሔር በሾመው ላይ እኔ ምን ተገብቶኝ ብለው በትሕትና ሊሰበሰቡና በጸሎት ሊተጉ ይገባቸዋል። ከተቻላቸውም ራስን ዝቅ ከማድረግ ጋር «ምነው አባቴ?» ብለው መጠየቅ ይችላሉ።

ይህም ከራሳችን አቅንተን የምንናገረው የግል አስተያየት ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ነው። ከላይ የተመለከትነውን ቃል የተናገረውን የቅዱስ ዳዊትን ድርጊት በምሳሌነት እናንሣ። ዳዊት

በጠላትነት ያሳድደው የነበረውን ጠላቱን ንጉሥ ሳኦልን ከነ ሠራዊቱ ተኝቶ አግኝቶት ነበር። አቢሳ የተባለው የዳዊት ወታደር ሳኦልን ተኝቶ ባየው ጊዜ ዳዊትን፡- ዛሬ እግዚአብሔር ጠላትህን በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል። አሁንም እኔ በጦር አንድ ጊዜ ከምድር ላጣብቀው ሁለተኛም አያዳገምም አለው። ዳዊም አቢሳን፡- እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን የሚዘረጋ ንጹሕ አይሆንምና አትግደለው አለው። ደግሞም ዳዊት፡- ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር ይመታዋል ወይም ቀኑ ደርሶ ይሞታል። ወይም ወደ ሰልፍ ወርዶ ይገደላል ፤ እኔ ግን እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን እዘረጋ ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ያርቀው አለና ለምልክት የሳኦልን ጦርና የውኃ መንቀል ይዞ ማንም ሳያውቅ ሄዶ ወደዚያ ተሻግሮ ከተራራው ራስ ላይ ሆኖ የሳኦል ባሪያ አበኔርን ጮኸ ጠራው። አበኔር ማን ነህ? ብሎ ሲመልስለትም ሳኦልም በሰማ ጊዜ! በድያለሁ ልጄ ሆይ ዳዊት ተመለስ ዛሬ ነፍሴ በዓይንህ ፊት ከብራለችና። ከዚህ በኋላ ክፉ አላደርግብህም አለው። ቅዱስ ዳዊትም መልሶ እግዚአብሔር በእጁ አሳልፎ ሰጥቶህ ሳለ እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን እዘረጋ ዘንድ አልወደድሁምና ለሁሉ እያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደ ጽድቁና እንደ አምነቱ ፍዳውን ይክፈለው አለው። (፩ኛ ሳሙ ፳፮፥፱-፳፫)

ይህን ታሪክ ከላይ ካህናትን መንቀፍ አይገባም ብለን ያነሣነውን ሃሳብ የሚያጠናክሩ ብዙ ነጥቦችን ይዞአል። ዳዊት ስለ ንጉሥ እንዲህ አለ እንጂ መች ስለ ካህን ተናገረ ቢሉ ከክህነትና ከመንግሥት የቱ ይበልጣል? ብለን እንመልሳለን። ሳያል የተቀባው ሥጋን ሊያስተዳድር ነው። ካህን ግን ነፍስና ሥጋን ሊያስተዳድር ነው ቅቡዕነቱ የእርሱ ይበልጣል።

በዚህ ታሪክ ውስጥ ቅዱስ ዳዊት ከተናገራቸው ሦስት ኃይለ ቃላት የተለያዩ ቁም ነገሮችን መጨበጥ ይቻላል። በመጀመሪያ ወታደሩ

አቢሳ ሳያልን ልግደል ባለ ጊዜ «እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን የሚዘረጋ ንጹሕ አይሆንም» ብሏል። ለዚህም እግዚአብሔር በሾማቸው ላይ ክፉ ቃልን የሚናገር ቅድስናን እንደማያገኝ እንረዳለን። «ሕጅን መዘርጋት መማታትና መግደል እንጂ ክፉ መናገር ነው ወይ?» ተብሎ ቢጠይቅ በመጻሕፍት እንደበት ንግግርን (ቃልን) እጅ ብሎ መናገር ልማድ ነው።

ለምሳሌ የዳዊት ልጅ አቤሴሎም አህቱን ያስነወረበትን አምኖንን በገደለው ጊዜ ከዳዊት ተጣልቶ ተራርቆ ነበር። በኋላ አቤሴሎምን ወደ ቤቱ እንዲመለስ እንዲፈቅድለት ለማድረግ ኢዮአብ እንዲት ሴት ልኮበት ነበር። ይህች ሴት በዳዊት ፊት ቀርባ በፈለጥ ንጉሡን እንድትነግረው አደረጋት። በዚህ ጊዜ በሴቲቱ ንግግር ሊተላለፍለት የነበረውን መልእክት የተረዳው ንጉሥ ዳዊት ኢዮአብ እንደላካት አውቆ በዚህ ሁሉ የኢዮአብ እጅ ከአንቺ ጋር ነውን? አላት ይላል (፪ኛ ሳሙ.፲፬፥፲፱) በዚህ ሥፍራ «የኢዮአብ እጅ» የተባለው የኢዮአብ ንግግር (ቃል) ነው። በሙሴና በአሮን እጅ ሲባል ፤ ወይም በካህናት እጅ ኃጢአት ይሰረያል ሲባል በሙሴና በአሮን ቃል ወይም በካህናት ቃል ማለት ነው። ስለዚህ እጅ የሚለው ቃል «የእንደበትን ንግግርም» ሊተካ ይችላል። በዚህም መሠረት «እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጁን የሚዘረጋ ንፁሕ አይሆንም» የሚለው ቃልም «ክፉን ንግግርን የሚናገር» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ቅዱስ ዳዊት ቀጥሎም እጁን አልዘረጋም ካለ በኋላ ስለ ሳኦል «ሕያው እግዚአብሔርን! እግዚአብሔር ይመታዋል ወይም ቀኑ ደርሶ ይሞታል . . . » ብሎ ነበር። ሳኦል ዳዊት እጁን ስልዘረጋበትም ያሰው በሕገ እግዚአብሔር የሚሄድ ነው ብሎ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለቀባው አክብሮት ነው። ደግሞም እኔ አልደፍረውም እግዚአብሔር ግን ይመታዋል ብሎ ፍርድን ለፈጣሪ ትቶአል።

እግዚአብሔር የሾመው ካህንን ክፉ ሆኖ የሚያዩትም እግዚአብሔር እንደሚቀጣው አውቀው መተው አለባቸው። ዳዊት «እግዚአብሔር የቀባውን ጌታችሁን አልጠበቃችሁምና ሞት ይገባችኋል» በማለት የሳኦልን ባሮች እንደ ገሰፀ ከርስቲያኖች የአባቶቻቸውን የስዩማን ካህናት ክብር ተግተው የማይጠብቁ ከሆኑ እንደ ዳዊት ካሉ አማንያን ይቅርና በአሕዛብም ዘንድ ለነቀፋ ይጋለጣሉ። በስተመጨረሻው ዳዊት እጁን ልዘረጋ አልወደድሁም እግዚአብሔር ለሁሉ እንደ ጽድቁና እንደ እምነቱ ፍዳውን ይክፈለው በማለት ነገሩን ፈጽሞአል ፤ ምዕመናንም ምንም በካህን ላይ ክፉ ቢያዩና በካህን ክፉ ቢደርስባቸው ዕደ ልሳናቸውን (የአንደበት እጃቸውን) ባለመዘርጋት ሁሉ እንደ ምንባሩና እንደ ሃይማኖቱ መጠን ፍዳ እንደሚጠብቀው በማወቅ ሊታገሡ ይገባቸዋል።

ንዋየ ጎሩይ (ምርጥ ዕቃ) የተባለ ቅዱስ ጳውሎስ በአንድ ወቅት ሊቀ ካህናቱን (የብሉይ ኪዳን)፦ አንተ በኖራ የተሰሰነ ግድግዳ . . . » ብሎ ገሥጾት ነበር። በዚህን ጊዜ በአጠገቡ የቆሙት፦ የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህናት ትሳደባለህን? አሉት ቅዱስ ጳውሎስም «*ሊያእመርኩ ኦኃውየ ለእመ ሊቀ ካህናት ውእቱ ፤ ወይብል መጽሐፍ ኢታሕስም ጫቢ መኰንን ሕዝብ* ወንድሞች ሆይ ሊቀ ካህናት መሆኑን ባላውቅ ነው። በሕዝብ አለቃ ላይ ክፉ ቃል አትናገር» ተብሎ ተጽፎአልና በማለት መልሷል (ዘጸ.፳፪፥፳፰ ፤ ሐዋ.፳፫፥፭) የሐዲስ ኪዳን ካህን ሐራሴ ወንጌል (የወንጌል ገበሬ) የሆነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለኦሪት ሊቀ ካህናት ክብር «ባለ ማወቁ ተናገርሁ» ካለ በካህናተ ሐዲስ ላይ ነቀፋን መናገር እንዴት ያለ አለማወቅ ይሆን!?

በካህናት ላይ የስድብን ቃል መናገር በሸማቸው በመንፈስ ቅዱስ ላይ መናገር ነውና ቀኖናው ጽኑዕ ነው። ክብር ይግባውና

መንፈስ ቅዱስን ስለመስደብ የተነገረው ኃይለ ቃል ከዚህ ጋር ተያይዞ ይተረጎማል። «ሕዝባዊን የስድብ ኃጢአቱ ይሠረይለታል ፤ ኤጲስ ቆጶስን (ካህንን) የሰደበ ግን አይሠረይለትም» በማለት በካህን ላይ በድፍረት የሚናገር እንደምን ባለ ጽኑዕ ፍዳ እንደሚያዝና ያለ ጽኑዕ ቀኖናም እንደማይሠረይለት ያስረዳል። (ማቴ.፲፪፥፴፪)

ይህን ሀሳብ በእመቤታችን ተአምር ላይ ተጽፎ እናገኘዋለን። በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ የሚቀድሰውን ካህን በድፍረት የተሳደበን አንድ ሰው አስመልክቶ በተጻፈበት አንቀጽ «እግዚአብሔር በሾመው ካህን ላይ የስድብን ቃል ሲናገር የሰሙት ሁሉ ተንቀጠቀጡ መንፈስ ቅዱስን የሰደበ አይሰረይለትም የተባለው ታወቀ ተረዳ» ይላል። (ተአ.ማር.፲፫፥፴) ፍትሐ ነገሥትም «በኤጲስ ቆጶሱ ላይ ክፉ ቃልን የሚናገር እነሆ እግዚአብሔርን በደለ ፤ በአማልክት ላይ አትናገሩ ያለውን አልሰማችሁምን? ስለ ጣዖቱ የተባለ አይምሰልህ ስለ ካህናትና ስለ ዳኞች እንጂ /መዝ.፹፩፥፮ ፤ ዘጸ.፳፪፥፳፰) ሕዝባዊውን (ጨዋውን / ምእመኑን) አንተ ከእርሱ ወይም ስነፍ የሚለው በቅጣት የማይድን ከሆነ ይህ ተግዳሮት በክርስቶስ ላይ ነው። በአንበሮተ ዕድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን በሰጣችሁ በኤጲስ ቆጶስ ላይማ ይህን የተናገረ እንዴት ይሆን?» በማለት ያብራራዋል (ፍት.ነገ.መ.፱፥፫፻፲፫)

ብዙዎች በካህናት ላይ የማይገባ ንግግርን እየተናገሩ ከካህናት የሚገኘውን አገልግሎት ግን ይፈልጋሉ። አለቃ ጎሩይ ወልደ ሥላሴ «ለእባት መታሰቢያ ለልጅ ምክር» በሚል መጻሐፋቸው «ካህኑን አትንቀፍ ከነቀፋቸው አስተምረኝ አጥምቀኝ አቁርበኝ አትበለው» ያሉት እንደዚህ ላሉት ነው። ዛሬ በካህናት ላይ አፋቸው ያመጣላቸውን የሚናገሩ ኋላ በሞቱ ጊዜ በዕደ ካህን እንደሚወድቁ መዘንጋት የለባቸውም። «*ዘይኤብስ ቅድመ ፈጣሪሁ ይወድቅ በዕደ ዐቃቤ ሥራይ*»

አባቶች ካህናትን መንቀፍ በአባትነታቸው አለማመንን ያሳያል። መምህራን ቤተ ክርስቲያን ካህናት ምእመናንን በትምህርት የሚወልዱ ከሥጋ አባት የሚበልጡ የነፍስ አባቶች ናቸው። ታዲያ በካህናት ላይ ነቀፋንና ስድብን የሚናገር ሰው በአባትነታቸው የማያምን ነው። ምክንያቱም ሰው እንኳን የመንፈሳዊ አባቱን በሥጋ የወለደው አባቱን ነውር እንኳን በአደባባይ ለመግለጥ አይሻም። በመጽሐፍ እንደምናነበው የካም ልጅ ከነዓን የተረገመው ካም የአባቱን የኖኅን ራቁትነት ለወንድሞቹ በመናገሩና በመሳለቁ ነበር ፤ ሴምና ያፌት ግን የአባታቸውን ዕርቃን ላለማየት የኋሊት ሄደው ሸፍነውታል። በዚህም ክብርን አግኝተውበታል ፤ ዛሬም ከብቃት ደርሰን ጳድቁን ከኃጥኡ ለይተን ማየት የሚቻለን ቢሆንና ከጸጋ እግዚአብሔር በኃጢአት ምክንያት የተራቆተ መንፈሳዊ አባታችንን ማየት ብንችል ከመግለጥ ይልቅ ዕርቃኑን በመሸፈን የበለጠ ክብርን እናገኛለን ፤ ከዚሁ ታሪክ ሳንወጣ ኖኅ የካምን ጥፋት ባወቀ ጊዜ ርግማኑን የጀመረው በካም ሳይሆን በካም ልጅ በከነዓን ነው። የዚህም ምክንያቱ ካም ተመርቆ ስለነበር እግዚአብሔር የመረቀውን መርገም ስለማይቻል ነው። (ዘፍ.፱፥፳-፳፭)

በቀናች ሃይማኖት እስካሉ ድረስ አባቶቻችንን በምግባር ደከሙ ብለን መንቀፍ አልተፈቀደልንም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በተግሳጽ *«ሊይደሉ ንሕንን ካህናተ በእንተ ገድሎሙ ወመንፍዓትው ለነ ንጉዮይ አምኔሆሙ»* / ገድል ፈቱ ብለን ካህናትን መንቀፍ አይገባም። እሊህን ከመንቀፍ እንለይ ዘንድ ይገባል እንጂ ብሏል። (ተግሣጽ ፴፬) እንዲያውም አንድ ሰው አባቶች በአገልግሎታቸው ያልተገባ ነገር ቢያይባቸው ዝም ብሎ እንዲጸልይላቸው ያን ማድረግ ባይቻለውና አንደበቱን መቆጣጠር ቢያቅተው ግን ሀገር ሰቶ እንዲሸሽ ይመክራል ፤

እንድተጻፈ፦

«ወአንተሰ ሕዝባዊ አልብከ ሥልጣን ከመ ትኅንኖ ለኅሀን በእንተ መሥዋዕት አላ ሰበ ትሬእዮ ይገብር ከመዝ ጕየይ ጥበ ካልእ መካን ወኢትቅንኖ» / ሕዝባዊ ሆይ! አንተ ግን ስለ መስዋዕት አቀራረብ (መስዋዕት ቢሉ ብዙ ወገን አለ) ካህኑን ትነቅፈው ዘንድ ሥልጣን የለህም ፤ ካህኑ እንዲህ ያለ ሥራ ሲሠራ ብታየው ሸሽተህ ወደ ሌላ ቦታ ሂድ እንጂ አትንቀፈው ፤ አትዝለፈው» (ሃይማኖተ አበው ዘሮቱ ምዕት፡ ፳፱፤፲፪) ይህ ቃል በእውነት ትልቅ መልዕክት አለው። አባቶች በዋሉበት እየዋሉ ባደሩበት እያደሩ ነውራቸውን ከመቁጠር መሸሽ ይመረጣል።

አባቶችን በመዝለፉና በማማቱ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ተጎጂ ሕዝቡ ራሱ ነው። ይህ በቅዱስ ዲሜጥሮስ ታሪክ ታውቆአል። ቅዱስ ዲሜጥሮስ መስተገብረ ምድር (ገባሬ) ነበርና ዕርፍ አርፎ ዲኮ ታጥቆ ይኖር ነበር። የአንቱ ልጅ እናት አባቷ ሞተው ከእርሱ እናት አባት ጋር ትኖር ነበር። ዘመናቸው ዓላውያን የበዙበት ክርስቲያኖች ያነሱበት ነበር። ሁለቱም ለአቅመ ውርዛዌ ሲደርሱ ሕንጻ ሃይማኖት ከሚፈርስ (ከዓላውያን ከሚጋቡ) ሕንጻ ሥጋ ይፍረስ (ከሥጋ ዘመድ ይጋቡ) ብለው አጋብተዋቸው ሥርዓተ መርዓዊ ወመርዓት ያድርሱ (የሙሽራ ሙሽሪት ልማድ ይፈጽሙ) ብለው መጋረጃ ጥለውባቸው ወጡ።

እርስዋ «ወንድሜ ይህን ሥራ የሠራኽውን እኔን ንቀህ ነው ወይስ ተዘምዶውን (ዝምድናውን)» አለችው። እርሱም «አንቺንም ተዘምዶውም ንቁ አይደለም የእናት አባትን ፈቃድ ማፍረስ ይሆንብናል ብዬ ነው እንጂ አላት አሁንስ ፈቃድሽ ከሆነ አንተወውምን?» አላት «እሺ» አለችው። «እንኪያስ አንቺንም ለሌላ እኔንም ለሌላ እንዳያጋቡን በአንድ እንኑር» አላት። ከዚያ በኋላ «ጌ ዘመን አንድ ልብስ ለብሰው

በአንድ ምንጣፍ ተኝተው ይኖሩ ነበር። ረድኡተ እግዚአብሔር ጠብቋቸው መልአከ እግዚአብሔር ከልሏቸው ኖሩ።

ያን ጊዜ ዮልዮስ (ዮልያኖስ) የተባለ የማርቆስ ፲፮ኛ ሊቀ ጳጳሳት ነበር። ሕዝቡን ሰብስቦ «እኔ አረጀሁ ቀጥሎ የሚሾምላችሁን ምረጡ» አላቸው። ሕዝቡ «አባታችን፡ አንተ አዘንህ ተክዘህ (ወደ እግዚአብሔር አመልክተህ) ንገረን እንጂ» አሉ። «በሉ እናንተም እዘኑ እኔም አዝናለሁ» ብሎአቸው ሱባኤ ገባና መልአኩ «ያለ ጊዜው ያፈራ ሦስት የወይን ዘለላ ያመጣልሃልና ከአንተ ቀጥሎ የሚሾመው ያ ነው» አለው።

ይህ ዲሜጥሮስ ወይኑን ለማቃናት ከአታክልቱ ቢገባ ያለ ጊዜው ያፈራውን የወይን ዘለላ አግኝቶ ወስዶ ለሚስቱ ሰጣት ፤ እርስዋም «ይህንስ እኛ ልንበላው አይገባንም ወስደህ ለሊቀ ጳጳሳቱ ሰጥተህ አቡነ ዘበሰማያትን ተቀብለህበት ና!» አለችው። እርሱም ወስዶ ለሊቀ ጳጳሳቱ አበርክቶ ሲመለስ ሊቀ ጳጳሳቱ «ከእኔ ቀጥሎ የሚሾመው ይህ ነው ነገር ግን አይሆንም ይላችኋልና ግድ ብላችሁ ሹሙት» አላቸው። ወዲያው አልሰነበተም ሊቀ ጳጳሳቱ ዐረፉ።

እርሱን ቀብረው «ወንበር አለ ሹም አያድርምና ተሾምልን» አሉት። እርሱም «ንጹሕ ድንግል በሚቀመጥበት ወንበር እንደእኔ ያለ ሕጋዊ (ያገባ) ፤ ወዲህም ያልተማርኩ ስሆን እንዴት እሾማለሁ?» ብሎ አይሆንም አላቸው። እነርሱም «አባታችን ነግሮናል አይሆንም ተሾምልን» አሉ። «እንግዲያውስ ሕጉን ሥርዓቱን ንገሩኝ» አላቸው። «አልተማርኩም ብትለን ነውንጂ አባታችንስ አንቀጸ ብፁዓንና አንቀጸ አላግዕን ተርጉሞ ይነግረን ነበር» አሉት። ወዲያው ያልተማረው አንቀፀ ብፁዓንና አንቀጸ አላግዕ ፤ ብሉይና ሐዲስ ተገልጸለት አስተምሯቸዋል።

ሕዝቡ ሊቀርቡ ሲመጡ ኃጢአታቸው ተገልጾ እየታየው አንተ

ቆይ አንተ ቁረብ ይል ጀመር። ሕዝቡ ግን በንጹሑ በማርቆስ መንበር መቀመጥ አንሶት አንተ ቆይ አንተ ቁረብ ይል ጀመር እያሉ በሐሜት የሚጎዱ ሆኑ። መልአኩ «ሊትፍቅድ አድኅኖ ርእስከ አላ ክሥት ዘሀሉ ምስሌከ ወማእከለ ብእሲትከ / በአንተና በሚስትህ ያለውን ግለጥ እንጂ ራስህን ማዳንን አትውደድ።» አለው።

እርሱም ሕዝቡን ዕንጨት ይዘው እንዲሰበሰቡ በአዋጅ ነግሮአቸው ይዘው ተሰበሰቡ ፤ ያንን እንደ መስቀል ደመራ ደምሮ ቅዳሴ ገባ። ከዚያ ወጥቶ አቃጥሎ በውስጡ እየተመላለሰ ያጥን ጀመር። ሚስቱን ከምቅዋመ አንስት (ከሴቶች መቆሚያ) አስመጥቶ «ለፍሐ ለጸፈኪ / መጎናጸፍያሽን ዘርጊ» ብሎ ከፍሕሙ እያፈሰ ከልብሷ ላይ አደረገላት። ሕዝቡን ዞራ ብታፍሰው ከልብሷ አንድ ስንኳ ሳይጠቁር ተገኝቷል።

«አባታችን እንዲህ ያለውን ሥራ የሰራኽው በምን ነገር ነው?» አሉት።«እኔ እከብርበት እሾምበት ብዬ አይደለም እናንተ በሐሜት የምትጎዱ ብትሆኑ ግለጽላቸው ብሎኝ ነው እንጂ እርሷ ሴት እንደሆነች እኔም ወንድ እንደሆንኩ እስከ ዛሬ በግብር አንተዋወቅም» አላቸው። በዚህ ጊዜ «ኦ አቡነ ሥረይ ለኑ» ብለው ከእግሩ ሥር ወደቁ እርሱም «ይፍታሕ ወይሥረይ ይጎድግ ወያንጽሕ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ» ብሎ አስተስርዮላቸዋል። ኑዛዜ ሥርየት በዚህ ጊዜ ተጀምሯል ይላሉ።

«እኔ እከብርበት እሾምበት ብዬ አይደለም እናንተ በሐሜት የምትጎዱ ብትሆኑ ግለጽላቸው ብሎኝ ነው» የሚለው ቃል አባቶችን በማማት ምን ያህል ሕዝቡን እንደሚጎዳ ያስረዳናል።

በመዝ.፴፫ ÷ ፲፪-፲፫ላይ፡- በጎ ዘመንን ለማየት ብትወድድ . . . አንደበትህን ከክፉ ከልክል» ተብሎ ተጽፎአል። በትርጓሜው ላይ

አንደበትህን ከክፉ ከልክል የሚለው ቃል «ንጉሥን ጳጳስን ከማማት ከልክል» በሚል ተተርጉሞአል።

ከዚህም ባሻገር ምእመናን የሚያሙት ካህን ምናልባት እነርሱ እንደሚገምቱት በደለኛ ላይሆንም የሚችልበት ሁኔታም እንዳለ እንረዳለን። ቅድስናውን ሰውሮ በትሕትና የሚኖር ፣ ሰው ሳያየው የሚተጋና የሚያነባ ነገር ግን ስሙ በበጎ የማይነሳ ካህን ሊኖር ይችላል። በደለኛስ ቢሆን ሲሠራ ስላዩት በደል ፈጥኖ ንስሐ ገብቶ እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎለት እንደሆነስ? ማን ያውቃል!

ሦስት ጊዜ የካደውን ቅዱስ ጴጥሮስን ዳግመኛ ምሕረት አድርጎ ምእመናንን አደራ ሰጥቶት የለ?! ፣ ፍቅሩን መማለጃ አድርጎስ ሾሞት የለ!? ፣ታድያ ይህን በደለኛ ካህንስ ከጭቃ የወደቀን ዕንቁ ወልውለው ለንግለው ከቦታው እንዲያኖሩት ንስሐውን ተቀብሎ ንጹሕ አድርጎት እንደሆነስ ምን ይታወቃል? ስለዚህ ምእመናን በካህን ላይ ክፉ ቢያዩና ቢሰሙም የውስጥ የአፍአን በሚያይ ለእግዚአብሔር ሊተዉ ይገባል።

እግዚአብሔር ካህኑን ቢቀጣው እንኳን በምእመናን ፊት በግልጥ አይደለም። ወንድማቸው ሙሴን አብረው ያሙት የማርያምና የካህኑ አሮን ነገር ለዚህ አይነተኛ ምሳሌ ነው። ማርያምን በለምጽ ኖራ እስክትመሰል ያነደዳት እግዚአብሔር አሮንን ግን የቀጣው በውስጥ ነበር። ምክንያቱም ካህንን በተገለጸ ነገር በሕዝብ ፊት ይቀጣው ዘንድ ስላልወደደ ነው።

በሃይማኖተ አበው ቃለ ግዝት ላይ ቅዱስ ዮሐንስ ዘቡርልስ ካህናትን ከመንቀፍ ጋር በተያያዘ ጠንካራ እውነትን ያዘለ ሃሳብን አስፍሮአል «የቀና ሃይማኖት ያለው ኤጲስ ቆጶስ የለም ፣ ቂስም የለም ፣ ዲያቆንም የለም የሚል ቢኖር ውጉዝ ይሁን» ይላል። ይህን ተግባር

ይህ አባት «ጥምቀት የለም ፣ ሥጋወ ደሙም የለም ፣ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አልፋለች» ከማለት ጋር አነጻጽሮታል። ክነባራዊው ሁኔታ ጋር አዛምደን ስንመለከተው የዚህ አባት ንግግር ልክ እንደሆነ እንረዳለን።

አንዳንዶች «አባቶች የሉንም፣ ድሮ ቀሩ...» ወዘተ እያሉ ባልተሰጣቸው ሚዛን ቤተ ክርስቲያንን ሲመዝኑ ይታያሉ። ክፉም ሆኑ ደግ አባቶች የሚሾሙት በፈቃደ እግዚአብሔር ብቻ ነው። (ሳኦልንም ዳዊትንም የሾመው እግዚአብሔር ነውና።) ታዲያ የተሾሙና የሚሾሙ አባቶችን ሹመታቸው በሰው ፈቃድ የሆነ ይመስል ልክ አይደለም እስከ ማለትና ሌሎችንም እስከ ማሳመን የሚደርሱ ሰዎች አሉ። ክፍ ሲልም መስቀሉ የክርስቶስ መሆኑን በመዘንጋት የእነ "እንጨን መስቀል አትሳለሙ ፣ አትቀበሉአቸው! እስከ ማለትም የሚደረስበት ጊዜም አለ።

ይህን ድርጊት በመጽሐፈ ኪዳን ላይ የሚነገር አዋጅ በምሥጢር ያነሳዋል። «ነቢያትን የሚያቃልል ቢኖር ክወልድ ዋሕድ መዓት ራሱን ያርቅ መስቀልን አይበድል!» በማለት፤የዚህ አዋጅ ትርጉም የተናገሩትን መንቀፍ አድሮ ያናገራቸውን መንቀፍ ነውና ማንም አባቶችን አይንቀፍ «ነዋ መስቀለ ሰላም» ብሎ ቄሱ መስቀል ባቀረበለት ጊዜ አክብሮ ይሳለም የሚል ነው።(ቅዳሴ እግዚእ)

የአባቶች ሹመት አይሰራም የሚለው አባባል በቀላሉ የሚታለፍ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕልውና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው ነው። ምክንያቱም ይህ ማለት እሊህ አበው ከተሾሙበት ጊዜ ወዲህ ማዕረገ ክህነትን የተቀበሉ ከዲያቆናት እስከ ጳጳሳት ያሉ ካህናት ሁሉ ሥልጣናቸው ሥልጣን አይደለም እንደማለት ነው። ይህ ደግሞ «ሹመታቸውን አትቀበሉ» በተባሉት አባቶች ዘመን የተጠመቁ ሕጻናትና ሥጋ ወደሙን የተቀበሉ ምእመናን ሁሉ እንዳልተቀበሉ እንዳልተቆመቁ

፣ በተክሊል የተጋቡትም ጋብቻቸው እንዳልጸና ያስቆጥራል። ይህ ማለት ደግሞ ቅዱስ ዮሐንስ ዘቡርልስ እንዳለው «ኦርቶዶክስ ሃይማኖት አልፋለች» እንደማለት ነውና የተወገዘ ሃሳብ ነው።

በዚህ ጽሑፍ መቅድም ላይ እንደገለጥኩት ካህናትን መንቀፍ አስመልክቶ የሚነሳው ሃሳብ የማይዋጥላቸው ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እንዲያውም «ያልተነካ ግልግል ያውቃል ፥ ስላልደረሰበት ነው . . . » የሚል አስተያየት የሚኖራቸውም እንዳሉ አውቃለሁ። ይሁንና ካህናትን መገሠጽ ለሁሉም፤ መንቀፍ ደግሞ ለማንም አይገባም የሚለውን ሃሳብ አጽንኦት የምሰጠው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በካህን ድክመት ተሳሂ ሳልሆን ወይም ቅር የሚያሰኙ ነገሮች ሳይገጥሙኝና ሳላይ ቀርቼ አይደለም። ነገር ግን የግል አመለካከትንና የቤተ ክርስቲያን ትምህርትን በማስተላለፍ መካከል ሰፊ ልዩነት አለ። በዚያ ላይ ካህናትን የመተቸት መብት በር በትንሹም ቢሆን ከተከፈተ መዘዢያ የሌለውና አደጋው የከፋ ነው።

«አባቶች ይህን ይህን አያደረጉ . . . » የሚል ክርክር ለሚያነሡ ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ለአንድ ተቀርቋሪ መሳይ መናፍቅ ምላሽ በሰጠበት ርቱዕ መጽሐፋቸው ላይ ያነሱትን ሃሳብ ደግሜ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ፦

«እኔ መልስ የምሰጥህ ስለ ሃይማኖትና ስለ ምግባር ስለ ሕግ ብቻ እንጂ ስለ አያንዳንዱ ሰው ተግባር አይደለም። ስንኒንስ በማላውቃቸው ሰዎች ተግባር ገብቼ ፈጸሙ አልፈጸሙም ብዬ መልስ ልሰጥ ፣ እኔንም ራሴን ሕግ አፍራሽ ነህ ብትለኝ አምን ኃጢአተኛ ነኝ ከማለት በቀር የምሰጥህ መልስ የለኝም!!!» ክኮሐ ሃይማኖት

ባለንበት ዘመን ካህናትን መንቀፍ ከመጠን በላይ የተስፋፋበትና «ይህ ወቅት በሐሳዊ መሲሕ ጊዜ ለሚፈጸመው ፣ቅትለተ ዘካርያስ፤ /የካህኖት መገደል/ ዋዜማ ይሆንን?» የሚያሰኝ ነው። ካህናትን

የሚያቃልሉ ቃላትንና ሃሳቦችን በየቀልዶችና በተውኔቶች ላይ መስማት እየተለመደ መጥቶአል።

ይህን የሚያደርጉ ሰዎች ምእመናን ከሆኑ «በአባትዋ የምታላግጥ የእናትዋንም ትዕዛዝ የምትንቅ ዓይን የሸሰቀ ቁራዎች ይነጠጡአታል።» በማለት በተነገረው ቃል መሠረት ከሥጋ አባት አልፈው በመንፈሳዊ አባታቸው የሚያላግጡና የእናታቸው ቤተ ክርስቲያንን ትእዛዝ የሚንቁ በመሆናቸው በሲያል አበጋዞች በአጋንንት እጅ ይወድቃሉ። (ምሳ.፴፥፲፯)

ዓለማውያን በአባቶች እንዲያፌዙ ያደፋፈራቸው የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮችና ምእመናን ስለ አባቶቻቸው የማይቆጩና አብረው የሚስቁ ሆነው ቢገኙ ነው። ምእመናን በሥጋ ለወለዷቸው አባቶቻቸው የሚቆጩትን ያህል ለመንፈስ አባቶቻቸው መቆርቆር ባይወዱ ነው። «ባለቤቱን ያቀለለውን አሞሌ ባለ ዕዳ አይቀበለውም» እንዲሉ (ካህናት ከአሞሌ አይከብሩምን?) የምእመናን ልልነት ዓለማውያኑ የማይደፍሯቸውን ካህናት ደፍረው እንዲያፌዙ መንገድ ይከፍታል፤። ቀድሞ «ይህስ የዚህኛውን የሃይማኖት ተስታዮች ክብር ይነካል» እየተባለ ይቆረጥ የነበረው ቃለ ተውኔት ዛሬ ያለ ከልካይና ያለ መሰቀቅ በአደባባይ መሰማቱ የሕዝቡን እና የአገልጋዮችን ለዘብተኝነት ተገን አድርጎ ነው።

አባቶችን ከማማት ባሻገር በግልጽ የሚሳደቡና የሚያቃልሉ ሃይማኖታዊ ፋይዳ የሌላቸው መጻሕፍት ፣ ኦርቶዶክሳዊ ላህይ (ለዛ) *የሌላቸው፣ በመናፍቃን ቋንቋ የተዋዙ፣ ነቀፋን የተሞሉ* ስብከቶች ትችቶች በልዩ ልዩ የመገናኛ ዘዴዎች እየተሰራጩ ከፍተኛ ተቀባይነትን እስከ ማግኘት መድረሳቸውም የትውልዱን የሥልጣነ ክህነት ግንዛቤ ከጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው። እነዚህን መሰል ጽሑፎች ከየትኛውም

አቅጣጫ ሆነን ብንመለከተውቸው ለምእመናን መንፈሳዊ ሕይወት የሚሰጡት ምንም ጥቅም የለም።

አንዳንድ ሰባክያንና አገልጋዮች በቅድስት ቤተ ክርስቲያን መድረክ ሳይቀር ካህናትን እየነቀፉ ሲያስተምሩ ይታያል። ይህ ድርጊት በመጀመሪያ የቆሙበትን ቤት ምሰሶ ለማፍረስ እንደመነቅነቅ ይቆጠራል። ምክንያቱም ጥበብ ኢየሱስ ክርስቶስ በቤቱ በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ያቆማቸው ሰባቱ አዕማድ በሰባቱ ማዕርጋተ ክህነት ያሉ ካህናት ናቸውና። (ምሳ.፱÷፩ ትር) ታዲያ በክብር መድረኳን ሰጥታ ያቆመቻቸው አንዳንድ ሰባክያን በወውደ ምሕረቷ ቆመው ከምሰሶዋ ጋር መታገላቸው የሚደገፍ አይደለም። ከጉባኤ ባይውሉ ምሥጢር ባያደላድሉ ነውም ያሰኝባቸዋል። ለዚህ ተግባራቸው የሚጠቅሱት የመጥምቁ ዮሐንስን የድፍረት ተግሣጽ ነው። ይሁንና መጥምቁ የገሠጸው የጉዳዩን ባለቤቶች በቀጥታ እንጂ ለማይመለከታቸው ሰዎች በማወጅና በመቀስቀስ አልነበረም። በዚያም ላይ መጥምቁ ምን ዓይነት ሕይወት ነበረው የሚለውም መታሰብ አለበት።

ከዚህም አልፎ «ወገዱሂ ከመ ራእየ መብረቅ / ፊቱም እንደ መብረቅ ምስያ ነበር» ተብሎ የተነገረላቸውን የእግዚአብሔር ፊቶች እንደ መብረቅ የሚያስፈሩ የቤተ ክርስቲያን ግርማዎች ጳጳሳትን ያለ ፍርሃትና መሰቀቅ በግልጥ በአደባባይ እስከ መዝለፍ መድረስ እግዚአብሔርን አለመፍራት በደሙ የዋጃት ቤተ ክርስቲያንንም መናቅ ነው። እርግጥ ነው በዚህ ድርጊት በአላዋቂዎች ዘንድ «ደፋር ነው / ልክ ልካቸውን ነገራቸው» የሚል ሙገሳና ስምን ማግኘት ይቻል ይሆናል። ነገር ግን መንፈሳዊ ዋጋን ማግኘት አይቻልም። ምክንያቱም በየትኛውም የገድል መጽሐፍ አባቶች ካህናትን አቃሎ ቅድስናን ያገኘ የለምና።

ደግሞም የሰባኪ ዓላማው ተወዳጅነትንና አድናቆትን ማትረፍ አይደለም።«አድማጮችን እገሌ ታዋቂ ሰባኪ ነው በሚያሰኘው ስብከትና ንስሓ ልንገባ እንፈልጋለን... በሚያሰኘው ስብከት መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ፤ዋናው ቁም ነገር ራሱን ሰባኪ፤መምህር -ማድረግ- አይደለም፤ትክክለኛው ዓላማ ነፍሳትን ማዳን ነው።የተዋጣለት ሰባኪ የሚባለው ነፍሳትን ለእግዚአብሔር የሚያሰባስበው እንጂ ከአድማጮቹ ውዳሴን የሚያሰባስበው ሰባኪ አይደለም።» (መንፈሳዊ ውሂያዎች)

አንድ ሐኪም አንድን በሽተኛ ከሕመሙ እንዲድን ሊያደርገው የሚችለው የታማሚውን ውስጣዊ ሕመም እየመረመረ ነው እንጂ የሌሎችን በሽታ እየነገረ አይደለም። ሰባኪውም ምዕመናንን ከኃጢአት ሕመም ሊፈውሳቸው የሚችለው በቃለ እግዚአብሔር ሕይወታቸውን በመመርመር ነው እንጂ የአባቶችን ኃጢአት በመንገር አይደለም። ቤተ ክርስቲያን መድረኩን የሰጠችው ምእመናንን ለንስሓ እንጂ ለሐሜት እንዲያበረታታ አይደለም። ብሶትም ካለ በወንጌል አገልግሎት ወቅት ሊቆጣጠሩት የሚገባ ነው። የቤተ ክርስቲያን ዐውደ ምሕረትም የግል አመለካከትና ስሜት የሚንጸባረቅበት አይደለም።

አባቶችን በመንቀፍና በአደባባይ በማዋረድ መገሥጽ ፣ ጥቡዕ የሆኑ ፣ ተጋድሎን የፈጸሙ ፣ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የቀኑ የሚመስላቸው የዋሃንም አሉ። ነገር ግን አባቶችን ከመንቀፍ ራስን መንቀፍ የሚበልጥ ዋጋ አለው። ይህ ማለት ግን የሚገባቸው መምህራን ቤተ ክርስቲያን ከላይ እንደተገለጠው ካህናትን መገሠጽ የለባቸውም ማለት አይደለም። ነገር ግን ተግሣጽ የሚደረገው ሊገሠጽ በሚገባው ካህን ፊት ለፊት እንጂ ለማይመለከታቸው ለሌሎች በማወጅ አይደለም። ይህንን ማድረግ ቤተ ክርስቲያንን ሰድቦ ለሰዳቢ መስጠት ነው።

የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ

በአንድ ወቅት የተናገሩትን ንግግር ለዚህ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። ከዝዋይ ሐመረ ናኅ የካህናት ማሠልጠኛ ዕቃ ሠርቆ የጠፋን አንድ ወጣት አሳድደው የያዙ ደቀ መዛሙርት ለፖሊስ አንስጠው ሲሏቸው፡- «አርቶዶክሳውያን ተሰራርቀው ተካስሰው መጡ ይበሉን ወይ?» በማለት ሌባውን በነጻ ለቅቀውታል። ከእኅህ ደገኛ አባት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ምን ያህል ገመና ከታች መሆን እንደሚገባቸው መማር ይቻላል።

ምእመናን ስለ አባቶቻቸው ስለ ካህናት መጸለይ ይገባቸዋል። ያለ ካህናት የሚሆን ነገር የለምና። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ካህናት አባቶች ይተለዩትን ሕዝብ «ንጉሥ ሌላው ሠራዊት ፣ ቀዛፊ በሌለው መርከብ» ይመስለዋል። «ሠራዊት ያለ ንጉሥ በሥርዓት እንደማይጸና ለሊቀ ጳጳሳት የተለየ ምዕመንም በሥርዓት አይጸናም ፣ ቀዛፊ የሌላት መርከብ እንደምትሰጥም አበው መምህራን ጳጳሳት ወራት ዘመን (ጊዜ) ከሕዝቡ ከለያቸው ሕዝቡ በነፍስ በሥጋ ይጎዳል» በማለት ያብራራዋል (ድርሳን ካ4) በታሪክ ካህን አጥተው ቤተክርስቲያንን የሚያገለግል ፣ቀድሶ የሚያቆርባቸው ፣ የሚያጠምቃቸው አጥተው እያነቡ ቤተ ክርስቲያንን ይዘሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩም አይዘነጋም። (የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ)

እኛ ግን ክብር ይግባውና አባቶች አሳሳጣንምና አክብረን ልንይዛቸው ይገባል። አባቶች ባይኖሩ ምን እንሆን ነበር? ማለትም ይገባል። *«ወሶበ አኮ እግዚአብሔር ጸባኦት ዘአትረፈ ለነ ዘርዓ ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ አመሰልነ / ጌታ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን እንደ ገሞራም በመሰልን»* እንዳለ ነቢዩ (ኢሳ.፩፥፱) አበው ካህናትን እግዚአብሔር ያስቀረልን ባይሆን ሰዶምና ገሞራ የሚያስተምራቸው የሚመክራቸው አጥተው እንደጠፉ በጠፉን ነበር።

እንኳን ያሉትን መቃወም ዓረፍተ ዘመን ገትቷቸው በሞቱ ጊዜ እንኳን በመንበራቸው እግዚአብሔር እንዲተካ የምንጸልየው የአበው ሕልውና የምዕመናንና የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሕልውና ስለሆነ ነው። ጳጳስ በሞተ ጊዜ «አ እግዚኦ አእርፍ ነፍሰ አቡነ እገሌ» ተብሎ ከተጸለየ በኋላ *«ኦ እግዚኦ አንብር ለነ ዲበ መንበሩ ናሳዊ ኄር ኢንሁን ከመ መርዔት ዘአልቦ ናሳዊ ወኢይምሥጠነ ተስላ መሳጢ / አቤቱ* (በሞተው ፈንታ) በመንበሩ ላይ አስቀምጥልን። እረኛ እንደሌለው መንጋ አንሁን ፣ ነጣቂ ተኩላም አይንጠቀን» በማለት የሚጸለየው ለዚህ ነው።

የእገሌን ግብሩ አንዲህ ነው እያሉ ፍዳ ማቆየት ለምእመናን አይጠቅምም። አባቶችን በመንፈሳዊ ዓይን እየተመለከቱ ማክበር ስለነእርሱ መጸለይ እንጂ። መጽሐፈ ቅዳሴም *«ኢትጎድሃኬ ለካህን ዘይጸሊ ወያቄርብ መሥዋዕተ በእንቲያከ / ስለአንተ መሥዋዕትን* የሚቀርበውንና የሚጸልየውን ካህን አትተወው» (ሥርዓተ ቅዳሴ ፪፥፲)

ካህናትን መቃወምና መንቀፍ የእግዚአብሔርን ዓይን እንደመውጋት ፣ እጁን እንደመንከስ ፣ እግሮቹን እንደመቀጥቀጥ ነው። ቀደም ሲል በጠቀስነው በዳንኤል ትንቢት *«ወነፍስተሂ ከመተርኤስ ፣ ገጹሂ ከመራእየ መብረቅ አእይንቲሁ ከመ ማኅቶተ እሳት ፣ እደዊሁ ወእገሪሁ ከመብርት ርሱን / አካሉም* እንደ ቢረሌ ይመስል ነበር ፣ ፊቱም እንደ መብረቅ ምስያ ነበረ። ዓይኖቹም እንደሚንበለበል ፋና ክንዶቹና እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ» በማለት የተነገረው ሲተረጎም «ኤጲስ ቆጶሳት እንደ ዕንቁ ናቸው ፣ ጳጳሳት እንደ መብረቅ ያስፈራሉ ፣ ሊቀ ጳጳሳት እንደ ደፋር ናቸው። ክንዶቹ (ቀሳውስት) እና እግሮቹ (ዲያቆናት) እንደ ጋለ ናስ ናቸው።» የሚል ነው።

በራእ ፲፥፲፭ ላይ ደግሞ *«ወአእይንቲሁ ከመ ነደ እሳት*

ወአገሪሁ ከመ ብርተ ሊባናስ ዘአርስንም በእሳት / ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ ፤ እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር» ይላል። በእነዚህ ሁለት የትንቢት ቃላት የእግዚአብሔር ፊቶች የተባሉ ግሩማን (የሚያስፈሩ) ጻጻሳት ሲሆኑ ፤ በእግዚአብሔር እጅና ዓይን የተመሰሉት ደግሞ ቀሳውስት ናቸው። ዓይኖቹ የተባሉት ምሥጢራትን ስለሚያዩ ፤ እጆቹ የተባሉት ደግሞ በእጅ ማንሳት መጣል እንደሚቻል ፈርዶ ገነትንና ሲያልን የሚሰጥባቸው ፤በኃጢአት የወደቁትን በንስሓ የሚያነሳባቸው እጆቹ በመሆናቸው ነው።

ለቤተክርስቲያን መቆርቆር እንደ አላውያን በመዝሰፍ አይደለም። ከልክ አልፎ በዚህ ግብር መገኘት *«ዘይሁብ መርሐ ርቱዐ ለቤተ ክርስቲያን / ዘተክላ ሳቲ ምዕራፈ ስብሐተ ሃይማኖት/* አምነው ለሚያቀርቡት ምስጋና ማረፊያ ማላረፊያ ላደረጋት ለቤተ ክርስቲያን ቅን መሪን የሚሰጥ» ከተባለለት ከእግዚአብሔር በላይ *ለቤተ ክርስቲያን* እቆረቆራለሁ ማለት ይመስላል።

«በክርስቶስ ሁሏጊዜ ድል በመንሣቱ ስሚያዞረን *በስኖም* በየሥፍራው የሰውቀቱን ሽታ *ስሚገልጥ ለለምሳለ ምስጋና ይሁን!!!»*

ስሜን!

ዋቢ መጻሕፍት

ሀይማኖተ አበው ፤ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት ፤ 1986 ዓ.ም. አዲስ አበባ

ሕዳወተ ዉፉቱት ቁ.1 1997 ዓ.ም

መርሐ ጽድቅ ዳሕለ ሃይማኖት

መጽሐፍ ቅዱስ 1980 ዓ.ም. ናይሮቢ

መጽሐፈ ኢሳይያስ ትርጓሜ ማኅበረ ቅዱሳን 1996 ዓ.ም

መጽሐፈ ሕዝቅኤል ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1990 ዓ.ም.

መጽሐፈ ኤርምያስ ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1998 ዓ.ም

መጽሐፈ ዳንኤል ትርጓሜ 1998 ዓ.ም.

ወንጌል ቅዱስ ስንድምታ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1980ዓ.ም.

ዘዝሙረ ዳዊት ስንድምታ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም

መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ ትር. ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም

መጻሕፍተ ሠለስቱ ሐዲሳት ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1989 ዓ.ም

መጻሕፍተ ጠንሳሳት ሠለስቱ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት1982 ዓ.ም. አዲስ አበባ አ.አ.

መንፈሳዊ ውጊያዎች አያሌው ዘኢያሱስ (ትርጉም) ብራና ማተሚያ ቤት 1998 ዓ.ም. አ.አ.

የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ትርጓሜ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም. አ.አ.

ፍኖተ ስእምቢ ፤ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም. አ.አ.

ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1995ዓ.ም.አ.አ.

ተስምረ ማርያም ትንሣኤ ማተሚያ ቤት 1988 ዓ.ም. አ.አ.

ተስምረ ኢየሱስ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1990 ዓ.ም. አ.አ.

ገድለ ስዙነ ተክለ ሃጻማኖት ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት 1984 ዓ.ም. አ.አ.

ገድለ ቅድስት ስምነ ወሰተ ጴጥርስ 1997 ዓ.ም. አ.አ.

ደቂቀ ነቢያት አንድምታ የብራናው ቅጂ
ፈውስ ዘኀፈሳዊ ፣ የብራናው ቅጂ
ርቱዐ ሃይማኖት ፣ የብራናው ቅጂ
ገድለ ስዑነ ሰማዕ ፣ የብራናው ቅጂ
ቤተ ክርስቲያንና ሥርዓቷ ፣ አባ ኪዳነ ማርያም ጌታሁን 1950 ዓ.ም.
ሰዓሊ ምክር ስለባተ መታሰቢያ ፣ አለቃ ጎሩይ ወልደ ሥላሴ
የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጤ ዐፄ ድንግል እስከ አጤ ቴዎድሮስ 1961 ዓ.ም. አ.አ.
የቁርጥ ቀን ወዳጅ ፣ አባ ወልደ ማርያም 1999 ዓ.ም. አ.አ.
ተምህርተ ስዑ ነፍስ ፣ አባ ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፣ 1953 ዓ.ም.
የንስሐ ሕይወት ፣ ዲ.አሸቱ ታደሰ (ትርጉም) ፣ 1989 ዓ.ም.
የጲያቢሱስ ውጊያዎች ፣ አያሌው ዘአ.የሱስ (ትርጉም) ፣ 1994 ዓ.ም.
ተግሣጽ ዘቅዱስ ዮሐንስ ዘፈለወርቅ ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ፣ 1987ዓ.ም. አ.አ.
መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኦርዮን (ዜና አይሁድ) ቅጂ
መጽሐፈ ሰዋስው ጠግሥ መመዝገቢ ቃላተ ሐዲስ ፣ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ
Priesthood ; H.H. Pop Shenouda III ; Amir Hanna; 1997.
The seven Sacraments ; Habib Giorgis.
Penance ; Author unknown../

በደቡብ ግብፅ በሀገረ ቱና ይኖር የነበረው ይህ አባት ክህነቱን ጠብቆ ሥርዓቱን አውቆ የሚኖር ነበር። ከዕለታት በአንድ ቀን ልብሰ ተክህኖ ለብሶ ቤተ መቅደስ ከገባ በኋላ «*አባትህ ታሞ ለሞት ቀርቧል ፣ እርሱንም ለምጠልኝ ብሏል*» ብሎው መልእክተኞች ነገሩት ቀሲስ ብንያሚ ግን «የቁርባኑን ሥርዓት ሳልፈጽም ልብሰ ተክህኖውን አላወልቅም እግዚአብሔር ከፈቀደ ከመሞቱ በፊት ይቆየኛል ፣ ካልፈቀደ ግን እግዚአብሔር የወደደው ይሁን!» ብሎ ለእግዚአብሔር ሥርዓት መፈጸም አደላ። በዚህም የአባ ብንያሚ ክህነት የተባረከ በመሆኑ ልብሱ እጅግ መልካም መዓዛ ይሸት ነበር።

ለዚህም ነው እመቤታችን «*መዓዛ ጸጌያት ጥዕምት አም ዜና ልብሱ ለአባ ብንያሚ* / ከአባ ብንያሚ የልብስ መዓዛ ይልቅ የሚበልጥ መዓዛ ያለሽ» ተብላ የምትመሰገነው (ማኅሌተ ጽጌ) በዚህ አባት ታሪክ ብዙ ሥጋዊ ፈተናዎችና አስገዳጅ ማኅበራዊ ችግሮችን ተቋቁሞ የክህነት ሥልጣን ማክበርን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማስከበርን መማር ይቻላል።

ስለዚህም ካህን ቃለ እግዚአብሔርን ከአንደበቱ የማይለይ የንስሓ መምህር ፣ሥልጣኑን የሚያከብር ፣ በአምላኩ ፊት በቅንነት የሚመላለስ ፣ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ የታመነ መሆን አለበት- እንደ ሌዊ። «በእውነት ሕግ በአፉ ውስጥ ነበረች ፣ በከንፈሩም ውስጥ በደል አልተገኘበትም። ከእኔም ጋር በሠላምና በቅንነት ሄደ። ብዙ ሰዎችንም ከኃጢአት መለሰ።» ብሎ እግዚአብሔር መስክሮለታልና። (ሚል ፪፥፮)

ምዕራፍ አምስት

የንስሐ አባትና የንስሐ ልጅ
(ንስሐ እና ሥርዓተ ኑዛዜ)

በንስሐ ሊደት የካህኑ ድርሻ

፩. መልካም አረኛ መሆን

❖ ምሕረት መንፈሳዊን በማድረግ!

«ምሕረት መንፈሳዊ» ማለት ክፉ ግብር በጎ ግብር መስሏቸው እየሠሩ ለሚኖሩት ለኃጥአን መራራት ማዘን ነው። (ማቴ ፭፥፯ ትር) በመጽሐፍ «እርስ በእርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ» (*ያዕ ፭፥፲፮*) ተብሎ የተነገረው ናዛዚው ካህን ከተነሳሒው ጋር በባሕርይ አንድ ስለሆኑ መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል። ስለዚህ ካህን በባሕርይ የሚመስሉትን ምእመናንን በደል ሲሰማ በባሕርይው ከእነርሱ ጋር አንድ መሆኑ እንዲራራላቸው ችግራቸውንም እንዲረዳ ያደርገዋል።

ለዚህ ነው ለመናንያን መናኒ ካህን ፣ ለሰብአ ዓለም ደግሞ ሕጋዊ ካህን /ያገባ/ መምህረ ንስሓ እንዲሆናቸው የሚመክረው። ካህኑ እንደ ምእመናኑ በነገር ሁሉ የሚፈተን በመሆኑ ለምእመናን ድካም ሊራራ ይገባዋል። በመራራቱም ኃጢአታቸውን ለመናዘዝ እንዲበረታቱ

ያደርጋል። ቃልን በማሻሸር ፣ ፊትን በማጥቆር የሚቀበላቸው ከሆነ ግን ተነሳሒያኑ ለመናዘዝ አቅም እንዲያጡ ብሎም ኃጢአታቸውን እንዲደብቁ ያደርጋቸዋል።

እመቤታችን በአንድ ወቅት አባ ፋቁኤል ለሚባል ካህን ከተናገረችው ቃል የካህን አቀባበል በተነሳሒያን ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ልንረዳ እንችላለን። ይህ ካህን ኑዛዜውን እንዲቀበለው የሚመጣን አንድ ተነሳሒ «ሂድ ለሌላ ካህን ተናዘዝ» እያለ ሲያንገላታው ርኅርኅተ ልቡና የሆነች ድንግል ማርያም «ኃጥአንን ወይም ንስሓ የሚገቡትን ሰዎች ሁሉ ተስፋ አታስቆርጣቸው!» ብላዋለች። (ተአ.ማር ፩፻፲፮) «ተስፋ አታስቆርጣቸው» የሚለው ሐረግ ኃጢአታቸው ከብዷቸው ፣ ሥርየትን ሽተው ወደ እግዚአብሔር መልእክተኛ ወደ ካህን የሚመጡ ምእመናን ከካህኑ አለ-ታዊ ምላሽ ቢያገኙ ምንኛ እንደሚጎዱና «እግዚአብሔር እንደጠላቸው» ሊገምቱ እንደሚችሉ ያስረዳል።

ተነሳሒው ምናልባት ደጋግሞ በኃጢአት የሚዘፈቅ ቢሆን እንኳን ቅዱስ ጴጥሮስ «ወንድሜን ስንቱ ይቅር ልበለው?» ብሎ ሲጠይቅ ጌታችን «እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ ሰባት ጊዜ አልልህም» እንዳለው (ማቴ ፲፰÷፳፪) መምህረ ንስሓው ከተግሣጽ ጋር በርኅራኄ ፍጹም ይቅርታን ሊሰጠው ይገባል። ምናልባት ተነሳሒው ብዙ ተመክሮ አልታረም የሚል ፣ በተባለው የማይገኝ አባቶቻችን እንደሚሉት «አድሮ አነስ ፣ አድጎ አነስ» ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መምህረ ንስሓው ሊታገሥና በፍቅር ሊቀበለው ይገባል።

ጌታችን ይህንን በተግባር አሳይቶናል። «ከእንግዲህ አታጠምድም ሰውን እንድታጠምድ አደርግሃለሁ» ብሎ የጠራውን ቅዱስ ጴጥሮስን ከትንሣኤ በኋላ ያገኘው ሰው ሲያጠምድ አልነበረም፤አሣን እንጂ። ይሁንና ቅዱስ አውግስጢኖስ እንደገለጠው ጌታችን ቅዱስ ጴጥሮስን

በሚቆጠቁጥ የቁጣ ቃል አልተናገረውም፤ «ምእመናንን ጠብቅ» አለው እንጂ።

ካህን ለንስሓ ልጁ የሚያሳየው ርኅራኄ ከተነሳሒያኑ በተጨማሪ ለራሱም ይጠቅመዋል። በወንጌል የተመሰለው ምሳሌም የዚህ ማስረጃ ነው። ምሳሌው ባለጠጋው ከመጋቢነቱ ሊያሰናብተው «ሂሳብ አስረክበኝ» ያለው መጋቢ ከመሻሩ በፊት ከጌታው ባለ ዕዳዎች እያንዳንዳቸውን ጠርቶ፡- ለጌታዬ ምን ያህል ዕዳ አለብህ? እያለ ጠይቆ መቶ ማድጋ ዘይት ያለበትን «ሃምሳ ብለህ ጻፍ!» ፣ መቶ ጫን ስንዴ ያለበትን «ሰማንያ ብለህ ጻፍ!» ብሎ ዕዳቸውን አቀለለላቸው። በዚህን ጊዜ ባለጠጋው ጌታ መጋቢው ልባምነትን ስላደረገ አመሰገነው። «የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸው» ይላል። የዚህ ትርጓሜ አንድም ምእመናንን የሚያስተምር ንስሓን ሥጋ ወደሙን የማይሰጥ ካህንን እግዚአብሔር በደዌ ይጠራዋል። መምህረ ንስሓም በበኩሉ ምእመኑን ጠርቶ «አንተ ምን ሠራህ?» እያለ አናዝዘው። «ፍጹም ኃጢአት ሠርቻለሁ» አለው። «እኩሉን ጸም እኩሉን እኔ እጾምልሃለሁ» አለው። በዓመጻ የሚፈርድ ጌታ እግዚአብሔር መምህረ ንስሓውን አመሰገነው። ራሳቸውን ጠብቀው መንግሥተ ሰማያት ከሚገቡ ውስደ ብርሃን ጻድቃን ይልቅ ፣ ብዙ አሳምነው አስተምረው ወደ ኃጢአት ወደ ክህደት የሄደውን ወደ ንስሓ መልሰው ብዙ ሆነው ይገባሉና መምህራን ንስሓ ካህናት ልባሞች ናቸው የሚል ነው።

ሰተነሳሒያንን መራራት አንድም ደግሞ ችግርን መረዳትና መፍትሔን መስጠትን ፣ አቅምን ያገናዘበ ቀኖና መስጠትንም ያካትታል። እንደ ፊሪሳውያን በጣት ሊነኩት የማይሹትን በሰው ላይ መጫን ግን የመልካም እረኛ ጠባይ አይደለም። በአንድ ወቅት ቅዱስ

ጴጥሮስ ለቀሳውስት በጉባኤ መሐል ተነስቶ «አባቶቻችን እኛ ልንሸከመው ይቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ስለምን ትፈታተናላችሁ?» ብሎ ነበር። (ሐዋ ፲፭፥፲) መምህራኑ ንስሓም የቅዱስ ጴጥሮስን ሥልጣን ይዘዋልና እንደ አነርሱ ርኅራኄን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በፍትሐ ነገሥት ላይ «ካህኑ ሐዋርያት ከሠሩት ሥርዓት የወጣ ሥርዓት ለሕዝቡ አያጽናባቸው» ተብሏል። (ፍ.ነገ ፭)

መምህሩ የተነሳሒውን አቅም በማገናዘብ ቀኖናን መስጠት አለበት። *«ሥራዕ ለሠቱ ጸመ በእንተ ኃጢአቱ በለምጣነ ክሂሎቱ/* በችሎታው መጠን ስለ ኃጢአቱ ጾም ሥራለት» እንዲል መጽሐፍ። ገና ክርስቲያናዊ ሕይወት ለመጀመር መጥቶ ንስሓ የሚገባን ምእመን ያልኖረበትን ጾም ፣ ጸሎት ፣ ስግደት ፣ ምጽዋት ቢጭነበት ከመመለስ ይልቅ ተንገሽግሾ ወደ ዓለም እንዲመለስና ተስፋ እንዲቆርጥ ሊያደርገው ይችላል።

ጌታችን በወንጌል «በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚያኖር የለም መጣፊያው ልብሱን ይቦጫጭቀዋልና መቀደዱም የባሰ ይሆናል ፣ በአረጀ አቁማዳ አዲስ ወይን የሚያኖር የለም ቢደረግ ግን አቁማዳው ይፈነዳል የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል።» በማለት ገና ከዓለማዊ አሮጌ የኃጢአት ሥራ ባልታደሰ ጀማሪ ተነሳሒ ላይ ከእርሱ አቅም ጋር የማይሄድ ቀኖናን መስጠት እንደ አሮጌው ልብስና እንዳሮጌው አቁማዳ ዳግም እንዳይመለስ አድርጎ ማጥፋት ነው። (ማቴ ፱፥፲፮ ፡- ፲፯) ስለዚህ መምህረ ንስሓ የተነሳሒውን አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ቀኖናን መስጠት አለበት።

ካህናት በንስሓ የሚያክሙና በሥርየት የሚፈወሱ የድዉያነ ነፍስ (ኃጥአን) ባለ መድኃኒቶች መሆናቸውን ቀደም ባሉት ንዑሳን አርእስት

ተመልክተናል። ንስሓ ደግሞ *«ወበተራርኖ ታስተጠግዕ ዘተሰብረ /* የተሰበረውን በመራራት ትጠግነዋለች» ተብሎ የተነገረላት ፍቱን መፍትሔ ሥራይ ናት (አረመን አ. ፳፱) ብልህ ባለመድኃኒት ክርስቶስ ያዘጋጃት ፣ ከቁስሉ ያገባትን ሁሉ ፈጥና የምታድን መድኃኒት ንስሐ ናት። ቁሱ ለምእመናን የንስሐን መድኃኒት ሲሰጥ በርኅራኄ ሊሆን ይገባዋል። ቁስልን እየጨፈለቁ መድኃኒት ማድረግ ሕመምን እንደሚጨምር ናህኑ በርኅራኄ ካላደረገው ቀኖናው ሊጎዳ ይችላል።

ርኅሩኅ ባለመድኃኒት በምላጭ በጥቶ በሕማም አስጨንቆ በሕሳት ተኩሶ እንደማያስቃይና በማዘን ኣፍ ኣፍ እያለ መድኃኒትን በቁስል ላይ እንደሚያደርግ የታወቀ ነው።

ደጉ ሣምራዊ ክርስቶስ በእንግዶች ማደሪያ በቤተ ክርስቲያን ያስቀመጠውን ድዉይ ምእመን «አስክመለስ ድረስ የሚያስፈልገውን አድርጉለት» ብሎ አደራ የሰጣቸውን ካህናትም በርኅራኄ ሊያክሙት ፣ እርሱን ለማዳን ብለው የሚጎዱበት ነገር ካለም ክርስቶስ ሲመጣ እንደሚክሳቸው በማመን የድዉያን ክፉ አመል ታግሰው ሊያድኑት ያስፈልጋል። (ሉቃ ፲፥፴፭-፴፯)

እንዲሁም ካህናት በመጽሐፍ «አንተና አሮን የሕግ አፍራሾችን በደል ትሸከማላችሁ» እንደሚል የንስሐ ልጃቸውን ኃጢአት አስበው ቀኖናውን ሊንፈሱለትም ይጠበቅባቸዋል። (ዘኁ.፲፰፥፩)

ፈውስ መንፈሳዊ የተባለው መጽሐፍ ከካህን ስለሚጠበቀው ርኅራኄ ሲናገር «የበደለውንም አንተ ተመለስ እኔም ስለ እኔና ስለ ሁሉ በሞተው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላል ሞትን እቀበላለሁ ይበለው» ይላል። ግእዙ እንዲህ ይነበባል ፦ «ወይቤሎ ለዘአበሰ ተመየጥ አንተ ወስነ እትቄከፍ ሞተ ሀየንቴከ አምላለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘሞተ በእንቲአየ ወበእንተ ኵሉመ»

ካህናት ለምእመናን የሚያሳዩት ርኅራኄ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅርም ይለካል። ጌታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ «ተወደኛለህን? ፤ እንግዲያውስ ግልገሎቼን አሰማራ፤ጠቦቶቼን ጠብቅ፤በጎቼን አሰማራ» የሚል ቃልን መናገሩ «ካህን ሆይ የምትወደኝ ከሆነ ለእኔ ስትል ምእመናንን ጠብቅ!» የሚል መልእክትን ሲያስተላልፍ ነው፡(ዮሐ.፳፩÷፲፫-፲፯)

ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ «አንዳንድ ተከራካሪዎችን ውቀሱ ፤ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳን እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ።» በማለት መምህረ ንስሓ የማይገባ ግብር የያዙትንና የደነደኑትን ሲኖዶስ ባስቀመጠው ሥርዓት መሠረት እንዲወቅስና እንዲገሥጽ በኃጢአት ብዛት የተጨነቁትንም ኃጢአታቸውን እንጂ እነርሱን ሳይጠላ ከእሳተ ገሃነም ነጥቆ እንዲያወጣ ተናግሮአል (ይሁ ፩÷፳፫)

❖ በርኅራኄ በመገሠጽ፤

በመጽሐፍ *«ወመገሥጽሂ ሊይኩን ከመ መዐትም ወጽኑዐ ቃል አላ ይኩን ከመ ብእሲ የዋህ ወርኅሩኅ ዘይፈሥጽ ባሕቲቱ* /የሚያስተምርም ቃለ ሻካራ ግንባረ ቆጣራ አይሁን ብቻውን እንደሚመክር እንደ የዋህ ባልንጀራ ሆኖ ያስተምር» ተብሎ ተጽፎአል (ተግሳጽ ፴) መምህረ ንስሓ ለምእመናን ለድካማቸው ሳይራራ ፈጥኖ ቃሉን የሚያሻክርና በቁጣ ቃል የሚያወግዝ ቢሆን «ለበጎች አይራራምን?» ያሰኝበታል። የጠነከረ ተግሣጽ ለመቀበል የሚችለው የጠነከረ መንፈሳዊ ሕይወትና ግንዛቤ ያለው ሰው ነው። ገና ከዓለማዊነት ያልወጣውን ፤ የኃጢአት ጠባሳው ያልጠፋውን ተነሳሒ ማጽናናት እንጂ ማስመረር አይገባም። በሰው ቁስልም እንጨት እንደ መስደድ ይቆጠራል። አባ ጳውሊ ገሥጸ የመለሰው መነኩሴ ታሪክ ምንኛ መካር ነው?

አንድ ጸር የጸናበት ወጣኒ (የዲያቢሎስ ፈተና የበዛበት ጀማሪ መነኩሴ) ወደ አንድ አባት እየመጣ የደረሰበትን ሲያማክረው «የእንጦንስ የመቃርስን አስኬማ ጭነህ እንዴት እንዲህ ትላለህ!?» እያለ እያስበረገገ ከአንዱም ሁለት ጊዜ አባረረው።

በኋላ ወጣኒው (ጀማሪው) ከስድብ በቀር ምንም አላተርፍም ብሎ ተስፋ ቆርጦ ከገዳሙ ሲወጣ አባ ጳውሊ ከመንገድ ይዞ አነጋገረውና ነገሩን ስምቶ የዚህ ወጣኒ ጸር በዚያ መነኩሴ ላይ እንዲመጣበት ጸለየ ፤ መነኩሴውም ጸር ሲጸናበት በአቱን ለቅቆ ሮጦ ሲሔድ እነ አባ ጳውሊ ካሰቡት ደረሰ ፤ አባ ጳውሊ ሲይዘው ያ መነኩሴ እየተሰቀቀ «ልሂድ ተወኝ ልቀቀኝ!» አለው። እርሱም «ይህ ወጣኒ ሁለት ሱባኤ ታግሦ ነበር ፤ አንተ አንድ ሱባኤ መታገሥ አቃተህን?» ብሎ እርሱ እንኳን ስባ ሰማንያ ዓመት ሁኖት ሳለ ጸር እንዳልጠፋለት ነግሯቸው አቡነ ዘበሰማያት ሰጥቶአቸው ወደ በአታቸው መልሶአቸዋል።

ዲያቢሎስ ፈተና አጽንቶበት ነፍሱ ተጨንቃ ያለን ሰው በተግሣጽ ማስጨነቅ አይገባም በርኅራኄ ማጽናናት እንጂ። ጻድቁ ኢዮብ በመከራ ተይዞ እያለ በነገር እየዘበዘቡ በቁስሉ ላይ እንጨት ይሰድዱበት የነበሩትን ባልንጀሮቹን «የምታዳክሙ አጽናኞች ናችሁ . . . ነፍሳችሁ በነፍሴ ፈንታ ቢሆን ኖሮ እኔ በአናንተ ላይ ቃል ማሳካት ፤ ራሴን በአናንተ ላይ መነቅነቅ በተቻለኝ ነበር ፤ በአፌም ነገር ባበረታኋችሁ ነበር . . . ነፍሴን የምትነዘንዙ በቃልስ የምታደቅቁኝ እስከ መቼ ነው?» ብሎ የተናገራቸው ተግሣጻቸው ከቁስሉ በርትቶበት ስለነበር ነው። (ኢዮ ፲፮÷፪ ፤ ፲፱÷፩) መምህረ ንስሓም ተግሣጹ ከዲያቢሎስ ፈተና ልቆ ምእመናንን እንዳያስቅቅ ሊጠነቀቅ ይገባል።

መምህረ ንስሓ የመገሠጽ ሙሉ ሥልጣን ቢኖረውም ተግሣጹ የሰሚውን አቅምና የአኗኗር ሁኔታ ፣ መንፈሳዊ ጥንካሬን ያገናዘበ መሆን አለበት። ባሕር ውስጥ በመስጠም ላይ ያለን ልጅ «ለምን ወደ ባሕር ሄድህ?» ብሎ ከመቆጣት በፊት ማውጣት እንደሚቀድም ካህኑም አጠንክሮ ከመገሠጹ በፊት ምዕመኑን ከገባበት የኃጢአት ዐዘቅት ሙሉ ለሙሉ ማውጣቱንና ከሕመሙ እንዲያገግም ማድረጉን ማረጋገጥ አለበት።

ካህኑ ዔሊም እመ ሳሙኤል ሐና በቤተ እግዚአብሔር ቆማ ጸሎትን በለኖሳስ ስታደርግ ችግሯን ሳይረዳ እንደ ሰከረች ቆጥሮ ለተግሣጽ በመቸኮል፦ «ስካርሽ እስከ መቼ ነው? የወይን ጠጅሽን ከአንቺ አርቂው» ብሎ በቁጣ ተናግሮአት ነበር። ሐና ግን በነቀፋው ሳትቀየም «እኔ ልብዋ ያዘነብኝ ሴት ነኝ ጠጅና ሌላ የሚያሰክር ነገር አልጠጣሁም . . . ባሪያህን እንደ ምናምንቴ አትቁጠረኝ» በማለት በትሕትና ክኅሠኑ የተሻለች ሆና አሸንፋዋለች። ዔሊም ወዲያው ስኅተቱን ተረድቶ «በደህና ሒጂ የእስራኤልም አምላክ የለመንሽውን ልመና ይስጥሽ!» ብሎ ቡራኬውን ሰጥቶአታል። (፩ሳሙ ፩፥፲፪-፲፯)

ካህን ምእመናን ላይ ፍርድን ከመስጠቱ አስቀድሞ ነገሮችን ሊመረምርና ችግራቸውን ሊረዳ ይገባል ፣ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ካህን በተናገረበት ሥፍራ «*ዘሊያፈጥን ዕዴሁ ለዘቢጥ ፈጥኖ የማይማታ*» እንዳለ ካህን በዕደ ሥልጣኑ ፈጥኖ ከመገዘቱ በፊት ግራና ቀኝ ማየትና በርኅራኄ መገሠጽና መምከር ይኖርበታል። ደግሞም በግልፍተኝነትና በግላዊ ጥላቻ የሚገዘት ምክንያት የለሽና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ያልተከተለ ግዝት «*ግዘት ብዝት! ወፈ ገዘትከ*» ከመባል በላይ ምንም አያመጣም። (ፊጢሞ ፫፥፫ ትር)

ቸሩ አረኛ ከርስቶስ ግን ፈጥኖ ከመፍረድ ይልቅ የጠፋትን ከያለበት ፈልጎ ማግኘትንና እስኪያገግሙ ድረስ ታግሶ መሸከምን

አስተምሮአል። «*ናላዊ ኀር ዘበአማን ዘኀሠሥ ለበግዕ ግዱፍ ወሶበ ረከቦ ጸሮ ዲበ መትከፍቱ / የጠፋ በግ አዳምን የፈለገው በአገኘውም ጊዜ የተሸከመው እውነተኛ ቸር ጠባቂ!*» የሚባለውም ለዚህ ነው። (ተአምረ ማርያም መቅድም ፤ ሉቃ. ፲፭፥፫) ለምእመናን የሚያስፈልገው የጠፋ በግን የሚፈልግና ድካማቸውንና ክፉ አመላቸውን ታግሶና ራርቶ የሚሸከማቸው ካህን ነው።

የመምህረ ንስሓ ቁጣ የተሞላበት ንግግር ተነሳሒውን ለበጎ ምግባር ከማነሣሣት ይልቅ ተስፋ ወደ መቁረጥ ይመራዋል። ቅዱስ ያዕቆብ ሐዋርያ በመልእክቱ «ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገር የዘገየ ፤ ለቁጣም የዘገየ ይሁን ። የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አያደርግምና» ብሎአል (ያዕ ፩፥፲፱) ይህ ቃል አንድም መምህረ ንስሓ ለመስማት የቸኮለ (ታግሶ የሚያዳምጥ) ለመናገርና ለመቆጣት ግን የዘገየ መሆን እንዳለበት ያስረዳል። ተነሳሒው «*እንዲሀ ያለ ኃጢአት ሠርቻለሁ*» ብሎ ሲነግረው «*እንዲህ አደረግህን?*» ብሎ የተጣላው እንደሆነ እንኳን ተጸጽቶ ምግባሩን ሊያስተካክል ሁለተኛም ወደ መምህረ ንስሓው አይደርስም። የመምህረ ንስሓ ቁጣ ተነሳሒውን እግዚአብሔር የሚወደውን የጽድቅ ሥራ አያሠራውምና። ስለዚህ «***ገሥጾ ለጥዓ ከመ ኢትክሙ / ኃጢአተኛውን እንደ ወንድማችሁ ገስጹት***» እንደተባለ መምህረ ንስሓም በፍቅር መገሠጽ ይገባዋል። (ቅዳሴ አትናቴዎስ)

❖ ስለ ንስሓ ልጆቹ በመጸለይ

ሌላው የመራራት መገለጫ ደግሞ ስለ በጎች (ምእመናን) መምህረ ንስሓው የሚያደርገው ጸሎት ነው። ካህን ከመምከርና ከማስተማር ባሻገር ከምእመናን ሕይወት በጎ ፍሬን ለማግኘት መለመን ይገባዋል። «*ወያስተበቁዖ ለእግዚአብሔር በኵሉ ልብ ወበኵሉ ድካም ከመይኩን ቃሉ ዘይብሎ ኪያሁ ከመ ይፍረይ ውስተ ሰማዕያኒሁ ፍሬ መንፈስ ቅዱስ / በፍጹም ልብ በፍጹም ድካም እግዚአብሔርን*

ይሰምነው፤ የሚያስተምረው ትምህርት በሰሚዎቹ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬ ያፈራ ዘንድ» እንደ ተባለ (ፍ.ነገ.አ ፭) ገበሬ የዘራው ዘር ፍሬ እንዲያፈራለት ፣ ተባይ እንዳያበላሽበት ፣ በረዶ እንዳያወድምበት እንደሚጸልይ ሁሉ መምህረ ንስሓም የቃለ እግዚአብሔርን ዘር የዘራባቸው ምእመናን ፍሬ ምግባርን እንዲያፈሩ ፣ ዲያቢሎስ እንክርዳድ እንዳይዘራባቸው ፣ በመከራ መጽናት ተስኗቸው እንዳወድቁ ሊጸልይላቸው ይገባዋል።

እንዲሁም ኢዮብ ጻድቅ ስለ ሥጋ ልጆቹ በደል መሥዋዕትን ይሰዋ እንደነበር (ኢዮ ፩፥፭) ካህኑ የመንፈስ ልጆቹን በደል እግዚአብሔር እንዳይቆጥር መለመንና ምሕረትን እንዲሰጥ መማፀን ቀኖናን መካፈል ይገባዋል። እንደ አባ ተክለ ሐዋርያት ስለ ንስሓ ልጁ ምሕረት ማግኘት ራሱን በጋለ አሸዋ ውስጥ መቅበር ባይቻለው ተግቶ መለመን ግን ካህን ሁሉ ይጠበቅበታል። (ገድለ ተክለ ሐዋርያት) *«ዘሰኢይኃዝን በእንተ አበሳ ካልው ድልው ውእቱ ለተሐምሞ / ስለ ሌላው በደል የማያዝን ወቀሳ ይገባዋል»* በማለት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገረውም ይህንኑ ነው (ተግሣጽ ፲፫)

መምህረ ንስሓ የልጆቹን በደል በሰማ ቁጥር ኀዘንንና ልመናን ማድረግ ይገባዋል፤ ይህም ከሐዋርያት የተማርነው ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ ከተግሣጽ ጋር እንባና ጸሎትን ስለ ምእመናን ያደርግ ነበር *«ተዘከሩ ከመ ሠለስተ ዓመተ ኢነሥን አንብዕየ ሌሊተ ወመዓልተ አንዘ አሜህረክሙ ኩልክሙ / ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትኑ»* ብሎ የተናገረውም ለዚህ ነው። (ሐዋ ፳፥፴፩)

ካህናት ምንም ምእመናን በኃጢአት ሲወድቁ እየገሠጹና እየመከሩ ቢመልሱም በእግዚአብሔር ፊት ግን ዘወትር ስለ ልጆቻቸው

ይቅርታን ይለምናሉ ፤ ያማልዱማል። በቀደመው ዘመን ርኅሩኑ እግዚአብሔር ሳይቀር «አስከ መቼ ታለቅሳለህ?» ብሎ እስኪቆጣው ቀብቶ ለሾመው የመንፈስ ልጁ ለንጉሥ ሳኦል ያለቅስ የነበረው ሳሙኤል ነቢይ ለዚህ ምሳሌ ነው። (፩ሳሙ ፲፮፥፩) ሳሙኤል ሳኦል ትእዛዘ እግዚአብሔርን በማፍረሱ የሚገባውን ተግሣጽ የገሠጸው ቢሆንም ስለ አመፀኛው ንጉሥ ግን ማልቀሱና መለመኑን ግን አላቆመም ነበር።

ካህናትም በጥምቀት የልጅነት ሥልጣንን ለሾሙአቸው ምእመናን ማልቀሳቸው ይልቅ የተገባ ነው። ምእመናን ከኃጢአት ሳይለዩ ምግባር ትሩፋትን ሳይሠሩ ሲኖሩ እግዚአብሔር (በሥርዓተ ቤተክርስቲያን) እንዲያወግዙ ባዘዘበት ገንዘብ እንኳን «መክሬ አስተምሬ ሃይማኖት አስካስይዛቸው ፤ ምግባር አስካሠራቸው ድረስ የዘንድሮን ተዋቸው» እያሉ እንደ መላእክት የሚያማልዱና የንስሓ ጊዜን ማሰጠት የካህናት ሥልጣን ነው። (ሉቃ ፲፫፥፱ ትር)

ካህን ስለ ምእመናን በመጸለዩ የሚጠቀሙት ምእመናን ብቻ አይደሉም ካህኑም ጭምር እንጂ። በያዕ ፭፥፲፱ «ከእናንተ የታመመ ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት• ይጥራ ዘይትም ቀብተው ይጸልዩለት» በሚለው ኃይለ ቃል አንድም ዘይት የተባለ የካህናቱ ጸሎት ነው። ዘይት የሚቀባ ሰው እጁን ሳይነካው እንደማይቀር ለምእመናን የሚጸልዩ ካህናትም ከሚጸልዩት ጸሎት ተጠቃሚዎች ናቸው።

፪. ሳይታክቱ ማስተማር

ቃለ እግዚአብሔርን ማስተማር የመምህረ ንስሓ ተቀዳሚ ተግባርና ግዴታ ነው። «መምህር» መሰኘቱ ለሌላ ለምንም አይደለምና። ቀሲስ ማለትም አበ ሕዝብ ፤ መገሥጸ ሕዝብ ፤ መስተስርየ ሕዝብ

ማለት ነው። ጌታችን በወንጌል «መብራትን አብርተው ከእንቅብ በታች ያኖሩታልን?» እንዳለ በየትኛውም መዓርግ ያለ ካህን መሾሙ ከአዳራሽ ገብቶ ፣ ከእልፍኝ ከትቶ ፣ ተሰውሮ ሲበላ ሲጠጣ ሊውል አይደለም። ይህን ቢያደርግ ብርሃኑ በሰው ፊት ሊበራ አይችልም። ሰዎችም እርሱን ተመልክተው በሰማያት ያለውን አምላክ ያከብሩ ዘንድ አይቻላቸውም። (ማቴ. ፭፥፲፮) ማስተማርን ትተው ቀሚላቸውን አንጸተው ሰናፊላቸውን አንሰርተው ከተማ ለከተማ የሚዞሩ ካህናት ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በድለዋልና ይቀጣሉ።

ቅዱስ ጳውሎስ «ወንጌልን ባልሰብክ ወዮልኝ!»ያለው ለዚህ ነው። (፩ኛ ቆሮ ፱፥፲፮) ይህ ሐዋርያ ባለማስተማር የሚመጣውን ዕዳ ጠንቅቆ ያወቀ በመሆኑ ከመናገር ባሻገር የእግሩ ጫማ ሦስት ጊዜ እንደ ሽንኩርት ተልጦ እስኪወድቅ ዞሮ በማስተማር ለመምህራን አብነት ሆኖአል።

ካህን የቱንም ያህል የጠለቀ መንፈሳዊ እውቀት ቢኖረው ካላስተማረ ዕዳ ይሆንበታል። ሊያተርፍበት የተሰጠውን መክሊት በመቅበሩና ሊመጸውተው የተሰጠውን የትምህርት ሀብት ባለመመጽወቱ (ማስተማርም ምጽዋት ነውና) እግዚአብሔር ይጠይቀዋል። «ውሻ እየበላኝ የተማርሁትን ትምህርት እንዴት ለማንም እነግራለሁ?» እያለ የሚሰስት ከሆነ የተማረው ይከፈልበታል ፤ እውቀትን እንደገበቴ ውሃ ማፍሰስ የሚቻለው አምላክ እንዳይሆን እንዳይሆን ያደርገዋል። «የእውቀትን መክፈቻ ስለወሰዳችሁ ወዮላችሁ! ራሳችሁ አልገባችሁም የሚገቡትንም ከለከላችሁ።»የሚለው እንዲህ ስላለው ሰው ነው።(ሉቃ.፲፩፥፶፪)

«የተሰወረ ጥበብ እንደ ተቀበረ ወርቅ ነው ፤ የሁለቱስ ጥቅማቸው ምንድርን ነው?» ተብሎ በሲራክ የተነገረውም ይህንኑ

ነው። (ሲራ ፳፥፴) ለዓመታት ከጉባኤ ጉባኤ እየዞረ ፤ መዛግብት እየዘረጋ ያከማቸውን የመንፈሳዊ እውቀት ሀብት የማያስተምረው ከሆነ ጥቅሙ ምንድርን ነው?

የቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ዜና ሕይወት ሐዋርያው ያስተምራቸው ነበሩትን ደቀመዛሙርቱን ሰብስቦ «ከማውቀው ትምህርት ከማንኛውም ጥበብ ሁሉ ያልነገርኋችሁ የሰወርኩአችሁ ነገር የለም። አብዝቼ አትረፍርፈ በሚገባ ከሰያል የምትጠበቁበትን ሌሎችንም የምትጠብቁበትን ነገርኋችሁ . . . ያስተማርኋችሁን ትምህርት ባታስተምሩ እኔ ከደማችሁ ንጹሕ ነኝ!» ብሎ እጁን በፊታቸው ታጠበ» ይላል።

በእርግጥም ተምሮ አለማስተማር «እኔ ያወቅሁትን ሌላው አይወቅ!» የሚል ምቀኝነት ነውና ያስጠይቃል። ይህ እንግዲህ ዕውቀትን ስለማካፈል የሚነገር ነው። ከዚህም ሳይደርስ ግን መምህረ ንስሓ ለምእመናን ብዙ እውቀትን ባይሰጥ እንኳን ጽድቅን ከኃጢአት የሚለዩበትን እና ለመንግሥተ ሰማያት የሚበቁበትን ትምህርት ማስተማር ግዴታው ነው።

የማስተማርና ምእመናንን የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን የማይወጡትን ካህናት ጌታችን ዳግመኛ በመጣ ጊዜ ከካህኑ ማግኘት ያለባቸውን መንፈሳዊ እንክብካቤ ባላገኙ ምእመናን ተገብቶ «በኃጢአት ከሥጋ ወደሙ ብክለክልና ብራብ ብጠማ በንስሓ ሥጋወ ደሙን አላበላችሁኝም! ፤ በኃጢአት ከማኅበረ ቅዱሳን (ከቅዱሳን ማኅበር) እንግዳ ብሆን በንስሓ አልተቀበላችሁኝም ፤ ከልጅነት ጸጋ ብራቅት በንስሓ አላለበሳችሁኝም ፤ በማዕሠረ ኃጢአት (በኃጢአት ማሰሪያ) ብታሰር በንስሓ ከእስራ አላስፈታችሁኝም!» ሲል ይወቅሳቸዋል። (ማቴ ፳፫፥፴፪ ትርጓሜ)

የሰው ባሕርይው እንስሳዊና መልአካዊ ነው። እንስሳዊ ባሕርይው ምግብን ሲያጣ ይራባል። መልአካዊ ባሕርይው ደግሞ መንፈሳዊ ትምህርትን ሲያጣ ይራባል። «ብምድር ላይ ራብን የምስድድበት ዘመን ይመጣል ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት እንጂ እንጀራን ከመራብና ውኃን ከመጠማት አይደለም።» (አሞ ፰፥፲፩) የሚለው ቃል ለዚህ ማስረጃ ነው። ስለዚህ «በራብ አላበላችሁኝም» ማለት ለመምህራን «አላስተማራችሁኝም!» እንደማለት ነው።

መምህራኑ ንስሐ ካህናት መጋቢያን ቃለ እግዚአብሔር ናቸው። ካህን ማስተማር ግብሩ እንደሆነ የበለጠ ለማስረዳት ዘወትር በካህን አንደበት የሚነገርን አዋጅ መጥቀስ እንችላለን። ዘወትር በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተአምረ ማርያምን የሚያነብ ካህን በመቅድሙ ላይ «እኔ ለምእመናን ወንጌልን የማስተምርስት የጌታዬ እናቱ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ!» በማለት በራሱ ላይ ያዳኛል። ለማያስተምር ግን ይህ ቃል ምንኛ ይከብድ?

ስለዚህም ምግበ ነፍስ የሆነውን ቃለ እግዚአብሔር ለነፍሳት ሁሉ መመገብ ይጠበቅባቸዋል፡ «ካህናት *አዕይንተ እግዚአብሔር/ የእግዚአብሔር ዓይኖች* ናቸው። ሕዝቡን ካላስተማሩ ግን ክብር ይግባውና እግዚአብሔርን ዕውር ያስኙታል።» በማለት የሚነገረውም የሐላፊነታቸውን ክብደት ለመግለጥ ነው።

፫. ያለ ማድሳት ሁሉን ማገልገል

ካህናት የእግዘኢአብሔር ፈቃድ አስፈጻሚዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ደግሞ «ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነቱን ወደማወቅ እንዲደርሱ ነው።» አባቶች «ለነፍሳት ሁሉ ቃሉን መመገብ» አለባቸው ሲባል ዕድሜን ፤ ጸጋን ፤ ዘርን ፤ የኑሮ ደረጃን ፤ የመንፈሳዊ ሕይወት ጥንካሬን ሳይለዩና ሳይመርጡ ሁሉንም ማስተማር

እና ማገልገል አለባቸው ለማለት ነው።

❖ በዘፈቀደና በሰዶማዊ አሰጣጥ

ከላይ እንደተገለጸው ቃለ እግዚአብሔር የነፍስ ምግብ ናት። ነፍስ ደግሞ እንደ ሥጋ በጾታ በዕድሜ የምትመዘን አይደለችምና ካህናት ሴት ፣ወንድ ፣ ሕጻን፣ አረጋዊ ሳይሉ ቃሉን መመገብ ይገባቸዋል። ይህን ስንል ዕድሜንና ጾታን ያገናዘበ ትምህርት የመስጠት አስፈላጊነት እንዳለ ሆኖ ነው። ጌታችን ብርስፌንያ የምትባለውን ሳምራዊቷን ሴት ምሁራኑ አሪት (አሪትን የተማሩ) አይሁድ ያላመነብኝን ይህች ሴት እንዴት ታምንብኛለች? ሳይል በማስተማሩ ሐዋርያቱን አስደንቋቸው ነበር። (ዮሐ ፬፥፳፯) አነርሱም ለሴቶች ጉባኤን ዘርግተው ማስተማራቸው መንፈሳዊ ትምህርት ጾታን ሳይለይ የሚፈጸም አገልግሎት መሆኑን ያስረዳል። (ሐዋ ፲፮፥፲፫)

በዕድሜም ቢሆን ጌታችን ክርስቶስ «ሕጻናትን ተዉአቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው» በማለት የተናቁትን ሕጻናት ከትምህርቱ ሳይለይ በመባረኩ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅሙ ሆነዋል። ሕጻናት የተዘራባቸውን ቶሎ የሚያበቅሉ አማንያን ናቸውና በንጹሕ የልጅነት አእምሮአቸው ፍቅረ እግዚአብሔር ቢሳልባቸው ፈሪሐ እግዚአብሔር ቢያድርባቸው ለቤተ ክርስቲያንም ለሀገርም ይበጃሉ። ቅዱስ አለ አስክንድሮስ ሕጻኑን አትናቴዎስን ለቤተ ክርስቲያን ዐምድ ለመሆን እንዲበቃ ያደረገው ከጨዋታ ሜዳ ጠርቶ መሆኑ ለዚህ ጉልሕ ማስረጃ ነው። ስለዚህ ካህናት *«ሴት ናት ምን ይጠቅማታል?»! «ሕጻን ነው ምን ይረባዋል?»* ሳይሉ ጾታና ዕድሜን ሳይለዩ ሊያስተምሩ ይገባል። አንድ የታሪክ ሰውም «የዓለምን ሕፃናት ስጡኝና በመጪው ዘመን ዓለም ሁኑ እኔ የምከተለውን ሃይማኖት ተከታይ እንዲሆን አደርገዋለሁ» እንዳሉ ይነገራል። ይህም ሕጻናትን መያዝ ነገን መያዝ

መሆኑን ያስረዳል። ካህናት ለሕጻናት የሚያሳዩት እንክብካቤ ሕጻናቱ ለቤተ ክርስቲያን የሚኖራቸውን እይታ የሚወስን ነው።

አንዳንድ ጊዜ ዕድሜአቸው ንስሓ ለመግባት የሚያስችል ሆኖ ለአካለ መጠን ግን ያልደረሱ ልጆች ወደ ካህን ቀርበው ቀኖና ሲጠይቁ *«አንተማ /አንቺማ ገና ሕጻን ነሽ ምን ኃጢአት አለብህ/ሽ?»* ተብለው የሚመለሱበት ጊዜ አለ። ነገር ግን የአምላክ ቸርነት ወደ ንስሐ መርቶት ኃጢአትን ከሥሩ ሊነቅል ፣ ገና በሕጻንነት ዕድሜው ከኃጢአት ጋር ሊዋጋ የመጣን ሕጻን ዕድሜው ለጉባዜና ለጸጸት እስኪበቃ ድረስ አክብሮ መስማትና ተገቢውን ምክርና ተግሣጽ መስጠት ያስፈልጋል እንጂ አሳፍሮ መመለስ አይገባም። በሕጻን አእምሮው በደል መስሎ የታየው ነገር በደል የሚባል ባይሆን እንኳን ትሕትናንና ኃጢአትን መናዘዝ እንዲለምድ ሲባል በጥንቃቄ ማስተናገድ ይገባል።

ከዚህ ባሻገር በተለይ በከተሞች አካባቢ የሚያድጉ ሕጻናት በዕድሜ ብዙም ከፍ ሳይሉ ለኃጢአት የሚጋለጡ ናቸውና *«ምንም አይሠሩም»* ብሎ መደምደምም አይገባም። በተጨማሪም ካህን ልዩ ልዩ ዓይነት የከበደ ኃጢአትን ከተለያዩ ተነሳሒያን የሚሰማ ቢሆንም የአንዱን ከአንዱ እያነጻጸረ *«የአንተ ቀላል ነው አንተማ ምን አደረግህ . . . »* እያለ ብዙ ያልበደሉትን ማደፋፈር የለበትም። በሕጻንነቱ ንስሓ የሚገባን ልጅ ካህኑ ገና ሕይወቱ በኃጢአት ሳይቆሽሽ ሊጠበቀው ይችላል።

❖ በዘርና በቋንቋ አስመልክቶ

ካህናት ለሕዝቡ ሁሉ አባት ይሆኑ ዘንድ የተሾሙ ሁሉ *«አባ አባት»* የሚላቸው ናቸው። ይህን የብዙኃን አባትነት ለመወጣት ደግሞ ከወገንተኝነት መላቀቅ ያስፈልጋል። የጉራጌና ሐድያና ስልጤ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ በአንድ መንፈሳዊ

መጽሔት ላይ ከጻፉት ጽሑፍ ላይ ያነበብኩትን ሀሳብ እዚህ ላይ ባነሣው የበለጠ ነገሩን ግልጥ ያደርገዋል። አብራም (አበውኑዳን /የጥቂቶች አባት/) የነበረው አብርሃም (አበ ብዙኃን /የብዙዎች አባት/) ለመሆን የአባቱንና የዘመዶቹን ሀገር እንደተወ የብዙ ምእመናን አባት የሚሆኑ በየትኛውም የክህነት መዓርግ ያሉ ካህናትም አባትነታቸውን ለመወጣት ከወገንተኝነት መላቀቅ ያስፈልጋቸዋል።

ካህን መንፈሳዊ አገልግሎትን ለመስጠት ዘር የሚለይ ከሆነ ለማስተማርም ፣ ለመባረክም የሚመርጠውና የሚንቀው ካለ የክርስትናን ጽንሰ ሐሳብና የኩላዊት ቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ ያዛባል። «የመንግሥቱ ሰማይ ዜጎች ናችሁ!» ብሎ ለምእመናን ለማስተማርስ እንደምን ይቻለዋል?

ካህን የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ የሚንቀው ዘርና ወገን የለም። ለቅዱስ ጴጥሮስ እንዳሳየው፦ «በራሱ ሰማይ ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ። በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም ፣ በምድር የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት ፤ *«ጴጥሮስ ሆይ ተነሳና አርደህ ብላ!»* የሚል ድምጽ ወደ እርሱ መጣ ጴጥሮስ ግን፦ *«ጌታ ሆይ አይሆንም! አንዳች ርኩስ የሚያደርገውም ከቶ በልቼ አላውቅምና»* አለ። ደግሞም ሁለተኛ *«እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው!»* የሚል ድምጽ ወደ እርሱ መጣ ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ። ወዲያውም ዕቃው ወደ ሰማይ ተወሰደ።» (ሐዋ ፲፥፲፩-፲፮)

ይህ ራእይ አንዳንዶች አለቦታው እንደሚጠቅሱት ስሌላ የታየ ሳይሆን የቅዱስ ጴጥሮስን አመለካከት ለማረም የታየ ነው። በአራት ማዕዘን የተያዘው መጋረጃ በአራቱ ወንጌላውያን የተጻፈች የወንጌል ፤ እንስሳቱም፤ አእዋፍ - የነቢያት የካህናት ፤ አራዊት- የምዕመናን

አሕዛብ ፤ እንስሳት- የምእመናነ እስራኤል ምሳሌ ናቸው። «አርደህ [9]ብላ» ማለቱ «አሕዛብን አስተምር!» ሲል ነው ሁሉም ሲያርግ ማየቱ እስራኤላዊውም አሕዛቡም ያመኑ ሁሉ በአንድነት መንግሥተ ሰማያት የመግባታቸው ምሳሌ ነው። ይህን ሲያስረግጥም በቁጥር ፭፰ ላይ «ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ለው ርኩስና የሚያስጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ» በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ ተናግሮአል። ስለዚህ ቃለ እግዚአብሔርና መንፈሳዊ አገልግሎት የማይገባው ወገን / ጎሣ የለምና ዘር ሳይለዩ አስተምሮና መክሮ ለመንግሥተ ሰማያት ማብቃት የመምህራን ኃላፊነት ነው።

❖ በምግባር ስለመለያየት

ከምእመናን ወገን በጎዎች እንዳሉ ሁሉ ምግባራቸው ያልቀና ፤ መንፈሳዊነት የሌላቸው ፤ አለባበሳቸው ፤ አነጋገራቸው አኗኗራቸው ሁሉ ከሥርዓት የወጣ የሆኑ አሉ። ካህናት የእነዚህም ሁሉ አባቶች ናቸውና ሳይጠየቁና ሳይንቁ ማስተማር አለባቸው። የምእመኖንን ሕይወት ማስተካከል ፤ የተቃናውን ብቻ ሳይሆን የተጣመመውንም ማቅናት የካህን ድርሻ ነው።

ጌታችን በወንጌል «ሕመምተኞች እንጂ ባለጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም . . . ኃጢአተኞችን ወደ ንስሓ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም» በማለት እንደተናገረ (ማቴ ፱፥፲፪) በኃጢአት ድውያነ ነፍስ የሆኑትን መቀበልና ፈውስን መስጠት የካህናት ሐላፊነት ነው። ስለዚህ በበጎ ምግባር የጸኑትን ብቻ ሳይሆን በጎ ምግባር

[9] መብላት በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ‹ማስተማር› ተብሎ ይተረጎማል። ለምሳሌ ጌታችን በዮሐ፬፥፴፪-፴፬ ላይ ‹‹እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል አለኝ›› ሲል ማስተማሩን መብላት ብሎታል። በመጽሐፈ ኢሳይያስም ‹‹ቅቤና ማር ይበላል›› ተብሎ የተጻፈው ብሉይና ሐዲስን ያስተምራል ተብሎ ይተረጎማል። /ኢሳ.፯፥፲፭/

የሌላቸውንም የጊዜው ድክመታቸውን ታግሰው በየውሀት መንፈስ ሊያቀኑ ይገባል። ሐኪም ጤነኞችን ብቻ ካልሆነ በጣምታመመውትን አሳክምም ካለ ሐኪምነቱ ትርጉም ያጣል። ክህነትም ጥሩዎችን ብቻ ልጅ አድርጎ እየያዘ ብልሹዎችን ከሸሸ የአባትነቱ ትርጉም ያጣል። ኃጥእን ከጻድቅ ምእመንን ክመናፍቅ ሳይለይ ዝናብና ፀሐይን የሚያወጣ አምላክ አገልጋይ መሆኑም ያጠራጥራል። /ማቴ. ፭፥፵፭/

[10]ሙሽራው ክርስቶስ በገዛ ሥጋና ደሙ ዕድምተኞችን በሚጋብዝባት ሰርግ ቤት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከሰርጉ ይታደሙ ዘንድ የሚጠሩት በሠርጉ ቤት መንገድ ላይ ያሉ ሁሉ ናቸው። እንዲህ ተብሏልና «*እንግዲህ ወደ መንገድ ሄዳችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሠርጉ ጥሩ አለ እነዚያም ባሮች ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን ሁሉ ክፉውችን በጎዎችንም ሰበሰቡ። የሠርጉንም ቤት ተቀማጮች ሞሉት*» (ማቴ ፳፪፥፱-፲) በዚህ ኃይለ ቃል «*ክፉዎችን በጎዎችንም ሰብስቡ*» የሚለው ሐረግ የበለጠ ክላይ የተገለጠውን ሀሳብ ያብራራዋል በምግባራቸው ክፉ የሆኑትንም ጥሩአቸው ማለት ነውና። ስለዚህ ካህናት ድኩማኑንም ወደ መንፈሳዊው ማዕድ ሊጠሩ ይገባል። ከዚህም አልፎ «ለደካሞች እጠትም ዘንድ ደካማ ሆንሁ» እንዳለ ሐዋርያው የደከመውትን ክሸክማቸው በማሳረፍ በርኅራኄ እንዲጠቅመአቸው ከካህናት ይጠበቃል።

❖ በምድራዊ ክብር ስለመለያየት

ለዚህች ዓለም ኑሮ በለጋች መካክል በምድራዊ ሀብት ፤

[10] ‹‹መኑ ዘርእየ መርዓዊ ዘይጠብህ ሥጋሁ በጊዜ ክብክቡ ለዘይትበላዕ ለግሙራ›› ‹‹በገዛ ሥጋው ዕድምተኞቹን የሚጋብዝ ሙሽራን ያየ ማን ነው›› ሥርዓተ ቅዳሴ መግቢያ

በምድራዊ ሥልጣንና በምድራዊ እውቀት ልዩነትና መበላለጥ ይኖራል። ይህም ለብዙ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ችግሮች መንሥኤ ይሆናል። በተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም ሆነ በየትኛውም ሥፍራ የሚሰጠው አገልግሎትና መስተንግዶ እነዚህን ምድራዊ ነገሮችና የሰዎችን አፍአዊ ገጽታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ይህ የዚህች ዓለም ሕግ ነው።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሥጋ ያይደለ የነፍስ አገልግሎት የሚገኝባት መንፈሳዊት ሥፍራ ናት። በውስጧም ያሉ አገልጋዮች መንፈሳውያን እንደሚሆኑ ይጠበቃል። በሥጋ እንጂ በነፍስ መበላለጥ የለምና ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ አገልግሎትም ያለ ማበላለጥ ሊሰጥ ይገባል። አገልጋዮች ካህናትም ሆኑ መምህራን ሰዎችን በምድራዊ አቋማቸው ፣ በሀብታቸው ፣ በሥልጣናቸው ሳይሆን በነፍሳቸው ተመልክተው ማገልገል ይጠበቅባቸዋል።

ካህኑ ባለጠጋው በጎ ነገር ሲናገር «አያችሁልኝ ይህን የመላእክት ቅዳሴ!» እያለ እያደነቀ፣ ክፉ ሲናገር ደግሞ «ጌታው እንጂ እንዲህ ማለታቸው ነው!»እያለ ነገሩን እያቃናለት ፣ደሃውን ግን በጎ ሲናገር «እዩት አሁን እኮ በጎ የተናገረ መስሎት ነው » እያለ ነገሩን እያቃለለ ክፉ ሲናገር ደግሞ «እግዚአብሔር ያጥፋህ!» እያለ የሚኖር ከሆነ *«ወኢትሣኦ ብኩርናከ እንበይነ መብልዕ / ለምግብ ብለህ ብኩርናህን* (ክብርህን) አትሸጥ» የሚለው ቃል ይወቅሰዋል። (ሃይ.ዘሠሊ. ፳፭፥፳)

መጽሐፍ ቅዱስም ደሃውንም ሀብታሙንም የፈጠረ አንድ እግዚአብሔር መሆኑን ለማዘከር «ሁላችንም አንድ አባት ያለን አይደለንምን?» በማለት ይገሥጸዋል (ሚል.፪፥፯) መምህረ ወንጌል ካህን ሆኖ ሳለ ለዚህ «ጎልፈቱ ቅድመ አስተርእዮቱ» ለሆነ ብዕለ ዓለም

(ማለፉ ከመታየቱ በፊት ለሆነ የዚህ ዓለም ሀብት) ከተገዛ እንደምን ለምእመናን ዓለምን ስለመተውና ለመንግሥተ ሰማያት ሲሉ መከራን ስለ መቀበል ሊያስተምር ይችላል?

አንድ ካህን እየሔደ የሚጎበኘው ፣ ጠበል የሚረጨው ፣ ሲታመሙ የሚጠይቀው ፣ ሲሞቱ የሚያጽናናው ባለጸጎችን ብቻ ከሆነ ምእመናን ለካህናት ያላቸውን አክብሮት ይቀንሰዋል። ለድሆች ፊት እየነሣ ባለጸጎች ፊት የሚሽቆጠቆጥ ካህን ክብሩን እያዋረደ ነው። ምንም ላይሰቀምም ክብሩን ያጣል። እንደ አንድ ቄስ፦

አንድ ባለጠጋ ታምሞ ሰሞት ደርሶ ሳለ ይህ ካህን ከዚህ ሰው ላይለይ *«አይዞህ አትሞትም! ብቻ ገንዘብህን ተናዘዝ»* እያለ ይወተውተው ነበር። በዚህ ሰዓት አንዲት ደሃ ባልቴት ልትሞት እንደሆነና ሥጋ ወደሙን እንዲያቀብላት መልእክት ይደርሰዋል። ይሁንና ይህ ካህን *«እንዴት ይህን የከበረ ሰው ትቼ እሄዳለሁ?»* በማለት ይመልሳል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህች ባልቴት ሥጋ ወደሙን ተቀብላ በክብር አረፈች። ካህኑ ግን ደጅ የጠናው ባለጸጋ ምንም ሳይሰጠው ሞተ ከድካምም በቀር ያገኘው ነገር አልነበረም። ነገር ግን ያጣው ክብርና የሚጠብቀው ቅጣት ብዙ ነው። ተአምሩም ሲያበቃ «ወውእቱሰ ቀሲስ አልቦ ዘረከበ ወኢምንተኒ ዘእንበለ ጻማ ወድካም›› ‹‹ይህስ ካህን ከድካምና መከራ በቀር ምንም አላገኘም›› ይላል። (ተአ.ማር ፩የ፱፫)

ካህን በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በምድራዊ እውቀትና በሥልጣን ከፍ ያሉ ሰዎች ቢገጥሙት ከክህነት የሚበልጥ ክብር የለምና ከትሕትና ባሻገር በበታችነት ስሜት ሊሸቆጠቆጥና ማዕርጉን ሊጥል አይገባም። ክብሩን አዋርዶ ቢቀርባቸው ይወድዱኝ ያላቸው ይንቁታል። በሥጋዊ

ነገር የከበሩ ሰዎችን ካህኑ እንደማንኛውም ምእመን ሊመለከታቸው ያስፈልጋል።

ለምድራዊ ሀብትና እውቀት የተጋነነ አድናቆት ያለው ካህን በእርሱ አባትነት የንስሓ ልጁ መኩራት ሲገባው እርሱ በንስሓ አባትነቱ ኮርቶ «እገሌ እሰ የእኔ ልጅ ንስሓ ልጅ ነው!» እስኪል ይደርሳል። ይህም ክብርን አለማወቅ ነው። ካህኑ ሲማር የኖረውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዝቅ እያደረገና እየተቆጨ ምድራዊውን የምእመኑን እውቀት እያደነቀ የሚናገር ሲሆን አድማጭ ክህነትን ንቆ እንዲመለከት ያደርገዋል። ከዚህም አልፎ ምድራዊ ክብር ያላቸውን ሰዎች በሆነ ባልሆነው የሚያወድስና የሚመርቅ ‹‹ጻድቁ ! ትልቁ!›› እያለ መወድስ የሚያበዛ፣ ባለጸጋ በሞተ ቁጥር ‹‹ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር›› የሚል ከሆነ የያዘው አባትነት ነው ወይንስ ባርነት ያስብላል። ዘመነኞችና ፈዘኞችም በካህናት እንዲቀልዱ በርን ይከፍታል።

፩. የንስሐ ልጆችን ሕይወት መከታተል

መምህረ ንስሓ ምእመናን የተጫናቸውን የኃጢአት ሸክም በሥልጣኑ ካራገፈላቸው በኋላ ዳግመኛ ሸክም እስኪጭኑ ድረስ ሊተዋቸው አይገባም። ቀስ በቀስ ከኃጢአት እየተለዩና የኃጢአትን ምንጭ እያደረቁ በመንፈሳዊ ሕይወት የሚበረቱበትና ትሩፋትን የሚሠሩበትን መንገድ መቀየስ ይጠበቅበታል።

በትሕትና ተንበርክኮ የደቀመዛሙርቱን እግር ያጠበ ጌታችን ማጠብን ብቻ ሳይሆን ማበሻ ጨርቅ ይዞ ማድረቅንም አሳይቶአልና ካህኑም አንድን ተነሳሒ ቀኖናውን አስፈጽሞ ኃጢአቱን ካጠበው በኋላ

በኃጢአት የራሱ ማንነቱን እስኪያደርቅለት ድረስ ሊተወው አይገባም። የዲያብሎስን ፈተና የሚቋቋምበትን መንገድ እየጠቆመው በየጊዜው ሊከታተለው ይገባል። ከነአመም «የነፍስ አባት» ነውና ሥጋ ሠልጥኖ ነፍስ ተንድታ እንዳትኖር እየተከታተለ መንከባከብ ይገባዋል።

ዘር የዘራ ሰው ካላረመውና ካልኮተኮተው አይሆንም ፤ ካህኑም የንስሓ ልጆቹን ካልተከታተለ ዋጋ አይኖራቸውም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቅዱስ በርናባስ እንዲህ ነበር ያለው፦ «ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ ወንድሞችን እንንብኖቸው እንዴት እንዳሉም እንወቅ» (ሐዋ ፲፭፥፴፮)

በተለይ «እንዴት እንዳሉም እንወቅ» የምትለዋ ሐረግ ካህን የልጆቹን ወቅታዊ መንፈሳዊ አቋም በየጊዜው መገምገም እንደሚገባው ያስረዳል። ዕለት የማያደርሰውና ልጆቹን በቅርበት ለመከታተል የማይችል መምህረ ንስሓም ቢሆን ለሌላ መምህር አስካላስረከበ ድረስ በመልእክትም ቢሆን አቅሙ በሚፈቅድለት መገናኛ ዘዴ የልጆቹን መንፈሳዊ ሕይወት መከታተል ይኖርበታል።

ቅዱስ ጳውሎስ «ፈታኝ (ዲያብሎስና ቢጽ ሐሳውያን) ምናልባት ፈትኖአቸው ድካማችንን ከንቱ ሆኖ ይሆንን?» ብሎ እምነታቸውን ለማወቅ ጢሞቴዎስን ወደ ተሰሎንቄ ምእመናን እንደላከ «ጻድቅ ለእንስሳው ነፍስ ይራራልና» አባባዕ ምእመናንን የሚመራ እረኛ ካህን የሚያሻቸውን አውቆ በየጊዜያቱ የሚያስተምር የሚመክር ሊሆን ይገባል። (ምሳ. ፲፪፥፲)

አንድ ባለ መድኃኒት አንድን በሽተኛ ሰው ሊያድን ቢደክምና ዋቂት ሲሻለው ፈጽሞ ሳይድን መድኃኒት ማድረጉን ችል ቢል ትጋቱ ሁሉ ከንቱ ይቀራል። በሽተኛውም ሕመሙ አገርሽቶበት ሊሞት

ይችላል። እንዲሁም መምህረ ንስሓ በደዌ ነፍስ (በኃጢአት) የተያዘን ምእመን በንስሓ ከመለሰው በኋላ መንከባከቡን ጀምሮ ቢተወው ያ ተነሳሒ ዳግም ወደ ቀደመ ግብሩ ይመለሳል። ዳግመኛም ወደ ንስሓ የመመለስ አዝማሚያው የጠበበና ለመንፈሳዊ ሕይወት የሚኖረው ሥዕልም «የተወሳሰበና አስቸጋሪ» የሚል ይሆናል። ስለዚህ መምህረ ንስሓ ለተነሳሒው የማያቋርጥ ክትትልን ማድረግ ይኖርበታል።

፩. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማስከበርና ሳይፈሩ መገሠጽ

ሠራዒ ሥርዓት (ሥርዓትን የሠራ) ኢየሱስ ክርስቶስ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን መመሪያ ይሆን ዘንድ የሰጠውን ሥርዓት ያስከብሩ ዘንድ ያቆማቸው ዐቃብያነ ሕግ ካህናት ናቸው። መጽሐፍም «ካህናትን ስለ ሕጉ ጠይቅ» ይላል። (ሐጌ ፪÷፳) መምህራነ ንስሓ ካህናት ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማክበርና ምእመናን እንዲያከብሩ ማስተማሮና መከታተል አለባቸው።

ካህን ምእመናን ሥርዓትን ሲጥሱ ዝም ብሎ መመልከትም ሆነ ፣ እንዲያፈርሱ ማደፋፈር የለበትም። ለምሳሌ በፍትሐ ነገሥት ላይ «ከቀሳውስትና ከዲያቆናት ወገን አንዱስ እንኩዋን ተደፋፍሮ ከደሚ ያልነጻችውን ሴት ሥጋ ወደሙን ያቀበላት ከመዓርጉ ይሻር» የሚል ቃል ተጽፎ ይገኛል። (ፍ.ነገ.አ ፮)

ይህ ኃይለ ቃል በወር አበባ ወቅት ሥጋ ወደሙን መቀበል የማይገባ እንደሆነ ፣ ይህን ሊያውቅ ተደፋፍሮ ሥጋ ወደሙን ከግዳጅዋ ላልነጻች ሴት የሚያቀብል ካህን ቅጣት እንደሚገባው ያስረዳል። ይሁንና ከወር አበባ ባሻገር ሌሎች ወደ ሥጋ ወደሙ ከመቅረብም ሆነ የቤተ ክርስቲያንን ምሥጢራትን ከመፈጸም የሚከለክሉ ነባራዊ ሁኔታዎችን

አያውቅ የሚያልፍ ካህን እንደሚቀጣ ለመረዳት ይቻላል።

መምህረ ንስሓ የሆኑ ካህናት አንዳንድ ጊዜ ለልጆቻቸው ካላቸው በጎ ምኞትና ቶሎ ፍሬን ለማግኘት ከሚኖራቸው ጉጉት ለሥጋ ወደሙም ሆነ እንደ ተክሊል ላሉ መንፈሳዊ ምሥጢራት ገፋፍተው ያለ አውቀት እንዲገቡ ሊያደርጓቸው ይችላሉ። ይህ ግን ተገቢ አይደለም። ሳያለሰልሱ መዝራት ፍሬ እንደማይሰጥ ሳያስተምሩ መንፈሳዊ ምሥጢራትን ማስፈጸምም መንፈሳዊ ፍሬን አያስገኝም።

ለምሳሌ ምእመናን ስለ ሥጋ ወደሙ ምሥጢር ሳይረዱ ሥርዓቱንም ሳያውቁ ቢቀርቡ ዕዳ ሊሆንባቸው ይችላል። ሥጋ ወደሙን ለመቀበል በመጡ ጊዜ *ክታላቅ ሉዳራሽ ንብተን ሰንዴ ዳቦ በልተን የወይን ጠጅ ጠጥተን ሔድን* እንዳይሉ ጎብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደሙ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር እንደሚሆን ሊያስተምራቸው ይገባል። «የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና» (፩ኛቆሮ.፲፩÷፳፱) እንዳለ ሐዋርያው።

ካህኑ ሳያስተምር ምእመናኑ የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታ እንደሚያሟሉ ሳያደርግ መንፈሳዊ ምሥጢራትን (እንደ ተክሊል ፣ ቁርባን) ያስፈጸማቸው ምእመናን በኋላ የማይገባ ኑሮ ውስጥ ቢገቡ እንኳን «ሳላውቅ ተገፋፍቼ የገባሁበት ነበር ፣ እንዲህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ አልገባበትም ነበር» ሊሉ ይችላሉ። ካህናት የሥጋ ወደሙ አጋፋሪዎች ናቸውና እንደቅዱስ ዲሜጥሮስ በቅተው ኃጥኡን ከጻድቁ መለየት ባይችሉ ምእመናን በንስሓ ታጥበው፣ ምሥጢሩን ተረድተው እንዲቆርቡ ማድረግ ይገባቸዋል። መዓርገ ቅስና በሚሰጥ ጊዜ የሚገባውም ቃል ናህኑ ለሥጋ ወደሙ የታመነ እንዲሆን ያዝዛል። ካህኑን በሰማይ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ እንዲጠብቅ በቆመው በኪሩብ የሚመሰለው ሲሆን እውነተኛው የሕወት ዛፍ የሆነ

የጌታን ሥጋና ደም የማይገባው ሰው እንዳቀበል ካህኑ የመስቀልን ስይፍ ይዞ መጠበቅ ሐላፊነቱ ነው። ይህ ሲባል ማናችሁም ፈጽሞ ሥጋ ወደሙን አትቀበሉ እስከማለት እንዲደርሱም አይደለም።

መምህረ ንስሓ ርኅራኄን ማሳየትም ሆነ ምእመናንን ማቅረብ ያለበት ያልተሰጣቸውን መብት በመስጠት አይደለም። ካህኑ በራሱ አስተያየት የሚሰጣቸው ከሥርዓት ውጪ የሆነ መብት መሰጠት የሚገባው ቢሆን ኖሮ «በድካማችን የሚራራልን» የተባለለት ሊቀ ካህናት ክርስቶስ በሥርዓት ውስጥ እንዲኖር ባደረገ ነበር። ሁሉን የሚያውቅ ፈጣሪ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ከሠራው ውጪ ካህኑ «ለምእመናን የራራ» መስሎት መብት ቢሰጥ ግን «ከፈጣሪ በላይ ለምእመናን አዛኝ ነኝ» እንደ ማለት ነው።

እንግዲህ ካህን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ጥሶ የማይገባቸውን መብት ለምእመናን መስጠት አይገባውም፤ አይችልምም። ስንል ለምሳሌ ቅድመ ጋብቻ ሩካቤን መፍቀድ ፣ እጮኛሞችን ከተክሊል በፊት (ባልተሠራ ሥርዓት) ማማማል ፣ ተነሳሒያን የሚናዝዙትን ኃጢአት «ይሀችማ ምንድር ናት?» እያሉ ኃጢአትን ቀላል እንደሆነ ማሳሰብ ፣ በመቅረጸ ምስል (ቪዲዮ ካሜራ) ሊቀረጹ የማይችሉ መንፈሳዊ ሥርዓቶችን ና ምስጢራትን እንዲቀረጹ መፍቀድ የመሳሰሉት ቀሰል ያሉ ማሳያዎች ናቸው።

በምእመናን ዘንድ መንፈሳዊ ዝለትና ሥርዓትን መጣስ በሚከሰትበት ወቅት መምህረ ንስሓ የሆኑ ካህናት ጠንክር አድርገው የመገሰጽ መብትና ግዴታ አለባቸው። ካህናት የሚገሥጹት ምእመን ንጉሥ ፣ ባለጸጋ ፣ ባለሥልጣንም ሊሆን ይችላል። ይሁንና መከረውና

ገሥጸው ከክፉ መንገድ ባይመልሱት «ደሙን ከእጅህ እፈልጋለሁ» ብሎ የሚጠይቃቸው አምላክ አለና ሳይፈሩ ሊገሥጹ ይገባል። (ሕዝ ፫፥፲፰) ተግሣጽ አልቀበልም ባይም ከሆነ አባትነትን እስከ መተውና «ከደምህ ንጹሕ ነኝ» እስከ ማለትም ወዳጅነትን ፣ ጥቅምን ፣ አጣለሁ ሳይሉ እስከ ማውገዝም ሊዘልቅ ይችላል።

ተግሣጻቸውን ባይሰማ ሚማቸውን እያራገፉ «እኛ ደከምንላችሁ በእምቢተኝነታችሁ ቀረባችሁ» እንዳሉ ሐዋርያት ተመክሮ የማይሰማን ሰው በጊዜ ማሰናበት ይገባል። ነቢይ «*ቦኑ ዘየሐርስ ፈቃሁ አሚረ ሖሐርስ / የሚያርስ ሁልጊዜ ያርሳልን?*» (ኢሳ፳፰፥፳፬- ትር) እንዲል በትዕግሥት የሚገባውን ከመናገር በኋላ አልሰማ ያለውን መወትወት ንቀትን ማትርፍ ነው። ይሁንና ካህን የነፍስ ልጁ የሆነውንም ያልሆነውንም ምእመን በክፉ ግብር ሲያገኘው ቢሰማውም ባይሰማውም የመገሰጽ ግዴታ ግን አለበት።

ብፁዕ አባታችን አቡነ ቀውስጦስ «ይግባኝ ለክርስቶስ» በሚል ደንቅ መጽሐፋቸው ላይ ያሰፈሩት ሀሳብ ይህን የበለጠ ያጠናክርልናል። የማይገባ ሥራ የሚሰሩትን ሁሉ ሳይፈሩና ሳያፍሩ መገሠጽ የካህናት ኃላፊነት እንደሆነ ከገለጡ በኋላ «ፀሐይ የሚሞቀኝ የለም ብላ ከመውጣት ፣ወንዝም የሚጠጣኝ የለም ብሎ ከመፍሰስ እንደማያቋርጥ ሁሉ መምህራንም የሚሰማን የለም ብለው ዝም ማለት የለባቸውም፡ጌታ ባይሰሙም ለአይሁድ ነግሮአቸዋል» ብለዋል (ይግባኝ ለክርስቶስ ገጽ ፶፰)

ካህን ለተግሣጽ እንዳይቸገር አስቀድሞ ከተነሳሒያኑ ጋር የዝምድናም ሆነ የጥቅም ትስስር ባይኖረው ይመረጣል። ምክንያቱም

ኃላ ችግር ሲከሰት ፣ ሃይማኖት ሲጎድል ፣ ሥርዓት ሲፈርስ ውለታን ማሰብና ይሉኝታ ይመጣል። ዝምድና ያለው ከሆነ «የዘመድ ቁስ ሲፈታ ያለቅስ!» እንዲሉ ጠንክሮ ለመገሠጽና ቁርጥ ውሳኔን ለመስጠት ሊያቅተው ይችላል። ቀደምት ኢትዮጵያውያን ካህናት የምእመናንን ቤት ጠበል የሚረጩት አርብና ረቡዕ እንዲሁም በጾም ቀን ነበር። ይህን የሚያደርጉት በነጻነት ከመገሠጽና ከማስተማር የሚከለክላቸው ነገር እንዳይኖር ነበር።

የጥቅም ትስስር ደግሞ ከዝምድና የባሰ ነው። ኢሳይያስ ነቢይ ንጉሥ ያዝያንን ለመገሠጽ እንቅፋት የሆነበት ግብረ በል መሆኑ አይደል? ይህ ነቢይ የምድራዊ ንጉሥን ግርማ ፈርቶ ቤተ መቅደስን ሲዳፈር ዝም ብሎት ነበር።ለዚህም ነው ንጉሡ ያዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔር «የፈራኸው ንጉሥ ሞተ እኔ ግን በዙፋኔ አለሁ!» ሲል ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ሆኖ የታየው።(ኢሳ፮÷፩ትር.)

ክፉ ነገር ሲደረግ አይቶ ዝም ማለትም በካህን ላይ ፍርድን ያመጣል። «የሚፈረድበትም የበደለ ብቻ አይደለም። ኃጢአት ሲሠራ አይቶ ዝም ያለውም ነው እንጂ። እርሱ የበደለ ሆኖ አይደለም አይቶ ዝም ስላለው ነው እንጂ ፣ በኃጢአቱም መስለው በእንዲት ፍርድ ይፈረድባቸዋል።» (ሃይ.ዘሠለስቱ ምዕት ፮)

መንፈሳዊ ሽመትን «ሽህ ሞት» የሚያስኝውም ይኸው ነው። ካህን ለራሱ ምንም ጻድቅ ንጹሕ ቢሆን እንኳን ተግቶ ካላስተማረ በሕዝቡ ኃጢአት ይፈረድበታልና ነው። ካህኑ ዔሊ በልጆቹ ምክንያት እንደ ሞተ መምህረ ንስሓውም በልጆቹ በደል ይጠየቃል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ «ወኢይኩኑ አምውስቴትክሙ ብዙኃን መምህራን ፣

አኃዊነ ተአምሩ ከመ እንተ ተዓቢ ደይነ ንህነሰ / ወንድሞች ሆይ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁ።» (ያዕ ፫÷፩) በማለት በመልእክቱ እንደተናገረ መንፈሳዊ ሹመት ትልቅ ኃላፊነትና ዕዳ ነው። አባ መቃርዮስ የተባለ ሊቀ ጳጳስ ከወላጅ እናቱ የተማረውም ይህንን ነበር።

ይህ አባት በሕጻንነቱ መንኖ (ዓለምን ንቆ) ወደ ገዳም ይገባል። ኃላ መብቃቱን አይተው ለአስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ አድርገው ሾሙት። እናቱን «የምሥራች ተሾምሁ!» ብላችሁ ንገሯት ብሎ መልእክተኞችን ላከ። ሄደው ቢነግሯት ቀና ብላ መልስ ሳትመልስላቸው ቀረች። ተመልሰው ሄዱ። «ምን ብላ ነው?» ብሎ አልባስ ሊመቱን (የሹመት ልብሱን) ለብሶ ማኅበሩን አስከትሎ ሄደ። «እናቱ ተሾምሁ!» አላት። ቀና ብላ ሳታየው ቀረች። «ምነው አላወቅሽኝም ልጅሽ አቡ ነኝ» አላት።

እርሷም «አንተ አላወቅህም እንጂ እኔስ አውቄሃለሁ ፣ ዛሬ በሹመት ልብስ አጊጠህ ካይህ (ከማይህ) በልብሰ መንነዝ ተተብትበህ ወደ መቃብር ስትወርድ ባይህ ይሻለኝ ነበር» አለችው። ደንግጦ «ምነው እናቴ?!» አላት። «እስከ አሁን የምትጠየቀው በራስህ ኃጢአት ብቻ ነበር ፣ ከእንግዲህማ በሕዝቡ ሁሉ ኃጢአት ሊፈረድብህ አይደለምን?» አለችው። «ይህ የእናቴ ቃል ተግሣጽ ሆኖኝ እስክሞት ድረስ ከማስተማር አላርፍም!» ብሏል።

ካህን በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ውጪ ምንም ነገር ሲፈጽም ከተመለከተ ወኪልነቱ የቤተ ክርስቲያን ነውና ጠንክሮ መገሠጽ ፣ ሰማ ካጣም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ «ከደሙ ንጹሕ ነኝ» ማለት ይገባዋል። (ሐዋ. ፲፰÷፮) «ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት እንደ አረመኔና ቀራጭ ይሁንልህ» (ማቴ ፲፰÷፲፯) ተብሎ እንደ ተጻፈ የቤተ ክርስቲያን

አባቶችን የማይሰማ ከሆነ ቤተ ክርስቲያንን አልሰማምና ከዚያ ሰው ጋር መተባበር አይገባም።

በፍትሐ ነገሥት ላይ «አኅትማማቾችን ወደ አገበ ሰው ሰርግ ቁሱ ለምሳ አይሂድ» የሚል ቃል ተጽፎአል። ይህ ትእዛዝ ከላይ ሲታይ አንድን ድርጊት አስመልክቶ የተነገረ ቢመስልም በውስጡ ግን ብዙ መልእክት ያስተላልፋል። «አኅትማማቾችን ማግባት» በክርስትና የተከለከለ ነው። ይህን የፈጸመ ሰው ጋብቻ ላይም መታደም ለካህን አይገባም።

ከዚህም አልፎ በጋብቻ ሥርዓት ላይ ሌሎች በርካታ የተከለከሉና መፈጸም የሌለባቸው ነገሮች አሉ። እነዚህን የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች እያወቀ የሚጥስ ሰው ሰርግ ላይ መገኘትም ለካህን አይገባም። ለምሳሌ በሥጋ ወደሙ መፈጸም የሚገባውን የጋብቻ ሥርዓት «በዓለማዊ መንገድ ካልፈጸምን» የሚሉ ምእመናን ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ወቅት ካህኑ የሚገባውን ተግሣጽ ከተናገረ ወዲያ ባይሰሙት ተቶ መሄድ ይኖርበታል እንጂ «ካላችሁ ይሁን» ብሎ ከሰርጉ ታድሞ በሚዘፈንበት መድረክ ጸሎት ሊያደርስ የሚቆም ሊሆን አይገባም።

ለዚህ ታሪክ በቀጥታ አርአያ የሚሆኑ አንድ አባትን ልንጠቅስ እንችላለን «መምህር ወመገሠጽ ዘኢያደሉ ለገጽ» ባለው ሐዋርያዊ መጠሪያ የሚወሱት አቡነ አንድርያስ ቀዳማዊ የንጉሡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ቤተሰብ የሆነች ልጅ በዓለማዊ ሰርግ ስታገባ በዓለማዊ ሰርግ አልታደምም ብለው መቅረታቸው ለካህናት ትልቅ ምሳሌ ነው።

ሕገ ቤተ ክርስቲያንን አልከተልም የሚል ካለ ንጉሥም እንኳን

በሆን ካህን ሊገሥጸው ይገባል። የካህኑ ሥልጣን ከንጉሡ ይበልጣልና። በ፲፫ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የተፈጸመው ክስተት ልብ የሚነካ ነበር። አጼ ዓምደ ጽዮን ከአባቱ ዕቁባት መካከል አንዷ የነበረችውን «ገድለ አሮን» (ዛንመንገሳ) የምትባል [1]ዕቅብት «በሚስትነት ካልያዛት መንግሥቱን እንደማይጸና» ጠንቋዮች ነግረውት ነበር። የእነርሱን ቃል የያዘው ንጉሥ ሴቲቱን በሚስትነት ይሏት መኖር ጀመረ።

በወቅቱ የነበረው ጳጳስ አባ ያዕቆብ ቢገሥጸውም ከጠንቋዮች በተሰጠው ክፉ ምክር የተሞላው ጦረኛ ንጉሥ «ያልወለደችኝን ባገባ የሚከለክለኝ የለም!» በማለት አሻፈረኝ አለ። ኋላ ይህ ንጉሥ በሥርዓተ ቅዳሴ ጊዜ ሥጋ ወደሙን ሊቀበል ሲመጣ በወቅቱ ሠራዒ ካህን የነበረው ጳጳሱ አባ ያዕቆብ «የተቀደሰውን ለውሾች አልሰጥም!» በማለት ገሥጾ መለሰው። አብረው የነበሩት ካህናትም የጳጳሱን ቃል ተቀብለው ተናገሩ።

ንጉሥ ዓምደ ጽዮን እሊህን ቀሳውስት ጠርቶ ግብጻዊውን ጳጳስ እንዳይሰሙ ቢያስፈራራቸው በንጉሡ እንሾም እንሽለም ሳይሉ «መኻታህን ያረከሰህ ነህ!» በማለት መልሰውለታል። በሥርዓተ ቅዳሴም ስሙን አንጠራም አሉ ፤ መከራን ቢያጸናባቸውና ቢያሥራቸውም ካህናቱ ግን ጽኑዓን ነበሩ። በተለይ ከጳጳሱ ቀጥሎ ንጉሡን የገሠጸው ካህን አባ አኖሬዎስ ብዙ ስቃይ ጸንቶበት ነበር። በስተ መጨረሻ በካህናቱ ጥበዓትና ጽንዓት ንጉሡ ተጸጽቶ ተመልሷል።

«አ ካህን ለእመ ርኢከ ዕውቀ ኃጢአቶ ለብእሲ ኢያፍርኅከ

[1] ዕቁባት ብዙ ቍጥር ሲሆን በነጠላ ሲነገር ‹‹ዕቅብት›› ነው።

ሰይፍ ወኢሰደቅ / ካህን ሆይ የታወቀ የሰውን ኃጢአት ብታይ ሰይፍ ወይም ቀስት አያስፈራህ።» (ድርሳነ ጽዮን ዘረቡዕ) እንዲል ፊትን አይተው ሳያደሉ ፣ ዘመን የወለደውን ፣ ንኡሥ የወደደውን ሳይሉ ማስተማርና መገሠጽ የካህናት ሓላፊነት ነው። አቡነ ጴጥሮስ ስማዕተ ጽድቅ ዘኢትዮጵያ መከራን ሳይሰቀቁ ችግርን ተጋፍጠው እውነትን ገልጠው ሰማዕት በመሆናቸው ፣ አቡነ ቴዎፍሎስ ከእህል ውኃ ተከልክለው በገመድ በመሞታቸው ፣ እውነተኛ እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ የሚሰጥ መሆኑን በተግባር አስተምረዋል። ነገሥታቱ አማንያን ባይሆኑ እንኳን አቡነ ቀውስጦስ እንደተናገሩት «እኔ በእነርሱ ሥራ አልገባም እነርሱም በእኔ ሃይማኖት አይግቡብኝ» ማለት ከካህን ይጠበቃል።

በንስሐ ሂደት የምእመናን ድርሻ

፩. መምህረ ንስሐ መያዝ

«ሰውነታችንን መክረን አስተምረን ማኖር እንደምን ይቻለናል?» ብለው በትሕትና በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖሩ ምዕመናን ንዑዳን ክቡራን ናቸው። (ማቴ ፭÷፭) ምክንያቱም የሰው ልጆች ድኩማን (ደካሞች) ናቸውና ሕይወታቸውን የሚመራ መንፈሳዊ አባት ያስፈልጋቸዋል። በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የማኖሩ ሰዎች ኃጢአትን ከመናዘዝ ባሻገር በሥጋዊ ሕይወታቸውም መሪን ያገኛሉ ፣ ያለ ምክረ ካህን የሚኖር ክርስቲያን ያለ ቀዛፊ የሚሄድ መርከብ ነው። ብዙዎች በሕይወታቸው የሚገጥሟቸውን ችግሮች መፍታት ሳይችሉ የሚቀሩት ካህን ስለማያማክሩ ነው። ከስነ አእምሮ ጠበብት ይልቅ ብዙ ጉዳዮች የሚፈቱበት መንፈሳዊ ጸጋ ያላቸው ካህናት ናቸው።

ለምሳሌ ወጣቶች ከዕድሜአቸው አንጻር የሚገጥማቸው ፈተና ብዙ ሊሆን ይችላል። ብሎም ዲያብሎስ የብዙ ወራዙትን (ወጣቶችን) ልቡና «ሁሉን ልፈኒብጥ / ሁሉን ልያዝ» በሚል ስሜት እንዲታወክ ያደርጋል። ረጋ ብለው ካለማስብና በስሜትም ከመገፋፋትም ቀሪ ዘመናቸውን ሁሉ የሚጸጸቱበት ስኅተት ውስጥ እንዲገቡ ይሆናል። ገና ብዙ ሳይኖሩ ሕይወትን እንዲያማርሩ ብሎም ራስን እስከማጥፋት የሚያደርስ ውሳኔ ሳይቀር ይወስናሉ። ነገር ግን ይህ ሁሉ ፈተና በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖሩትን አይነካቸውም።

በማቴ ፮÷፲፰ ላይ ጌታችን የተናገረው ቃል ለዚህ ይጠቀሳል ፦ «ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል ፣ ዝናምም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንንም ቤት ገፋው በዓለት ላይም ስለተመሠረተ አልወደቀም» ይላል። የዚህ ቃል ትርጓሜው ብዙ ቢሆንም አንድም በምክረ ካህን ስለመኖር ጥቅም ያስረዳል። ይህም ለምሳሌ አንድን ወጣት ዲያብሎስ እንደ ነፋስ /ፍራን ከገለባ እንደሚለይ/ በሕሊናው «ንጽሕ ጠብቂ! ከሴት ርቂ! እንደ እንጦንስ መቃርስ መንኜ እኖራለሁ!» ሊያሰኘው ይችላል።

ቆይቶም እንደ ፍሬአማ ዝናማት «እንደ ኢዮብ ፣ እንደ አብርሃም በሕግ ጸንቼ ዘር ተክቼ እኖራለሁ!» ሊያሰኘው ይችላል። ደግሞም እንደሚጠራርግ ጎርፍ «ሁለቱም አይሆንም!» ሊያሰኘው ይችላል። ይህ ወጣት በዓለት ላይ እንደ ተመሠረተ ቤት በምክረ ካህን የሚመራ ከሆነ መምህረ ንስሓው ነገሩ የሰይጣን ጾር እንደሆነ አውቆ «ቆይ! ጹም ስገድ» እያለ ያቆየዋል። አጋንንትን ድል ነስቶ ሕይወቱን እንዲመራም ያደርገዋል። ምክረ ካህንን ንቀው አቃልለው በራሳቸው ማስተዋል የሚደገፉ ግን በአሸዋ ላይ የተመሠረቱና በቀላሉ የሚፈርሱ ቤቶችን ይመስላሉ።

በሌላም ሥፍራ «ብእሲ ዘየሐውር መዓልተ ኢይትዓቀፍ እስመ ይፈኢ ብርሃኖ ለዝንቱ ዓለም ወዘሰ የሐውር ሌሊተ ይትዓቀፍ» / በቀን የሚሄድ ሰው አይሰናከልም የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና በጨለማ የሚሄድ ግን ይሰናከላል» ብሎ ተናግሮአል። (ዮሐ. ፲፩፥፱) የዚህ ቃል ትርጓሜ አንድም በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን የሚኖር ሰው ነፍሱን ከኃጢአት እንደምትጠበቅ ያስረዳል። የዚህ ዓለም ብርሃን የተባሉ ጌታችን «የዓለም ብርሃን ናችሁ!» ያላቸው ካህናት ሲሆኑ በቀን የሚሄድ የተባለው ደግሞ በምክረ ካህን የሚኖር ሰው ነው።

በቀን የሚሄድ እንቅፋት እንደማይበዛበት ይህም በካህን ምክር ያለ ሰው ዕትፍተ ነፍስ (የነፍስ እንቅፋት) አይጸናበትም። ምክንያቱም በየጊዜው የሚገጥመውን መሰናክል ለካህን ስለሚያማክር ነው። በጨለማ የሚሄድ የተባለው ደግሞ በምክረ ርእሱ (በራሱ ምክር) የሚመራ ፤ በራሱ ማስተዋል የሚደገፍ «አቶ ካህን ለምኔ?!» ነው።

ብዙዎች በኃጢአት ሊወድቁና የሕይወት አጣብቂኝ ውስጥ ሲገቡ፤ ተስፋ ሲቆርጡ የሚታዩት ፤ የጥንቆላ ጋዜጦችን (አስትሮሎጂ) እና የሥነ ልቦና መጻሕፍት ቀመሮችን እያነበቡ ሕይወታቸውን የሚያመሰቃቅሉት በምክረ ካህን የማይመሩና መምህራነ ቤተ ክርስቲያንን የማይጠይቁ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትንም የማይመለከቱ የጨለማ ተጓዦች ስለሆኑ ነው።

በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን መመራት በቤተሰብና በማኅበራዊ ኑሮ የሚገጥሙ ችግሮችንም ለመፍታት ይረዳል። ቅዱስ ጳውሎስ በትዳር ጉዳይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመፍታት በየፍርድ ቤቱ የሚሄዱና በመንፈሳዊ ስፍራ (ማዕረግ) ቦታ በሌላቸው ዓለማውያን ፊት የሚነታረኩ ፤ ችግሮቻቸውን በምክረ ካህን የማይፈቱ ምእመናንን

«የትዳር ጉዳይ ይቅርና በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን? እንግዲህ ስለ ትዳር ጉዳይ ፍርድ ቤት ቢያስፈልጋችሁ በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጆች አድርጋችሁ ታስቀምጣላችሁን? አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ። እንደዚህ ነውን በወንድሞች መካከል ሽማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን? ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይክሳል ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን?» በማለት ገሥጾአል። (፩ኛ ቆሮ ፮፥፫፡፮)

በምክረ ካህን መኖር ማንኛውንም የኑሮ እቅድ ለመምህረ ንስሓ ማማከርንም ይጨምራል። ምናልባት የምእመኑ ሀሳብ ካህኑ *ከመንፈሳዊ ሕይወት አንጻር* የማይበጀው እንደሆነ ሲነግሩት ሀሳቡን ለመለወጥ የሚያስችል እምነት በመምህሩ ላይ መጣል ይኖርበታል።

አንዳንዶች በራሳቸው መንገድ የፈለጉትን ርቀት ያህል ከተጓዙ በኋላ ካህን ትዝ ይላቸዋል። ለምሳሌ ምክረ ካህን ሊለየው የማይገባውን የእጮኝነት ሂደት ያለ ካህን አሳልፈው ለጋብቻ ሲደርሱ በሰርጋቸው ዕለት መምህረ ንስሓቸውን ምግብ ባርኩልን ብለው የሚጠሩ የካህንን ጥቅም የማይረዱ አሉ። ነገር ግን በማንኛውም ጉዳይ በምክረ ካህን መኖር ለምእመናን ይገባል።

በምክረ ካህን መኖር ራሱ ትልቅ መንፈሳዊ መዓርግ ነው። የሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ከብሉይ ኪዳን ሰዎች የሚከብሩትን ያህል በምክረ ካህን የሚኖሩ ምእመናን ከአማንያን በላይ የከበሩ ናቸው። (ማቴ ፲፥፵፩ ትርጓሜ) አዳም በገነት ለሰባት ዓመታት ከቆየ በኋላ በዲያብሎስ ተፈትኖ እንደወደቀ በኃጢአት መፈተንና መውደቅ የሚጸናበት ዕድሜ ከሰባት ዓመት ጀምሮ ያለው ነውና ማንኛውም ምእመን ከሰባት ዓመቱ ጀምሮ ወደመምህረ ንስሓ መቅረብ ይኖርበታል። ለወይን ሥፍራው

ሠራተኞችን ይቀጥር ዘንድ በማለዳ ወጣ በዐሥራ አንድ ሰዓትም ቀጠረ የሚለው ምሳሌ ሲተረጎም በሰባት ዓመት ዕድሜ መምህረ ንስሐ መያዝ እንደሚገባ ያስረዳል። /ማቴ. ፳፥፩/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ከመምህራን ጋር መገናኘቱ እያንዳንዱ ክርስቲያን ከልጅነት ዕድሜው ጀምሮ ከመምህራን ጋር መገናኘት ይኖርበታል። ዕድሜው ለኃጢአት የደረሰ ሁሉ ለኑዛዜም ደርሶአል። በሥጋም በነፍስም ሲታመም የሚጠራቸው ዐቃብያነ ሥራይ (ባለሙያ ኃኒቶች) እነርሱ ናቸውና። (ያዕ ፭፥፲፬)

፪. ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ

የኑዛዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊነት

ንስሓ እንደ እንደ ክህነት ሁሉ በብሉይና በሐዲስ ኪዳን የኖረ ምሥጢር ነው ፤ ኃጢአትን መናዘዝም እንዲሁ። ንስሐና ኑዛዜ በሁለቱም ኪዳናት ሲኖር የቻለው ኃጢአት በሁለቱም ኪዳናት ዘመን ሲፈጸም ስለኖረና ስለሚኖር ነው። ኃጢአትን ለእግዚአብሔር በካህኑ በኩል መናዘዝ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ነው።

እግዚአብሔር አዳም በበደለ ጊዜ «አዳም ወዴት ነህ?» ብሎ ሲጠይቀው አዳም እንዲናዘዝ ስለፈለገ እንጂ አዳም ያደረገውን ሳያውቅ ቀርቶ አልነበረም። «አም ቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም የአምር ግብሮ» «አዳምን ከመፍጠሩ በፊት ሥራውን ያውቃል።» እንዲል።አዳምም እግዚአብሔር በጠየቀው ጊዜ «ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ስጠችኝና በላሁ» ብሎ ተናዝዞአል። (ዘፍ. ፫፥፲) የአዳም ልጅ ቃየንም የዋህ ወንድሙን አቤልን ገድሎ በመጣ ጊዜ «ወንድምህ አቤል ወዴት ነው?» ብሎ የጠየቀው ሳያውቅ ቀርቶ ሳይሆን አምኖ እንዲህ አደረግሁ ብሎ እንዲናዘዝ ነበር።

በዘመነ አሪት «ከእነዚህ ነገሮች በአንዲቱ በደለኛ ሲሆን የሠራውን ኃጢት ይናዘዛል ፤ ስለ ሠራው ኃጢአት ለእግዚአብሔር የበደል መሥዋዕት ያመጣል ፤ እርሱም ከመንጋው የበግ ወይም የፍየል እንስት ለኃጢአት መሥዋዕት ይሆናል ናህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሰርይለታል።» ዘሌ.፭፥፮፤፲፯ በሙሴ እግር በተተካው በኢያሱ ዘመንም ኑዛዜ ተፈጽሟል ኢያሱ አንል ለተባለ ሰው «ልጄ ሆይ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር ክብርን ስጥ ፤ ለእርሱም ተናዘዝ ፤ ያደረግከውን ንገረኝ አትሸሸገኝ» ሲል እንዲናዘዝ አድርጎታል። (ኢያ.፯፥፲፱)

ነቢይም ሐዋርያም የሆነ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በነበረበት በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መንክልም ኑዛዜ ተፈጽሟል። «ያን ጊዜም ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር ፤ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር።» (ማቴ.፫፥፭-፮) ጌታችን ወደ እርሱ ሊጠመቅ ሲመጣ ዮሐንስ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!» ብሎ የመሰከረው የንስሐ ጥምቀት በሚያጠምቅበት ስፍራ ጌታ መምጣቱን አይተው ኃጢአት ኖሮበት ሊናዘዝና ሊጠመቅ የመጣ እንዳይመስላቸውና «ኃጢአትን የሚያወግድ» አምላክ መሆኑን እንዲያውቁ ነበር። (ዮሐ. ፩፥፳፱) በሐዋርያትም ዘመን ኑዛዜ ነበር። «አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር» ይላል። (ሐዋ.፲፱፥፲፰)

ጌታችን ለቅዱሳን ሐዋርያት ሥልጣነ ክህነትን ሲሰጥ «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ይቀርላቸዋል» ብሏል። (ዮሐ ፳፥፳፫) ነገር ግን ያለ ኑዛዜ ይህ የሚታሰብ አይደለም። ኃጢአተኞች በደላቸውን በመናገር ካልገለጡ ካህናት እንዴት አውቀው ይቅርታን ሊሰጡ ይችላሉ? ደግሞም ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናና ሰጲራን እንዳወቀ የሰው ክፉ ሥራ ሳይነገራቸው የሚያውቁበት ጸጋ ያላቸው ካህናት

ቢኖሩ እንኳን ሳይነገራቸው በጸጋ አውቀው ሥርየት ቢሰጡ «ልትድን ትወዳለህን?» ሳይሉና ፈቃድን ሳይጠይቁ በግድ ከመፈወስ ይቆጠርባቸዋል። ነገሩም ንስሓ /ጸጸት/ ሊሰኝ አይችልም ፤ ፍትሐዊም አይደለም። ስለዚህ ሥርየተ ኃጢአትን ለማግኘት ራስን ለካህን በንስሓ ማሳየት ይገባል።

ጌታችን ከለምጽ የፈወሰውን ሰው «ሂድና ራስህን ለካህን አሳይ» (ማቴ ፰፥፬) ያለውን ቃል በዚህ ሥፍራም ልንጠቅሰው እንችላለን። እርግጥ ነው ይህ ቃል የተነገረው በቀጥታ ኃጢአትን ለካህን ስለመናዘዝ አይደለም። ከለምጽ የሚነጻ ሰው ወደ ካህን ሒዶ መንጻቱን እንዲያሳይ እና ካህኑም ደም እየረጨ ንጹሕ ነው እንዲሰው በሙሴ ሕግ ሥርዓት ተሠርቶ ስለነበር ነው። (ዘሌ.፲፬፥፪) ይህ ትርጉም እንዳለ ሆኖ ግን ይህ ታሪክ በምሳሌነት ይተነተናል። በቀደመው ዘመን ለምጽ ከእግዚአብሔር ሕዝብ የሚለይ እንደነበረ እንዲሁ ኃጢአትም ከምእመናን ማኅበር የሚለየን የነፍስ በሽታ ነው። ከዚህ ለምጽ ይህን ሰው ጌታችን እንዳነጻው «ከአመጻ ሁሉ» ከኃጢአትም ሁሉ ሊያነጻን የሚቻለው መድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ከለምጽ የነጻውን ሰው «ነጽተሃል» የማለትን ሥራ ጌታችን ወደ ካህኑ እንዳስተላለፈ ከእርሱ የምናገኘውን የኃጢአት ይቅርታ የሚያውጁልንና «እግዚአብሔር ይፍታህ!» የሚሉን ካህናት ናቸው። ይሁንና ከሥጋዊ የለምጽ ደዌ የነፍስ ደዌ ኃጢአት እንደሚከፋ የምናውቅ ክርስቲያኖች እህተ ሙሴን ከከነዓን ገዛ እንዳዘገያት ለምጽ ከመንግሥተ ሰማያት የሚያስቀረን ከለምጽ የከፋ ኃጢአትን ለማጥፋት ራሳችንን ለካህን እናሳያለን።

በመጽሐፍ ቅዱስ ምናልባት ለካህን ሳይናዘዙ ንሐሓ ገቡ ሊባሉ የሚችሉ ተነሳሒያን ቅዱስ ዳዊት ፣ ቅዱስ ጴጥሮስ እና ከጌታ በስተ ቀኝ የተሰቀለው ግብጻዊ ወንበዴ ጥቦስ ናቸው። ነገር ግን አልተናዘዙም ብሎ መደምደም አይቻልም። ቅዱስ ዳዊት የሠራውን ኃጢአት እንዳይናዘዝ የእግዚአብሔር ነቢይ ናታን ኃጢአቱን በምሳሌ አሳምሮ

አስቀድሞ ነግሮታል። ስለዚህ በድያለሁ ከማለት ውጪ ምንም ሊል አይችልም። (፪ሳሙ.፲፪፥፩-፲፫) ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታውን ከመንዱ በፊት ሦስት ጊዜ እንደሚክደው አስቀድሞ በሐዋርያቱ ፊት ነግሮት ነበር። ፈያታዊ ዘየማን ግን በዝርዝር ለመናዘዝ ሁኔታዎች ባፈቅዱለትም በአንዲት ዐረፍተ ነገር ኃጢአቱን ተናዝዟል። «ስለአደረግነው የሚገባንን እንቀበላለን» ማለቱ ለተረገመው የመስቀል ሞት የሚያበቃ ኃጢአትን ሠርቼአለሁ ማለት ነውና። (ሉቃ. ፳፫፥፵፩)

ለምን ለእግዚአብሔር ብቻ እንናዘዝም?

በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ኃጢአትን መናዘዝ በአፈጻጸም ደረጃ በአራት ይከፈላል። የመጀመሪያው በጸሎት ለእግዚአብሔር መናገርና ይቅርታን በመለመን ነው። ሁለተኛው በሥርዓቱ መሠረት በእግዚአብሔር ካህን ፊት የምናቀርበው ኑዛዜ ነው። ሦስተኛው በኃጢአታችን ሰውን በድለን ከሆነ በበደልነው ሰው ፊት ሔደን ጥፋታችንን አምነን መናገር ነው።(ማቴ. ፭፥፳፫)

አራተኛው ደግሞ ለራስ የሚደረግ ኑዛዜ ነው። የጠፋው ልጅ በእርያ መንጋ መንክል ሆኖ በረሃብ ሲሰቃይ ወደ ልቡ ተመልሶ የፊት ክብሩን የኋላ ኃሣሩን እያሰበ «እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሙያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በረሃብ እጠፋለሁ። ተነሥቼም ወደ አባነ እሔዳለሁና ፦ አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም ከሞያተኞችህ አንዱ አድርገኝ አለዋለሁ» ሲል የተናዘዘው ለማይሰሙት እርያዎች ሳይሆን ለራሱ ነበር። (ሉቃ. ፲፭፥፲፯)

ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ ለእግዚአብሔር አለመናዘዝ አይደለም። ኃጢአትን ለካህን መንገር ለእግዚአብሔር መናዘዝና ክብርን መስጠት ነው። ኢያሱ እንዳለ «ልጄ ሆይ! ለአምላክ ክብርን ስጥ

ለእርሱም ተናዘዘ። ያደረግኸውንም ንገረኝ አትሸሸገኝ» (ኢያ ፯÷፲፱) ፤ ኢያሱ «ክብርን ስጥ!» ያለው ለእግዚአብሔር፤ «ተናገር» ያለው ግን ለራሱ መሆኑ ኃጢአትኽ ለካህን መናዘዝ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት እንደሆነ ያስረዳናል። አበው ካህናትም ኑዛዜን ከተቀበሉ በኋላ «እግዚአብሔር ይፍታህ» እንጂ «ፈትቼሃለሁ!» አይሉም። ይህም ምንም በእነርሱ ፊት ብንናገረው ሰሚውም፤ በእጃቸው ሥርየት የሚሰጠውም እርሱ ባለቤቱ ስለሆነ ነው። «ሁለት ወይም ሦስት በሚሆኑበት በዚያ ከመካከላቸው እገኛለሁ» ብሎ ቃል የገባ እምላክ በናዛዚው ካህንና በተናዛዚው ምእመን መካከል በመካከላቸው ሆኖ ይሰማል ፤ የኃጢአት ይቅርታንም ይሰጣል።

ይህንን ስንል አንድ ሰው «አይ እግዚአብሔር ይቅርታውን እንዲሁ ሊሰጠኝ ይችላል ፤ ለካህን ኃጢአቴን መናዘዜ አስፈላጊ አይደለም» ሊል ይችላል። እንዲህ የሚልን ሰው ግን ሲታመም ወደ ሐኪም ቤት ሔዶ በሐኪሙ ፊት «ቆስጠኝ ፈለጠኝ ፤ ወጋኝ» ሊል ልናገኘው አንችላለን። ጭንቀት ሲይዘው ወደ ሥነ አእምሮ ባለሙያዎች ሲሔድ እናገኘዋለን። ካህናትስ የነፍስ ከመሆኑ በስተቀር ከዚህ የተሰየ ምን አገልግሎት ይፈጽማሉ? ወደ ሐኪም ቤት የምንሔደው እግዚአብሔር ፈዋሽ መሆኑን ክደን ነው? ለምንስ በሽታችንን ለሐኪም እንናገራለን? እግዚአብሔር ለሰው ሳንናገር ሊያድነን ይችል የለምን? በሐኪሙ ምክንያትነት የሚያክመን ፈቃዱም ከሆነ የሚፈውሰን እግዚአብሔር እንደሆነ ስለምናምን ግን እኛ ክርስቲያኖች ሕክምናን አንቃወምም። ለሥጋ በሽታ ስለምንታከመው ሕክምና ተቃውሞ የሌላቸው ሰዎች የነፍስ ሕክምና በካህናት እጅ መፈጸሙን ግን መቃወማቸው ያስደንቃል።

አንዳንዶች ኃጢአትን ለካህን ከመናዘዝ ይልቅ *«በቀላሉ ለምን በቀጥታ ለእግዚአብሔር ኃጢአታችንን አንናገርም»* በማለት

«የኃጢአተኛ ትዕቢተኛ» ሲሆኑ ይታያል። ሲሆን ሲሆን ንስሐ የሚገባ ሰው ወጉ «ከበደሌ ብዛት የተነሳ ቀና ብዬ የሰማይን ርዝመት አይ ዘንድ አገባቤ አይደለም» ማለት ነበር። (ጸሎተ ምናሴ) ደግሞስ ንቀውት አጥቅተውት እንጂ ለማስፈራትስ የሚያስፈራው ማን ነው? እንዲያውም በኃጢአቱ ራሱን የወቀሰ ሰው «ለእግዚአብሔር ከምናዘዝ እንደ እኔ በደለኛ በሆነ በሰው ፊት ብናገር ይቀልለኛል» ቢል የሚመስል ነበር።

የሰው ልጅ ኃጢአትን ተሸሽጎ ጨለማን ተገን አድርጎ ሰው አየኝ አላየኝ ብሎ የሚሠራው ከፈጣሪ ይልቅ ሰውን ስለሚፈራና ስለሚያፍር ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር «እርስ በእርሳችሁ ኃጢአታችሁን ተናዘዙ» ተብሎ እንደተጻፈ በባሕርይ ለሚመስለው ከሰው ልጅ ወገን ለሚመረጥና ለሚሾም ካህን እንዲናገር አደረገ። ይህም እግዚአብሔር የሰው ልጅ ኃጢአቱን በሰው ፊት ተናግሮ በተዋርዶ ለልዕልና እንዲበቃ ፤ ዳግመኛም ወደ ኃጢአት ለመመለስ እንዲሰቀቅና እንዲታረም መንገዱንም እንዲያቀና የፈጠረለት መላ ነው።

እስቲ ብዙዎች *(ኃጢአትን ለካህን መናዘዝን የማይደግፉ ሰዎች)* እንደሚፈልጉት *ንስሓ ቀጥታ በእግዚአብሔር ፊት ለጸሎት በቀመጥ ጊዜ የሠራነውን ኃጢአት በመናገር የሚፈጸም ቢሆን ኖሮ* ብለን እናስብ። የሰው ልጅ ልጓም እንደሌለው ፈረስ ይሆን አልነበር? ሰው ኃጢአት የሚሠራው እግዚአብሔር ያየኛል ሳይል ነው። ታዲያ ያየኛል ይሰማኛል ሳይል የሠራውን ኃጢአት እንዴት ያየኛል ይሰማኛል ብሎ ይናዘዛል?፤ ለመናዘዝ ሲባል የሚያስበውን አምላክ ምነው ሲበድል አያስበው? ከመናፍቃኑና «ኑዛዜን በቀጥታ ለእግዚአብሔር እንናዘዝ» ከሚሉ ሰዎች በስተጀርባ የሰይጣን ተንኮል አይታያችሁም?

ሰይጣን የሰው ልጆች ኃጢአትን ያለ አንዳች መሰቀቅና ፍርሃት እንዲሠሩ ይፈልጋል። በሥጋዊ ድካም የሠሩትን ክፉ ሥራ «እንደ

ኃጢአት» እንዲያስቡት አይፈልግም። ስለዚህ «*የፈለግሁትን እየደረግሁ ሥጋዊ ምኞቴን እያረካሁ ለደቂቃዎች ያህል እግዚአብሔር ሆይ ይህን አድርጌአለሁ ብዬ ብላገል እችላለሁ*» የሚል ሀሳብ ይዘው እንዲከራከሩ ያደርጋል። ኃጢአትን የመሥራት ነጻነት እንዲያገኙ ስለሚሻ ኑዛዜን ያለ ካህን እንዲፈጸም ይቀሰቅሳል።

አንዳንድ መናፍቃን (ሮማን ካቶሊክና አንግሊካንን የመሳሰሉት) ደግሞ ንስሓን ተናዛዢውና ናዛዢው ሳይተያዩ እንዲፈጽሙ መከለያ መስኮት (confessional) የሚሠሩም አሉ። ከፍ ሲልም ኃጢአትን ሲነግሩት ቀኖናውን ሠፍሮ የሚነግር የመተየቢያ ሥርዓት (የኮምፒውተር ሶፍት ዌር) መፈልሰፋቸውም ይነገራል። እርግጥ ነው ይህ መንፈስ ቅዱስ ለተለየው ሕይወት የሚሠራ ሥርዓትን እንደመሆኑ ከሚዛን ውስጥ አይገባም። ይሁንና በሃይማኖታዊ ሚዛን ሲመዘን ግን የኑዛዜን ጽንሰ ሀሳብ ያለመረዳት ውጤት መሆኑ ግልጥ ነው።

እግዚአብሔር ኃጢአት ለካህን «በመናገር ብቻ!» ከዘላለም ጥፋት እንድንድን ያስቀመጠልንን ልዝብ የንስሓ ቀንበር እንደ ከባድ ቆጥሮ ከካህን መሸፈንም ተገቢ አይደለም። ቀኖና ሰፋሪው መሣሪያም ቢሆን *የሰው ሥርየት በእግዚአብሔር ቸርነት መሆኑ ቀርቶ በሰጠደውና በጸመው ልክ* አድርጎ ከማሰብ የመነጨ ሲሆን ፣ ለክህነትና ለሃይማኖት ዋጋና ክብር አለመስጠትን አጉልቶ ይሳያል። በእኛ ቤተ ክርስቲያን ግን የሚናዘዘው ተነሳሒ ከካህኑ ጋር ፊት ለፊት እየተያየ መናዘዝ ይገባዋል። ስለ ኃጢአቱም እንዲሰቀቅና በዚህም የሚገኘውን መንፈሳዊ ጸጋ እንዲያገኝ ይደረጋል።

ኑዛዜን አንደሚገባ በዝርዝር መፈጸም

እግዚአብሔር ማእምረ ኅቡዓት (የተሰወረውን የሚያውቅ) አምላክ ነው። የሰው ልጅን የጸጉር ቁጥር እንኳ የሚያውቅ እርሱ

ኩላሊት ያጤሰውን ፣ ልቡና ያመላለሰውን የሚያይ ነውና ኃጢአትን እንኳን ስንፈጽማትና ስንናገራት ስናስባትም ያውቃል። «የሰውን ድካሙን አንተ ታውቃለህና በማሰብም ቢሆን በመናገርም ቢሆን በልቡና ክፋትም ቢሆን አንተን ብንበድል ተውልን አስተሰርይልን አቃልልን ይቅርም በለን» ተብሎ የሚጸለየውም ለዚህ ነው (ጸሎተ ንስሓ)

«ሰው ኃጢአቱን ልሸሽግ ከእግዚአብሔር ላምልጥ ቢል የሚሮጥበት ሜዳ የሚወጣበት ቀዳዳ ፣ የሚገባበት ዋሻ የሚመክትበት ጋሻ ፣ የሚጠጋበት ቅጠል የሚንጠላጠልበት ገደል የለም» ይላሉ አበው። ሰው እንኳን ከፈጣሪ ይቅርና ከሰማይና ከምድር ፣ ከብርሃንና ጨለማ መሸሸግ አይችልም። ሰው ኃጢአቱ ቢሰውር ኃጢአቱ ስትወቅሰው ፣አጋንንትም ሲከስሱት ይኖራል። ስለዚህ ለምን ይሰውራል። ይህን የተረዳ ግን እንዲህ ይላል፦

«ኃጢአቴን ለመናገር ለምን አፍራለሁ አለመናዘዜስ ለምን ነው? የሚከሱኝ ጠላቶቼ የሚመስክሩብኝም ኃጢአቶቼ ሳሉ እንግዲህ ኃጢአቴን እናገራለሁ። የተሰወረውን በሚያይ አፍ የተናገረውን ልቡና የመከረውን መርምሮ በሚያውቅ እግዚአብሔር በዓይኖቹ ፊት የተገለጸ ሲሆን እኔ ለምን አሰውረዋለሁ? ፣ እኔም ብሰውረው ኃጢአቱ ሊከሰኝ ይጮኻል በደሌን ለማመን እኔ እንግዲህ ለምን ዝም እላለሁ? የሠራሁትም ክፋ ሥራዬ ያሳጣኛል እኔ እንዳልሠራ ለምን እሆናለሁ? የሚዘልፈኝ ምስክር አልሻም እኔ ለራሴ የራሴን ዘለፋ አነባለሁ እንጂ» (አር.ጋኖን ዘረቡዕ ፯፥፫-፮)

አንድ ሰው አንድን ሲሰርቅ ተደብቆን ብናየው ወይም በተሰወረ መቅረጫ (Hidden camera) ተቀርጾ ብናየው እና ስንጠይቀው ጥፋቱን ቢያስተባብል ወይ ያደረገውን በትክክል ባይናገር እንበሳጭበታለን። «ከዓይኔ ወዲያ? ከሌብነቱ ውሸቱ ባሰ!» እያልን እንብከነከናለን። እግዚአብሔርም ያለ መቅረጫ በሁሉ ቦታ ስላለ ሁሉን

ያያል። ስንሠራው ያየንን ኃጢአት እንዳልሠራ ብንሆን ከዓይኑ ፊት መንድ ነው። እግዚአብሔር በሾመው ካህን ፊት ኃጢአትን ለመሸሸግ መምከር ከእግዚአብሔር ዓይኖች (አዕይንተ እግዚአብሔር) ለመደበቅ መሞከር ነውና ተገቢ አይደለም። ካህኑን መዋሸት ደግሞ እግዚአብሔርን ማዋሸት ነው። ካህኑ ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናንያና ሰጲራ ሊያታልሉት በተነሡ ጊዜ ለሐናንያ ፦ ሐናንያ ሆይ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለምን ሞላ?» ብሎታል። ይህንን የተናገረው መንፈስ ቅዱስ የሚታለል ሆኖ ሳይሆን ካህኑን ለማታለል መሞከር መንፈስ ቅዱስን ለማታለል እንደመሞከር ስለሚቆጠር ነው። (ሐዋ. ፭፥፱)

እኛ ግን ባለማስተዋል ሁሉን ከሚያይ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰው ብቻ እንዳያየንና እንዳይታዘበን እንጠነቀቃለን። «እስመ ዓይነ ሰብእ ያፈርሖሙ ወኢየአምሩ ከመ ዓይነ እግዚአብሔር ያበርህ እም አእላፍ ፀሐይ» ይላል መጽሐፍ «የሰው ዓይን ያስፈራቸዋልና ፤ የእግዚአብሔር ከአእላፋት ፀሐያት እንደሚያበራ አያውቁም።»

በአሞጽ ፫፥፮ ላይ «የሰውሩት ፪ቱ ኀቡረ አንዘ ኢይትረአዩ / ሁለት ሰዎች ሳይተያዩ አብረው ይሄዳሉን?» ተብሎ ተጽፎአል። ይህም አብረው የሚሄዱ እንደሚተያዩ ያህል ኃጢአት ሠርቶ እግዚአብሔር አያውቅብኝም ማለት እንደማይቻል ያስረዳል። እርሱ ሁሉን ያያልና ተደብቀን ኃጢአትን ስንሠራ በዚያ ሥፍራ እግዚአብሔር እንደነበረ ማሰብ ይገባል። ዮሴፍ የጲጥፋራ ሚስት ለዝሙት ስትጋብዘው የተናገረውም ለዚህ ማስረጃ ነው። «በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍ ፴፱፥፱)

«ተዘከር አንተ ቅድመ አበሳከ ከመ ኢይዘክር ብከ ፈጣሪከ / ፈጣሪህ እንዳያስብብህ በደልህን አስቀድመህ አስብ» እንዲል አምላክ ኃጢአታችንን ሳያስብብን እኛ አስበን ልንጸጸት ይገባል። ሰው ኃጢአቱን

ሊያስብ እግዚአብሔር ይረሳሰታል። ኃጢአቱን ሲዘነጋ ግን እግዚአብሔር ያስታውስበታል።

«በሽታውን የደበቀ መድኃኒት የለውም» እንዲሉ የነፍሱን ደዌ ኃጢአቱ የሚደብቅ ሰውም እንዲሁ ነው። «ኃጢአቱን የሚሠውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» ተብሎም ተጽፏል። (ምሳ ፳፰፥፲፫) አንድ ተክል ለማ ማለት ጸደቀ ማለት እንደሆነ አይለማም ማለትም አይጸድቅም ማለት ነው።

አንዳንዶች ከካህን ፊት ከቀረቡ በኋላ በደፈናው «ኃጢአተኛ ነኝ» አለዚያም «አድርጉ የተባለውን ሁሉ አሳደረግሁም አታድርጉ የተባለውን ሁሉ አድርጌአለሁ» ብለው የብልጠት ኑዛዜ ሊናዘዙ ይሞክራሉ። ነገር ግን በደለኛ ነኝ ማለት በራሱ የንስሓ (የጸጸት) ምልክት አይደለም። ለዚህ ለዚህማ ፈርዖን ፣ በለዓም ፣ ሳኦል ፣ ይሁዳ «በድያለሁ» ብለው ተናግረው ነበር (ዘዳ ፱፥፳፯ ፣ ዘኁ ፳፪፥፴፬ ፣ ፩ኛ ሳሙ ፲፭፥፳፬)

የታመመ ሰው ከሐኪም ዘንድ ቀርቦ «ታምሜአለሁ!» «በሽታ የተባለ ሁሉ አለብኝ!» ብሎ ብቻ መድኃኒት እንደማያገኝ ለካህንም ያደረጉትን በዝርዝር መግለጥ ያስፈልጋል። ሐኪም ቤት ሔዶ ከበሽታው ግማሹን ብቻ የተናገረ ሰው ለሌላ ችግር እንደሚያስከትል ኑዛዜውን በትክክል ያልተናዘዘም ስርየት አያገኝም። ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ «ካህኑን እንደ መንፈሳዊ አባትነቱ እየው ፤ ልክ በሽተኛ የተሸፈኑ ቁስሎቹን ለሐኪም እንደሚያሳይና እንደሚፈወስ ምሥጢሮችህን በግልጥ ንገረው» ሲል አስተምሮአል።

በኑዛዜ ወቅት ለካህኑ በሚገባ ግልጽ ቋንቋ ፣ ባልተድበሰበሰ አነጋገር በመሥራት ፣ በመናገርና በማሰብ (በኃልዮ ፣ በነቢብና በገቢር) የሠራነውን ኃጢአት መናዘዝ ይገባናል። ባለፉት አንቀጾች የጠቀስነው ኃጢአቱን ለሊያሉ የተናዘዘው አካን የተባለ ሰው ኑዛዜ ይህንን

ያስረዳል። እንዘን በኢያሱ ፊት እንዲህ ብሎ ነበር። «በእውነት የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን በድያለሁ እንዲህና እንዲህም አድርጌአለሁ። በዘረፋ መካከል አንድ ያማረ የሰናዖር ካባ ሁለት መቶም ሰቅል የሆነ ወርቅ አይቼ ተመኝቼው ወሰድኳቸውም እነሆም በድንኳኔ ውስጥ በመሬት ተሸሽገዋል ብሩም ከሁሉ በታች ነው አለው።» (ኢያ. ፯፥፳ -፳፩) አካን «ተመኝቼው» በማለት የሃሳብ ኃጢአቱን ጭምር የተናዘዘ ሲሆን «ብሩ ከሁሉ በታች ነው» ማለቱ ደግሞ የኃጢአት ተጠቃሚ እየሆኑ ኑዛዜ እንደሌለ ያስረዳል። ከሰው ገንዘብ ዘርፎ ከባንክ አኑሮ ኑዛዜ ይመልሱ እንደሌለ ማለት ነው።

ምናልባት አንዳንድ ሰው በዝርዝር ኃጢአትን መናዘዝ ለምን አስፈለገ ፤ ከእንግዲህ ለመተው ከፈቀድኩ አይበቃም ሊል ይችላል። ኃጢአትን በካህኑ ፊት መዘርዘር ዳግመኛ በዚያ ኃጢአት ላለመያዝ የሚያስችል ኃይልን የሚሰጥ ነው። «እመሰ ወሰከ ላዕሰ አበሳሁ ድፍረተ ወጥላቶተ ኢይክል ተዐቅቦተ እምወዲቅ በዘከማሃ» «በበደሉ ላይ ድፍረትንና ሽንገላን ቢጨምር /ኃጢአት ሠርቶ አልሠራሁም ቢል/ ከዚያች ኃጢአት መጠበቅ አይችልም ፤ እርስዋን በሚመስል ኃጢአት ከመውደቅም አይድንም» (ተግሣጽ ዘቅዱሐአፈ.) ገታችን በዕለተ ሐሙስ መሥዋዕተ ወንጌልን /ምሥጢረ ቁርባንን ሲመሠርት/ አስቀድሞ መሥዋዕተ አሪትን ፈጽሞ ነበር። ይህም አንድ ንጉሥ የሚሽረውንና የሚሾመውን ግራና ቀኝ አቁሞ ፤ የሚሽረውን ወቅሶ የሚሾመውን አሞግሶ እንደሚያከብር አሪትን ለመሻር ወንጌልን ለማጽናት ነው። ያለፈ ኃጢአታችንን በካህኑ ፊት ስንዘረዝርም ያለፈውን ሽረን በሚመጣው ሕይወታችን ስኅተታችንን እንዳንደግም እየወሰንን ነው።

«ወይሐሥማ ኃጥእ ለንዴቱ በአፉሁ /ደሃ ድህነቱን በአፉ ይጠላታል» እንዲል (ሲራ ፲፫፥፳፬) *እንደ እኔ ያለ ኃጢአተኛ ክፉሰ ማን አለ?* እያሉ ኃጢአትን በአፍ መጥላት ገና ከኃጢአት ፍቅር ያለመላቀቅ ምልክት ነው። ኃጢአትን የጠላ ግን በንስሓ ገልጦ ያርቃታል።

አንዳንዶች ደግሞ *ኃጢአተኛ* ነኝ እያሉ በመናገር ብቻ ትሑታን የሆኑ ይመስላቸዋል። ነገር ግን ትሕትና በልብ ኃጢአተኛ እንደሆኑ ማመን እንጂ በየደረሱበት ትሑት ይበሉኝ በሚል ከንቱ ምኞት «ኃጢአተኛ ነኝ!» እያሉ ማወጅ አይደለም። ትሕትናስ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዳለው «ኃጢአተኛ ነኝ ማለት ሳይሆን ኃጢአተኛ ሲባሉ መታገስ ነው።»

ኃጢአትን ለመሰወር መሞከር ግን ሌላ ኃጢአትን ይጨምራል። ይህ በቃየን እና በንጉሥ ዳዊት ታውቋል ቃየን «የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን» ብሎ ኃጢአቱን ባለመናዘዙ በምድር ላይ ተቅበዝባዥ ሆኖ የከፋ ሞት ሞቷል። ተነሳሒው ንጉሥ ዳዊት ደግሞ የፈጸመውን ዝሙት እደብቅ ብሎ ሰው እስከ መግደል ደርሶ ነበር። ይሁንና ይህም ኃጢአቱን አልሰወረለትም ለዘመናት በታሪክ እየተነገረለት ንጉሥ ነውም ሳይባል በወንጌል ሳይቀር ተገልጦበት ይኖራል። (ማቴ. ፩፥፮ ትር.) አሁንም እያነበብህ / እያነበብሽ ያለሽው / ያለሽው ይህንን የዳዊት ኃጢአት ነው። እግዚአብሔርም «አንተ በስውር አድርገህዋል እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ» ብሎታል (፪ሳሙ ፲፪፥፲፪)

ብዙዎች ኃጢአትን ገልጦ ለመናገር ይሰቀቃሉ እርግጥ በነውር መሰቀቅ የሥራ ዋጋ ነው። ቀደም ሲል ያነሣናት በቅዱስ ኤፍሬም ዘመን የነበረች ተነሳሒት እንዳደረገችው አፍሮም ቢሆን ፤ መናገር ሳይችልም ቢሆን ፤ የማያናግር ደዌ ገጥሞትም ቢሆን ተነሳሒ በወረቀት ጽፎ እንዲናዘዝ ይፈቀዳል። ነገር ግን ካህኑ ኑዛዜውን ሲያነብቡ ተነሳሒው ፊት ለፊት መቀመጥ አለበት ይህም የኑዛዜ ዓላማ

ሰው ስለ ኃጢአቱ እንዲሰቀቅ ስለሆነ ነው። ከጽሑፍ ባሻገር በስልክና በሌሎች መገናኛ ዘዴዎች ኑዛዜን መፈጸምን የሚመለከቱ ጥያቄዎችም አሉ። ከካህን የሚገኝን ምክር በተመለከተ ምክር በማንኛውም ሁኔታ ሊሰጥ ስለሚችል መልሱ አወዛጋቢ አይሆንም። ኑዛዜን በተመለከተ ግን ንስሐ ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ስለሆነ በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ ብቻ መፈጸም ያለበት በመሆኑ እንዴት ይሆናል የሚል ጥያቄን መውለዱ አይቀርም። አንዳንድ አኃት አብያተ ክርስቲያናት በይፋ በስልክ ኑዛዜን ፈቅደው በኋላ ግን ፖሊስ መስመሩን የጠለፈው በመሆኑ ምክንያት የስልክ ኑዛዜ እንዲያቆሙ ለምእመናን መግለጫ መውጣቱ የቅርብ ጊዜ ዜና ነበር። ያም ሆነ ይህ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዘህ ጉዳይ የተገለጠ አቋም ባይኖርም ዘመን ስሚፈጥራቸው ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ስለሚኖርበት ወደፊት ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ እንደሚያሳልፍባቸው ከሚጠበቁ በርካታ ጉዳዮች አንዱ ይሆናል።

ስለዚህ ሲሠሩት ያልፈሩትን ኃጢአት ሲናገሩት መፍራት አይገባም። ሲስቡት ያፈሩትን ሲገፉት ፣ ሲበሉት ያልፈሩትን ሲተፉት መፍራት ነውና። ደግሞም ከአንድ ቁስ የሸሸግነው ኃጢአታችን በፍርድ ቀን ይገለጣል። እግዚአብሔር በዕለተ ምጽአት ስለ ሠራነው ኃጢአት *«ይህንን አድርገሃልና፣ ይህንን ደግሞ ለኅደረግህም»* ብሎ የሚወቅሰን ለየብቻችን ጠርቶ ከአልፍኝ አግብቶ አይደለም። በፍጥረት ሁሉ ፊት በአደባባይ ይገልጥብናል እንጂ። ታዲያ ለአንድ ካህን መናዘዝ አይቀልልም? እናም ምረረ ገሃነም (የገሃነም ምሬት) ካህን ፊት ከመናዘዝ እንደማይከሩ ትረድተን ! ጣዕመ መንግሥተ ሰማያትን እየተዘከርን (እያሰብን) ኃጢአታችንን ልንናዘዝ ይገባናል።

በኑዛዜ ወቅት «ታንኚን እያጠሩ ግመልን አንደ መዋጥ» ታላላቅ ኃጢአቶቻችንን ከኅን ትተን ጥቃቅኑን ብቻ መናገርም ስኅተት

ነው። እውነተኛ ተነሳሒ ግን ኃጢአቱን በግልጥና በቀጥታ መናገር ስለበት «የሆነውን ሆነ» ማለት እንጂ የተድበሰበሰ ኑዛዜ አይጠቅምም። ስለባበሰ ያረሰ በአረም እንደሚመለስ ሁሉ ኃጢአቱን በግልጽ ሳይናገር ቀኖና የፈጸመ ሰውም ንስሓውን ጨርሶም እንኳን የነፍስ እረፍትን አያገኝም ሰላሙም አይመለስለትም። ኑዛዜ የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጓሜው «መረጋጋት» ማለት ነው። በትክክል ኃጢአቱን ያልተናገረ ሊረጋጋ አይችልም። ኃጢአታችን እንደ ውኃ ሽታ እንዲጠፋ ከፈለግን በልባችን የሸሸግነውን ክፉ ሥራ በአግዚአብሔር ፊት መግለጥ አለብን። «በጌታም ፊት ልብሽን እንደ ውኃ አፍስሺ» እንደተባለ በግልጥ ስንናዘዝ ምንም የበደል ቅሪት ሳይኖር ንጽሕናን ማግኘት እንችላለን። (ሰ.ኤር. ፪፥፲፱)

ይልቁንም «ከቆረበች አፈረሰች ከመነከሰች ባሰች» እንዲሉ እንዲያውም ለባሰ ኃጢአት ይጋለጣል። ሽክሙ ቢከብድ እንጂ አይቀልለትም። ኃጢአት ሠርቶ አልሠራሁም ማለት ወይም መሸሸግና መደበቅ በኃጢአት ላይ ኃጢአትን ይጨምራል። የዋህ ወንድሙን አቤልን በግፍ የገደለ ቃየን በፍዳ ላይ ፍዳ በኃጢአት ላይ ኃጢአት የተጨመረበትና ተቅበዝባዥ ሆኖ የቀረው እግዚአብሔር ወንድምህ አቤል ወዴት ነው? ባለው ጊዜ *«ቦኑ ዐቃቢሁ አነ / ጠባቂው እኔ ነኝን?»* በማለት ኃጢአቱን በመሸሸጉ ነው።

በኑዛዜ ወቅት ስኃጢአት ምክንያትን መደርደር ፣ በኃጢአት ትዝታ ተወስዶ ያለ ጸጸት መናዘዝ ሊወገድ የሚገባው ነው። ንስሓ የራስን በደል ብቻ መናገር ነው። የሌሎችን ኃጢአት በመናገር *(እገሌ እንዲህ እንዳደረገ ገፋፋኝ)* እያሉ ሌላውን መክሰስ ግን ይቅር ሳይሉ ይቅርታን መሻት ነውና አይጠቅምም። አዳም ስለ በደሉ ሲጠየቅ «የሰጠሽኝ ሴት እርስዋ ስጠችኝና በላሁ» በማለት እግዚአብሔርን «እርሷን ባትሰጠኝ ኖሮ አልበላም ነበር» ፣ ሔዋንንም «እንድበላ

ባትሰጠኝ ኖሮ ባልበላሁ ነበር» ብሎ ከሰሶ ነበር ፤ *ያገኘው ጥቅም ግን* አልነበረም። ጌታችንም በወንጌል «ከሳሾችሽ ወዴት አሉ?» ያላትን ሴት «እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ» ብሎ በይቅርታው ያሰናበታት ስለ ከሳሾቿ አንዳች ባለመናገሯ ነበር። (ዮሐ. ፰፥፲፩ ትር) ስለዚህ ሥርየተ ኃጢአትን የሚሻ ቀድሞ የሌላውን በደል መተው ይኖርበታል።

ክርስቲያንም ልቡናው ኃጢአቱን ገልጦ እንዳይናገር ቢቃወመው እንኳ «ፈጣሪዬ ሆይ አስችለኝ!» ብሎ እያመለከተ የሠራውን (ኃጢአቱን) ሁሉን ለሚያውቅ ፈጣሪ በአንጻረ ካህን ሊገልጥ ይገባል። *«ክስት ድካመክ ለማእምረ ኩሉ /ሁሉን ለሚያውቅ ድካምህን* (በደካማነትህ የሠራኸው ኃጢአት) ግለጥ» እንዲል (አረ.መን ፴፫)

በንስሓ ኃጢአትን አለመናዘዝ የእግዚአብሔርን ብዝኃ ትዕግሥቱን እንደ መናቅ ነው። አምላክ በቸርነቱ ለንስሓ ጊዜን ሰጥቶ ታግሦ ሲጠብቀው ራሱን ከንስሓ የሚያሸሽ ሰው ትዕግሥቱን እንደናቀ ይቆጠራል። ሐዋርያውም «የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱን ባለጠግነት ትንቃለህን? ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቁጣ ቀን ቁጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ።» (ሮሜ ፪፥፫) ብሏል።

ንስሓ ዲያብሎስ በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ሲገነባው የኖረውን ጥቅመ ኃጢአት (የኃጢአት ግንብ) በአንዴ የምታፈርስበት ናት። ለዚህም ነው ምዕመናን ኃጢአታቸውን ለካህን ገልጠው ንስሓ እንዳይገቡ ፍራቻን ፣ ጥርጣሬን የመሳሰሉ ዘዴዎችን በመጠቀም ወደ ኋላ የሚያስብላቸው። «ኃጢአቴን ለካህኑ ስናገር ቢታዘቡኝስ? እርሳቸው እንዲህ ያለ ክፉ ግብር እያለባቸው እንዴት እኔን ከማዕሠረ ኃጢአት

ሊፈቱ ይችላሉ? ወዘተ . . . » የሚሉ ጥርጣሬዎችን በመፍጠር ሰይጣን ምዕመናን በኑዛዜ ወደ ካህን እንዳይቀርቡ ያደርጋል።

«አስመ ይጸልዖ ለዘፈነወኪ / የሚልክሽን ይጠላዋልና» እንዲል ሰይጣን በንስሓ ሥርየት ሰጥተው የሚልኩ ካህናትን ይጠላል። ምዕመናንም ኃጢአታቸውን እንዳይገልጡ ያደርጋል። ስለዚህ ምዕመናን ይህን የዲያብሎስ ሴራ አውቀው በግልጽ በመናዘዝ *«ብዙኅን እለ ተኃድገ ሎሙ ኃጢአቶሙ»* ከተባለላቸው «ኃጢአታቸው በንስሓ ከተተወላቸው ከንዑዳን ክቡራን» ጋር ሊደመሩ ይገባል። (መዝ. ፶፩፥፩ ትር)

ኃጢአትን አምኖ በካህን ፊት መናዘዝ ብዙዎች እንደሚገምቱት ለጊዜው ተዋርዶ (መዋረድ) ቢመስልም የሚያሰጠው ክብር ግን ታላቅ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ *«ሰጎሕቱ እንክ ርእሰክሙ ታሕተ ዕዴሁ ለእግዚአብሔር ጽንዕት ፣ ከመ ያሴእሰክሙ አመ ይሔውጸክሙ* / በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ» በማለት ተናግሯል። (፩ኛ ጴጥ ፭፥፮) በዚህ *ሥፍራ «ዕዴሁ ጽንዕት* / ኃይለኛው የእግዚአብሔር እጅ» የተባሉት ካህናት ናቸው። በእጅ እንደምናነሣና እንደምንጥልበት ሁሉ አምላክም ፈርዶ ገሃነመ እሳትን ለኃጥአን መንግሥተ ሰማይን ለጻድቃን የሚያወርስባቸው እጆቹ ካህናት ናቸው። ስለዚህ ምእመናን እርሱ ፈጣሪ *«ከመ ያሴዕለክሙ አመ ይሔውጸክሙ»* /በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ» እንዳለ ሕዝቡን ሊጎበኝና ሊፈርድ በሚመጣበት በምጽአት ጊዜ ክብርን ለመቀበል ከጽኑዓን እጆቹ ከካህናት ሥር ራሳችንን በንስሓና በኑዛዜ ማዋረድ ይገባናል።

በወንጌል «ከዘር ሁሉ የምታንስ የሰናፍጭ ቅንጣት ባደገች ጊዜ ከአታክልት ሁሉ ትበልጣለች ፣ የሰማይ ወፎች መጥተው በቅርንጫፎቿ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች።» ተብሎ እንደተጻፈ

በምክረ ካህን ያለ ሰውም ኃጢአቱን ሲናዘዝ በተዋርዶ ቢሆንም ቀኖና ተቀብሎ በፈጸመ ጊዜ ግን ከሁሉ የሚበልጥ ይሆናል። ያቺ ቅንጣት ዘር አድጋ የአእዋፍ መሥፈሪያ እንደሆነች በንስሓ የተመለሰ ሰውም ሰው ሁሉ መጥቶ ከእግሩ ሥር ወድቆ «ለሰበኝ / ለተርሳኝ» እስኪለው ድረስ ይከብራል። (ማቴ. ፲፫፥፴፪ ትር) በመመለሱም ታላቅ መንፈሳዊ ኃይልን አምላክ ይሰጠዋል።

ኃጢአትን በግልጽ መናዘዝ የሕሊና ዕረፍትና መንፈሳዊ ፈውስ ነው። ብሎም ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንድ የሚያደርግ ነው። *«ተአምኖ ኃጣውእሰ ፈውስ መንፈሳዊ ውእቱ / ኃጢአትን ማመን መንፈሳዊ ፈውስ ነው።»* እንዲል ኃጢአትን መታመን መንፈሳዊ ፈውስ ማግኘት ነው። የመንፈስ መባሉም ሥጋዊ ተዛምዶ ከሥጋ ጋር እንደሚያዛምድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለሚያዛምድ ነው። (ፍ.ነገ ፬፮፲፬)

❖ በኑዛዜ ወቅት ተስፋ መቁረጥ ፣ ትዕቢትና መዘናጋት

ንስሓ ከገባን በኋላ ደግመን ኃጢአት ብንሠራ ተስፋ አለመቁረጥና ከዕለት ዕለት ኃጢአትን እየተውን ለመሄድ መሞከር ይገባናል። ሰው ሰውነቱ ከወሸባ ቤት (መታጠቢያ ቤት) ገብቶ የሚታጠበው ዳግመኛ አልቆሽሽም ብሎ አይደለም። በንስሓ ኃጢአቱን የሚናዘዝም ሰው ዳግመኛ አይበድልም ማለት አይደለም። ስለዚህ በኑዛዜ ስንኖር ከንስሓ በኋላ ተፈትነን በኃጢአት ብንወድቅ ተስፋ ሳንቆርጥ ወዲያው ንስሓ ልንገባ ይገባል። «መልሼ ለምበድል ለምን ንስሓ እገባለሁ?» ማለት ግን «መልሶ ለሚርበኝና ለሚጠማኝ ለምን እበላለሁ እጠጣለሁ?» «መልሼ ለምቆሽሽ ለምን ሰውነቴን እታጠባለሁ?» እንደ ማለት ነው።

አንድ ሰው የለበሰው ልብስ ትንሽ ጭቃ ቢነካው መንካቱ ካልቀረ ብሎ ክጭቃ አይለወስም ፣ የቆሸሸውን አካሉን ፈጥኖ ይታጠባል። ሰውነቱ የቆሰለ ሰውም «ቀይ ትንሽ ያመርቅዝ ፣ በደንብ ይዳረስ» አይልም ወዲያው ይታከመዋል። አንዱ በኃጢአት ስንወድቅም ፈጥነን በንስሓ መታጠብ እንጂ ንስሓ ባለመግባት ለባሰ በደል መዳረግ የለብንም። ሰው ወደ ቤቱ ለመመለስ የሚፈጅበት ጊዜ ከቤቱ የራቀውን ያህል እንደሆነ ከአምላካችን በኃጢአት ርቀን ስንቆይም መመለሱ እየከበደን በዚያው ልንቀር እንችላለን። ስለዚህ እንደወደቅን መነሣት ይገባናል።

ኃጢአት በእሾህ ትመሰላለች። እግዚአብሔር ለአዳም «ምድር ከአንተ የተነሣ የተረገመች ትሆናለች ፣ እሾህና አሜከላንም ታበቅላለች» ብሎ ሲረግመው በዕለተ ማክሰኞ ያልተፈጠረ እሾህና አሜከላ ኖሮ እንዳዲስ ይፈጠራል ለማለት ሳይሆን ምድር የተባለ ሰውነትህ «ክፋ ምኞትንና ኃጢአትን» ታበቅልብሃለች ሲለው ነበር። በወንጌልም ጌታችን እሾህን «የዚህ ዓለም ሃሳብ ፣ የባለጠግነት ምኞት ፣ የሌላውም ነገር ምኞት» ብሎ ተርጉሞታል። (ማቴ. ፲፫፥፳፪ ፣ማር.፬፥፲፰) እሾህ የወጋው ሰው ወዲያው ይነቅለዋል እንጂ ትንሽ ልቆይ አይልም። ኃጢአትንም ያለ ቀጠሮ ወዲያው መናዘዝ ይገባል። ለንስሐም ያለ ተስፋ መቁረጥ ፈጥነን መነሣት አለብን።

በመጽሐፈ መነኮሳት ላይ ያለ አንድ ቃለ ምልልስ ይህን ሀሳብ ያጠናክርልናል። አንድ መነኩሴ ወደ አባ ቢሶይ መጥቶ «እስከ መቼ ብዙ ጊዜ እየተሰነካከልኩ ስወድቅ ስነሣ እኖራለሁ?» ቢለው «እስክትሞት ድረስ» ብሎታል። ስለዚህ በኃጢአት በወደቁ ጊዜ ያለ ቀቢፀ ተስፋ (ተስፋ መቁረጥ) ፈጥኖ ንስሓ መግባት የሚገባ ነው ማለት ነው።

ብዙ ምእመናንን የንስሓን ሕይወት ጀምረው እንዲያቆሙ ምክንያት የሚሆናቸው ይህ ተስፋ መቁረጥና በተደጋጋሚ በኃጢአት ከመውደቅ የሚመጣ ዝለትና መሰላቸት ነው። እግዚአብሔር ይቅር ማለት ሳታክተው እኛ «ይቅር በለን» ማለት የሚሰለቸን መሆኑ ጅግ ያስደንቃል። ግንዛቤው ላያንሳቸው በተስፋ መቁረጥ የሚርቁ ብዙዎች ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- «የወደቀ አይነሣምን? የሳተስ አይመለስምን?» (ኤር ፰፥፬) ፤ በእርግጥም እግዚአብሔርን የሚያሳዝነው ከሰው ከመውደቁ ይልቅ አለመነሣቱ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም «መውደቅ አዳማዊ ነው ወድቆ አለመነሣት ግን ዲያቢሎሳዊ ነው» ያለው ይህንን ነው። እናም በእምነት ያሉ ሁሉ ረድኤተ እግዚአብሔርን ታምነው ተስፋ ሳይቆርጡ በንስሓ መነሣት አለባቸው።

ኑዛዜን የፈጸመ ተነሳሒ ኃጢአትን ዳግመኛ ከሠራ በኋላ ፈጥኖ እንዳይናዘዝና ተስፋ እንዲቆርጥ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ በኑዛዜ ወቅት በስሜታዊነት የሚገምተው ግምትና የሚገባው ቃል ነው። አንዳንድ ተነሳሒያን በንስሓ ኃጢአታቸውን በተናዘዙበት ወቅት ከሚሰማቸው መንፈሳዊ ብርታትና ከሚያገኙት ውስጣዊ ሰላም ፤ እንዲሁም ቀኖናቸውን (ጸም ፤ ጸሎት ፤ ስግደት) በሚፈጽሙበት ወቅት ከሚያገኙት መንፈሳዊ ጥንካሬ በመነሣት ዳግመኛ የማይበድ እና በኃጢአት የማይሸነፍ መስሎ ይሰማዋል። ንስሓ ከገባ በኋላ በኃጢአት እንዳይወድቅ የሚያግዝ ልዩ ኃይል እንደሚሰጠውም ይጠብቃል።

ከዚህም አልፎ በመምህረ ንስሓው ፊት «ከእንግዲህ ይህን ባደርግ ይህን ብሠራ ይህን ያድርጉብኝ! ይህን ይጨምርብኝ!» ብሎ ሊፎክርና ሊምል ሊገዘትም ይችላል። እንዲሁም «እስከዚህ ሰዓት ድረስ እጾማለሁ! በቀን ይህን ያህል እሰግዳለሁ! ወዘተ. . . » እያለ ለራሱም ለንስሓ አባቱም ቃል ሊገባ ይችላል። በዚህ ወቅት ምናልባት መምህረ

ንስሓው «ተው ቀስ በል በመጠን ኑር» ያሉት እንደሆን መንፈሳዊነት የጎደላቸው ቢሆኑ ነው ብሎ ያስባል። *«እሰመ ንህነ በረዘ ጽጋብ ይመስለነ ከመ ንክል ጸዊመ* / በጠገብን ጊዜ አብዝቶ መጸም የሚቻለን ይመስለናል።» (ተግሣጽ) እንዲል ፤ ሁልጊዜ ፋሲካ ያለ መስሎት ብዙ ያቅዳል። ክዐ መናድን የሚያውቅበት ዲያቢሎስ ታዲያ ይህን የዋህ ሰው ዕቅዱን አበላሽቶ ካላሰበበት የኃጢአት መስክ ያውለዋል። ከዚህ በኋላ ለራሱም ለመምህረ ንስሓውም የገባውን ቃል አስቦ እንዲያፍርና ዳግመኛ እንዳይናዘዝ ያደርገዋል።

አንድም ይህ ክስተት የእግዚአብሔር ፈቃድ አለበት ፤ ይህ ተነሳሒ እንደዚህ እየወደቀ ካለየው አቅሙን ሊያውቅና ትሕትናን ገንዘብ ሊያደርግ ፤ ረድኤተ እግዚአብሔርንም ጥግ ሊያደርግ አይችልምና። ሠራዊተ መላእክት ከዲያቢሎስ ጋር ሲዋጉ ሁለት ጊዜ ተሸንፈው በሦስተኛው እንዲያሸንፉ ያደረጋቸው በራሳቸው ኃይል እንደለሌላቸው እንዲያውቁ ነበር። ይህ የእግዚአብሔር አሠራር በቅዱስ ጴጥሮስ ሕይወትም ታውቋል።

ቅዱስ ጴጥሮስ «ሌሎቹ ሁሉ ቢክዱህ እኔ አልክድህም!» ብሎ በአምላኩ ፊት ቃል ገባ። በዚያች ምሽት ቅዱስ ጴጥሮስ እርሱ አምላኩን ስላለመካዱ እርግጠኛ ነበር። ጨምሮም ወንድሞቹ ግን ሊክዱ እንደሚችሉ መላ ምት አስቀመጠ። የበለጠ የከፋው «አልክድህም» ከማለቱ ይልቅ ወንድሞቹ ሊክዱ እንደሚችሉ መተንበዩ ነበር።
ኢትዮጵያዊው ሊቅ ርቱዐ ሃይማኖት «ኦ ጴጥሮስ በምንት ትትናገር ዘከመዝ ነገረ ዘኢይደሉ ደዳስ ስምስቈሎሙ ለስግብርተ እግዚአብሔር ከመ ያንጽሑ ርእሰሙ ወያርኩሱ ቢጾሙ ፤ ርቱዕስ ትዜኢ ስነኒ ሲዩክህዴክ ወስንሙየ ሲዩክህዴክ ስንዘ ጸጋክ የስቀበነ ሲተቢኑ በትሕትና ወበፍቅር» «ጴጥሮስ ሆይ ፈሳቸውን ንጹሕ አድርገው ባዕንጀርቻቸውን ርኩስ ማድረግ ከማይገባቸው ከእግዚአብሔር ባፈያዎች ስፍ ሊጠማ የማይገባን ነገር በምን ተናገሬስህ? እንደሚገባውስ በትሕትናና በፍቅር ጸጋህ

እየጠበቀን እኔም አልከድህም ወንድሞቼም አይከዱህም ስትል ነበር?» (ሮቱዐ ሃይማኖት / በአንተ ከሀደት ጴጥሮስ)

ይሁንና ፈተና ሲጸናበት ከአንዴም ሦስት ጊዜ ካደው። ምሎ ተገዝቶም «የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ» ያለውን ክርስቶስ «ሰውዬውን አላውቀውም» አለ። በዚህን ሰዓት «ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» ያለው መምህረ ንስሓው ክርስቶስ ቀና ብሎ ተመለከተው። ሐዋርያው ይህን የትዝብት ቀኖና ተቀብሎ «ከሁሉ ይልቅ እወደው ከሁሉ ቀድሜ እክደው!» ብሎ እያለቀሰ ቀኖናውን ፈጸመ። ይህ ሁሉ የሆነው ድካሙን ይረዳ ዘንድ ነበር። በኋላም ጌታችን ሰው ለማጥመድ የተጠራው ቅዱስ ጴጥሮስን ከትንሣኤው በኋላ አሣ ሲያጠምድ ሲያገኘው በሚቆጠቁጥ ቃል አልተናገረውም «ወደኛለህን?» «ምእመናንን ጠብቅ!» ብሎ አደራ በመስጠት ይቅር እንዳለው ገለጸለት እንጂ።

«ሰው ሆኖ የማይበድል እንጨት ሆኖ የማይጤስ የለም» እንዲሉ ሰው ሁልጊዜ ንጹሕ ይሆን ዘንድ አይችልም። በኃጢአት መውደቁም አይቀርም። መጽሐፍ ይህን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፦ «እነሆ በቅዱሳኑ እንኳን አይታመንም፤ ሰማያትም በፊቱ ንጹሐን አይደሉም ፤ ይልቁንስ አጸያፊና ዐረከሰ ፡ ኃጢአትንም እንደ ውኃ የሚጠጣ ሰው ምንኛ ያንስ?!» (ኢዮ. ፲፭÷፲፮) በማለት።

ጠቢቡ ሰሎሞን *«ሰብዓ ይውድቅ ጻድቅ ወይትነሣእ ወረሲዓንሰ የአክዩ በእኩይ / ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ፤ ይነሣማል ! ኀጥአን ግን በክፉ ላይ ይወድቃሉ።»* እንዲሉ እውነተኛ ክርስቲያን ሲበድልና በንስሓ ሲነሣ ኖሮ በመጨረሻም ንስሓ ገብቶ ይሞታል። እግዚአብሔርን የዘነጉ ሰዎች ግን ንስሓ ሳይገቡ በኃጢአት ሳሉ ይሞታሉ። (ምሳ ፳፬÷፲)

ይህን ስንል ግን ንስሓንና የእግዚአብሔርን ቸርነት እንደ መተማመኛ እየቆጠሩ ወደ ኃጢአት አውቆ መነከር ይገባል ለማለት አይደለም። «አጠንናለሁ ብሎ መሰበር እንደሌለ ንስሐ እገባለሁ ብሎም ኃጢአትን መሥራት አይገባም።» (ማር.ይስ.) መጽሐፍ ቅዱስም «ስለ ኃጢአትህ ንስሓ መግባትን አትፍራ ፤ የእግዚአብሔር ቸርነቱ ብዙ ነው እያልክ በኃጢአት ላይ ኃጢአት አትሥራ» ይላል (ሲራ ፭÷፰) ነገር ግን ተነሳሒው ከኃጢአት ለመላቀቅና ብሎም የኃጢአትን ምንጭ ለማድረቅ መታገል ይኖርበታል። ራስን ወደ ኃጢአት በሚመራ መንገድ ላይ አቁሞ ከኃጢአት መለየት አይቻልምና በተቻለ አቅም መሸሽ ያስፈልገዋል።

ኃጢአትን እንደ ጀብድ ቆጥሮ ዘና ብሎ መናዘዝ ጸጸት የሌለበት ኑዛዜ ነው። «ስንቱን አየነው..! አይቆጨንም!» እያሉ በትዝታ ባሕር እየዋኙ ኃጢአትን መናገርም ሆነ፤ ኃጢአትን እያጣጣሙ የልብን ሠርተው ወደ ካህን እየመጡ ነውርን እንደ ክብር እንደ ዘገባ (ሪፖርት) ማቅረብ ኑዛዜ አይደለም ። አበው ካህናት *«ለበጎች የማይራሩ» ተብለው ከፍርድ አንዳይገቡ* ታግሰው ኑዛዜያችንን ቢሰሙን እንኳ እኛ ግን ገድል እንደፈጸመ ሰው ኃጢአትን ሳንቃወም እየሠራን ልንመጣ አይገባም። የሠሩትን ሠርቶ «ሰይጣን ፈተነኝ» ማለትም የሚያስኬድ አይደለም። ራሱን ለኃጢአት ከሚመራ ሁኔታ ላያርቅ በሰይጣን የሚያሳብብ ሰው ከሰይጣን ይልቅ ራሱን በራሱ እየፈተነ ነው።

በየዕለቱ የምንወድቅበትን ኃጢአት እንድንሠራ የሚያደርጉን ምክንያቶች በመለየት የኃጢአትን ምንጭ ማድረቅ ይጠበቅብናል። እዚህ ላይ «ቤትሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ ንጉሥ ውበትሽን ወዲልና» ተብሎ ለእመቤታችን ቤተ መቅደስ መግባት የሚተረጎመውን ቃል ለምእመናን መተርጎሙንም ልናነሣ እንችላለን። ክብርንና ንጽሕናን የሚያሰጥ ሰዎችን መተው ሳይሆን ግብራቸውን መተው ነውና ንስሓ የሚገባም

ሰው ለበደል የሚመሩትን ሁኔታዎችንና ባልንጀራዎችን በመተው ኃጢአቱን ለመቀነስ መታገልና መወሰን ይኖርበታል። ኃጢአትን በንስሓ ለመናዘዝ ቀጠሮ አያስፈልገውም። «ከዛሬ ነገ ፣ ከዘንድሮ ከርሞ ኃጢአቴን ለመምህረ ንስሓዬ ነግሬ ፣ የወዲያ ዓለም ቤቴን ሠርቼ ከፈጣሪዬ ታርቄ እሞታለሁ» ብሎ የሚያስብ ሰው ንስሓ ሳይገባ ከፈጣሪው ሳይታረቅ ንግድም ቢሉ ፣ ዘመቻም ቢሉ በሄደበት ግልድው ብሎ ሊቀር (ሊሞት) ይችላልና «የመዳን ቀን ዛሬ» መሆኑን አስተውሎ ቶሎ ከፈጣሪው መታረቅ ለክርስቲያን ይገባዋል። ለንስሓ ቀጠሮን የሚሰጥ ግን ከላይ እንደተገለጠው ምቹ ጊዜ ሳያገኝ ክፉ ሞትን ይሞታል። *«ሞቱ ለኃጥእ ፀዋግ / የኃጥእ ሞት የከፋ ነው»* እንዲል። (መዝ ፴፫ ፥ ፳፩)

ኑዛዜና ንጽጽር

ሌላው በኑዛዜ ወቅት መወገድ ያለበት ደግሞ የራስን ኃጢአት ከሌሎች ሰዎች ኃጢአት ጋር ፣ ከዘመኑ ሁኔታ ጋር ፣ ተነሳሒው ራሱ ቀድሞ ከነበረበት ክፉ ግብር ጋር ማነጻጸር ነው። አንዳንዶች *«እነ እገሌ ይህን ይህን እያደረጉ እኔ ይህን ባደርግ . . . »* እያሉ ለራሳቸው ይቅርታ በመስጠት ኑዛዜያቸውን በሚገባ አይፈጽሙም። ይሁንና እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ እንደሥራው ይሰጣል እንጂ እያነጻጸረ «የአንተ ይሻላል» እያለ አይፈርድም «ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ» ብሏል። (ራእ.ሯ፪ ፥ ፲፪) ከዚህም ሌላ በክፉ ዓለማዊ ግብርና በኃጢአት ሲኖሩ ቆይተው በንስሓ ከተመለሱ በኋላ የሚሠሩትን ኃጢአት ቀድሞ ይሠሩት ከነበረው ጋር እያነጻጸሩ «አሁን ተሻሽዬአለሁ» በማለት ተግተው ከመናዘዝ ወደ ኋላ የሚሉም አሉ ፣ ይህም የሚገባ አይደለም። ለራስ ይቅርታ እያደረጉም ንስሐ የለም።

የኃጢአት ትልቅ ትንሽ የለውም። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ አለ። «ጥቂት እንደ በደልክ አትንገረኝ (ጥቂት በደልኩ አትበለኝ) የኃጢአት ጠብንዩ አንድ ነው ፣ ልዩነት የለበትም፣ ይህንን የሚያስረዳ ነገር የጎልማሳ ገዳይና የሕጻን ገዳይ እኩል መሆናቸው ነው።» ብሏል። አሥር በሮች ያሉት ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው ዘጠኙን በሮች ዘግቶ አንዱን ከፍቶ ቢተው ሌባ በአንዲቱ በር ገብቶ ከኩተት እስከ ሽበት ፣ ከልጅነት እስከ እውቀት ያፈራውን ሀብቱንና ንብረቱን ይዘርፍበታል። እንደዚሁም ሁሉ ብዙ ሕግጋተ እግዚአብሔርን በመጠበቅና ጥቂቶቹን ችል በማለት አልጎዳም ማለት አይቻልም።

ንስሐ ከገቡም ኋላ ስላለፈው ኃጢአት መጨነቅ አይገባም። እግዚአብሔር «ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ ኃጢአትን አትሥራ» ብሎ እንደተናገረው ስለወደፊቱ እንጂ ስላለፈው መጨነቅ አይገባም። መጽሐፈ ቀሌምንጦስም «ወኢትኩን ንሱሐ ላዕለ ዘኀለፈ ግብር» «ባለፈው ሥራህ /ንስሐ በገባህበት/ የምትጸጸት አትሁን» ይላል።

፪. ቁኖናና መንፈሳዊ ሥርዓቱ

«ቀኖና» ማለት «መሥፈሪያ» ማለትሲሆን እንደየአገባቡ የተለያየ ትርጓሜን እየሰጠን የምንጠቀምበት ቃል ነው። በምሥጢረ ንስሐ ካህኑ ተናዛዚው ያለበትን ደረጃ በማገናዘብ እንዲፈጽም የሚያዘዛቸው መንፈሳዊ ክንውኖች ቀኖና ተብሎ ይጠራል። ቀኖና ቅጣት ሳይሆን ሕክምና ነው። ዓላማውም አንድን ሰው ለሠራው ኃጢአት እንደ ክፍያ እንዲሆን መቅጣትና መበቀል ሳይሆን ከኃጢአት እንዲላቀቅ የሚሰጥ መፍትሔ ነው። ሐኪም ለበሽተኞቹ የሚሰጠው መድኃኒት ፣ እንዲመገቡና እንዳይመገቡ የሚሰጠው መመሪያ ፣ የሚነግራቸው የአድርጉና የአታድርጉ ትእዛዛት በሚሉ በሽተኛውን ከበሽታው ለማላቀቅ የሚሰጥ እንጂ ታማሚውን ለመቅጣት የሚደረግ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ካህኑም ለልጆቹ የሚሰጠው ቀኖና ከዚህ አንጻር ሊታይ ይገባል።

ቀኖና በቀል ነው እንኳን ቢባል በቀልነቱ በኃጢአት ላይ ነው እንጂ ንስሐ በገባው ሰው ላይ አይደለም። ሐዋርያው «መታዘዛችሁም በተፈጸመች ጊዜ አለመታዘዝን ሁሉ ልንበቀል ተዘጋጅተናል» እንዳለው ነው። (፪ቆሮ.፲፥፮)

ይኸው ሐዋርያ «እንደዚህ በሠራው ላይ በጌታችን ስም ፈርጀበታለሁ . . . መንፈሱ (ነፍሱ) በጌታ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው» ብሏል። (፩ኛ ቆሮ ፭፥፬-፭) ይህም ስለ ቀኖና የተነገረ ሲሆን የሚሰጥበት ዓላማ ነፍስን ለማዳን እንደሆነ ያስረዳል። «ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው» ማለቱ በቀኖናው ወቅት የንስሓ ጉዞውን ለማሰናከል ሰውን ይፈትናልና ተነሳሒው ቀኖናን በመቀበል መከራን ለሚያጸና ለሰይጣን እንዲሰጥና ድል ነስቶ ክብርን እንዲያገኝ ፍርዴ ነው ማለት ነው።

በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ካህናት የሚሰጡት ቀኖና የተለያየ ነው። ጸም ፣ ጸሎት ፣ ስግደት ፣ ምጽዋት ፣ ከማኅበረ ምእመናን መለየት (፪ተሰ.፪፥፲፬) በአብዛኛው የሚታወቁት ናቸው። እንዲሁም «የካህኑ ቁጣ» ብቻም እንደ ቀኖና እንደሚቆጠርና ተቆጥቶ ብቻ ሊሸኘው እንደሚችል ፈጠሳ መንፈሳዊ የተሰኘው የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ያስረዳል። እንዲሁም ምእመናን ለንስሐ አባታቸው የሚያደርጉአቸው ልብስ እንደ መግዛት ፣ ጥምጣም እንደ መስጠት ፣ በቤት እንደማስተናገድ የመሳሰሉ አገልግሎቶች አሉ። እነዚህን ሥጦታዎች «ከእንተ እጅ አልቀበልም!» ብሎ በመወሰን ካህኑ ቢቃወም ይህም እንደቀኖና እንደሚቆጠር ይኸው መጽሐፍ ያስረዳል። (ፈጠሳ መንፈሳዊ ፭፥፻፴፮) ይህ ዓይነቱ ቀኖና እንኳን ካህንን በማገልገል የሚገኘውን መንፈሳዊ ዋጋ ጠንቅቆ ለተረዳ ሰው ነው እንጂ ለሌላው ሰው

ከግልግል የሚቆጠርና ሁልጊዜ ይህ ዓይነቱ ቀኖና ብቻ በተሰጠኝ የሚያስብል ነው።

የቀኖና አሰጣጥ እንደሚገመተው ብዙ ኃጢአት ላሰበት ብዙ ቀኖና ፣ ጥቂት በደል ለሠራ ሰው ደግሞ ትንሽ ቀኖና የሚሰጥበት አካሔድ የለም። እንዲያውም የቀኖና አሰጣጥ ከዚህ በተቃራኒ ነው። ብዙ ኃጢአት ለሠራ ሰው ጥቂት ወይም ምንም ቀኖና ሊሰጠው ይችላል። እንዲያውም ብዙ በደል ያለበትን ኃጢአተኛ «አይዞህ ፣ መውደቅ ያለ ነው!» ብሎ ማጽናናትና ማመስገን ይገባል። «ወባርክዎ ሰርጉም ከመ ጸትባረክ ፤ ወመጽክዎ ሰኃጥኦ በዘኢኮነ ድልወቱ» «ርኁመ ይባረክ ዘንድ ባርኩት ፤ ኃጢአተኛውንም የማይገባውም ቢሆን አመስግኑት» እንዲል። (ገጸ ሰዙ ሰላማ) ይህ ሃሳብ «ሰውን በማይገባውም ነገር ቢሆን አመስግነው ፤ ምስጋና ለሰው ኃይልን ይጨምርለታልና» («ወድሶ ለሰብ በዘኢኮነ ድልወቱ እስመ ወድሶ ለሰብእ ይዌስኮ ኃይለ») ከሚለው ቃለ ሊቃውንት ጋር ይሔዳል።

እጅግ በደልን የፈጸመ ሰው ቀኖና ቢያከብዱበት ተስፋ ወደ መቁረጥ ያመራል። በርትቶ ቀኖናውን ቢፈጽም እንኳን ምሕረት ያገኘው በእግዚአብሔር ቸርነት ሳይሆን በገዛ ጉልበቱ እንደሆነ ሊሰማው ይችላል። «ወሰእመ ርኢኮ ለኃጥእ ገሥፆ በንስቲት ወኢታፍጥን ሰዲዶቶ ሥራዕ ሎቱ ጸመ በአምጣነ ክሂሎቱ አሐደ ወክልዔተ ሱባኤያተ» «ኃጢአተኛውን ባየህ ጊዜ በጥቂት ገሥጸው ፤ ለማባረርም አትቸኩል (ለማውገዝ) ፤ በሚችለው መጠን አንድም ሁለትም ሱባኤ ጸምን ሥራለት።» ይላል። (ፍትሐ ነገሥት ክን. ፭)

በብሱይ ኪዳን ለምጽ የነበረበት ሰው ይደረግበት የነበረው ነገርም ለዚህ ምሳሌ ነው። ለምጹ ሙሉ በሙሉ በሰውነቱ ከታየ ከሰው ጋር እንዲቀላቀል የሚፈቀድለት ሲሆን ይህም ተስፋ እንዳይቆርጥ ነበር። በአንጻሩ ለምጹ ዝንጉርጉር የሆነ እንደሆን ግን ከክተማ

ያስወጡት ነበር። ይህም ምሳሌ ነው ፤ ዛሬ ጽኑዕ ኃጢአት ለሠራ ርኅራኄ እንደሚደረግለትና ጥቂት ለሠራ ግን ቀኖናው እንደሚጸናበት ያስረዳናል።

በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብርቱ ሆኖ ግን ጥቂት ኃጢአት ለሠራው ሰው ከበድ ያለ ቀኖና ይሰጠዋል። ይህም በጥቃቅኑ ኃጢአት ጀምሮ ከባድ ኃጢአት እንዳይሠራ «ጥቃቅኖቹን ቀበሮዎች» አጥምዶ ለመያዝ ነው። «ሕፃናቶችሽን በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው» ተብሎ እንደተጻፈ በሕፃንነት ያለውን የሃሳብ ኃጢአት መግደል ከተቻለ ወደ መናገርና ወደ መሥራት ኃጢአት አያድግምና የተጸነሰች ምኞት አድጋ ኃጢአትን ከመውለዷ በፊት በአጭሩ ለመቅጨት ቀኖናን ያጸኑበታል። (መዝ. ፻፴፮፥፱) ፈጪ መንፈሳዊም «ያክብዱ ላዕሌሁ ክቡዳተ ቀኖናተ ከመ ይትባዝኅ ጽድቁ ወይፈደፍድ አስቡ» ይላል። «ጽድቁ እንዲበዛ ዋጋውም እንዲልቅ ክብድ ቀኖናዎችን ይጫኑበት»

ጸም ፣ ጸሎት ፣ ስግደትና ምጽዋትም የሚሰጡበት ሁኔታ የተናዛዚውን የመንፈሳዊነት ፣ የዕውቀት ፣ የአኗኗር ደረጃ በማገናዘብ ነው። ለምሳሌ ሠርቶ ለሚገባና የወር ገቢ ላለው ሰው የምጽዋት ቀኖና አይሰጠውም። ምክንያቱም ባለ ደመወዝ እስከሆነ ድረስ ከደመወዙ ለቀኖና የሚከፍለውን ገንዘብ እየመደበ ያሻውን ኃጢአት እንዲሠራ ሊበረታታ ይችላል። ለባለጸጋም መጽውት ቢሉት ገንዘቡን እየዘገነ እየሰጠ ኃጢአት መሥራቱን ይቀጥላል። ቀኖናውም ከኃጢአት መላቀቂያ መድኃኒት መሆኑ ቀርቶ ኃጢአት ለመሥራት የሚከፈል ቀረጥ ይሆናል። ስለዚህ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ላሉ ሰዎች ከምጽዋት ይልቅ ሰውነታቸውን ለመግዛት የሚያስችላቸው ጸም ፣ ጸሎትና ስግደት ይሰጣቸዋል። በአንጻሩ ከአነርሱ አቅዋም ለተለየው ደግሞ ምጽዋት ይሰጠዋል። ባይኖረው እንኳን ተሸክሞ ፣ የተዋረደ ሥራ ሠርቶም

በሆን ምጽዋትን ይከፍላል። ገንዘቡን ለማግኘት የሚያልፈው ውጣ ውረድ ከኃጢአት ሃሳብ እንዲላቀቅ ይረዳዋል።

አበው ካህናት ከሚሰጧቸው ቀኖናዎች በተጨማሪ በቀኖናው መፈጸሚያ ሰዓት ላይም ይወስናሉ። ተነሳሒው በሌሊት እንዲሰግድ ፣ ማልዶ እንዲነሣ ፣ ከሰው ሳይገናኝ እንዲቆይ ወዘተርፈ በማድረግ ትኃትን እንዲለማመድ ፣ የጸሎት ሕይወት እንዲኖረው ያደርገዋል።

መምህረ ንስሓን የሚይዙ ሁሉ ቀድመው ለምክሩና ለትእዛዙ ለመገዛት ጎሊናቸውን ያዘጋጁና ያሳመኑ መሆን አለባቸው። የንስሓ አባት ብለው የያዙትን አባት አለመስማት ግን «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል» ብሎ የሾማቸው ፈጣሪን ማስቀየም ነው። (ማቴ ፲፥፵) ንጉሥ እሰሩ ፍቱ ብሎ ሥልጣን ሰጥቶ የላካቸውን መኳንንቱን በንቀበት አርሱን እንደ ናቁት ይቆጠራል። ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁምና። ለካህናትም አለመታዘዝ ለሾማቸው ለእግዚአብሔር አለመታዘዝ ነው።

የንስሓ አባት ሥራው ማዕድ መባረክና ጠበል መርጨት ብቻ ላይሆን የበጎቹን መንፈሳዊ ሕይወት መምራትና መምከር ከፍ ሲልም መገሠጽ ነው። *«ንስሓ ግቡና በሥጋ ወደሙ ተወሰናችሁ ኑሩ ፤ ጋብቻችሁን በሃይማኖታዊ ሥርዓት መሠረት ፈጽሙ ፤ የተጣሉትሁትን ታረቁ»* ወዘተ ብሎ ካህን ሲነግራቸው *«ለሥጋ ወደሙ ገና ልጅ ነኝ ፤ ሠርግ ያለ ዳንኪራ ምን ሲደረግ? ፤ አገሌን / አገሊትን ይቅር ብል እንዲህ ይደርገኝ!»* ብለው ከካህን ጋር አሰጥ አገባ የሚይዙ «ምነው አባ ጠበሉን ረጭተው ዳቦውን ቆርሰው ቢወጡ!» የሚሉ ሰዎች አስቀድመው መምህረ ንስሓን ባይይዙ ይሻላቸው ነበር። ምንም ከማይናገራቸው ካህን ይልቅ የሚገሥፃቸውን ካህን ምእመናን መውደድ አለባቸው። አይቶ እንዳላየ ማለፍ የአባትነት ተግባር አይደለም።

እንደ ቅዱስ ዳዊት ያሉ የእምነት ሰዎች ግን እንደ ናታን ያሉ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ሲገሥፁአቸው «*እግዚአብሔርን በድያለሁ*» ብለው ሥርየትን ይለምናሉ። «*እግዚአብሔር ኃጢአትህን አርቆልሃል*» የሚል ይቅርታንም ያገኛሉ። (፪ሳሙ ፲፪፣፯-፲፪) በኋላ ዘመንም መምለኬ ጣዖት (ጣዖት አምላኪ) የነበረው መቃቢስ ረዓይ የተባለ ነቢይ መጥቶ ሲገሥፀው ጉድጓድ ቆፍሮ እስከ አንገቱ ገብቶ ጽኑ እንባን አንብቶ ንስሓ መግባቱ የእግዚአብሔር መልእክተኞችን ተግሣጽ መስማትና ኃጢአትን ማመን እንደሚገባ ያስተምራል። (፪ኛ መቃ ፪፣፩-፲፩) የንስሓ አባት ይዘው ንስሓ አንገባም የሚሉ ግን ሐኪም ይዘው አንታከምም የሚሉ ይመስላሉ።

ለካህን ትእዛዝ የማይገዛ ምእመን የካህንን ሥልጣን የማያውቅ ነው እንጂ ቢያውቅ በፍርሃት በፈጸመ ነበር። ምእመናን ባይታዘዙአቸው «ለካህናት ከአፋቸው ቃል በፍጥነት የሚታዘዙ መላእክት አሏቸው። የአፋቸው ቃል በሁለት ወገን የተላለ ሰይፍ ነው።» (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ) ሐናንያና ሰጲራን እሳት እንደ ገባ ገለባ ያደረጋቸው በቅዱስ ጴጥሮስ የተነገረ የካህን ቃል አይደለምን?

ሐናንያና ሰጲራ መንፈስ እግዚአብሔርን አታልላለሁ መሰሏቸው (አታልላለሁ ብለው) የገንዘባቸውን መጠን ሸሽገው በተቀሠፉ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስን ደቀ መዝሙሩ ቀሌምንጦስ «እንደምን ነው?» ብሎ ጠይቆት ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስም «ተናግሬ አስክጨርስ መልአክ ሰይፉን መዝዞ ይጠብቀኛል ስጨርስ ይቀጣቸዋል» ብሎታል።

ይህ የሚያስደንቅ አይደለም። እንኳን በደገኛው የሐዲስ ኪዳን ካህን በቅዱስ ጴጥሮስ ቃል ይቅርና በብሉይ ኪዳን ነቢይም ይህ ተፈጽሟል። ነቢዩ ዳንኤል ሶስናን በሐሰት የከሰሷትን ረበናተ አይሁድ (የአይሁድ መምህራን) በሕዝብ ፊት ጠይቋቸው መልሳቸው በተለያየ

ጊዜ «*ይሰጥቅሙ አግዚአብሔር ከመ ሔርጋሔ* / እግዚአብሔር እንደ አክርማ ይስንጥቃችሁ» ባለ ጊዜ ተናግሮ ሳይፈጽም የታዘዘ መልአክ ሰንጥቋቸው የለም?። አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም ስለ ካህን ሲናገር «እንደበቱ መናፍቃንን ከምእመናን ለመለየት ሰይፍ ሆነለት» ብሏል። (አርጋኖን ዘሰኑይ) ታዲያ እንዲህ ላለው የካህን ትእዛዝ መገዛት አይገባምን? ይህ እንግዲህ ጨርሰው ለካህን አንታዘዝም ለሚሉት ነው።

ምእመናን ለካህናት መታዘዝ ያለባቸው ትእዛዙ ከሃይማኖት መንገድ የሚያወጣ እስካልሆነ ድረስ ብቻ ነው። ካህኑ መንፈሰ እግዚአብሔር ርቆት ክፉ ምክርን ቢመክር እያወቁ አባቱ አዝዘውኛል ብሎ መፈጸምም አይገባም። «ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ... እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና ተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው» ተብሎ ተጽፏል። (ኤፌ.፮÷፩-፬) ይህ ቃል ለሥጋ ወላጆችም ሆነ ለነፍስ አባቶች የሚሠራ ነው። ለወላጆቻችሁ «በጌታ ታዘዙ» የሚለው ቃል ለሥጋም ሆነ ለነፍስ አባቶቻችን መታዘዝ የሚገባን «በጌታ» (በሃይማኖት መንገድ) ብቻ መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን «በጌታ ተግሣጽና ምክር አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው» የሚለው ደግሞ ወላጆች የሥጋ ልጆቻቸውን ካህናት የነፍስ ልጆቻቸውን «የጌታ ተግሣጽና ምክር» በሆነ በእግዚአብሔር ቃል እንዲያሳድጉና ልጆቻቸውን በእግዚአብሔር እንዳያስቀሥፏቸው /እንዳያስቀሥፏቸው/ የሚያዝዝ ነው።

አንድ ሰው ከሐኪም ዘንድ ቀርቦ ከታየ በኋላ መድኃኒቱን በአግባቡ ባይወስድ ፈውስ እንደማያገኝ ቀኖናውን ያልፈጸመም እንዲሁ ነው። በሽተኛው ሰው ባለ መድኃኒቱ «*ልገምህ ልተኩህ*» ሲለው «*ያመኛል ይፈጀኛል!*» ፣ «*መድኃኒት ጠጣ*» ሲለው «*ወገቤን ያመኛል!*» ፣ «*ጹም*» ሲለው «*አልችልም!*» ፣ «*መጸውት*» ሲለው «*የለኝም!*» እያለ የሚያመካኝ መሆን የለበትም። «*ወግበር ሎቱ ለዐቃቤ ሥራይ እስመ ሎቱኒ እግዚአብሔር ፈጠሮ ወአታርሕቆ እምነቢሕ እስመ ሎቱኒ*

ትፈቅዶ / እግዚአብሔር እርሱን መርጦታልና ሰባስ መድኃኒት ሥራውን ሥራለት (ታዘዘው) እርሱን ትሻዋለህና ከአንተ አታርቀው» ተብሎ እንደተጻፈ (ሲራ ፴፮፥፲፪) በወንጌልም *«ወለዘሂ አስጠለ አሐደ ምዕራፈ ሑር ምስሌሁ ፪ተ / ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውንም ከእርሱ ጋር ሂድ»* ተብሏልና መምህረ ንስሓው አንድ ሱባኤ ቀኖና የሰጠው ተነሳሒ ሲሆን ሲሆን *«ይህስ ተስማምቶኖል ይገባኖል ጨምርልኝ»* ብሎ ከመምህረ ንስሓው አስፈቅዶ ሁለት ሱባኤ ቢጾም የተመረጠ ነው። (ማቴ ፭፥፵፩ ትርጓሜ) ባይቻለው ግን የተሰጠውን በአግባቡ መፈጸም ይኖርበታል።

አንዳንዶች ንስሓ ገብተው ምንም የጤና ችግር ሳይኖርባቸው ቀኖናው ሁሉ በገንዘብ (በምጽዋት) እንዲለወጥላቸው ይፈልጋሉ። እርግጥ ነው ካህናት «ከሚሰበር ይሰንጠር» እያሉ ቢቀበሏቸውም ሰው ከእርሱ በአፍአ (ውጪአዊ) በሆነ ነገር ከሚቀበለው ቀኖና በሰውነቱ የሚቀበለው ጾምና ስግደት ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር እንደሚያቀርበውና ተነሳሒ (የጸጸት ሰው) እንደሚያደርገው አጥተውት አይደለም። በተአምረ ማርያም የተጻፈ አንድ ታሪክ ትዕዛዘ ካህንን ስለ ማክበር እንደ ምሳሌ ሊቀርብ ይችላል።

አባ ፋቁኤል የተባለ ካህን አንድ የንስሓ ልጅ ነበረው ፤ ይህን ተነሳሒ አባ ፋቁኤል በእግር ብረት አስሮ ቁልፉን ለእመቤታችን አመልክቶ ከባሕር ጨመረው። ሰውየውንም ያለ ጨውና ያለ እንጀራ በቀር ምንም አንዳይመገብ አዘዘው። ይህ ሰው ለሦስት ዓመታት ያህል በዚህ ሁኔታ ከእስሩ ሳይፈታ ቆየ።

በኋላ በጽኑ ደዌ ታመመ። ለሚስቱም *«ዓሣ መግቢኝ?»* ብሎ ለመናት ፤ እርሷም *«ቁሉ ሳይፈቅድ አይሆንም!»* ብላ ወደ አባ ፋቁኤል ዘንድ ሄዳ ጠየቀችው። ካህኑም አባ ፋቁኤልም *«ለአንድ ዲናር አስገዝተሽ*

አንድ ዓሣ ብቻ መግቢው» አላት። ሴቲቱም እሺ ብላ ዓሣውን አስገዝታ ልትሠራ ስትል ከዓሣው ሆድ ውስጥ አባ ፋቁኤል ባልዋን ያሰረበትን የእግር ብረት ቁልፍ አገኘች። ሄዳም ለአባ ፋቁኤል ሰጠችው። እርሱም እግዚአብሔር ቀኖናው ይብቃው እንዳለ ተረድቶ አመቤታችንን አመስግኖ ፈታው። /ተአ.ማር. ፩፻፲፯/

በዚህ ታሪክ ውስጥ ከተነሳሒውና ከሚስቱ ለካህን ትእዛዝ ከፍተኛ ክብርን መስጠትን መማር እንችላለን። እርሱ በትሕትና በእግር ብረት ለመታሰር ፈቃደኛ መሆኑና ለሦስት ዓመታት ከምግብ መከልከሉ ፤ ሚስቱ ደግሞ ባልዋ ዓሣ መግቢኝ ሲላት ካህኑን ለማስፈቀድ መሄዷ ፤ በኋላ የእግር ብረቱን ቁልፍ ስታገኝ ደግሞ በትዕግሥት ለካህኑ መስጠቷ ለካህን ትእዛዝ እስከ ምን ያህል መገዛት እንደሚገባ የሚያስተምር ነው።

አንዳንድ ሰዎች በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ እውቀትና ሀብት ከመምህረ ንስሓቸው ከተሻሉ ወይም የተሻሉ መስሎ ከታያቸው መምህረ ንስሓን ንቀው አቃልለው ይመለከታሉ። ይሁንና በክርስቶስ ራስነት የአካል ብልቶች የሆኑ ምእመናንን *«ንቀው አቃልለው ቢያዩት አንሂ ክብርን የሚያበዛላቸው ንዑስ መሐሊት (ታናሽ አካል)»* መምህረ ንስሓ ነውና ሊታዘዙት ይገባቸዋል። «ውበከ መለያልይ ዘታስተሐቅሮ ፈድፋደ መፍቅደከ ወገዘኩ ዘታንእሶ ያፈደፍድ ለከ ክብረ» እንዲል። (፩ቆሮ ፲፪፥፳፫) ስለዚህ በካህኑ አጅ የሚገኘውን መንፈሳዊ ጸጋ በማሰብ ቀኖናን በአግባቡ መፈጸም ይገባል።

ሰው በኃጢአት የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖ ከኖረ በኋላ ፈጣሪ የሚያውቀውን ኃጢአቱን «በመናገር ብቻ ይቅር እልሃለሁ» ብሎ መጥራቱ የአምላክን የምሕረቱን ብዛት ያሳያል ፤ ከኑዛዜ በኋላ የሚሰጠው የጾም የስግደት የምጽዋት የመሳሰለው ቀኖናም ቢሆን ሰው

ከሚሠራው ኃጢአት ጋር የሚመጣጠን አይደለም። ሰው ምሕረት የሚያገኘው በስገደው ፣ በጸመውና በመጻወተው ልክ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቸርነት ነው። «ወነሰጠኩ በከንቶ በሣህለ ዚአሁ /ያለ ዋጋ በይቅርታው ብዛት እንነጻለን» እንደተባለ (ማር. ይስ ፸፮፥፩) ስለዚህ የአምላካችንን ቸርነት ተረድተን በንስሓ ኃጢአቱን ልንናዘዝና በጥቂት ዋጋ የቀረበልንን ሥርየት ፈጥነን ልንቀበል ይገባል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ንስሓ የእግዚአብሔር የቸርነቱ ስጦታ መሆኑን ሲያጠይቅ «ወወሃበነ ፈውሰ ወገበረ ንስሓ ዘይበቍዓነ ከመ ይሥረይ ወያእትት ኩሎ ኃጥአውኢነ ለእመ ጠየቅናሃ ወአእመርነ ግብራ በዘይደሉ / የሚጠቅመንን ንስሓና ፈውስን ሰጠን እንደሚገባ አድርገን ሥርዓቷን አውቀን ብንፈጽማት ኃጢአታችንን ይቅር ይለን ያርቅልን ዘንድ» በማለት ተናግሯል። (ተግሣጽ ዘቅ.ዮሐ.አፈ፱) «አንደሚገባ አድርገን» ያለው «ለይጣን አስቶን ሰው አንብሮን ነውና የበደልነው» ብለን ምክንያት ሳንሰጥ ፣ ከሚሰጠን ቀኖና ሳንከፍል /ሳንቀንስ/ ፣ ጹሙ ቢሉን ልባችንን ፣ ስገዱ ቢሉን ወገባችንን ሳንል ብንፈጽማት ፈጣሪ ያለፈውን ይቅር እንደሚለን የሚመጣውንም እንደሚያርቅልን ሲያስረዳን ነው።

፪. መምህረ ንስሓን ስለ መምረጥና ስለመለወጥ

ምእመናን መምህረ ንስሓ ይሆናቸው ዘንድ ካህን የሚመርጡበት መሥፈርት የካህኑ ሃይማኖት የቀና መሆኑ እና ቤተ ክርስቲያን የምታውቀው በአገልግሎት ላይ ያለ ካህን መሆኑ ነው። እንዲሁም በሚገባ ክትትል ለማድረግ የሚችል መሆኑንም አስቀድሞ የማጣራት መብት አላቸው። ከዚህ ባሻገር «የእገሌ ምግባሩ እንዲህ ነው» እያሉ በማይመለከታቸው ጉዳይ ሊገቡ አይገባም። ሰው የሥጋ

አባቱን መርጦ (እንዲህ ካለው ሰው ልወለድ ብሎ) እንደማይወለድ ሁሉ የነፍስ አባቱን ምግባርም መመዘን አይችልም።

ተነሳሒ (ንስሓ የሚገባ ሰው) መምህረ ንስሓው በምግባር በመንፈሳዊ እውቀትና በመሳሰሉት ሁሉ ፍጹም እንዲሆን መጠበቅ የለበትም። ምንም ካህን ቢሆን ሰው ነውና ድክመት አያጣውም። በመንፈሳዊ እውቀትም ቢሆን ካህኑ ሰው እንደመሆኑ ሁሉን ያወቀ የጠነቀቀ ሊሆን አይችልም። አንደኛ ሁሉንም ነገር ለመማርና ለማወቅ ዕድሜውም አይበቃውም። ሁለተኛ ደግሞ ብዙ የተማረ ቢሆንም እንኳ ሰው እንደመሆኑ እውቀት ሊክፈልበት (ሊዘነጋው) ይችላል። ስለዚህ ተነሳሒው ከካህኑ ሁሉንም ነገር ካላገኘሁ ማለት የለበትም። በየጊዜው የሚኖረውን ጥያቄ ደግሞ የመምህረ ንስሓውን የእውቀት ደረጃ እያገናዘበ ሊጠይቅ ይችላል። ምናልባት የምናነሣው ጥያቄ በመምህረ ንስሓችን የማይመለስ ቢሆን እንኳን ሌሎች መምህራን ቤተ ክርስቲያንን የመጠየቅ መብት አለን።

በመጽሐፈ ሲራክ ላይ «ብዙኃን ይከውኑከ ለእርከተ ሠለሙዳ ለምስሉ ይኩንከ ምስሌሁ ዘተተናገረ ምክረከ / ብዙ ሰዎች ወዳጆች ይሁኑህ ከብዙዎች አንዱ ምክርህን የምትነገረው ከልቡናህ ጋር አንድ ይሁን» ተብሎ ተጽፎአል። (ሲራ. ፮፥፮)

ይህ ቃል ስለ ባልንጀርነት የሚያስረዳ ሲሆን በሌላ ትርጓሜው ምእመናን ስለ ሃይማኖትና ምግባር የሚያስተምሯቸው መምህሮቻቸው ብዙዎች ሊሆኑ ከብዙዎች አንዱ ደግሞ ንስሓቸውን የሚነግሩት መምህረ ንስሓ ሊሆን እንደሚገባም ያስረዳል ፣ ስለዚህ «ለጠየቅሁት ነገር ሁሉ ምላሽ ሊሰጠኝ አልቻለምና መምህረ ንስሓ ሊሆነኝ አይችልም» ማለት ተገቢ አይደለም። እንዲሁም ተነሳሒው ሌሎች መምህራንን መጠየቅ ይችላል ማለት ከሌላው እየጠየቀ መምህረ

ንስሓውን መፈታተን የበላይ ለመምሰል መሞከር ይገባል ማለትም አይደለም። እንዲህ የሚያደርግም ሰው ምንም ያህል ቢያውቅ «ልጅ ቢሮጥ አባቱን አይቀድምም!» እንዲሉ በካህኑ ካለች ጸጋ አግዚአብሔርና ልዕልት ሥልጣን ሊቀድም እንደማይችል ማወቅ አለበት።

የኃጢአት ይቅርታን የሚፈልግ ምእመን ካህኑ በፍቅር ባይቀበለው እንኳ ታግሶ ደጅ ሊጠና ይገባዋል። በወንጌል ጌታችን እንዲህ ሲል በምሳሌ ተናግሯል፦ «ከእናንተ ማናቸውም ወዳጅ ያለው በእኩለ ሌሊትስ ወደ እርሱ ሄዶ፦ ወዳጄ ሆይ! ሦስት እንጀራ አበድረኝ እንድ ወዳጄ ከመንገድ ወደ እኔ መጥቶ የማቀርብለት የለኝምና ይላል፦ ያም ከውስጥ መልሶ አታድክመኝ አሁን ደጁ ተቆልፎአል ፤ ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ ተነሥቼ ልሰጥህ አልችልም ይላልን? እላችኋለሁ ወዳጅ ስለሆነ ተነስቶ ባይሰጠው እንኳ ስለ ንዘነዛው ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ ይሰጠዋል» ይላል።

እንዲሁም ተነሳሒ ወደ መምህረ ንስሓ ሄዶ አባቴ ሆይ ሞትን በምታስፈርድ ኃጢአት ተይዤአለሁና ሞትን የማስቀርበት ሃይማኖት ምግባር የለኝምና የንስሓ ዕድሜን (ጊዜን) አሰጠኝ ብሎ ቢጠይቀውና በመምህረ ንስሓው ያደረ አግዚአብሔር ምሕረት ተከልክሏል ቢለው (ሥርየትን) ባይሰጠው በኋላ ግን ራርቶ ልመናውን ከአምላክ ያገናኝለታል። በሦስቱ እንጀራ የተመሰሉ ጥምቀትን ፤ ንስሓንና ሥጋወ ደሙን ይሰጠዋል። አንድም ከሥላሴ ጋር አንድ ያደርገዋል። ስለዚህ ሥርየት በእጃቸው ነውና መምህራነ ንስሓን ደጅ መጥናት የሚገባ ነው። እንኳን ለሥርየት ለሹመትም ደጅ ይጠናል። ደግሞም ጌታችን እንዳለ «ኃጢአትህ ተሰረየችልህ!» ከመባል በላይ ምንም ነገር የለም።

ተነሳሒያን ምናልባት ከመምህረ ንስሓቸው በጎ አቀባበልና አቀራረብ ባይገጥማቸው እንኳ ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም።

ምክንያቱም መምህረ ንስሓው ይህን የሚያደርግበትም ምክንያት ሊኖረው ይችላል። ባይኖረውም ግን መታገሥ ይገባል። ስለዚህ ተነሳሒው የካህኑን ቁጣና ሌላም ነገር ሁሉ እንደ ቀኖና ቆጥሮ የሥራዬ ዋጋ ነው ብሎ ታግሶ ሥርየትን ማግኘት ይኖርበታል። ብዙ ጊዜን በኃጢአት አሳልፎ እግዚአብሔር ታግሶ ለንስሓ ያደረሰው ሆኖ ሳለ ዛሬ በንስሓ ወቅት የሚገጥመው እክል ለመታገሥ ፈቃደኛ ካልሆነ «የበደለኛ ጥጋበኛ» መሆኑ ነው። በንስሓ ወቅት የሚገጥሙ መሰናክሎች በትዕግሥት ማለፍ አለመቻል ለዲያብሎስ መሸነፍ ነው። እርሱ ተነሳሒያንን በተለያዩ ምክንያቶች ከንስሓ ለማራቅ ይፈልጋልና።

ቀደም ባሉት ምዕራፎች በንስሓ ወቅት ለሚያስፈልግ ታጋሽነት አብነት የምትሆንን አንዲት ሴት ከውዳሴ ማርያም መቅድም ጠቅሰን ነበር። ይህች ሴት ኃጢአቷን በወረቀት ጽፋ ወደ ቅዱስ ኤፍሬም ስትሄድ እርሱም ወደ ቅዱስ ባስልዮስ ሲልካት ቅዱስ ባስልዮስም አይቻለኝም ብሎ ወደ ቅዱስ ኤፍሬም ሲመልሳት ነበር። እነዚህ አባቶች ይህችን ሴት ካመላለሱባቸው ምክንያቶች አንዱ መመላለሷን ቀኖና ይሁናት ብለው ነው። ይህች ሴት ሥርየትን ፈላጊ በመሆኗ ወዲያ ሂጂ ወዲያ ሂጂ እያሉ ሲያመላልሷት ታግሣ ጸንታለች። የምትሻውንም ሥርየት አግኝታለች። «ካህን አልጠፋ ምን አንከራተተኝ?» ብላ ብትሸሽ ኖሮ ግን ከጸጋ ትጎድል ነበር።

ሌላው ዐቢይ ጉዳይ ደግሞ መምህረ ንስሓ መለወጥ የሚመለከት ነው። በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መምህረ ንስሓን ለመለወጥ የሚያስችሉ /የሚፈቀድባቸው/ በቂ ምክንያቶች አሉ። አንደኛ መምህረ ንስሓው በሞት የተለየ እንደሆነ ነው። ይህም ምንም ሥልጣኑ የማትሞት ብትሆንም ከሞተ ወዲያ ቀኖና መስጠትም ሆነ ክትትል ማድረግ አይቻለውና ነው። ሌላው ምክንያት ሊሆን የሚችለው ነገር ደግሞ በካህኑ ሕጸጸ ሃይማኖት (የሃይማኖት ጉድለት) ወይም ክህደት

የተገኘበት እንደሆነ ነው። ኑፋቄና አምልኮ ባዕድ ያለበት ካህን የምግባር ሳይሆን የሃይማኖት ችግር አለበትና እንዲህ ያለው ሰው እንኳ ክህነቱ ምእመንነቱም ፈርሷልና አባት ሊሆን አይችልም። ጌታችንም በወንጌል በምሥጢር «ለጣዖት ስገዱ የሚል አባት አይኑራችሁ» ብሏልና (ማቴ ፳፫፥፱ ትርጓሜ) ተነሳሒው ለንስሐ አባቱ ፍቅር ቢኖረው የሃይማኖት ችግር ካለበት ግን የሚያውቀው በመንፈሳዊ አባትነቱ ነውና ሊተወው ይገባል። ከመቀራረብ የተነሳ *«ከእርሳቸው ከምለይ»* ብሎ ቢሔድ ግን ሐሰተኛ አባት አልጣ ብሎ ሃይማኖቱን ያጣል። ጌታችንም በቃሉ *«ዘሚታደገ ዕባሁ ወእሞ ፈይከል ይዘመደነ / አባት ወይም እናቱን ያልተወ ሊከተለኝ አይችልም»* ያለው እንደዚህ ላለውም ነው።

ከእነዚህ ምክንያቶች ባሻገር መምህረ ንስሓን መለወጥ የሚበረታታ አይደለም። በቂ እንክብካቤ ማግኘት ባይቻል እንኳ ከላይ እንደተገለጠው ሌሎች መምህራንን መጠየቅ ይቻላል። ሰው ከሥጋ አባቱ ከአባትነት ባሻገር ትምህርቱንም ፣ ሕክምናውንም ፣ ምክሩንም ከእርሱ ሊያገኝ እንደማይችል ከነፍስ አባቱም ሁሉንም ነገር ሊያገኝ አይችልም። ስለዚህ «የሥጋ አባቴ ሁሉን አልሰጠኝም» ብሎ አባት እንደማይለውጥ የነፍስ አባቱንም መለዋወጥ የለበትም። በተለያዩ ማኅበራዊ ምክንያቶች ተነሳሒው ከመምህረ ንስሓው ጋር መገናኘት የሚችልበት ሁኔታ ባይመቻች በቅርብ የሚገኝ ካህን ለጊዜው «እንደ ሞግዚት አባት» አድርጎ በመቅረብ ኑዛዜን መፈጸምና ሥጋ ወደሙን መቀበል ይችላል። ይህ ማለት ግን የንስሓ አባት ለውጦአል ማለት አይደለም።

አንዳንዱ ንስሓ አባትን ለመለወጥ መፈለግ መንፈሳዊ አንክብካቤን ከማጣት ብቻም ላይሆን ይችላል። አንዳንዶች በኃጢአታቸው በመሰቀቅ ትዝብት ፍራቻም «ታጥቦ ጭቃ!» ላለመባል

ሲሉ መምህረ ንስሓን ሊለውጡ ይችላሉ። ይህም ሁሉን የሚያይ ፈጣሪን ከመፍራት ይልቅ ለይሉኝታ ቦታን መስጠት ነው።

የንስሓ አባትን መቀያየር በምእመኑ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ ዝግመትን ያመጣል። አንድን ችግኝ በየዓመቱ እየነቀሉ ከቦታ ቦታ ቢያዛውሩት በተፈለገው ጊዜ ፍሬን ሊያፈራ አይችልም። በአንድ ሥፍራ ጸንቶ ቢቆይ ግን ፍሬን ሊያፈራ ይችላል። እንዲሁም አንድ ምእመን በአንድ መምህረ ንስሓ መሠረት ላይ ቢተከል ካህኑ ጠባዩንም ሆነ ደካማና ጠንካራ ጎኑን ከጊዜ ብዛት እየተረዱ ስለሚሄዱ ከኃጢአት ሊያላቅቁትና ለትሩፋት ሊያበረቱት ይችላሉ። አባት በቀያየረ ቁጥር ግን የልጁን «የትመጣ» የማያውቁ አባቶች ሊያበረቱት ይቸገራሉ። ከሐኪም ሐኪም የሚቀያይር በሽተኛ እንደማይጠቀም መምህረ ንስሓን የሚለዋውጥም እንዲሁ ነው። *«ፊቱ ጠቆረ ቃሉ ሻከረ ፣ ይህ ይጎድሰዋል ይህን ነሣኝ»* እያለና እያማረጠ መምህረ ንስሓን የሚለዋውጥ ሰው ትዕግሥት ኖሮት ዕድሜውን ሙሉ ቢፈልግ እንኳ እርሱ እንደሚፈልገው ዓይነት የንስሓ አባት አያገኝም። ምክንያቱም እግዚአብሔር መርጦ የሾመውን ሲያቃልሉበት አይወድምና ነው። መምህረ ንስሓ ለመለወጥም ቢሆን ለካህኑ ከነምክንያቱ ማሳወቅ ያስፈልጋል እንጂ እንዲሁ እየተነሡ የንስሓ አባት መለዋወጥ የሚበጅ አይደለም።